
# መጫሚያ አልባው ንጉሥ

ፊሊፕ ማዝደን



ትርጉም
በሽዋዬ ለገሠ

# መጫሚያ አልባው ንጉሥ

ፊሊፕ ማዝደን

ትርጉም በሸዋዬ ለገሠ

የአፄ ቴዎድሮስ 200ኛ ዓመት የልደት በዓል ሲታሰብ

በ2011 ዓ.ም ጥር ወር ታተመ

የመጀመሪያ እትም

## ምሥጋና

« ነአኩቶ ለእግዚአብሐር እስመረዳዓኒ በበኩሉ ጊዜ!» ምሥጋና የዘወትር ገንዘቡ ለሆነው ፈጣሪ ዓለማት ቀዳሚው አኩቴት ይድረስ! አነሳስቶ በማስጀመር ከፍፃሜ አድርሶኛልና። የሀገር ፍቅር እንዲኖረኝ፣ ኢትዮጵያ የፈጣሪ ድንቅ ጥበብ መገለጫ መሆኗን እየነገረና ታሪክም እያወጋ ያሳደገኝን፣ ማንበብ እና ዝም ብሎ መጻፍ የማይሰለች፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት አባቴን ላሳደረብኝ መነቃቃት ልባዊ ምሥጋናዬን ባላቀርብ ራሴን እታዘበዋለሁ። ይህን መጽሐፍ እንዳነበው የሰጠኝን ውድ ወንድሜ ዘውዴ፣ የምትኖርባት አምስተርዳም ከተማን ባሕር ላይ ያንሳፈፏት ሀገሬው ቢሆኑም ዕውቀትን ያደላቸው የበሐውርት ባለቤት እጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ውለታህን አይርሳብኝ። ለመተርጎም ስነሳሳ ከማደፋፈር፣ ከመገፋፋት ባሻገር፣ አለቀ ወይ እያልክ ስታቻኩለኝ የከረምከው ምገደኛው ወንድሜ መምህር ዘመድኩን በቀለ፣ ጭቅጨቃህ ፍሬ አፈራ መሰል፣ ልትመሰገን ይገባል። የቀድሞ የሥራ ባልደረባዬ እንጋፋውና ታሪክ አዋቂው ጋዜጠኛ ተከሌ የኋላ፣ የመጽሐፉን ትርጉም ለማረም ላሳየኸኝ ትዕግሥት እና ማበረታታት፣ ለድንቅ ምክሮችህና የፊደላት እርማቱ፤ ማስተካከያው ሁሉ በየደረጃው እየዘረዘርኩ ባመሰግንህ በወደድኩ፣ ብቻ ተባረክልኝ። እንዲሁም ሌላዋ የቀድሞ የሥራ ባልደረባዬ ወ/ሮ ንጋት ከተማ፣ የፊደላት እርምቱ ለወደፊትም ስንቄ ነውና አክብሮቴ ላቅ ያለ ነው፤ ሁሉም ተለቅሞ እንደሁ ግን እንጃ፤ ብቻ አመሰግናለሁ። የታሪክ ተመራማሪ እና ተንታኙ ልዑል ዶክተር አስፋወሰን አስራተ ካሣ፣ የጊዜ እጥረትና የሥራ ጫና ሳይገድብዎት አንብበው ለሰጡኝ አበረታች አስተያየት ሳላመሰግን አላልፍም። መጽሐፉን ለሕትመት በማዘጋጀት የረዳኸኝ ወንድሜ በለጠ ከፍሌም ምስጋናዬ ከልብ ነው። የሽፋን ዲዛይን በመሥራት የተባበራችሁኝ ጆኒ እና ዳኒም እውቀታችሁን ፈጣሪ ይባርከው። በሃሳብም በጉልበትም በምትችሉት ሁሉ የረዳችሁ ያበረታታችሁኝን ከልብ አመሰግናለሁ።

ሸዋዬ ለገሠ

## የታሪክ መነፅርነት

ትናንት የዛሬ ታሪክ መነሻ እና መንደርደሪያ ነው። ስለዛሬ እና ነገ ለማለምም ሆነ ለመነጋገር ትናንት ላይ መመርኮዝ ግድ ነው። የዛሬው እኛነታችን በትናንቱ ማንነታች መሰታወትነት ይንፀባረቃል። ትናንትን እየሸሹ ነገ አይታለምም። ልጆች ካሉ ወላጆች እንደነበሩ ሁሉ፣ ትውልድ ካለ ቀደምት እንደነበሩት እያሻማም። የትናንቱን ቀዳሚ ትውልድ ታሪክ አጨልሞ መቅረፅ በዛሬ እኔነት ላይ ማላገጥ አለያም መጨከን ነው። «አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል?» ሲል ልዑል እግዚአብሔር «እንደ ልቤ» ሲል ያደነቀው ቅዱስ ዳዊት አምላኩን ይጠይቃል፤ «በቅንነት የሚሄድ… ዘመዶቹን የማይሰድብ…» እያለ ይቀጥላል። በዚህም ወገንን ማጣጣል እና ማንቋሸሽ በፈጣሪ ዘንድ ሳይቀር የተነቀፈ ተግባር መሆኑን ልብ ይሏል። ለምንስ ሲባል የቀደምት አበው ሚና ሊጠለሽ ተፈለገ? ተወደደም ተጠላ፣ በጎም ሆነ መጥፎ ቀደምት በመኖሩ ዛሬ ተገኝቷል። ቀደምቶቻችንን ማንነታቸውን ማንም እንዳሻው እንዲቀርፅልን ከፈቀድን በአባት እናቶቻችን የማንኮራ ወፍ ዘራሾች እንዳይጠናወተን ያሰጋል። በተቃራኒው በትናንት ውስጥ ሁሉ በጎ፣ ሁሉ ብርሃን ነበር ማለትም ድፍረት ይሆናል። ሁሉን እንደ ጊዜው እና እንደየዘመኑ መመዘኑ ግን ትርጉም የሚሰጥ እና አግባቢ ነው። የቀደምቶቻችን ታሪክ እንደየተራኪያቹ መንፈስ እና አላማ፣ ፍላጎት እና አዝማሚያ የሚዘምም መሆኑንም ልብ ይሏል። «መጫሚያ አልባው ንጉሥ» የዚህ ግሩም ማሳያ ነው። ሌላው እኛ በድሮ ታሪክ ላይ ስንጨቃጨቅ ምዕራቡ ዓለም በዘመን ቀመሩም ሳይቀር ቀድሟችኋለሁ እያለ በ1840 እና 60 ላይ በዚያች ሀገር ውስጥ የተከናወነው ጉዳይ ሲያሳክከው መመልከት ለእኛ የንቄ ደወል ካልሆነ ምን ሊባል ይችላል?! ፈረንጆቹ ያኔ ጨለማ ከሚሉት አህጉር እና ሀገር ምን ቀረን ብለው ኖሯል ሲመላለሱ የኖሩት? አውሮጳውያኑ አንድ አንድ እያሉ ውለው አድረው ሊቀራመቱ የዘመቱባት አፍሪቃ ዛሬም ድረስ ትተውላት በወጡት ጦስ ከመታመስ አልወጣችም። ኢትዮጵያም ከመዘዙ ትገላገል ይሆን? ምጥ ከጠናባት ግን ሰነበተ። የጭንቅ አማላጇ ትቅረባት! ታሪካችንን ማንም ይከተበው ማን፣ «የተጻፈው ሁሉ ለእኛ ለተግሳፅና ለምክር ተጻፈ.» እንዲል ታላቁ መጽሐፍ በዚህ መንፈስ እየተመለከትን ልንማርበት ይገባል እላለሁ። መማር ለመታነፅ ለመታረምም ነው እና ካለፈው ጠማማውን እያቀናን በጎውን እያጎለበትን ለትውልድ የሚበጅ አስተዳደር እና የሀገር የወገን ፍቅርን የመላበስ ቀና መንፈስ እንዲያድለን ልመኝ።

## ወደ ምንባቡ ማሸጋገሪያ

በግሌ የሀገሬን ታሪክ ቦር እያሉ መፈተሽ፣ እንዲሁም ታሪክ ከሚያውቁ ታላላቆቼ ጋርም ማውጋት ያስደስተኛል። በዚህም እኛ ለእኛ ያለን ግምት እና ባዕዳን እኛን የሚያዩበት መንገድ እጅግ መለያየቱን ታዝቢያለሁ። እርግጥ ነው «ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው » ብሎ የባዕዳኑን እይታ ችላ ማለት ይቀል ይሆናል፤ ግን ደግሞ እኛ ስለራሳችን ያለን ግምት በሌሎች ሚዛን ቢመዘን ማስከላዊውን ምልከታ ሊሰጠን ይችል ይሆናል። እንደ እኔ እንደ እኔ አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያውያን የፅናት እና የአልበገር ባይነት ተምሳሌት በመሆን የሚታወቁ ያለዘመኑ ታይቶ የተሰወረ ጀንበር ነው። ለቴክኖሎጂ በነበረው ጥማት እስከ ከፋት መጥተው ሊያስተብሩት የተመኙትን ምዕራባውያን «ኔጮች » ወዳጆቻቸውን እስር የሚፈልጉትን የጦር መሣሪያ እንዲሠሩለት ያደረገው መከራ እና ድፍረት ያበሳጫቸው ወገኖች ደግሞ ቁጣቸውን ይገልጹልናል ባሉት መልክ ቀርበውታል። ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያ ውስጥ በዘመነ ቴዎድሮስ ኖረው እስንም ቀረብ ብለው በሚያት ማስታወሻዎችን በሚላቸው የከተቡ ምዕራባውያን ምልከታ ያካተተ እንደመሆኑ መረጃው እንደየጸሐፊው ስሜት እና ከቴዎድሮስም ጋር እንደነበረው ግንኙነት የሚግል እና የሚበርድ፣ የሚያሞካሽ እና የሚያኮላሻ ቢጤ ነው። ጸሐፊው እነዚያን ማስታወሻዎች ቃኝቶ በግሉም መቅደላ ድረስ ተጉዞ ታሪኩን ሲያጠናቅር ሊልከው ያለመውን መልእክት እኔ ብቻዬን አንብቤ እጅብ ብዬ ከመቀመጥ ይልቅ ሌሎች ወገኖቼም ቢያነቡት ከሚል ጉጉት የተነሳ መንፈሳዊ ቅንነት ብርታት ሆኖኝ በተረዳሁት መጠን ቃል በቃል ሳይሆን ሃሳቡን ተከትዬ ወደ አማርኛ ለመመለስ ሞክርኩ። በትረካው አፄ ቴዎድሮስ «በአንተታ» ተገልጿል። እውነቱን ለመናገር አፄ ቴዎድሮስ የሀገሬ ንጉሥ ሆኖ ሳለ «አንተ» አለማለቱ ደፍሬው አይደለም። ታሪኩን ባነበብኩ እና በተረዳሁት መጠን ለሀገሩ የነበረው ራዕይ እና መቆርቆር የፈጠረብኝ ውዴታ ያመጣው መቀራረብ ነው። ሰማይ እና ምድሩን በውስጣቸው ካሉት የሚታዩ እና የማይታዩ ፍጥረታት ጋር ፈጥሮ የሚገዛውን ከሀሊ አምላክስ አንተም አይደል የምንለው? ውዴታ እና የመንፈስ ቅርበት እንጂ ይህ ንቀት አለመሆኑ ይታወቅ እና በዚሁ መንገድ ይታይ። ዓመተ ምሕረቶቹ ደግሞ ከጎርጎሪዮሳዊው ቀመር ላይ በግርድፉ ስምንት ዓመትን በመቀነስ ወደ ኢትዮጵያ ቀመር መመንዘሩ ይታሰብ።

ከቋራ ሸንተረሮች ተነስቶ መቅደላ ላይ የተቋጨው የቴዎድሮስ ታሪክ ዛሬም 200 ዓመታትን ተሻግሮ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መነጋገሪያ ሆኗል። ኢትዮጵያውያን አዳዲስ ነገሮችን ለመቀበል ጥርጣሬ ያበዛሉ፤ ይህ ደግሞ ዛሬ የመጣ ሳይሆን በቀደምት መሪዎቻቸው እና ወገኖቻቸው የታየ ውርስ ነው። የዛሬን አይበለው እና ፍትሃዊነት መገለጫቸው የሆነው በቅዱሳት ድርሳናት ብቻ አይደለም፤ የዓለም መንታ ፖለቲካዊ ጎዳናም ገና የገባቸው አይመስሉም፤ ለዚህ ደግሞ አፄ ቴዎድሮስ በአንድ ወገን ይቆማል ብሎ የገመተው ክርስቲያኑ ምዕራባዊ ዓለም ለምን በክርስቲያኒቱ ሩሲያ ላይ በተቃራኒ ጎራ ተሰልፎ ከሩሚያ ላይ ተቀጋ ለሚለው ጥያቄው መልስ ሲፈልግ መኖሩ ማሳያ ይሆናል። ዛሬም ጥያቄው ጥያቄ ነው። ሊላው ለኢትዮጵያውያን ንጉሥ ሁሉ ንጉሥ ሆኖ ሳለ እንግሊዞች «በሀበሻ ጨካኝ ንጉሥ» በሚል ታስረዋል ተብሎ እስረኞን ነፃ ለማውጣት ወደ መቅደላ የዘመተው የባዕድ ሠራዊት ግን በመጨረሻ ያስፈታው አንድ እንግሊዛዊ ሆኖ ሊሎች የሌላ ሀገር ኔጮች መሆናቸው የፈጠረበት ቅሬታም አንዱ የተራራቀ ምልከታ ነበራት ነው። በዚህ እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶችም መጽሐፉ ብዙ በቀጣይ ሊያነጋግሩ የሚችሉ ጭብጦችን አዝሏል።

መልካም ንባብ

# ምዕራፍ አንድ

ዋልተር ፕላውደን በመርከቡ ወለል ላይ ተኝቷል። 1839 ወርኃ ሚያዝያ ነበር። ባለ ሦስት ጎኑን ትልቅ መቅዘፊያ ከበላዩ ሞቃት አየር ከቦታል።ጀልባውን የቀይ ባሕር ተከታታይ አነስተኛ ሞገድ ዝቅ ከፍ ያደርገዋል። በስተደቡብ የኢትዮጵያ ተራራማ አካባቢ ከርቀት ጎላ ብሎ ይታየዋል። ከጉልት ጉልት፣ ከጦርነት ወደ ጦርነት እየተዘዋወረ በተራራዎቹ መካከል ከተንቀሳቃሹ ችሎት ጋር አራት ዓመታትን አሳልፏል። የትንባሆ ማጨሻውን አንሳና ከመኝታው ላይ በጀርባው ተንጋለለ። ከዚያ ስፍራ በመለየቱ ውስጡ በደስታ ተሞላ። በነገሥት በሚንጉዱት ማዕበሎች መካከልም እንዲህ ሲል ጻፈ። «ልቤ ረጋ ብላ ትመታ ጀመር።»

ፕላውደን ተልዕኮ ላይ ነበር። «የኢትዮጵያውን ገገር» ራስ አሊን አንድ ዘመናዊ የሆነ መንግሥት ሊያደርገው የሚገባ ነገር እንዳለ አሳምኗቸዋል። ይኸውም ከብሪታኒያ ጋር የንግድ ስምምነት መዋዋል ነው። ራስ አሊ ይህን ነገር አላስተዋሉትም ነበር። የንግድ ውሉ ደጃዝማች ውቤንም ሆነ ነዋግ እና ላስታን ህዝብ እንዴት ለመከታተል ይረዳል? ጎጃም ላይ በየዓመቱ የሚሸሙ ገዢዎችን ሲያርድ የቆየው ብሩ ጎሹን እና ባለቤቱንስ ለመቋቋም እንዴት ይጠቅም ይሆን?

ለማንኛውም ግን ይሁን በጀ ብለው ከወጣቱ እንግሊዛዊ ጋር አንድ የልዑካን ቡድን ይልካሉ። እናም ልዑኩ ይኸው። ምስኪን ደጎኖ። ከዚህ በፊት ባሕር አይቶ የማያውቅ፣ ሲጋት ባጠላባቸው ዓይኖቹ ፕላውደን ከሚገኝበት የመርከብ ክፍል ቁጢጥ ብሎ ዙሪያ ገባውን ይመለከታል። ራስ አሊ ለንግሥት ቪክቶሪያ ያዘጋጁትን ስጦታም ይዟል። የዛገ ጦር፣ ከጥጥ የተሠራ ሸማ እና ሦስት የሳላ ግልገሎች። ሳላዎቹ ራሳቸው ለባሕሩ እንግዳ ናቸው። ፕላውደን እናት ፍየል ገዝቶላቸዋል ወተት እንዲያገኙ። ድምጿን በሰሙ ቁጥር የመርከቧ ክፍል ትታመሳለች፣ ይጮኻሉ፤ ይበረግጋሉ። ይኸ ነበር የኢትዮጵያው የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ። ፍርሃት የተሞላነው አስተዳዳሪ፣ ያልተዋሐደ እና ተስፋ የሰነቀ ቡድን። ሥራ የፈታው ፕላውደን ቀኑን በመቀጥቀጥ ያሳልፋል። ይተኛል፤ ፒፓውን ያጨሳል፣ ቡናውን ይጠጣል። አሊጋው ላይ ረጃጅም እግሮቹን በመንጠራራት እየዘረጋ እና ዓይኑን ጨፍኖ የበረሃው ሞቃት ነፋስ ፊቱን ሲዳስሰው ያዳምጣል።

በሃያዎቹ የዕድሜ መጀመሪያ አካባቢ ከአራት ዓመታት በፊት በዚሁ ባሕር ላይ ተጉዟል። ያኔ ከካላከታው ካር ታአኅር እና ባልደረቦቹ የተጣለበትን የሞት ቅጣት አምልጦ ከሕንድ ወደ እንግሊዝ ነበር የተጓዘው። ስዊዝ ሲደርስም ስኮትላንዳዊውን የባሕር ቀዛፊ ጆን ቤልን አገኘ። የፕላውደን ወንድም እንደሚለው በወቅቱ በነበረው ገደብ የለሽ ምኞት ምክንያት ያለምንም ዝግጅት እና በቂ ገንዘብ ዓለምን ለማሰስ ከቤል ጋር ተቀናጀ። መጽሐፍ ቅዱስ እና ጥንታዊ

ታሪኮች ሳነበበው ፕላውደን በተራራዎች መካከል በሙስሊሞች የተከበበ ክርስትና ያለባት ሀገር ኢትዮጵያ ህብታም ነበረች። የቤል ዕቅድም ብዙም አልሰራም። ስለሆነም ታላቋን የጥንት ስልጣኔ መንኻሪያ የሆነችውን ግብፅን የሚያጥለቀልቀውን የአባይን ምንጭ በጋራ ለማሰስ ይችላሉ።

መርከባቸውን ከወደብ አስጠጉና የብስ ረግጠው ዝሆን አዳኞች መስለው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ከሳምንታት በኋላ ሀገሪቱ ውስጥ ባዩት ትዕይንት ተዋጡ። አባይን ዘነጉት። በእያንዳንዱ ጦርነት እና በድንኳን በሚካሄደው ችሎት፤ እንዲሁም ገበሬዎቹ ባሳይዋቸው ፍቅር ከውጭው ዓለም ራቁ።

ጆን ቤል የአካባቢውን ሴት አግብቶ የራስ አሊ ጦር ጀነራል ሆነ። ለሁለቱም ግን የማዘቱ ፈደሎች እንግዳ ናቸው። ፕላውደን በተለይ በመካከለኛው ዘመን ባስተዋለው የኢትዮጵያ ውበት ተዋኒዎቹ በሚያሳዩት የራስ ፍቅር፤ በፊውዳሎቹ ውበት ተመስጧል። ለእሱ የኢትዮጵያ ጥንታዊነት፤ ከሌሎች መገለል እና የራስዋ የሆነ ማንነት በወቅቱ ከተንሰራፋው ዘመናዊነት በልጦበታል። አዝማሪዎች ወዲያው እየገጠሙ የሚያዜሙትን ባህላዊ ዜማ ማፍቀሩ እየጨመረ ነው። ከድብድብ እና ግጭት የማይተናነሰውን የትግሎ ጨዋታ ተምሯል። እንደ ማኅበረሰብ አጥፊ ያስተዋለውን በማስታወሻው ላይ ያሰፍራል።

==============================================

«ልዩ የሆኑ ልማዶችን የተመለከተው ማስታወሻ»

«አሮጌው እንደ ሸዊው ሁሉ ዓሣ መብላትን ይጠየፋል፤ በጉዞ ወቅት ክርስቲያኖች ዲያብሎስ ወደአፋቸው እንዳይገባ ጸሎት ይደግማሉ፤ በቀደመው ሌሊት ከሴት ጋር ያደረ ሰው ጥላ እንደሚጎዳ ነገር ይቆጠራል።» ትግራይ ውስጥ ደግሞ፤ «ፀመድ እስኪሞት ድረስ ጥቅም የለውም።» የሚል የታወቀ አባባል ሰምቷል። ከዚህም ሌላ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ሴትን ልጅ የመግረዙ ልማድ ምን ያህል የተስፋፋ እንደሆነም አስተውሏል።

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በተለያዩ ዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ታዋቂ ሰዎች፣ የጦር መሪዎች እና ታላላቅ የአካባቢ አለቃዎች ችሎት እና መንደር ጊዜውን አሳልፏል። አብሯቸው ተጉዟል፤ አብሯቸው ዘምቷል ወይም ደግሞ በእነሱ ተይዟል። ብዙ ወዳጆችንም አፍርቷል፤ ፈረሶች፣ መሬት እና ልዩ ልዩ ስጦታዎችም ተሰጥተውታል። አንዳንዶቹም ልክ ፈረስ እንደሚያበድሩ ሁሉ ሚስቶቻቸውን ጋብዘውታል። እንደኛው አስተዳዳሪ እህታቸውን እና ሁለት ክፍለ ሃገራትን እንዲወስድ ጠይቀውታል። ነገር ግን ከዚህ አልፎ ወደሌላ ሸሰቶ፤ ወደሌላ በደን የተሸፈነ አካባቢ፣ ወደሌላ አዲስ ስፍራ መሄድን መረጠ።



ጦርነት የእያንዳንዱን ደገኛ ኢትዮጵያዊ ፍላጎት እና ፍቅር እንደሚቀሰቅስ ተረድቷል። ጦርነት በራሱ መጨረሻ ያለው የህይወት መንገድ ነው። ትልቁ የዝናብ ወቅት በመስከረም ሲያበቃ ወንዞች መጉደል ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜም በመላው ሀገሪቱ የነጋሪት ድምጽ ይሰማል። ወደጦርነት ዘማቹን የሚቀሰቅሰው ከበሮ። በመቶዎች እና በሺህዎች የሚቆጠሩ ወንዶች ታዲያ ወደ ሹሞቻቸው ያሄዳሉ። ሹሙ የአንበሳ ጎፈሩን አጥልቆ ከፍ ባለ ስፍራ በተዘጋጀ ድንኳኑ ውስጥ ተቀምጦ ይቀበላቸዋል።

ፕላውደን ለዚህኛው ዓለም የሚያሳየው ጉጉት የሞላው ፍላጎት በጻፈው መጽሐፍ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ጎልቶ ይታያል። ይህንንም በምስጢራዊ መለያ እና ቅደም ተከተል አስቀምጦታል።

የእያንዳንዱ ራስ ተከታዮች እና ተዋጊ ኃይሎች ይበላለጣሉ። ራስ አሊ ወደ ጦርነት ሲሄዱ ከ150.000 ህዝብ በላይ ተከትሏቸዋል። 88 ነጋሪት መቺዎች ከፊታቸው ቀድመው ነበር። ከወታደሮቹ ሌላ እያንዳንዱ የሥራዊት አባል በገደለው ብዛት ደረጃውን ይዞ ይሰለፋል። ድንኳን ጠባቂዎችም አሉ። የቀዳሚዎቹ ጠባቂዎች አለቃ እሊ ንጉሡ ነው። የምሽት ጠባቂዎች፤ ሴቶች የሚገኙበት አካባቢ ጠባቂዎች፤ ሰጠጅ ማር የሚያቀርቡ ሴቶች፤ ጠጅ የሚጥሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶች፤ ብቻ ሁሉም በየራሳቸው አዛዦች ሥር በስልጣን ተዋረዳቸው ይከተሟቸሉ። ማር አጣጆች፤ እንጨት ቆራጮች፤ መንገድ ጠባቂዎች፤ እታጣቂ መቺዎች፤ ከብት አራጆች እና ምግብ አብሳዮች ሁሉ ይከተሏቸዋል። ፕላውደን በሬ ታርዶ ሥጋው በመቶ ክፍልፋዮች ሲቆራረጥ እና ሲከፋፈል አይቷል። እያንዳንዱ ጉማጅ ታዲያ ደረጃውን የተከተለ ነው።

ጦርነት የተዋበና በጀግንነት የተደጎሰ ነው። በየዓመቱ ራስ አሊ ከጎጃሙ ገዢ ብሩ ጎሹ ጋር ለመዋጋት በሺዎች የሚቆጠሩ ድንኳኖቻቸውን አስጭነው ይዘምታሉ። ብሩ ጎሹ የራስን ሚስት ወስደዋል። በየዓመቱም ብሩ ራስ አሊ ትተውት የሄዱትን አገረ ገዢ የሚተካ እንዲሾሙበት ስጦታ ያቀርባሉ። ልክ ራስ አሊ እንደተመለሱም ብሩ አገረ ገዢውን ይገድሉና የሰጡትን ስጦታም ቀምተው የተገነባ ዓመት የዝናብ ወራት አብቅቶ ወንዞም ጎድሎ ራስ እስኪመጡ ለሌላ ጦርነት ያዘጋጃሉ። ጦርነቱ ጭካኔ የተሞላበት ነው። ተዋጊዎቹ ለጌቶቻቸው እንደሚበጁ ቢጤ ገዳይ ተብለው ይሞካሻሉ። ከጠላት ወገን የተሰለቡ የወንድ ብልቶች እንደዘውድ ይሰቀላሉ።

በኢትዮጵያ ሁኔታ የተመሰጠው በግሩም የቪክቶሪያ ስልት የተቃኘው ውጥቱ ፕላውደኔን ይህን ለማሻሻል ልቡ ተነሳሰቶ ነበር። ዓመታት ሲያልፉ የተነሳሳው መንፈሱ ሀገሪቱ ከነበረችበት የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ገፅታ ወደ ዓለም አቀፍ ይዞታ የማሻገር ምኞት አደረበት። ስለአየር ንብረቷ የነበረውን አድናቆት በየትኛውም ዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ቢል በጽሑፉ ገልጾታል። አፈሯ ለየትኛውም የእህል ዘር የሚመች፤ የእፅዋት እና አትክልቱ ስብጥር እንደሚያስደንቅ፤ አረንጓዴ መሬት

ለሻይ ተክል እልሚዎች፣ ወርቅ፣ መዳብና ፖታሺየም ደግሞ ለማዕድን አሳሾች ተሸከማለች ሲል ይተርካል። የወይን እርሻዋ የትኛውንም የቦርዶ-ሊስን ምርት ይፎካከራል። ከሕንድ ጋር ትመሳሰላለች። ግን አልተነካችም! የሀገሪቱ ብቸኛ ችግር ይላል ፐላውደን፣ አስተዳደር ነው። እጅግ ነውጠኛ የሆኑትን ገዢዎቿን የተረጋጋ እና ማማከርን ያካተተ ዲፕሎማሲ ሊያቀራርባቸው ይችላል።

ፒፓውን ማገ እና ቡናውን ተጎንጭቶ በቆዳ ጠፍር በተሠራው አልጋው ላይ ያጋደመውን እግሩን በጠርዙ ላይ አንጠለጠለው። ንፋሱ ግሩም ነበር። ቀዝፋውም የተስተካከለ ነው። እንግላንድ ለመድረስ ቸኩሏል። ከበስተኋላው የተወውንም አልዘነጋም። ጉዞው ወደአዲጋችነት ተሸጋገረ። የጀልባዋ ካፒቴን ለካስ አሳዋቂ ኖሯል። የፍየሏ ወተት ሲነጥፍ የመጀመሪያዋ ግልገል ሳላ ሞተች። ሊላኛዋ ጀዳ ላይ ከመስኮት ላይ ስትዘል ተደገመች። ሦስተኛዋ ደግሞ ጀልባዋ ከባሕር ቋጥኝ ጋር ተላትማ ስትሰባበር ሕይወቷ እዚያው ተቀጨ። ፐላውደን ብቻውን በስባሪው ጀልባ ላይ ተንጠላጥሎ ወደዳር መውጣት ቻለ። ለቀናት በሲና በረሃ በውኃ ጥም ጠውልጎ ሲታገል ከሞት አፋፍ ደርሷል። «እንዲያው በአንድ ጊዜ መሞት አይቻልም ወይ?» ብሎ እስኪያስብም መርርታል። እንዲህ ተዳክሞም ቢሆን ከሳምንት በኋላ ስዊዝ ደረሰ። ቀሪው የኢምባሲውን አባላት ከጀልባዋ አደጋ ተርፈው እዚያው አገኛቸው። ስጦታዎቹ ሁሉ ጠፍተዋል። ወይም ተበላሽተዋል። በዚህ ቢያበቃ መልካም ነበር። ይባስ ብሎ መልዕክተኛው ሰው ጀልባ ዳግም አታሳየኝ አለ። ፐላውደን ብቻውን ወደ ለንደን ተጓዘ።



## ምዕራፍ ሁለት

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ዋልተር ፐላውደን ኮቨንት ጋርደን ከሚገኘው ሆቴል ለውጭ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት መልእክት ላከ። እቅዱን በሁለት መንገድ ዘርዝሮ በእጅ ጽሑፍ ዘገባ አቀረበላቸው። የወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ፓመርስተን ነበሩ። እንደኢንግሊዝ ደግሞ ከ15 ዓመታት ቀደም ብሎም እንዲህ ያለ ተመሳሳይ ደብዳቤ ሲቀርብም እኚሁ ሰው ነበሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ። የመጀመሪያውን ደብዳቤ የላከው ዊልያም ኮፊን ነው። ኮፊን የየመን ገበሬ ልጅ ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ በመቆየቱም የሚናገረው እንግሊዝኛ መጠነኛ እስከመሆን ደርሷል። እሱ ያመጣው ከትግሬ ታዋቂ ሰው ለንጉሥ ጆርጅ 4ኛ የተላከ የወዳጅነት ደብዳቤ ነበር። ሆኖም የውጭ ጉዳይ ጽሕፈት ቤቱ ደብዳቤው ጠፋበት። መልስ እስኪሰጡት ኮፊን ለሦስት ዓመታት ለንደን መቆየት ነበረበት። ከዚህ አኳያ ፐላውደን ዕድለኛ ነበር። ፓልመርስተን አሁን ወዳያው በአክብሮት ነበር የተቀበሉት።

ወደ ሕንድ የሚወስደውን መንገድ ከፈረንሳዮች ለመከላከል ቀይ ባሕር ላይ እግርን መትከሉ አሁን ይበልጥ ጠቃሚነቱ የጎላ ሆኗል። ፐላውደን ስለንግድ አስተማማኝነቱ ያቀረበው ማብራሪያም አሳምኗቸዋል። እንግላንድ ውስጥ ባደረገው ጥቂት ቆይታ የወጣቱን ባሕርይ በመመርመርም ፐላውደንን በምዕዋ የከፍተኛው ተዕልኮ ቆንስላ አድርገው ሾሙት። ፐላውደን አሁን በዓመት 500 ፓውንድ ይከፈለዋል፤ ለራስ አሊም ስጦታ የሚያቀርብበት ተጨማሪ 400 ፓውንድ በጀት እንዲሁም በንግሥት ቪክቶሪያ የተፈረመ ደብዳቤም እንዲሁ ለራስ አሊ የሚያቀርበው 19 ነጥቦችን የያዘ ውል በእጁ ገብቷል።

ከስድስት ወራት በኋላ ፐላውደን ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። በእነዚያ የሰሜን ተራሮች መካከል ዳግም መግባቱ ደስታን ፈጥሮለታል። የጎንደርን መንገድ ተያያዘው። ወደ ሰሜን ተራሮች ከፍታ ሲወጣ አየሩ ይቀዘቅዝ ጀመር። የገደሎቹ ዳርቻ ካንዱ ጠባብ መተላለፊያ ወደሌላው ያሸጋግራል። ከታላቁ ሐይቅ ጣና በስተቀኝ በኩል ወዳለው የራስ አሊ ግዛት ገባ። ጓዙን እየጎተተም ደብረ ታቦር ዋና ከተማ ደረሰ። እዚያ እንደደረሰም ከራስ መኖሪያ ቤት ፊት ለፊት የቀድሞ ወዳጁን ጆን ቤልን አገኘው። በሕዝቡ መካከል እየተጋፋም በርካታ የቀድሞ ወዳጆቹን ያቅፍ ገባ። ድንግዝግዝ ማለት በጀመረው ጀንበርም ራስ አሊን ከመሬት በበሬ ቆዳ ላይ ተቀምጠው ችሎት ሲያስችሉ፣ ሠራተኛ ወንዶች እና የችሎት ሰዎች፣ ፈረሶች፣ ዝንቦች እና ልጆች ከበዋቸው አገኙ።

ራሱ ፐላውደን፣ «ሲመለከቱኝ በጣም ተደሰቱ፣» ብሎ ጽፏል። «ወዲያውም ምን ይገርሳቸው እንደመጣሁ የጥያቄ ናዳ አዥጎደጎዱ።»

እንደመጣ ካገኛቸው በኋላ ፕላውደን ወደሚገረፊያው ሄደ። የመጀመሪያው የራሱ ጥያቄ በተደጋጋሚ ካለበት ድረስ ደርሶታል።

«ስጦታዎቹን አዩኢ ልያቸው?» «ጠብመንጃ አመጣህ?»

ፕላውደን ምንም አልመለሰም። በሁለተኛው ቀን ወደ ራስ ችሎት ቀረበ እና ከንግሥት ቪክቶሪያ የመጣውን ደብዳቤ አነበበላቸው።

«ከበርናትዎ ተዕለኛው ከፀሐይ መውጫ እስከመጥለቂያዋ ከሆነው ከሉዓላዊቱ የብሪታኒያ ግዛት ጋር ኢትዮጵያ የሚኖራት የቅርብ ትሥሥር ትልቅ ጥቅም መሆኑን ይገነዘባል ብለን እናስባለን።» ቅልጥማሙን ፕላውደንን ራስ አሊ ከእግር እስከ ራሱ ተመለከቱት። «ፈረንጁ ምን አቶመው?» በሚል አይታ። ንባቡን ቀጠለ.........

«.....መርከቦቿ መሬትን ከሚያገናኙት ባሕሮቿ ላይ ከሚጋጠሙበት ......» ራስ አሊ ለሰባሕር የሚያውቁት የለም።

ፕላውደን ቀጠለና ስጦታዎቹን በፊታቸው ዘረገፈው። አፈ ንጉሡ ጠጋ ብለው «እያንዳንዱን ተራ በተራ ይሻላል።» ሲሉ ሹክ አሉት። ፕላውደን አልተቀበላቸውም። ንግሥቲቱ ግድ እንደሌላቸው ብቻ ነገራቸው። ለጥ ብሎ እጅ ነሳ እና ፀሐይ ለማግኘት ወጣ። ፕላውደን አሁን ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ሀገሩ ሲመለስ እንደነበረው ወጣት እና ጉጉው ፕላውደን አይደለም። አሁን የብሪታኒያዊቷ ንግሥት ቆንስላ ነው፤ እናም ራሱን ለማግባባት ሳይሆን ይህን ሥልጣኑን ይተውናል። ቀናት ሲያልፉ ራስ አሊ የተለመደ ጥያቄያቸውን ይጠይቁት ጀመር። ተጨማሪ ስጦታ። «ማስታወስ አያስፈልግም» ይላል ቆንስሉ። «እነዚያን በየአምስት ደቂቃው ያታክቱኝን የልጅ የመሰሉ ጥያቄዎች ማስታወስ አያስፈልግም።» ቀኖች አለፉና ፕላውደን ውል የመፈረም ጥያቄን አነሳ። ራስ በተራቸው ይቀልዱበት ጀመር። በእያንዳንዱ ስብሰባ ፕላውደን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የጉዳዩን ምንነት መተረክ ይኖርበታል።

«ይህ ውል በትክክል ምንድነው? »

«ለእኔ ምን ይጠቅመኛል? »

ፕላውደንም በየጊዜው ማስረዳት ይኖርበታል። «ሁለቱ ሃገራት ወዳጅነት እንዲመሰርቱ ነው።» በየጊዜውም ፕላውደን ስጦታ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል። እየቆየም ለራሱ ካመጣው ሁሉ ይዞ ይመጣ ጀመር። መጀመሪያ ከግብፅ ያመጣውን በባሩድ ዱቄት የሚተኮስ ጠብመንጃ፣ ቀጠለና ለራሱ መከላከያ

የያዛቸውን ጠብመንጃዎች እና ሽጉጦች አበረከተ። ይህም ሆኖ ራስ አሊ ስምምነቱን አልፈረሙም።

ከዚያም ፕላውደን የለመደውን ድምጽ ሰማ። የንጉሡ ድንኳኖች ከተተከሉበቸው ከደብረ ታቦር አካባቢ የራስ ነጋሪት ይጎሰም ጀመር። በሺህዎች የሚቆጠሩ ነፍሶች ተሰባሰቡ፤ ጓዛቸውን ሸከፉ፤ ድንኳኖቻቸውን ፈቱ፤ በጎች እና ከብቶቻቸውንም ሰበሰቡ። መሪዎቹም እጅ ጠባባቸውን አወለቁ፤ ወንዶች ከቤታቸው እየወጡ ከሚተመው ሠራዊት ጋር ተቀላቀሉ። ራስ ወደ ጦርነት እየዘመቱ ነው። በየዓመቱ ከብሩ ጎሹ ጋር ለሚያደርጉት ጦርነት ተንቀሳቀሱ። ፕላውደን ውሉን ይዞ እሳቸውን ከመከተል ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረውም።

የአባይ ሸለቆን አቋርጠው ወደጎጃም ተሻገሩ። ወደ ብሩ ጎሹ ምድር። ብሩ ተራራ ላይ ጠንካራ ቦታውን ይዟል። አሊ ከታች ሰፈሩ። ዝናብ ወረደና መሬት አጨቀየው። ዝናቡ ሲያባራ የራስ አሊ ጦር ጓዙን ጭኖ ተነሳ። በዚያን ጊዜ ነበር ራስ አሊ ፕላውደንን ያስጠሩት። ውሉን ለመፈረም ዝግጁ ነበሩ።

በተከበረው ንጉሣዊ ድንኳናቸው የተቀመጡት ራስ አሊ በዚያን ሰዓት ከሰዎቻቸው አንዱ ከሆነው ጋር ስለፈረስ ጉዳይ ይነጋገራሉ። ፈረሱ በአቅራቢያቸው ቆሟል። ጸሐፊያቸው በአማርኛ የተዘጋጀውን ውል ማንበብ ጀመረ።

«ይህ ውል ጠንካራ ይሆናል፤ በአቢሲኒያ ንጉሥ እና በኢንግላንዱ ንግሥት መካከል በእኩልነት እና በዘላለማዊ ወዳጅነት ይመሠረታል።......»

ራስ አሊ ስለፈረሱ ማውራታቸውን ቀጠሉ።

«ጌታዬ እባክዎን....... ይስሙኝ»

ራሳቸውን በአዎንታ አነቃነቁ።

«የአቢሲኒያ ንጉሥ የኢንግላንድን ንግሥት መልዕክተኞች ወይም ቆንስላ ይቀበላል። ከለላም ያደርግላቸዋል። ......... በተመሳሳይ የኢንግላንድ ንግስት የአቢሲኒያን ባለስልጣኖች ትቀበላለች ከለላም ታደርግላቸዋለች። ...... »

19ኙም አንቀፆች ተነብበው ሲያበቁ ሁሉም ወደራስ ተመለከቱ። ራስ በበኩላቸው ወደፈረሱ እየተመለከቱ ለስላሳ ጎኖቹን እና ጠንካራ እግሮቹን ያደንቁ ጀመር።

«በዚህ ውል ውስጥ ምንም ጉዳይ አይታየኝም ሆኖም ርባና ቢስ ይመስላል። አሁንም እንደሚታየው ሀገሪቱ ለነጋዴዎች ምንም አትጠቅምም። በ10 ዓመትም ሆነ ከዚያ በላይ ቢቆይ እዚህ መድረስ የሚችል የእንግሊዝ ነጋዴ አይኖርም።»

ሆኖም ግን ውሉን ፈረሙ። ፕላውደንም ወደ ባህሩ ጠረፍ ለመጓዝ ተዘጋጀ። ነገ
ግን ራስ አሊ እንዲሄድ አልፈለጉም። ፕላውደን ያለውን ምርጥ የጦር መሣሪያ
እንዲሰጣቸው ጠየቁት። እሱ ግን ፈቃደኛ አልነበረም። ቀናት አለፉ። ስንቁ እያለ
ትዕግስቱም እየተሟጠጠ ሄደ። ከብዙ ዓመታት በፊት እዚያ እንደነበሩት
የፖርቱጋል ልዑካን የብሪታኒያው ልዑክም ባልሰለጠነው የአቢሲኒያ ተራራማ
ስፍራ እስረኛ የሆነ መሰለው። ተስፋ ቆረጠ። በመጨረሻም ምርጡን መሣሪያውን
ለራስ አስረከበ ወደ ምፅዋ ተጓዘ። እዚያም በግዛቲቱ የሰላም አየር እስኪያገኝ ድረ
በመቆየት ነጋዴዎች እና የኪነጥበብ ሰዎችን በማግባባት ራስ አሊ የሚያስቡት
የተሳሳተ መሆኑን ለማረጋገጥ ወሰኗል።



## ምዕራፍ ሦስት

የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ማለቂያ ባጣው የእርስ በርስ ጦርነት አዙሪት ብቻ አይደለም የተንገላቱት። ያለፈው ገናና ታሪክ መኮሰስም እንዲሁ በጅምላ ጎድቷቸዋል። በእነሱ አይታም ራስ አሊ ሥልጣኑን በኃይል የያዙ ነበሩ። ራስ ኦሮሞ ናቸው። ኦሮሞዎች ደግሞ እነሱ የሚጋሩትን ከቀድሞው ዘመን ጀምሮ በእግዚአብሔር አገኘነው ከሚሉት በረከት አይጋሩም። ኦሮሞዎች ከብት አርቢዎች እና አብዛኞቹም የእስልምና እምነት ተከታዮች ነበሩ። በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ወደ ደጋማው አካባቢ የተስፋፉት። በጦርነት ወቅት ፍርሃት አይታይባቸውም። የንጉሡ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ንጉሡ ለጦርነት የሚያዘምቱት እነሱን ነበር። የክርስቲያኑ ዘመን ሲዳከም ኦሮሞዎች ተጠናከሩ። በ1795ዓ. ም የራስ አሊ አያት ራስ ጉግሣ የሀገሪቱ መሪ ሆኑ። ተከታዮቻቸውም እምነታቸውን ወደ ክርስትና ለወጡ።

ራስ ጉግሣ ለ22 ዓመታት ገዙ።የክርስቲያን ዜና መዋዕል ፀሐፊው አለቃ ዘነብ ለእሳቸው እናድርም ያሉ ወንዶች ብልታቸው፣ ሴቶች ደግሞ ጡታቸው እንዲቆረጥ ተደረገ ይላሉ። በ1830 የ12 ዓመቱ ራስ አሊ የሥርወ መንግሥቱ የበላይ ሆነ። በልጅነት ዘመኑም እናቱ መነን አገረ ገዢ ነበሩ። የወቅቱ ዘገባዎች ጊንጥ እና አፍረተቢስ ሲሉ ይገልጿቸዋል። በአንድ ወገን ከፈረሰው ከጎንደር ቤተ መንግሥት ተቀምጠው ነበር ሀገር የሚመሩት፤ በተፈረካከሰው ግንብ ውስጥ ሆነው ሳይታዩ የችሎቱን ጉዳይ ልቅም አድርገው ይከታተሉ ፤ ፍርድ ይበይኑ እንዲሁም ትዕዛዝ ያስተላልፉ ነበር። ከውጭ ለመግባት የማይፈቀድላቸው እጅግ በርካታ ገበሬዎች እና ወታደሮች፤ ታዋቂ ሰዎች እና ጥላ ያገኙ፤ ቀሳውስት እና የኔ ቢጤዎች ተሰባስበው ጉዳያቸው እንዲሰማ ይጮኹ እንደነበር ፕላውደን ጽፏል። ከእነሱ መካከልም በእሳቸው ትዕዛዝ ዓይኑ የጠፋው ሰው ዘወትር ከቤተ መንግሥቱ ደጃፍ ይቀመጥ ነበር።

የቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች ከ330 ዓ. ም ጀምሮ ክርስቲያኖች ሲሆኑ የዘር ሐረጋቸውን ግን ከንጉሥ ሰሎሞን እና ንግሥተ ሣባ ትስስር እንስተው የሚቆጥሩ ነበሩ። ሆኖም ከዓመታት በኋላ ይህ እየቀነሰ መጣ። ንጉሥ የሚሾሙት እና የአካባቢው ገዢዎች ንግሥት የሚሆኑትን ሴቶች ከውልደታቸው ጀምሮ ከሚጠበቁበት ተራራው አናት ላይ ከሚገኘው እስር ቤት እየመረጡ ያመጣሉ። ግን በንግሥናው መንበር ብዙም አይቆዩም። ጎንደርም ከመንበራቸው በተፈናቀሉ ነገሥታት ተሞልታ ነበር። *አብዛኞቹም ንግሥና ተቀብለው ከዙፋናቸው ከተነሱ በኋላ ዳግም የተቀቡ ናቸው። ተክለ ጊዮርጊስ ለምሣሌ ስድስት ጊዜ ዘውድ ጭነዋል። መነን ራሳቸውም ቢሆኑ በ1840 አንዱን ንጉሥ ነገሥት ዮሐንስ 3ኛ ብለው አንግሠው ነበር። በወቅቱ 16 ዓመቱ ሲሆን እቴጌነቱን ለመያዝ አገቡት።

ከዙፋኑ ላይ በተደጋጋሚ ሢቀመጥ እና ሲነሳ በመቆየቱም ጠጪ ሆነ። እንደውም የሐንስ ሞኙ የሚል ቅፅል ተሰጠውና አረፈው።

የደጋው አካባቢ ነዋሪዎች ክርስቲያኖቹ ገበሬዎች ለረዥም ዘመን መሬታቸው በሽፍታዎች እና በአካባቢው ጦር እንዳልነበረ ሲሆን መንፈሳቸውን የሚያሳርፍላቸው እምነታቸው ብቻ ነው። ካህናቱ ከኢያሱ ዘመን አንስተው እንስከ ንጉሥ ዳዊት ጊዜ የነበረውን ታሪክ እንዲያስተውሉት ይተርኩላቸዋል። የእስራኤል ልጆች በዘመነ መሳፍንት ያሳለፉትን ሲታይም ያስታውሷቸዋል። በብሉይ ኪዳን ያልተደረገ ነገር አሁን እየተደረገ እንዳልሆነም ያሳስቧቸዋል። እናም ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በዘመነ መሳፍንት ውስጥ እየኖሩ መሆኑን ይረዳሉ። የገጠማቸው ፈተናም በኃጢያታቸው ዋጋ የመጣ ቅጣት ነው። እናም እግዚአብሔር አመፀኛ ልጆቹን ሊቀጣ መሳፍንቱን ላካቸው፤ አንዱ ቀንም ይህ እንዲያከትም ያደርጋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ታላቅ መሪ ተነስቶ የክርስትናን ክብር ደግሞ እንዲያብብ እንደሚያደርገው ለረዥም ጊዜ የተነገረና የሚጠበቅ ትንቢት ነው። መሣፍንቱ በድርጊታቸው በገፉ መጠን ኢትዮጵያውያን ደግሞ ፍካሬ ኢየሱስን ይዘክራሉ። የኢትዮጵያን ትንሣኤ የሚያሳይ መሪ ይነሳል። ጠላቶቹን አጥፍቶ ሰላምን ያጎናጽፋታል። ይህ መሪ ደግሞ ቴዎድሮስ ይባላል። በ1830 በደጋማው አካባቢ ሹክሹክታ ይሰማ ጀመር። ወሬው ተዛምቶም በጣና ዳርቻ ኖኘ። ወደበጌምድር መንደሮችም ተሰራጨ በጎንደር ድንጋያማ ጎዳናዎችም ተዛመተ። መጣ! ቴዎድሮስ መጣ!

በቀሐ ወንዝ አካባቢ ወጣ ብሎ መሲሁ ራሱ ጥሩምባ ማሰማት ጀመረ። «ቴዎድሮስ የተባልኩት ንጉሥ እኔ ነኝ!»

ጎንደር ውስጥ ለአራት ትውልድ ሲገዛ የነበረው አሻንጉሊቱ ንጉሥ ሣህለ ድንግል የአዲሱን ንጉሥ መምጣት ሲሰማ ልክ እንደ ሄሮድስ ነበር የሆነው። ተነሳ እና ተዋጋው፤ በቀናት ውስጥ በዝንብ የተከበበው የቴዎድሮስ ጭንቅላት በጎንደር አደባባይ ተሰቅሎ ታየ። ራስ አሊ እና መነን ከሥልጣናቸው አልተነሱም። ጦርነቱ ቀጠለ፤ ዘመነ መሳፍንትም እንዲሁ።

# ምዕራፍ አራት

በባሕር ወደቡ አካባቢ ዋልተር ፕላውደን ከከባዱ የምፅዋ ሀሩር ለመሸሽ ወደ የቦስ ግዛት ጥቂት ማይሎች ገባ ብሎ መኖር ጀምሯል። ሙቀቱ መጠነኛ በሆነባት ምንክሉ ለራሱ ከዘንባባ እና ከሸንበቆ ጎጆ ቀልሷል። ከቆፈረው ጉድጓድ ያወጣው ውኃ በመስኖ በአካባቢው ያሉትን ተክሎች ያጠጣል። ዛፎችንም ተክሏል። በዚህ ስፍራ ለአስር ዓመታት መቀመጡ ኃይሉን አሟጥጦታል። በየጊዜው ይታመማል። ቆፍቶንም በመስላቸት እና በተከሳት አልጋው ላይ ተጋድሞ ያሳልፋል። ያስፈረመው ውል ያመጣለት ነገር የለም። ወደ ውጪ የሚወጣም ሆነ የሚገባ ንግድ የለም። የእውቀት ሽግግር የሚባልም የለም። ራስ አሊ ልክ ነበሩ። ፕላውደን በሚችለው ልክ የቆንስላነት ተግባሩን አከናውኗል። ስለባሪያ ንግድ፤ ስለፈረንሳዮች እንቅስቃሴ፤ ስለሚስዮናውያን ወደ ለንደን ሪፖርት ልኳል። በየሩብ ዓመቱም ደመወዙን ያገኛል። «በተሸከምኩት አገልግሎት በመቆየቴና ኃላፊነቴን በመወጣቴ ኩራት ይሰማኛል፤ እውነቱ ግን ያን ያህል አለመሆኑ ነው። የስም ቆንስል ነኝ።» ሲልም ጽፏል።

ምፅዋን ጠላው። ወበቅ እና ጭጋግ ያለበት የአየር ጠባዩም ቀፈፈው። «የቱርክ ባሮች ማከማቻ» ሲል ሰየመው። እሱን እና ሌሎች አውሮጳውያንን ከአካባቢው ጠራርገው ለማባረር ተስፋ የሰነቁት የኦቶማን ገዢዎች በትርጉም የለሽ ገደቦቻቸው እንዳይንቀሳቀስ ጠፍንገውታል። በተለይማ የመጨረሻው ፓሻ ለቆንስሉ ለየት ያለ አደጋ ነበር። በጉቦ፤ በጭቆናና በአስተዳደር ብልሹነት ፕላውደን ደጋግሞ ቅሬታ አቅርቦበታል።

አንድ ቀን ፕላውደን የውኃ ጉድጓዱን ዳግም ማስተካከል ፈለገ፤ ፓሻው ከቆስጥንጥንያ ፈቃድ ካላመጣ አንዲት ድንጋይ እንኳ ማንሳት እንደማይቻል ቁርጡን ነገረው። በቀናት ውስጥ ታዲያ እነዚያ በበረሃ ያጸደቃቸው ተክሎች እጁ ላይ እየጠወለጉ ከአፈር ተደባለቁ። በእነዚያ ዓመታት ፕላውደን በቻለ ጊዜ ሁሉ ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ግዛት ይሄዳል። ከተራራው የሚነፈሰውን ንፁሕ እና ቀጥቃዛ አየር እየማገ ከርቀት ያሉ አካባቢዎችን ዘቅዝቆ ማማተር ከሚቻልበት ከፍታ ድረስ ይዘልቃል። በሚንቆረቆረው ጅረት ገላውን ታጥቦም ቀዝቀዝ ባለው ምሽት ጥሩ የእንቅልፍ ጊዜ ያሳልፋል። ጆን ቤልን አግረ መንገዱን ይጎበኛል፤ በዚያውም ራስ አሊ ድል ቀንቷቸው አማፅያኑን ከአካባቢው አባርረው እንደሆነም ለመስማት። ይህ ከሆነም መኖሪያውን እዚያው ከደጋው ለመቀለስ።

በ1850 ድንገት የራስ አሊ ቀንደኛ ጠላቶች ደጃች ካሣ እና ደጃች ውቤ ከእጃቸው ወደቁ። ለዘመቻ የተጠሩት እነዚያ ደጃዝማቾች በሺ ከነሚቆጠረው ሠራዊታቸው ፈጥነው መጡ። በመላ ሀገሪቱም አስገራሚ ሰላም ሰፈነ። ሕዝቡም ዘመነ «መሣፍንት አከተመ ይሆን?» ማለት ጀመረ።

በጥር ወር በ1853 ፕላውደን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሚገኙ አለቆቹ በጻፈው ደብዳቤ፤ «ከራስ አሊ ሀገረ ገዢዎች አንዱ ደጃች ካሣ አመፁ።» በማለት ገልጾ፤ አክሎም የራስ ሥልጣንም ሆነ ኃይል ከእንግዲህ ብዙም ፋይዳ ሊኖረው እንደማይችል ዘርዝሯል።

ከአራት ወራት በኋላ የአማፅያኑ መሪ በራስ አሊ እና በደጃች ውቤ ላይ ወሳኝ ድል ማግኘታቸውን ጻፈ። ከሁለት ቀናት በኋላ ቀጠለ፤ «ደጃች ካሣ ጦራቸውን አጠናከሩ» ከሦስት ቀናት በኋላ፤ «ደጃች ካሣ ራስ አሊን ድል አደረጉ።»

ዜናዎቹ በብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚገኙ ባለስልጣናትን አላስደሰቱም። በቆንስላቸው አማካኝነት ስለኢትዮጵያ የሰሙት በሙሉ የውስጥ ትርምስን የሚያንፀባርቁ መጥፎ ዜናዎች እና ከቱርክ ፓሻዎች ጋርም ቢሆን ማለቂያ የሌለው ፀብ ነው። በአፀፋው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚከተለውን ጻፉለት። «የእንግሊዟ ንግሥት መንግሥት ባንተ አማካኝነት ከአቢሲኒያ ገዢዎች ጋር ስምምነቶችን በመፈራረም የብሪታንያን ጥቅሞች እንድታስከብር አጋጣሚውን ለመጠቀም ቢሞከርም የላከው ሪፖርት እንደሚያሳየው የተጨበጠ ነገር የተገኘ አይመስልም።»

ፕላውደን የግዱን ተስማማ። በ1854 ሐምሌ 10 ቀን በቆንስላነት ከተመደበ ከስድስት ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው፤ ለመጀመሪያ ጊዜ እረፍት ጠየቀ። ምላሽ እየጠበቀ ሳለም አዲስ አጋጣሚ ተከሰተ። ስለካሣ ወሬዎች መናፈስ ጀመሩ። ፕላውደን የተለመደ ነገር በደጋው አካባቢ ይኖራል የሚል ግምት ነበረው። ሰላም አደፍራሹ ደጃች ካሣ ሰላም አስፋኝ ሆኑ። ፕላውደንም የጉዞ ዕቅዱን አራዘመ።

በመጋቢት መባቻ በ1855 ለሎርድ ክላረንደን እንደጻፈው ደጃች ካሣ የመጨረሻውን ጠላታቸውን ደጃች ውቤን ድል አደረጉ። «በመጨረሻም አቢሲኒያ የንግሥቲቱን መንግሥት ወዳጅነት እና ድጋፍ ማግኘት የሚገባው በሉዓላዊ አስተዳደር ሥር አንድ የመሆን ዕድል ይኖራት ይሆናል።» ፕላውደን ስለአዲሱ ገዢ በሰማ ቁጥር ይበልጥ ይደሰት ጀመር። ደጃች ካሣ በይፋ የባሪያ ንግድን አስቀሩ፤ በጦር ሜዳ ላይ ግዳይ ጥሎ መስለብንም በአደባባይ ተቃወሙ። ለፕላውደንም ከአውሮጳውያን በተለይም ከእንግሊዝ መንግሥት እውነተኛ ወዳጅነት እንደሚፈልጉ በጽሑፍ ገለጹለት። ካሣ ዘውድ መጫናቸውን ፕላውደን ሲሰማ ፈነደቀ። ወደብሪታንያ ሊያደርግ ያሰበውን ጉዞ ሰርዞም ፊቱን ወደኢትዮጵያ መለሰ። እንዲህ ያለውን አጋጣሚ ሲጠባበቅ አስር ዓመት ሊሞላው ነው። ከእነሱ ይበልጥ ነፃ ማሻሻያዎችም ሆኑ የውጭ ግንኙነት ምንም ትርጉም የማይሰጣቸው ኢትዮጵያውያን ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብሎ ዘውድ የጫነውን መሪ ለማየት ረዥም ዘመን ጠብቀዋል።

## *ምዕራፍ አምስት*

ቴዎድሮስ ሁለተኛ ተብሎ የተቀባው ንጉሥ ካሣ ኃይሉ እንዴት እንደተነሳ በየመንደሩ እና በኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች የሚነገር ታሪክ አለ። ታሪኩ እየሰፋ እና እያደገ የሚሄድ ነው። እንደውም በአሪት ዘመን ከነበሩት የሕዝብ ጀግኖች፣ ቅዱሳን ወይም ታላላቅ ሰዎች ጋር የሚመሳሰል ይመስላል። ዜና መዋዕሉ ከሰሎሞን አባት ከንጉሥ ዳዊት ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ንጉሥ ዳዊት ነው ኢትዮጵያውያን ለረዥም ዘመን ታግሠው የጠበቁትን ዘመነ መሣፍንት እንዲያከትም ያደረገው። የእርሱ ታሪክ እና በመዝሙረ ዳዊት የተዘመረው ሁሉ ዳዊትን በቃላቸው እየደገሙ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ለእርሱ እንደተበረከተ ይቆጥሩታል። ካሣ በልጅነቱ ዳዊትን ጠንቅቋል። ኋላም የዳዊትን ታሪክ እና የመዝሙሩን ውበት እንዳስፈላጊነቱ ሲጠቀምበት ታይቷል። በአካል እሱን ያገኙት በሄደበት ሁሉ ዳዊቱን አንግቦ እንደሚጓዝ ይናገራሉ። በ1860ዎቹ መጀመሪያ ገደማ ወደኢትዮጵያ የመጣው ሔንሪ ዳፍተን «የንጉሥ ዳዊትን አርአያነት እና መገለጫ አሳቸው የሚያደርጉትን ለማረጋገጫ እንደመለኪያ አድርገው ይወስዱታል።» ሲል ገልጾታል።

እንደው የሆነው ነገር ግን የካሣ የቀድሞ ሕይወት ከወጣቱ ዳዊት ሕይወት ጋር አይመሳሰልም፤ አካላዊ ኃይላቸው፣ ወታደራዊ ጥበብ፣ እንዲሁም የእያንዳንዳቸውን ሰብዕና የቀረፀው የሕይወት ፍሰት አይገናኝም። እንደዳዊት ካሣ ከንጉሣዊ ቤተሰብ አልመጣም።

በ1811 ዓ. ም ገደማ ካሣ ተወለደ። አባቱ ደጃች ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ፤ ካሣ ገና ትንሽ ሆኖ ነው የሞቱት። የእናቱ ማንነት ዘመኑን ሁሉ ሲያስቸግረው ኖሯል። ጠላቶቹ እናቱ የሠራዊቱ ተከታይ የነበረች እና ወደ ደጃች ኃይሉ ድንኳን ሾልካ የገባች ናት ይላሉ። ኮሶ ሻጭ እንደነበረችም ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ አስገራሚ ውበት የተጎናጸፈች ታዋቂ ሴት ነበረች ሲሉ ይሰማል። ያም አለ ይሄ፤ እሷ ነበረች፤ አትጠግብ፤ ካሣ የቄስ ትምህርት ለረዥም ዓመታት እንዲማር የገፋፋችው። መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ወደ ሀገሪቱ የመጡ ሚሲዮናውያንን ያጥፉቸው ነበር። አረብኛም ጠንቅቆ አወቀ።

በወጣትነቱ በገዳመ ማሕበረ ሥላሴ ሳለ በጦር አበጋዞች ገዳሙ ጥቃት ደረሰበት። አዳዲሶቹ ገዳማውያን ሲታረዱ እና ሲኮላሹ ካሣ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት አመለጠ። ብዙም ከማይታወቅ ጎሣ ጋር ተደባልቆ በዱር በገደሉ ኑሮውን አደረገ። በደኑ ተጠልሎ ዋሻ ውስጥ ተቀመጠ።

ለጦር ያለው ጥንካሬ፤ የፈረስ ግልቢያ ችሎታው፤ ድፍረትና ዕድሉ በዙሪያው ያሉትን ሳባቸው። ከ12 ዓመት ከፍ ቢል ነው። አንዳንዴ እሱ እና ጓዶቹ ጭነት

ይዘርፋሉ፤ ወይም የኦሮሞ ተዋጊዎች ላይ ጥቃት ያደርሳሉ፤ ከዚያም የዘረፉትን ያከፋፍላል። ልክ ዳዊት ከአማሌቃውያን የመዘበረውን እንዳከፋፈለው።

ዓመታት አለፉ። ካሣ ከቆላው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ይዋጋል። ድሎቹ በፍጥነት ከፍ እያሉ ሄዱ እና እሱም ይህ ምሥጢር በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት እንደተከናወነ መስሎ ታየው። ከባድ ድርቅ ተከሰተ። ደጋማውን አካባቢም አዳረሰው። ራስ አሊ እና እናታቸው ለሕዝቡ ምንም ማድረግ አልቻሉም። ካሣ ተከታዮቹ የዘረፉትን እህል ይዘዋል፤ መሣሪያ እንዲገዙበት ካሣ ለሕዝቡ ገንዘብ ሰጠ። ከዚያም ራሱ አብሮ እየተራዳ ደኑን መንጥረው እህል ዘሩ። ጠፍ የነበረውን መሬት እንዴት አረንጓዴ ማልበስ እንደሚቻል አሳያቸው። የከፋቸው፣ እዳ ያለባቸው፣ ደስተኛ ያልሆኑ ሁሉ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ።

ጎንደር ላይ እቴጌ መነን የራስ አሊ እናት የካሣን መነሳት ሲመለከቱ፤ ሠራዊታቸውን እዘመቱበት። ዘግይቶ ነበር። የእቴጌይቱ ጦር ወደ ካሣ ሲሄድ በነበረው ዝናብ ብቻ ብዙም ሳይዋጋ ሸሸ። እቴጌይቱ፣ ራስ አሊና የኦሮሞ አለቃዎች በጣም ተቆጡ። በሕዝቡ ዘንድ ካሣ ከእነሱ ይበልጥ ድጋፍ ነበረው። ከእነርሱ ጋር ግንባር ይፈጥር እንደሆን ጠርተው ጠየቁት። መነን እና ራስ አሊ «ከእኛ ጋር ከሆንክ ያደረግከብንን ሁሉ ይቅር እንልሃለን።» አሉት። ካሣ ግን «እምቢ» አለ። የራስ አሊን ልጅ ተዋበችን እንዲያገባት ሰጡት።

«እናም ሳኦል ዳዊትን ትልቋን ልጁን መርአብን ውሰድ፤ ሚስት እንድትሆንህ እሰጥሀለሁ፤ ነገር ግን ጀግንነትህን ለእኔ ብቻ አሳይ።»

ካሣ በጣም ተገረመ። የራስ አሊ ልጅ በውበቷ የተደነቀች ናት። ስጦታውን ተቀበላቸው።

«ዳዊትም አለ፤ እኔ ማን ነኝ? ሕይወቴስ ምንድነው? የንጉሡ አማች ልሆን በእስራኤልስ የአባቴ ቤተሰብ ምንድን ነው? »

እናም ካሣ ሊያጠፋው የተነሳውን የገዢዎች የዘር ሐረግ ከዚያ በተገኘችው ሙሽራ ባይሠራም እንድትጠግነው ታለመ። ሆኖም ምንም እንኳን በአባቷ እና በአያቷ ላይ እያመፀ ችግር ቢፈጥርም እሷ ለእሱ ታማኝነቷን አፀናች፤ እንዲሁም እሱ ለእሷ። ምናልባትም ነፍስ ካወቀ በኋላ እምነት የጣለባት እሷ ብቻ ናት።

## *ምዕራፍ ስድስት*

በመዋዕለ ዜናው ስለካሣ የመጀመሪያ ሕይወት እና ወደ ስልጣን አመጣጡ የሚተርኩ አራት አጫጭር ጽሑፎች ብቻ ናቸው የሚገኙት። በምዕራባዊ ቆላማው ግዛት ስለነበረበት ጊዜ ይተርካሉ። የተጻፉት በአረብኛ ሲሆን በኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበር ለሚገኙት የአካባቢው ገገሮዎች የተላኩ ናቸው። ጀግኖች በዙሪያው ከተሰበሰቡ ሽንፈትን ከማያውቀው ድፍረት የተሞሉ ነበሩ። ጀግኖች በዙሪያው ከተሰበሰቡ ሽንፈትን ከማያውቀው ድፍረት የተሞሉ ነበሩ።

በ1838 ካሣ ድፍረት የተላበሰ ርምጃ ወሰደ። እቴጌ መነን ዋና ከተማ ጎንደርን ከነሠራዊታቸው ለቀው ሲወጡ፤ ካሣ ወደዚያው ተጉዞ ከተማዋ የእርሱ መሆንዋን አወጀ። አሁን ካሣ መናገሻዋን ከተማ ብቻ ሳይሆን እስከ ጣና እና ከዚያም አልፎ ሀገሩን ተቆጣጠረ። በ1839 ሰኔ ወር እቴጌ መነን ካሣን ጦርነት ገጠሙ። ካሣ ድል አደረገ። እቴጌይቱን ከሰሎሞን ዘር ከተገኙት ንጉሠ ነገሥት ባለቤታቸው ዮሐንስ ሞኙ ጋር በቁጥጥር ሥር አዋላቸው።

በ1844 ራስ አሊ ካሣ ላይ ጦር አዘመቱ። የጦሩ መሪ የብሩ ጎሹ አባት ራስ ጎሹ ነበሩ። የሁለቱም ጦር ጉራ አምባ ሜዳ ላይ ከተመ። የጎሹ ሰዎች ካሣን እንዲህ ባለ ገላጣ ስፍራ በማግኘታቸው ተደሰቱ። በቁጥር እና በትጥቅም ይበልጣሉ። የጎሹ አዝማሪ በወታደሮቹ ፊት ቆሞ ሊያነቃቃቸው ስለካሣ መዝፈን ጀመረ።

ይህን አላዋቂ እስኪ በሉ ተመልከቱታ

ጉራ አምባ ድረስ አስከትሎ መጣ እምስት ጋለሞታ ፤

እንዲያም ሆኖ ድል የካሣ ሆነ። ጎሹ ተገደሉ፤ ጦራቸውም ሸሸ። ብዙዎቹም ተማረኩ። አዝማሪውም አልቀረለትም። ካሣ «የቅድሙን ዘፈን እባክህ ድግመህ አሰማኝ፤» አለው። በለመደ አፉ ደገመና አዜመው። ሲጨርስ ካሣ በጅራፍ ይገረፍ ዘንድ ፈረደ። በግርፊያውም ሞተ። ራስ አሊ ከየግዛታቸው የጦር ኃይላቸውን ሰበሰቡ። ከወሎ እስከ ጎጃም፤ ከላስታ እስከ በጌምድር፣ የነጋሪት ድምፅ ተሰማ። ውቤም ጦር እንዲልኩ ጠየቁ። በብሩ አሊጋዝ እዝ ሥር አሰለፏቸው። በ1845 ሚያዝያ ወር በካሣ ላይ ዘመቱ ወደ ጣቁሳ። በሠራዊቱ ዘንድ ጎላ ያለ በራስ መተማመን ይታይ ጀመር። «ይህ ቆለኛ!» ይሉ ጀመር የራስ አሊ ሰዎች። «ይህ በርበሬ ተካይ እስኪ ይምጣና ይግጠመን?!»

«እንዴት ይደፍረናል? እኛ የእርሱን እስር እንሆናለን!»

«እሽሽ! ፈጣሪ ምን እንደወሰነ እንዴት ታውቃላችሁ?"

ፈጣሪ ድሉ ለካሣ እንዲሆን ወስኗል። ካሣ ከዚህ በኋላ ወደ ፊት ገሠገሠ። ወደ ደቡብ ዘመተ። ግንቦት ላይ የራስ አሊን መዲና ደብረ ታቦርን አጋየው። ሰኔ ወር በ1845 በመጨረሻ ካሣ ከአማቱ ከራስ አሊ ጋር ለጥ ባለ ሜዳ አይሻል አካባቢ ውጊያ ገጠሙ። ዜና መዋዕሉ ብዙ ደም እንደፈሰሰ መዝግቦታል። የራስ አሊ ወታደሮች ነፋስ ካወዛወዘው ዛፍ ላይ እንደሚረግፍ ቅጠል ተረፈረፉ። የቆሰሉት እና መንቀሳቀስ ያልቻሉት በቅዝቃዜው ባሉበት አለቁ። ራስ አሊ ከጦር ሜዳ ሸሹ። ኃይላቸውን ማጠናከር አልቻሉም። ዘመነ መሳንፍትም አከተመ።

አሁን ካሣ በአካባቢው ያለውን አንዳንድ ችግር ማረጋጋት ይኖርበታል። ወደ ትግራይ ያደረገው ድንገተኛ ዘመቻ አቡነ ሰላማ ወደ ካሣ ጎራ እንዲዞሩ ዕድል አመቻቸ። ወደ ደቡብ ፊቱን ያዞረው ካሣ በጎጃሙ ብሩ ጎሹ ላይ ዘመተ። ለዓመታት የብሩ ሠራዊት የራስ አሊን ግዙፍ ጦር ተቋቁሞ ቆይቷል። የአሁኑ ጠላት ግን በኦሮሞ የሚመራ ባለመሆኑ የብሩ ጦር አቡኑን አስከትሎ ከዘመተው የካሣ ጦር ጋር ለመዋጋት አሻፈረኝ አለ። ብሩ ጥይት ሳይተኰስ ተያዘ። ድንጋይ በትከሻው አሸክመው እየጎተቱ ካሣ ፊት አቀረቡት።

«በፊትህ እንዲህ ተይዤ የቀረብኩት እኔ ብሆን ምን ታደርገኝ ነበር?» ጠየቀ ካሣ።

«እገድልህ ነበር።» እንተመተመ ብሩ።

የካሣ ሰዎች ደሙን ማፍሰስ ፈልገው ነበር፤ ሆኖም ብሩን ራሱ ማረው እና አተረፈው። እንዲያም ሆኖ የአማፅያኑ መሪ ለቀጣይ 14 ዓመታት በእስር ቆየ። ይህ በእንዲህ እንዳለም በመላው ኢትዮጵያ ኢጋጣሚን የሚጠቀሙ መሆናቸው የሚነገርላቸው ደጃች ውቤ ሰሜኑን ይገዙ ነበር። የእሳቸው አስተዳደር ከራስ አሊም እንደሚቀድም ነው የሚነገረው። ካሣ ግብር እንዲከፍሉ ወደ ደጃች ውቤ መልእክት ላከ።

«ግብር የምገብርልህ አንተ ማን ነህ?» ደጃች ውቤ ጠየቁ።

«ታላቁ ጎልያድ! ማንነቴን ታያለህ!»

በ1846 ካሣ ወደሰሜን ዘመተ። ያለምንም እረፍት ተጉዞም ከነሠራዊቱ ደረስጌ ደረሰ። ሰማይ ጠቀሶቹ ቡናማ የሰሜን ተራሮች ላይ ሆነው ወደታች ሲያማትሩ ነጫጭ ድንኳኖች የተሰበሰቡበት ከተማ ከፊታቸው ተዘረጋ። ካሣ ወደ ሊቀመኳስ ዮሐንስ ዞር ብሎ በመነፅሩ ድንኳኖቹን እንዲመለከት ጠየቀው።



ዮሐንስ እንግሊዛዊው ጆን ቤል ነው። ራስ አሊ ሲሸነፉ በፈቃደኝነት ለካሣ አደረ። ቤል አቅርቦ የሚያሳይ መነፅሩን ወደ ዓይኖቹ አስጠጋ።

«አዎ ልክ ነው የውቤ ድንኳኖች ናቸው።» አረጋገጠ።

የካሣ ሠራዊት ደክሟል። ከታላቁ ውቤ ጦር ጋር የሚገጥመው ጦርነት አስፈርቶታል። ካሣ ወደፊት ለመግፋት ትዕዛዝ ሲሰጥ አልተንቀሳቀሰም። ከፊታቸው ቆመና፤ «ከዚያ ሁሉ ጦርነት በኋላ ይህን ሽማግሌ ፈራችሁት?» ጠየቀ። ሠራዊቱ አልተነቃነቀም።

«በጨርቅ የተጠቀለሉት ጠብመንጃዎች ነፍሳችሁን አራዱት?» ደገመ። መልስ የለም። ካሣ የመጨረሻ ተማፅኖውን «ስሜን እሰጣችኋለሁ!» ሲል አቀረበ።

አሁን የአንድ ወይም የሁለት ሰዎች የደስታ ድምፅ ተሰማ። ወዲያው ወደ ሌሎቹም ተዛመተ እና ሽለላ ፉከራው ተጀመረ። ደገኛው በቃላት ጨዋታ የተካነ ነው። «ስሜን» የውቤ የትውልድ ስፍራ ነው።

ጦርነቱ ቀላል አልነበረም። ቀኑን ሙሉ ዋለ። ጥቂት የካሣ ሰዎች ተፋላሚውን ውቤን ሲይዙ ሁሉም አከተመ። ካሣ አሁን ትግራይን ጨምሮ የደጃች ውቤን ንብረት ተቆጣጠረ። ከፍተኛው አምባ ላይ መቀመጫውን አደላድሎም እጅግ የበዛ ወርቅ እና ብርን አፈሰ። ገንዘቡን እንደየማዕረጋቸው ተዋረድ ለታዋቂዎቹ የጦር መሪዎች እና ወታደሮች አከፋፈለ። የማረካቸው የጦር መሣሪያዎች እጅግ ብዙ ነበሩ፤ ሁለት መድፎችም አሉ።

ከሁለት ቀናት በኋላ አቡኑ እና እጨጌው በተገኙበት ካሣ ዘውድ ጫኑ። ደጃዝማች ካሣ በዚህ ደረጃ የነገሥታት ንጉሥ የሚለውን ሥልጣን ወይም የሰሎሞን መንበር ወራሽ ነኝ አላለም። ሆኖም ግን ከዚያ በላይ ያደረገው ነገር አለ።

ቀደም ብሎ ለወታደሮቹ «ስሜንን እሰጣችኋለሁ» የሚል ቃል ገብቷል። አሁን ካሣ ቴዎድሮስ ሆነ። «ስወለድ እግዚአብሔር ከትቢያ አነሳኝ፣ ጥንካሬ ሰጥቶ አሳደገኝ እናም በመለኮታዊው ኃይል እሮሞን አባረርኩ።» ሲል በንጉሥ ዳዊት ቅላጼ ጽፏል።

የቴዎድሮስ ስኬት በአስደናቂዎቹ ወታደራዊ ድሎቹ ላይ ብቻ አይደለም የተመረኮዙት። አንዳንድ ሰዎች የሚከባቸው ያለ ግርማ ሞገሥ እና በውስጡ የሚንቀለቀለው ከሰዋዊ ጉልበት በላይ የሚገዝፈው ኃይሉ ብዙዎችን አስደምሟል። ምንም እንኳን የጥንቶቹን ታዋቂዎች ሊያሳምን ባይችልም የቴዎድሮስ ለዛና ግርማ ሞገስ ከግዙፍ ጠብመንጃዎች የበለጠ ውጤታማ እና በዘመኑ ሁሉ አብሮት የዘለቀ ነው።

## *ምዕራፍ ሰባት*

በጂዳ ሸለቆ ማዕከል ጥልቁን ወንዝ የተሻገረው ዋልተር ፕላውደንም አቀበቱን ተያያዘው። ከበላዩ 4000 ሜማ የደላንታ ገደልና ኮረብታ ተጋርጧል። እዚያ ላይ ነው ቴዎድሮስ ከነሠራዊቱ የሰፈረው። 50 ሺህ ወታደሮች እና 100 ሺህ ተከታዮች በአካባቢው ይገኛሉ። ብሪታኒያዊው ቆንስል ቃኚዎችና ነጋዴዎችን፣ ውኃ ቀጂዎችና እንጨት ሰባሪዎችን፣ በቅሎ ጫኞች ከነአህላቸው፣ የቴዎድሮስን ሠራዊት የሚቀልቡ አረኞችና ከብት አቅራቢዎችን ከነመንጋቸው እያለፈ ነው የሄደው። ከኮረብታው ሲደርስ በርከት ያሉ ጀነራሎች ወደ ጦር ሰፈሩ ሊሸኙ ተከተሉት። ባለዋሽንቶች ከጎናቸው ይጫወታሉ ፤ ከበሮ መቺዎች ከፍየል ቆዳ የተሠራውን አታሞ ይደልቃሉ። ድግሱ ወደ እንግዳ መቀበያው ድንኳን እስኪደርስ በርከት ያለ የጥይት ጩኸት ይቀበለዋል።

ወደ ውስጥ ሲገባ ድንገተኛ ጨለማ የተቀበለው ፕላውደን ዓይኑን አርገበገበ። ጨለማውን ሲላመድም ንጉሡን ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከተ። በግርማ የተቀመጠው ቴዎድሮስ በወርቅ የተጠለፈ እጀ ጠባብ ለብሷል። ቡብር የተለበጠው የንግሥናው ዘውድ ከጎኑ በክብር ተቀምጧል። መንግሥቱን የሚገልፀው ጦር ከበላይ ከፍ ብሎ ተሰቅሏል። አቡነ ሰላማ እና እጨጌው በግራና በቀኝ በኩል ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። የጦር መኮንኖቹም አካባቢውን እየቃኙ በተጠንቀቅ ቆመዋል። ፕላውደን እስከ ምንጣፉ ድረስ ዝቅ ብሎ እጅ ነሳ። ቀደም ሲል ውቤንም ሆነ ብሩን፣ መርሶንም ሆነ ራሲ አሊን አግዝፎ ገልጿቸዋል። ግን የቴዎድሮስን ያህል በተመስጦ የገለፀው የለም። ፕላውደን የቴዎድሮስ ትክክለኛ ሰውነት፣ ቅልጥፍና፣ አስተያየትና ወጣትነት ስቦታል። ኃይል የተላበሰው ገፅታው ከስስ ከንፈሩ ጋር ትክሻው ድረስ የወረደው ሹሩባው ተዳምሮ አቅንጅቶታል። በደላንታው የቴዎድሮስ ሰፈር ፕላውደን ለሁለት ሳምንታት ያህል ቆየ። ከዚያም ትዕግስት ለሌላቸው የውጭ ጉዳይ አለቆቹ ዝርዝር ዘገባ ጻፈ። ይህ ጽሑፉም ቴዎድሮስን ከገለፁ ዘገባዎች ሁሉ የላቀው ነበር። «ቴዎድሮስ በዕድሜ ወጣት፣ ጠንካራና ጤነኛ፤ በአስገራሚ ሁኔታ ትሁትና ደስተኛ ከሆኑ ፊታ ብለው የሚወያዩ፤ ከፍተኛ ጥንቃቄና ስልትም የሚያሳዩ ናቸው።» ብሎታል።

«በያዙት ጉዳይ የማይታከቱ፣ ሌትም ሆነ ቀን ጥቂት ብቻ እረፍት የሚያደርጉ፣ ሃሳበ ግልፅ እና ቁርጥ ያለ፤ ማቅማማት የማያውቁ።» በማለትም እንደፕላውደን ሁሉ ብዙዎች ገልጸውታል።

ለፕላውደን ያደረገው አቀባበል ቴዎድሮስ ለጉዳዩ የሰጠውን ስፍራ ያሳያል። አቀራረቡም ተራ እና አኩልነትን ያመለከተ ነበር። በቴዎድሮስ ሁኔታ የተመሰጠው ፕላውደን ሌላው ቀርቶ ንፍገቱን እንኳ በውበት ነው የገለጸው። «ከሚገባው በላይ ሊጋስና ለወርቅም ሆነ ለገንዘብ የማይሳሱ።» ብሎታል። በጦር ሠፈራቸው



ውስጥ የጋራ መገበያያ ሸርፍ እንዲኖር ያቀደው ቴዎድሮስ ለቀይ ባሕር ፖለቲካ እንዴት ያለ ጠቃሚ ተጓዳኝ ሊሆን እንደሚችልም አፅንኦት ሰጥቶ ነው ወደ ለንደን የጻፈው።

በባህሩ ዳርቻ ስለሚኖሩ ጎሳዎች ጨምሮ በቀጣዩ ዓመት በትግራይ ሰፈራ ላይ እንደሚያተኩር፤ እንዲሁም የምዕዋ መወረር እንደሚያስተካክለውም ጽፏል። «በግብፅ የተቆረሱትን የኢትዮጵያን ሰሜናዊ እና ምዕራባዊ ድንበሮች ዳግም ለማስመለስ ሳይጠይቁ አይቀሩም።»

ፕላውደን ስለቴዎድሮስ ያደረገው ግምገማ ስህተቶቹን ያለፈ ግን አይደለም። «ከባህሪያቸው እስከፊው እንዳዱ የሚታየው አመጽ የቀላቀለው ንዴታቸው፤ ባላቸው የንግሥና እና መለኮታዊ መብት ገደብ ያጣው ኩራታቸው እንዲሁም ፅንፍ የያዘው ሃይማኖታዊ ትጋታቸው ነው።» በዚያም ላይ ይላል ፕላውደን፤ «በዓለም ላይ እንደ አሳቸው ያለ ታላቅ ንጉሣዊ ሥርዓት አለ ብሎ ማመን ያዳግታቸዋል።»

ፕላውደን በአርሱ ሀገር እና በኢትዮጵያ መካከል ይፋዊ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ሃሳብ አቀረበ። ቴዎድሮስ ወደ ለንደን ኤምባሲ (ወኪል) እንዲልከም በመልሱም የእሱ ቆንስላነት እውቅና እንዲሰጠው ጠየቀ። ራስ አሊ የፈረሙት ውል ተተኪያቸውም በዚሁ እንደሚቀጥል የሚገልፅ አንቀፅ ይዟል። ፕላውደን ስለ ውሉ ማብራራት ሲጀምር ቴዎድሮስ ስለጉዳዩ ምንም እንደማያውቅ ገለጸለት። «እኔ ወጣት ነኝ እናም እንዲህ ስላለው መንግሥታዊ ጉዳይ ልምድ የለኝም።» አቅጨጩን ነገረው። ስለዚህ ፕላውደን ስለቆንስላ ምንነት ያስረዳው ጀመር። ቴዎድሮስ ወኪሉን ወደ ንግሥት ቪክቶሪያ እና ወደ ሲንት ጀምስ ችሎት መላክ እንደሚችል፣ በሀገሩ ያሉ ሕጎችም ሁለቱንም ወኪሎች እንደማይነኳቸው፤ እንዲህ ያለው ስምምነትም ሊያመጣ የሚችለውን ወታደራዊ ርዳታ፤ ድጋፍ እና የንግድ ጥቅም ዘረዘረ። በዚህ ሂደትም ፕላውደን የቴዎድሮስን ግልፅነት፤ ለአዲስ ሃሳብ እና ግንኙነትም ቅን መሆኑን ትኩረት ሰጥቶታል። ሆኖም የንጉሡ ጀነራሎች ወደ ጦርነት ለመመለስ ትዕግሥት አጥተዋል። እናም ቴዎድሮስ ከዚህ ፈረንጅ ጋር የሚያጠፉት አንዳንዴ ደቂቃ ሰጠላት ሁኔታዎችን ያመቻቻል ባዮች ናቸው።

የንጉሡን ምላሽ የሚያስተረጉመው ጆን ቤል ነበር። በቆንስሉ ጉዳይ አልስማማም አለ ቴዎድሮስ። «በግዛቴ ውስጥ ማንም ከእኔ ሕግ ነፃ ሊሆን አይችልም፤ ቆንስላ ሆነ ሌላ።» ፕላውደን ግራ ገባው። ራስ አሊ በዚህ ተስማምተው ነበር። ለሌላው ግን አለ ቴዎድሮስ፤ «ለሌላው ግን አሁንም ሆነ ወደፊት ላንተም ሆነ ለሌላ እንግሊዛዊ የፈለጋችሁትን ባደርግ ደስተኛ ነኝ።» አረጋገጠለት።

ፐላውደን ቴዎድሮስ በጊዜ ሂደት ይህንን አቋሙን ይለውጣል የሚል እርግጠኝነት አደረበት። መጠበቅን እንደሁ ተለማምዶታል። ለጥቂት ጊዜያት መጠበቅ ይችላል። የዝናቡን ወቅት ለማሳለፍ ወደ ጎንደር ተጓዘ። ቴዎድሮስ ጦሩን ይዞ የክርስቲያን ግዛት ወደሆው ሸዋ ተንቀሳቀሰ። የሸዋ ንጉሥ ከውጊያው ዕለት ቀድመው ማምሻውን አረፉ። የቴዎድሮስ ድንገት መድረስ ከንጉሣቸው ህልፈት ጋር ተዳምሮ ለሸዋ ክርስቲያኖች አዲስ ዘመን ከፊታቸው መምጣቱን አሳመናቸው። ያም ኃይለኛው ቴዎድሮስ ነበር። ለቴዎድሮስ በጎጃም እና ወሎ በበጌምድር እና ጎንደር፤ ትግራይ እና ስሜን ላይ ሸዋም ተጨመረ። የኢትዮጵያ ግዛትም ከሺህ ዓመታት በላይ ከነበረው ይዞታም ሰፋ።???!!!

## *ምዕራፍ ስምንት*

ቴዎድሮስ አስተዳደሩን ተከታታይ መመሪያዎችን በማስተካከል ተጀመረ። ተከታዮቹን «መሣሪያችሁን አስቀምጡ እና ወደ አባቶቻችሁ የትውልድ ሀገር ሂዱ። ወትሮ ትሠሩት የነበረውን መገልገያችሁን አንሱ።» አላቸው። ነጋዴው በሱቁ፣ ገበሬው በእርሻው ይወሰን። እሱ ራሱ እግዚአብሔር የመረጠው ቴዎድሮስም ወታደሮች ይኖሩታል፤ በባሩድ የሚሠራ መሣሪያ አጠቃቀም ያሰለጥናቸዋል። ወታደሮችም ደሞዝ ይከፈላቸዋል። ምግባቸውንም ከገበሬዎች ይገዛሉ። ከጉተራ መዝረፍ አይኖርም። በእጃቸው ካለው ጠብመንጃ ሌላ ቀሪው የጦር መሣሪያ ሁሉ ወደ ማረሻ እና ማጭድነት ይለወጣል፤ በመላ ሀገሪቱ የእርሻ በሬዎች ዋጋ ከጦር ፈረስ ይልቅ ይወደዳል። ሰላምን እሿት አለ አዲሱ ንጉሥ፤ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ኑሩ። በሽፍትነት የተያዘ ሳይሆን በሰላም ጊዜ በነበራችሁ ይዞታ ኑሯችሁን ቀጥሉ። ይህ ካልሆነ እንደ አዶኒቤዜቅ እጅና እግራችሁ ይቆረጣል።

ባርነት አይኖርም። በባርነት ያሉ ተሸጠው ገንዘቡ ለበጎ አድራጎት ይዋል፤ እነሱም ይጠመቁ። ቴዎድሮስ ራሱ ከሙስሊም ነጋዴዎች ላይ ባሮችን ገዝቶ እንዲጠመቁ ወደ ካህናት ሰደዳቸው። ሌሎችም የእርሱን አርአያ ተከትለው ጋብቻቸውን በካህናት ፊት እንዲያደርጉ እና ለመረጡት የሕይወት ተጣማሪያቸው ታማኝ እንዲሆኑ አበረታታ። በጦር ሰፈሩ ያሉትም ሆነ በከተማ እና ጠላ ቤት ያሉ ሴቶች ለገንዘብ ሲሉ ራሳቸውን ለወንዶች መሸጥ እንደማይኖርባቸው ተደነገገ። ነፍሰ ገዳዮች በብቀላ ለሟች ቤተሰቦች መሰጠታቸው ቀርቶ እርሱ ራሱ በሞት እንደሚቀጣቸው ተወሰነ። ቴዎድሮስ ዜጎች በሙሉ በመጨረሻ ይግባኝ ለእሱ የማቅረብ መብት እንዲኖራቸው አደረገ። ገና ሳይነጋ የአቤት ባዮች ጩኸት ድንኳኑን ይከባል። «ጃንሆይ! ጃንሆይ! ንጉሥ ሆይ! ፍትህ ይስጡኝ!»

መንገድ እንዲኖር ፈለገ። ከደብረ ታቦር አንስቶ ወደ ጎንደር፣ ወደ መቅደላ፣ ወደ ደቡብ፣ ወደ ጎጃም የሚወስድ የመጓጓዣ ሥልት እንዲኖር እቅድ አወጣ። «እስካሁን» አለ ጸሐፊው፤ «እስካሁን አንዲት መንገድ እንኳን አልተሠራችም።» የመጀመሪያው መሥመር የታቀደው እና የተነደፈው በጀርመናውያን ሚሲዮኖች ነበር።

ስለልብስም ቢሆን ቴዎድሮስ ዝም አላለም። በቀደመው አገዛዝ ዘመን ለሴትም ሆነ ለወንድ ከወገብ በላይ የሚለበስ ልብስ መኖር ዕድል ነበር። ንጉሡ ሁሉም ከጥጥ የተሠራ ሰፋ ያለ እጀጠባብ እንዲለብስ አደረገ። ወረድ ብሎ እስከ ጉልበት የሚደርስ ከሆነ ወይም ሐር ወይም ብሩህ ቀለም ካለው ወይ ደግሞ እጅታ ያለውን እጀጠባብ ለብሶ የታየ ሰው ለመንግሥት በሰጠው አገልግሎት ልብሱን ያገኘ ነው ማለት ነው። ቴዎድሮስ ለሀገሩ የነበረው ራዕይ በእርግጥም የማይካድ

ግሩም ነበር። ሌላው ቀርቶ በራሱ በቴዎድሮስ ከመቀጣት ተርፎ ከጎንደር የተባረረው የካቶሊክ ሚሲዮን ሊቅ ጀስቲን ደ ጃኮቢ፣ ቴዎድሮስን « የተለየ ሕግ እና የሚደነቅ ሥርዓትን ለሕዝቡ ብልፅግና እና ሞራል ያመጣ» ሲል በአድናቆት ገልጾታል።

ብሔራዊ አንድነትን የሚፈልገው ቴዎድሮስ የየአካባቢ መሪዎችን በመዋጋት ችግሩን ፈታው። በመሣፍንቱ ዘመን የየከፍለ ሀገሩ ገገርዎች ኃይላቸውን እያጠናከሩ፣ በአመፅ እና ከኦሮሞ ገዢዎች ጋር ግንባር በመፍጠር ኃያላን ሆነው ነበር። እንዲህ ካለው ሁኔታ ነፃ የሆነው ቴዎድሮስ በዘር ንግሥና ያላቸውን ሁሉ ከመንበራቸው ገለባበጣቸው፤ አደገኛ ካልሆኑት አብዛኞቹ ተራራው ላይ እግር እና እጃቸው በሰንሰለት ታስሮ ይንቀሳቀሳሉ። ቴዎድሮስም የራሱን ገገርዎች ሾመ።

ስለውጭው ዓለም ትኩረት ከሰጡት የኢትዮጵያ መሪዎች ቴዎድሮስ አንዱ ነው። በ1840 ዓ. ም ደባርቂ ላይ ጥቂት የግብፅ ሠራዊት በጠብመንጃቸው የእርሱ ኃይሎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል፣ ከደቡባዊ ቦስፎርስ ርቆ በቀይ ባሕር ዳርቻ ይገኝ የነበረው የኦቶማን ኃይል ተዳክሟል። ብሪታኒያ እና ፈረንሳይ ከፍተቱን ለመሙላት የነበራቸው ፍላጎት ምሥጢር አልነበረም። የአውሮጳውያን ፖለቲካ ቴዎድሮስን ግራ አጋብቶታል። በተለይም እሱ ስልጣን በያዘበት ወቅት የኦቶማንን ግዛት ያጠበበው በክሬሚያ ባህረ ሰላጤ የተነሳው ጦርነት ጥያቄ ፈጥሮበታል። ግንባር የፈጠሩትን ኃይሎች ጉዳይ የማወቅ ፍላጎቱን አንሮታል። እያንዳንዱን ሀገር ጎብኚ በፈጣሪ ስም ስለ ባላካላቫ እና ሴቫስቶፖል አዲስ ዜና እንዳለ ይጠይቃል። በእሱ ዙሪያ ሲሽኮቱ የቆዩት ፈረንሳይ እና ብሪታንያ ክሬሚያ ላይ ሙስሊሟን ቱርክን ለመርዳት ግንባር ፈጥረው ሩሲያ ላይ እንዴት ሊነሱ ቻሉ?

የኢትዮጵያውያን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ከእንግዲህ በድንበር ከልላቸው ውስጥ የመወሰኑ ነገር አብቅቷል። የሚመጡባቸውን የውጭ ዜጎች ሕይወት ማትረፍን ብቻ ሳይሆን እነዚህ እንግዶች እንዴት ያለ ጥቅም ይዘውላቸው ይመጡ እንደሆን ማጤንም ይኖርባቸዋል። ቴዎድሮስ ራሱ ከሁለቱ እንግሊዛውያን ከፕላውደን እና ቤል ጋር በተደጋጋሚ ይከራከራል። ቤል የቴዎድሮስ ሊቀመኳስ ሆኖ ሌሎችንም በመሳብ በብዙ ጉዳዮች እየተሳተፈ ከንጉሡ ጋር ብዙ ጊዜ አሳልፏል። እንደውስጥ አዋቂነቱ ግን ከፕላውደን ጋር ሲነጻጸር ብዙ አልጻፈም።

የቴዎድሮስን የአከስት ልጅ ወርቅነሽ አሰፋ ይልማን ያገባው ሊቀመኳስ ዮሐንስ (ቤል) የራሱ ፈረሰኛ ሠራዊት ሁሉ ነበረው። በዘመቻ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ከቴዎድሮስ ጋር ድንኳን ይጋራል። በየጊዜውም ከሼክስፒር ሥራዎች ለንጉሡ ያነብ ነበር። ቴዎድሮስ አዘውትሮ ቤል የሚያነበውን ይህን መጽሐፍ «የቤል

ቴዎድሮስ ሀገሩ ዘመናዊ፣ ባርነት እና ፊውዳል የሌለባት የክርስቲያን ግዛት፣ ዘመናዊ መሣሪያ በታጠቀ ቋሚ ጦር የምትጠበቅ እንድትሆን ይፈልግ ነበር። ከምንም በላይ ሕዝቡን እንደባሪያ እንቆ ያልያዘ ንጉሥን ይህ አድርግ፣ ይህን አታድርግ የማይል፤ ከተቆጣጠረው መሬት ሢሶውን ምርት የማይሰበስብ፣ አገልግሎቱን ሕዝቡ በማይጠቀምበት ቋንቋ የማያቀርብ ቤተ ክርስቲያን ቢኖር ይሻል። ፕላውደን በተደጋጋሚ በጽሑፉ ኢትዮጵያን እና የአውሮጳን መካከለኛ ዘመን ጎን ለጎን ለማስተያየት ሞክሯል። አንድነት እና ማዕከላዊ አስተዳደር ለመገንባት በነበረው ጥረት አውሮጳ ውስጥ ተከታታይ ንጉሦች ለማሳካት የሞከሩት ግብ ላይ ለመድረስ ሞክሯል፤ ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ ረገድም የራሱን ማስተካከያ አድርጓል። ስለዓለም ኃይሎች የነበረው አስተያየት በመጽሐፈ ሳሙኤል የተቃኘ እና መጠነኛ የአውሮጳውያንን ሰብዓዊነት በሚያንጸባርቀው «የቤል መጽሐፍ ቅዱስ» ምንባቦች የተደገፈ ነበር። ሆኖም ግን ፈጣሪ በቀላሉ ድልን አይሰጥም። እናም ቴዎድሮስ ህዝብ ለረዥም ዘመናት በጭለማ ውስጥ በመኖሩ እሱ ያስገኘለትን መጠነኛ ብርሃን ማጣጣም ጀምሯል። ትግራይ ውስጥ የውቤ ወንድሞች ንጉሤ እና ተሰማ ቴዎድሮስ ላይ አመፁ፤ ጎጃም ላይ ተድላ ጎሹ ሸፈተ። የከንቱ ልጅም አመፀ። የወሎ ኦሮሞዎች የገገርነት ዘመናቸው ማከተሙን ገና አልተረዱም። በመላው ሀገሪቱ ካህናቱ የቴዎድሮስ ድሎችን የፈጣሪ ትንቢት መገለጫዎች ናቸው ብለው ለመቀበል ጊዜ ወስዶባቸዋል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ሹማውን ከትከሻው ላይ ጣል አድርጎ በባዶ እግሩ ድንጋያማው መሬት ላይ የቆመው ቴዎድሮስ «ካለ ኢየሱስ ምንም የለኝ» የሚል ይመስላል። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት በዓለም ላይ ያለውን ሚና ተረድቷል። በተለይም ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን ከሙስሊም ተስፋፊዎች የማዳን ኃላፊነቱ ገብቶታል። በመጀመሪያ አሮምን ወደ ክርስቲያንነት ይለውጣል፤ ከዚያም በግዛ ለሚገኙ ቀሪዎቹ ሙስሊሞች ኢየሱስን ተከተሉ ወይም ግዛቱን ልቀቁ ሲል ምርጫውን ያቀርባል። በጉዞው ላይ የሚመጡበትን እንቅፋቶች አስቀድሞ ለማየ የአማልክት ስልጣን የለውም። ግን ደግሞ የማያወላውል ክርስቲያን ነው። የመስቀል ጦረኛ፣ በእግዚአብሔር የተመረጠ የዳዊት አልጋ ወራሽ፣ ብዙ ሥራ ያለበት የክርስቶስ ባሪያ።

እንዲያም ሆኖ ቴዎድሮስ ለቀሳውስቱ እጅግም ግድ የለውም። በዘመነ መሳፍንት እንደሚለው፣ አብዛኞቹ ከአንድ በላይ ሚስት የቤተ ክህነቱ ሰዎች ዜና መዋዕሉ ያላቸው፣ ጠጪዎች እና ጠንቋዮች ሆኑ። ቀን ቀን መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ይታያሉ፤ ማታ ማታ ደግሞ ጋለሞታዎች ቤት ይገኛሉ። ከዚህ የከፋው ደግሞ እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት ክርክር ሕዝቡን ማደናገር ኦርቶዶክስን ለማናጋት አና መከፋፈላቸው ነበር። በአራት ዘመን እንደነበሩት መሳፍንት፣ የእስራኤል ልጆች ኢያሱን ረስተው በዓልን እና ሌሎች ጣዖታትን ማምለክ እንደጀመሩት፤ ካህናቱም እውነታውን ረሱት።

በመጨረሻ ታዲያ «ለዚህ ሁሉ ትርምስ የውጭ ዜጎች ተጠያቂዎች ሆኑ።» በ16ኛው ክፍለ ዘመን ፖርቱጋላውያን ስለ ኢየሱስ ባህሪ የራሳቸውን ትርጓሜ አምጥተው በርካታ ኢትዮጵያውያንን እንዲቀበሉ አደረጉ። እነዚህኞቹ መጀመሪያ «ቅባት» ተባሉ። ከዚያም የፀጋ ልጅ፣ ቀጥለውም ሦስት ልደት የሚል አመጡ። እነዚህ ባለ ሦስት ልደት አማኞች ክርስቶስ ምሉዕ መለኮታዊነቱን የሚከዱበት ደረጃ አለ። ለእስክንድሪያ መንበር ተከታዮች ይህ የክርስቶስን መለኮትነት የሚክድ ሃራጥቃነት ነው። የባለሦስት ልደት ተከታዮች «ካራ ሃይማኖት» የሚል መጠሪያ ተሰጣቸው። ከትምህርታቸው ሦስተኛውን ልደት ቆርጠው ስለቀጠሉ።

ለዚህ ሁሉ ዝብርቅርቅ ታዲያ ቀብ አልነበረውም። እሱ የሚፈልገው ጥንታዊውን መንሻ ነው። ቤተ ክርስቲያን ሀገሪቱን አንድ ለማድረግ የምትረዳ ከሆነ በቅድሚያ ራሷ አንድ መሆን ነበረባት። በ1846 መጀመሪያ እንደ ሀገር መሪ በወሰደው ርምጃ የቤተ ክህነቱን ጉባኤ ጎንደር ላይ ሰበሰበ። ገና ንግሥናውን አልያዘም፤ ግን በወቅቱ ደጃች ውቤን አሸንፎ አብነ ሰላማን ከጎኑ ማሰለፍ ችሏል። አቡኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ናቸው። በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ብቸኛ ጳጳስም እሳቸው ነበሩ። ይህ ቦታ በኢትዮጵያውያን ሳይሆን በግብፆች የተያዘ ነበር። በዚህ ስልጣን ላይ

የተቀመጡት አሁን በዕድሜ የገፉ እና ከእስክንድሪያ የሚሾሙ አማርኛም የማይናገሩ ናቸው። በ1812 ላይ ደጃዝማች ሰባጋዲስ ከአቡነ ሰላማ ቀድመው ስለነበሩት አቡን ቅሬታቸውን ለእስክንድሪያው ፓትሪያርክ፤ «ኢትዮጵያን ስለሚጠሉ ይሆን እሳቸውን የላኩት?» ብለው ጽፈው ነበር። በመሐመድ አሊ ዘመን ግብፅ ግዛቷን ወደ ደቡብ እያስፋች ኢትዮጵያን የመውረሯ ስጋት በየአካባቢው ሲሰማም አቡኑ ላይ የነበረው ጥርጣሬ ከፍ አለ።

በ1833 ኢትዮጵያ የገቡት አቡነ ሰላማ ወጣት እና ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ነበሩ። ካቶሊክ ሚስዮናውያን በሰሜን ኢትዮጵያ ሲበራከቱ ከእስክንድርያ ጋር የሚኖረውን ትስስር ለመጠበቅ አቤቱታ አቅርበዋል። በቴዎድሮስ መነሳትም እንደ እሳቸው ያለ ጠንካራ እና ቆራጥ ሰው አገኙ። በ1846ቱ የካህናት ጉባኤ እሳቸው እና ቴዎድሮስ ባለ ሦስት ልደቶችን አገዱ። ለእስክንድሪያ ሃይማኖታዊ መርሆዎች አገዛለሁ ብሎ መናዘዝ ወይም የሞት ቅጣትንም ወሰኑ። የካቶሊክ ሚስዮኖችም ሀገር ለቀው እንዲወጡ አዘዙ። ከዚያም ብዙም ሳይቆይ አቡነ ሰላማ ለቴዎድሮስ ዘውድ ጭነው፣ ትዳሩንም በቤተ ክርስቲያን ቀደሱ። የሁለቱ ኅብረት በተለይ ሸዋን በወረሩ ጊዜ ጦሩን ከፊት እየመሩ መሣሪያነታቸው እጅግ ጠቃሚ ሚና ተጫውቷል።

እንዲያም ሆኖ በሁለቱ መካከል የተመሠረተው ፍሬያማ ትስስር ብዙም አልዘለቀም። አቡነ ሰላማ እንደ ቴዎድሮስ ሁሉ ከመጠን በላይ የጠና ፍላጎት እና ምኞት ነበራቸው። በዚህም መካከል የፍላጎት ፉክክሩ ቅራኔያቸውን ያበዛው ጀመር። ካህናቱም ቢሆኑ ቴዎድሮስ የጀመሩት ማስተካከያ ፍጥነት አልተመቻቸውም። በ1848 የዝናቡ ወራት እንዳበቃ ካላቸው ሀብት ላይ ግብር እንዲከፍሉ ለማግባባት ደግሞ ካህናቱን ጎንደር ላይ ሰበሰበ።

«ጠላቶቻችን ብዙ ናቸው። ስለዚህ ካላችሁ ላይ እኛን ለሚጠብቁን ቢከፈል ሚዛናዊ ነው» በማለት ቴዎድሮስ አስረዳ።

«ካህናቱም መብላት ይኖርባቸዋል።» የሚል መልስ ተሰጠው። ከወታደሮቹም በቁጥር ቢበልጡ እንጂ እንደማያንሱም ተነገረው። በተለይም አንዱ ቄስ፤ «እርስዎ ቢሆኑ ምን ያደርጉ ነበር?» ሲሉ ጠየቁት።

«ይህ ሲሰራበት የኖረው ሥርዓት ነው ጃንሆይ።» ቀጠለ ሌላው። ክርክሩ ቢቀጥልም አንዱ ሌላውን ሊያሳምን አልቻለም። በመጨረሻ ካህናቱ ፍትሀ ነገስቱን አወጡ። «ለቅድስተ ቅዱሳን የተሰጠውን ሁሉ መውሰድ አይገባም።» ማለትም ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን መሬት መንካት አይቻልም።

«ይህ መጽሐፍ ሺህ ጊዜ የተተረጎመ እና ሺህ ጊዜ የተብራራ ነው።» ንጉሡ ተቆጣ። «በዞፋኑ ላይ ሌላ ሰው ማስቀመጥ ከፈለጋችሁ ሞክሩት። አውሬውን ሁሉ ከሕዝቡ መሬት ላይ አሳድዳለሁ።» በተቀመጠበት ግራ እና ቀኝ ተንቆራጠጠ። ጠባቂዎቹ ከጀርባው ወደ እሱ ሲጠጉ ካህናቱ ተመለከቱ። የቁጣውን ያህል ቴዎድሮስ ወዲያው ይበርዳል። ቆየት ብሎ አቡነ ሰላማን ጠራ እና ሁለቱ ቅድመ ሁኔታዎች አስቀምጠው ተስማሙ።

ካህናቱ ቴዎድሮስ ቀረጥ ሊያስከፍላቸው መብት እንዳለው እንዲያምኑ፤ ቴዎድሮስም አሳድዳለሁ ያለውን ተግባራዊ ላለማድረግ ሊስማማ ተዋዋሉ። በማግስቱ የጎንደር ጎዳናዎች በካህናቱ ዝማሬ ድብልቅልቃቸው ወጣ። ከተማው በከበሮ እና በደብተራዎች ዜማ ተሞላ። የሙሴ የድል ዝማሬ። ቴዎድሮስ ተሸነፈ። መስፋፋት የጀመረው ግዛቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ደጃፍ ላይ ተገታ። ወደ ዘመቻው ተመለሰ።

## ምዕራፍ አስር

ከበርካታ ወራት በኋላ በጎርጎሪሳዊው 1848 ታኅሳስ ወር ማለቂያ ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ አባት የቅብጥ ፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስ 4ተኛ ወደ ጎንደር መጡ። ከእስክንድሪያ እዚህ ለመድረስ ብዙ ወራት ተጉዘዋል። በጥንታዊው ከተማ ኮረኮንች ጎዳናዎች፤ በአረንጓዴው ገጸ ምድር በእርጋታ የሚጓዙት ፓትሪያርክ ተከታዮች ከፊት ከፊታቸው እየሮጡ ሴቶችን ከመንገዳቸው ድንገት ሳያይዋቸው ያባርራሉ።

የፓትሪያርኩ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በቴዎድሮስ የመጀመሪያ የግዛት ዘመን ትልቅ አጋጣሚ ነበር። ፓትሪያርኩም ከውጭ ዜጎች ንጉሡን የጎበኙ ባለ ትልቅ ማዕረግ ሲሆኑ ቴዎድሮስ ከየትኛው የውጭ መንግሥት ጋር ጉድኝት ሊፈጥር እንደሚችል ተፅዕኖ ያደረገ እንደሆነም ይታመናል። በሕዝቡ ዘንድም የቴዎድሮስን ልክ ያሳየ ነበር።

አጀማመሩ መልካም ነበር። ቴዎድሮስ አቡኑን ደብረ ታቦር ላይ በትልቅ ሥርዓት እና አክብሮት ተቀበለ። ውሎ አድሮ ግን ንጉሡ በሰማያዊው ካባ ሥር የማይሆኑ ነገሮችን መመልከት ጀመረ። ፓትሪያርኩ ስለ ልጅ ቤተ ክርስቲያናቸው የተለያዩ ነገሮችን እንደሚናገሩ ቴዎድሮስ ሰማ። ለመስቀሉ እና ለቅዱሳን ይደረጋል ስላሉት ተገቢ ያልሆነ አምልኮ እንዲሁም ስለቅዱሳን ቀኖች አቡኑ ይተቻሉ። ከአቋሙ በቀላሉ ፍንክች የማይለው ሰው የሠራዊቱን ትኩረት ፓትሪያርኩ መሳባቸውን ተረዳ። ከዚህም ሌላ የግብፅ የጦር ግመሎች በምዕራብ የሀገሪቱ ድንበር አካባቢ መታየታቸውን ቴዎድሮስ ሰማ። ፓሻው ራሱ የግብፅን ድል ሱዳን ላይ ማብሰሩም ተነገረ። ድንገት ሁሉም ነገር ለቴዎድሮስ ፍንትው ብሎ ተገለጠ። የፓትሪያርኩ ጉብኝት ፓሻው ያቀነባበረው እና ከወረራው በፊት የኢትዮጵያን ደካማነት የፈተሸበት ስልት እንደሆነ ገባው። ምን ማድረግ ይችላል?

ቴዎድሮስ ፓትሪያርኩን አሠራቸው። ፓትሪያርኩን ከአቡነ ሰላማ ጋር በአንድ ስፍራ ዘግቶ በእሾህ አጠራቸው። ከዚያ በኋላ በታማኞቹ መካከል መከፋፈል ተፈጠረ። በርካታ ኢትዮጵያውያን በቴዎድሮስ ድርጊት ፍርሃት አደረባቸው፤ ለዚህ ሁሉም የውጭ ዜጎችን በተለይም የአውሮጳ ፕሮቴስታንትን ተጠያቂዎች አድርገው ከሰሱ። ቴዎድሮስ በበኩሉ ወደ ወዳጆቹ ፕላውደን እና ቤል ፊቱን አዞረ። እነሱ ደግሞ የእንግሊዝን ድጋፍ እንዲያገኝ ከንግስት ቪክቶሪያ ጋር ግንኙነት እንዲፈጥር ግፊት የሚያደርጉበት አጋጣሚ ተፈጠረላቸው።

ሃሳባቸው ግን የቴዎድሮስን ቁጣ አስነሳ። «ለመሆኑ እኔ ፈርቼ ይህን አጋጣሚ የምጠቀም ይመስላችኋል?» አፈጠጠ።

«የለም፡ ፓሻው ግን እኛ እየተቃወምን በዚህ ወረራ ይገፋበታል ብዬ አላስብም።» ፕላውደን መለሰ።

ቴዎድሮስ ፕሮቴስታንቶቹ ላይ ያለውን ጥርጣሬ አጠናከረ። ቅብጦቹ ታስረው ሳለ፤ አቋሙን ለማብራራት ከችሎት ቆመ። ወደ ጥንዶቹ ፕሮቴስታንት ሚሲዮናች እያመለከተ፤ «ሰላም ደስታ እና ዕድላችንን ፈልገው በቋንቋችን መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው መጡ፤ ሆኖም ቅዱሱ አባት እንደ ነጋዴ እና አምባሳደር ነው የመጣው፤ ሰም እና የዝሆን ጥርስ፤ በቅሎ እና የሜዳ አህያ ለንግድ በመጠየቅ ከመሐመዳውያን ጋር ወዳጆች እንድንሆን ጠየቀን።»

የእሱን ጊዜ የሌለው እና አጣዳፊ ተልዕኮ አስታወሳቸው። «እኔ የክርስቶስ ባሪያ ነኝ። በጠላቶቼ ላይ ሁሉ ድልን ሰጥቶኛል። ለእርሱ ክብር ነው የምደክመው፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ከሙስሊሞች ለመከላከል።» እንደ መሪያቸው ሊያምኑት ይገባል። «በሕይወቴ እስካለሁ ድረስ ፓትሪያርኩን ረግጬ አይዘዋለሁ፤ አቡኑ እና ሰይድ ፓሻን ጭምር፤ የእንግሊዟ ንግሥት ሊረዱኝ ይገባል።»

ሆኖም በታሰሩት የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምክንያት በቴዎድሮስ ላይ የተፈጠረው ጥርጣሬ ሕዝቡ የራሱን ምርጫ እንዲወስን አደረገው። ቴዎድሮስ እና ፕሮቴስታንት ወዳጆቹ መገለል ደረሰባቸው። ከቀናት በኋላ ንጉሡ ታላቅ ጉባኤ ጠራ። የችሎት ሰዎች፣ ሚኒስትሮች፣ ሚሲዮናውያኑና የውጭ ዜጎች፣ በሺህ የሚቆጠሩ ቄሶች እና ደብተሮች፤ እንዲሁም ከሺህዎች የሚበልጡ የራሱ ወታደሮችም ተገኙ። ቴዎድሮስ በዚህ ጊዜ ከፊታቸው የቆመው የወሰደውን ርምጃ ለመከላከል ሳይሆን ለኑዛዜ ነበር። የቤተ ክርስቲያንን ሰዎች እንዲህ ለማተላለት ያነሳሳኝ ሰይጣን ነው አላቸው። በእሾህ አጥር ወደተከበበው እስር ቤት የእርቅ መልእክት ላከ። ተቀባይነት ሲያገኝም በፓትሪያርኩ እና በአቡኑ ፊት ተንበርክኮ ይቅርታ ጠየቀ።

ፓትሪያርኩ ወደሀገራቸው ከመመለሳቸው አስቀድሞ ታዲያ በቴዎድሮስ ጭንቅላት እንዲት ዘር ዘሩ። «አውሮጳውያን የሚታመኑ አይደሉም። አላማቸው ራስ ወዳድነት ነው።» ቀደም ብለው ቴዎድሮስ ፕሮቴስታንቶችን ከሀገሩ እንዲያባርር አሳስበዋል። አሁን ደግሞ በግልፅ እንግሊዝ ወዳጅነቱን የምትፈልገው ኃይሉን በማጣጣል ሀገሩን ልትወር ነው በማለት ለንጉሡ ነገሩ። መጀመሪያ ቴዎድሮስ ይህን ለማመን አቃተው። ውሎ አድሮ ግን የእንግሊዝን የሚያምታታ የዲፕሎማሲ ምልክቶች ሲያስተውል አብዛኛውን ጊዜ የፓትሪያርኩን ማስጠንቀቂያ ያስታውስ ነበር።



## ምዕራፍ አሰራ አንድ

ፓትሪያርክ ቄርሎስ ወደ ቆላው ሲወርዱ ቴዎድሮስ ስጦታዎችን አሸክሞ ነው የሸኛቸው። የዝሆን ጥርሶች፣ ለሰይድ ፓሻ ደግሞ ሦስት ግሩም እና አራት መጠነኛ ፈረሶች፣ ጦር እና ጋሻ ላከ። ከዚህ ሌላ ሁለት ደብዳቤዎችን አንዱን ለፓሻ ሌላኛውን ደግሞ ለንግሥት ቪክቶሪያ ሰደደ። የውጭ ግንኙነት የመጀመሪያው ምዕራፍ።

በዐስራ አንድ ቀናት ውስጥ ለሰይድ ፓሻ የተጻፈው ደብዳቤ ከአማርኛ ወደ አረብኛ ተተርጉሞ ቀኑም ከኅዳር 5: 1842 ወደ ሂድራ 25 ራቢ አል አዋል ተለወጠ። መንደርደሪያ ሰላምታውም «ወዳጁ ሰይድ ፓሻ የግብፅ ገዢ» ከሚለው ልሙጥ የቴዎድሮስ አማርኛ፤ «የተከበሩ እጅግ የታፈሩ፤ አንፀባራቂው ደስታ እና እውነተኛ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሐመድ ሰይድ ፓሻ፣ የግብፅ ጠባቂ፤ የፍጥረታት ጌታ በጥበቃው አይለይዎ » ወደሚል አረብኛ ተተረጎመ።

የደብዳቤው ዝርዝር ራሱ ቴዎድሮስ በግብጽ ላይ የነበረውን አቋም መለወጡን ያመለክታል። በፓትሪያርኩ መታሰር የተሰማውን ለመሸፈንም፤ «ፓትሪያርኩ አባቴ እርስዎ እንደሚወዱኝ እና ወዳጅነቴንም እንደሚፈልጉ ሲነግሩኝ በጣም ተደሰትኩ። ....... እግዚአብሔር ወዳጅነታችንን ያበርክት።»

ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፈው ግን ከዚህ ይለያል። ፕላውደን ባያበረታታው ኖሮ እንደውም አይልከውም ነበር። ቴዎድሮስ ከፓትሪያርኩ እና ከግብጽ ጋር አዲስ ወዳጅነት ቢመሰርትም፤ ቆንስሉ ግን የራሱን ተምኔት ለማሳካት ጥረቱን ቀጥሏል።

«ይህ ደብዳቤ ከኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ተላከ፤ እንደምን አሉ? ደህና ነዎት? እኔ ደህና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን! መልእክተኛዎን ቡላዲንን (ፕላውደንን) በፍቅር እና በወዳጅነት ተቀብየዋለሁ። አሁን እርስዎ የክርስቶስ ልጅ ነዎት፤ እኔም የክርስቶስ ልጅ ነኝ። በክርስቶስ ፍቅር ወዳጅነት እሻለሁ።.........»

አሁን ፕላውደን ነው የተገለለው። ከቴዎድሮስ ደብዳቤ ጋር የራሱን ማብራሪያ አከሏል። በመጨረሻ ቴዎድሮስ ከብሪታኒያ የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን እስተዳረሩ ጭምር የሚሻውን ሚዛናዊ አድርጓል። ለቴዎድሮስ ቁሳዊ ድጋፍ መስጠት አማራጭ የለውም። ፕላውደን ከአንድ ዓመት በፊት ግብፆች ለፈረንሳዮች ስዌዝ ቦይ (ካናል)ን እንዲገነቡ መፍቀዳቸውን ያውቃል። አሁን ፈረንሳዮች ኢትዮጵያን ከቴዎድሮስ ለማጣላት እየሞከሩ ነው።

«ፈረንሳዮች እና የሮማ ካቶሊካዊ ሚሲዮን የሚቻል ከሆነ በሚል የእሳቸው
ተቀናቃኝ ይሆኑ ንጉሤ እንዲያምፁባቸው ያለ የሌለ ድጋፍ ሲያደርጉ ቆይተዋል።
ለዚህ ድጋፍም ሦስት መድፎች ምጽዋ ላይ ይገኙ ነበሩ።»

ቀይ ባሕርን ከፈረንሳይ ቁጥጥር ለማዳንም ፕላውደን የብሪታንያ የውጭ ጉዳይ
ሚኒስቴር በመቶዎች የሚቆጠሩ ጠብመንጃዎችና ጥይት ለቴዎድሮስ እንዲልክ
ሃሳብ አቀረበ። ቴዎድሮስ ራሱ እንዲጠቀምባቸው ይግባው «ቀንጆዎቹን»
እንዲላኩለት ጠየቀ። የፕላውደን ደብዳቤ ለንደን ላይ «ተቀባይነት» አግኝቷል።
የምትል የሎርድ ክላረንደን አንድ ቃል ምላሽ ነው ያገኘው። በተቃራኒው
ከግብፅ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የመልስ ደብዳቤዎች መጡ። የሰይድ ፓሻ
አምባሳደር ሬዥም የጣመለ ሰልፍ እና አጀብ አስከትሎ፤ ለቴዎድሮስም ክቡድ ያለ
ስጦታ ይዞ ከተፍ አለ። አንድ መቶ ባለ ጥንድ አፈሙዝ ጠብመንጃ፤ በርካታ
ድንኳኖች፣ ሃር እና ጣቃ ጨርቆች፤ እንዲሁም አራት ትላልቅ አዳፍኔዎች ጭኗል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ፕላውደን ለላከው ተማፅኖ ከሎርድ ክላርደን ጠረጴዛ
ላይ ተነስቶ በቀጥታ አውጣ ገዞ ወደ ጦር ክፍል ተመራ። አንድ ዓመት አለፈ።
የጦር ክፍሉ ጥያቄውን አጸደቀ እና ዝርዝሩ በትዕ ተሞላ።

ጠብ መንጃ ከነመፍቻው፤ አንድ

ሪቮልቨር ከነቀለሃው እና መፍቻው ጋር፤ አንድ

ማሕደር ፤ አንድ

ይኸው ነው። የጦር ክፍሉ በዚህ ወቅት ለቴዎድሮስ የጦር መሣሪያ መላክን «ተገቢ
ያልሆነ» ነው ብሎታል። ደብዳቤው ከኢትዮጵያ በተላከ በሁለት ዓመቱ
ፕላውደን በ1851 ተቀምጦ መጠይ ወደብ ላይ ከለው ወኪሉ መልእክት
ደረሰው። «መሣሪያው መጥቷል፤ ግን ጥይት የለውም።» ከሰራት ዓመት ተከትሎ
በፊት ለሎሮር ጊዜ አዲሱን ሀገረ ገዢ ለማየት ወደ ደጋው መጣ። ያኔ የእንግሊዝ
ቆንስሉ ወዳጅ ማግኘት ብቻ ሳይሆን የተላቻ ማተረምረምም አጀብት ነበር።
ኢትዮጵያውያን በአውሮጳ ክርስቲያኖች ላይ የነበራቸው የቆየ ጥርጣሬ ታድሷል።
ከሀገሩ መውጫ መንገዱ ደግሞ በሽፍታው ንጉሤ ተዘግቷል። ዋልተር
ፕላውደን ወጥመድ ውስጥ ነው።



# ምዕራፍ አስራ ሁለት

የግብፁ ፓትሪያርክ በ1849 ከጎንደር ከሄዱ በኋላ ቴዎድሮስ ወደ ደላንታ ዘመተ።
እዚያ የሚገኘውን ያመፀ ሀገረ ገዢ ድል አድርጎ አባይን ተሻግሮ የተጠናከረ አመፅ
ወደ ተነሳበት ወደ ጎጃም ተሻገረ። ከአማፅያኑ የአንዱን ሚስት ያዘ፤ በጥይት
ከመገደሏ በፊት ልብሷን አስገፈፈ። ከዚህ ቀደም ነፃ የለቀቃቸው አማፅያን
በድጋሚ ተያዙ። አሁን ግን አልማራቸውም። ጎጃም ውስጥ የባሪያ ገበያ አገኝ እና
የተያዙትን በሙሉ ነፃ ለቀቃቸው። አብዛኞቹም እርስ በርስ ተጋቡ። ወደ ሰሜን
ጉዞውን ቀጥሎም ከአገው ጋር ተዋጋ። መሪዎቹም ከእጁ ገቡ። የወገራ ገዢ ደግሞ
አመፀ። ቴዎድሮስ ከርሱ ሊዋጋ ጦሩን አስከትሎ ወደ ምዕራብ ገሠገሠ። ግን
አመለጠው። ጎርጎራ ላይ የእስረኞቹ እጅና እግር ተቆረጠ፤ ተሰቀሉም። ከዚያም
ወደ ዙር አምባ ዘመቻው ቀጠለ። ወደ ጎንደር ብሎም ወደ ወገራ አቀና፤ ከዚያም
ዳግም ወደ ዙር አምባ ተመለሰ።

ዓመቱ ዘመነ ማርቆስ ነበር። እንደ ወትሮው ሁሉ ቴዎድሮስ አማጽያንን
ለማንበርከክ ጦሩን በተራራማው አካባቢ ወደ ኋላና ወደ ፊት ሲያመላልስ፤
ሲያዘምት ነው ያሳለፈው። «መጣ! መጣ!» ብለው ያንቮካሹት እና እሱ
ከአካባቢው ሲሄድ አመፅ ይጀምራሉ። በሦስት የአገዛዝ ዘመኑ የእሮም ኃይልን
ማሸነፍም ሆነ ስልጣን የሰጣቸው የራሱ ሰዎች፣ የአቡን ሰላማ ወዳጅነት፣
ማብዮቹም ሆኑ ቧለ ድብት አላማዎቹ አውሮጳውያን እንዲያው ጠንክሮ የወጣ ነገር
የለም። ግዛቱ ሠራዊቱ ከሚሰፍርበት እነስተኛ ክፍለ ሀገር ትንሽ ከፍ ቢል ነው።
ቤተ መንግሥቱ የሚያርፍበት ድንኳን፤ ስልጣኑ ደግሞ በመጨረሻ ድል
የሚያደርገው ጦርነት ነው።

አስገራሚው ድል መከታተሉም ግዛቱን አንድ ላይ አሰባስቦለታል። በወሎ እና
በጊምድር መካከል ተራራ አለ። ጨለማ የለበሰው ገደሉ የትልቅ መርከብ ጎን
ይመስላል፤ ድልዳለው አናቱ ላይ ከብቶች ይሰማራሉ፤ እህልም ይበቅላል። ማንም
ቢሆን ሳይታይ ወደ ተራራው መቅረብ አይችልም። በአነስተኛ ጦር ይጠበቃል።
መቅደላ። ቴዎድሮስ ሲመለከተው ከተተራመሰው ዓለም ማረፊያ አድርጎ ነው
የወሰደው። «የሀበቱ ማከማቻ መቅደላ ይሆናል፤ የሚወዱኝ መጥተው
ይሰፍሩበታል።»

በጠላት የተከበበውን ያንን ስፍራ ቴዎድሮስ ብቻ ነው የወደደው። ከዓመታት
በኋላ «ኃያል እንዳለኝ አምኔ ክርስቲያኖችን ሁሉ ከኢአማንያን ምድር አውጥቼ
ወደዚህ አመጣኋቸው።» በማለት ፅፏል። እናም መቅደላ የጦር ሰፈር፣ መጋዘን፣
እስር ቤት፣ ጠንካራ ይዞታ እና ቤትም ሆነ። ከዓመታት በኋላም ለቴዎድሮስ ወሳኝ
የሆኑት ነገሮች ሁሉ መቅደላ ላይ ተከወኑ። ያሠራው መድፍ፣ የከበሩ ድንጋዮቹ፣
የተዘረፉት መጻሕፍት፣ እጅግ ጠቃሚ እና አደገኛ እስረኞቹ ሁሉ እዚያው ነበሩ።

ጎሹ ብሩ እና ትክክለኛው የሰሎሞን ዘር የሆነው ሞኙ ዮሐንስ መቅደላ ላይ ነው የታሰሩት። ተራራው ለቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት እና የንብረት ማሳረፊያ ተደርጎ ሲመረጥ አቡነ ቄርሎስ እና አቡነ ሰላማ በሥነስርዓቱ ላይ ተገኝተዋል። በዚህ ስፍራም በሚወደው መድኃኔ ዓለም ስም ቤተ ክርስቲያን አሰራ።

የሚወዳት ባለቤቱ ተዋበችንም በዚህ ስፍራ አስቀመጣት። በቻለ ጊዜ ወደ መቅደላ ብቅ ይላል። ከባለቤቱ ጋር ሲሆን የመረጋጋት መንፈስ እንደሚሰፍንበት በዙሪያው ያሉ ሁሉ አስተውለውታል። ከጠባቂ «መልአኮቹ» አንዷ ናት። ሌላኛው ደግሞ ጆን ቤል (ሊቀ መኳስ ዮሐንስ) እንደሆነም ይነገራል። ምግቡን የምታዘጋጅለት እራሷ ናት። መጽሐፍ ቅዱስ አብረው ያነብባሉ። ወራሽ ፍሬ ግን ገና አልሰጣቸውም፤ ለዚህ ደግሞ እግዚአብሔር የራሱን ጊዜ ይመርጣል።

በ1850 ክረምት ገና እንደገባ ቴዎድሮስ ወደ ተራራው ወጣ። ተዋበች የጦርነቱን አቧራ ከእግሩ አጠበችለት። ለተወሰነ ጊዜ ተረጋግቷል፤ ወደ የትም አልሄደም። ተቀምጦ የዳዊት መዝሙርን ያነብብ ጀመር። «አቤቱ ጌታዬ መከራዬን እንዴት አበዙብኝ! በእኔ ላይ የተነሱት ብዙዎች ናቸው,,,,,,» በየዕለቱ ደመናው በተራራው ላይ ይሰበሰብና ነፋስ ሲመጣ ተበትኖ ፀሐይ ጨረሯን በመካከሉ ትዘረጋበታለች።

ቴዎድሮስ መቅደላ ሳለ ተዋበች ታመመች። ዕለት ዕለት የንጉሡ ስጋት ከፍ እያለ ነው። የሚመገበው የፆም ሽሮ ብቻ ሆነ። ምሽቱንም ለእሷ በመጸለይ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ያሳልፋል። ጥቂት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንን መድኃኒት እንዲሰጧት ለመናቸው። መንቀሳቀስ የለመደው ሠራዊቱ ደግሞ መቅደላ አካባቢ የሚገኙ መንደሮችን ይዘርፍ ጀመር። ቴዎድሮስ በዚህ ጊዜ ከታማሚ ባለቤቱ ፊቱን አዙሮ ጦሩን እየመራ ወደ ደቡብ ዘመተ። ከኦሮሞ ሲዋጋ፡ ነሐሴ አጋማሽ በዕለተ ረቡዕ እቴጌ ተዋበች አረፉ። ቴዎድሮስ እዚያው ከሠራዊቱ ጋር ነው። ሲመለስ አስከሬኗ ከሳጥን ተከቶ ወሳንሳ ላይ ተቀምጧል። እንዳይፈርስ የተዘጋጀውን የሟች ባለቤቱን አስከሬን መቅደላ ተራራ ላይ ከአንዱ ወደ አንዱ የጦር ሰፈር አንቀራጠጠው። በድንኳኗ ውስጥ ሲያርፍም ቴዎድሮስ ከአስከሬኑ ጋር ለሰዓታት አብሮ ለብቻው ተቀመጠ። ከዚያም ወደ ግሸን አምባ ተወሰደች። የእቴጌ ተዋበች የቀብር ሥርዓት ሲካሄድም ቴዎድሮስ የሚከተለውን እንጉርጉሮ አሰማ፤

እስኪ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ

እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ፤

እጅግ ጥበብ ወዳድ ትናንትና ሞተች

በርካታ ማይሎች ራቅ ብሎ በኦሮሞዎቹ ግዛት ውስጥ ሌላ እንጉርጉሮ ይሰማ ነበር። የየጁው ራስ አሊ ሁለት ጊዜ ሳቧት ልጃቸው እቴጌ ተዋበች ስንኝ ቋጠሩ። ቴዎድሮስ ግዛታቸውን ቀምቶ ድል አድርጎ ካሳደዳቸው ጀምሮ ልጃቸውን አላይዋትም።

ጠጅ አማረኝ ስላት ማር ትሰጠኛለች

እራበኝም ስላት ፍሬ ታመጣለች

በረደኝም ስላት ሸማ ትልካለች

ሊባዬን ሰርቀውኝ ከሳጥን ገብታለች

እኔን ህዝብ በርሷ ቀን አስቆጥራዋለች።

እቴጌ ተዋበች ከመቀበራቸው ጥቂት ሳምንታት በፊት በሰማይ ላይ አመድ ፀሐይን ከብቦ ታየ። በየምሽቱ ፀጥታ በነገሰበት ተራራ ላይ ጨለማ ውስጥ ተቀምጦ የሰማዩን ትርኢት ይመለከታል። በ14ኛው ቀን ጠፋ። ቴዎድሮስ ወዲያው ሠራዊቱን አስከትሎ ወደ ወሎ ዘመተ እና ብዙዎችን ገደለ። በሺህዎች የሚቆጠሩ እንስሳትን ማረከ፤ ከዚያም ሥጋ ከጎመን ረከሰ። በአካባቢው የራሱን ታማኝ ሾመና እንደገና ወደ ደቡብ አቅጣጫ ለዘመቻው ገሠገሠ።

ሸዋ ላይ አንዳንዶች ሀገረ ገገርው ከአማፅያን ጋር በስውር እንደሚመሳጠር ሲያንሾካሹ ተሰማ። ቴዎድሮስ የቀድሞውን እስር አዲስ ሾመ። አዲሱ ሀገረ ገገርም ገና ቴዎድሮስ ሸዋን ሳይለቅ መክዳቱን አሳየ። ቴዎድሮስ ይህንንም አሰረው። በዚያም ላይ የወሎ ሀገረ ገገር ማመፁን ሰማ። ወደ ስሜን ዳግም ገሠገሠ፤ በሺህ እና በአስር ሺህዎች የሚገመቱ ተከተሉት። በዝምታም ተጓዘ።

## ምዕራፍ አስራ ሦስት

ዋልተር ፕላውደን አሳዛኝ ሆኗል። በደጋማው አካባቢ ያሉት ጥቂት ደጋፊዎች ብቻ ናቸው። ለቴዎድሮስ የሚያቀርበው አንዳች የለውም። ለንደንም ቢሆን ለእርሱ ተዕልኮ የነበራት ፍላጎት ጠፍቷል። ወደ ብሪታኒያ ለመሄድ ወደ ወደቡ መድረስ ቢፈልግም መንገዱ በንጉሤ እንደተዘጋ ነው። ፕላውደን ቴዎድሮስ በንጉሤ ላይ ዘምቶ፣ ምፅዋን ከቱርክ በማስለቀቅ የባሕር ወደቡን መልሶ እንደሚይዝ ጥርጣሬ አልነበረውም። ሆኖም በአራት ዓመታት ውስጥ በታየው አዝጋሚ ሂደት ጠብ ያለ ነገር የለም።

በኦሮሞ ግዛት ከተካሄዱት ዘመቻዎች በአንዱ ከንጉሡ ጋር አብሮ ነበር። «ኦሮሞን ይተው እና ንጉሤን ለመውጋት ወደ ሰሜን ሂዱ።» ሲልም ተማፅኗል። ቴዎድሮስ በጣሊቃ ገብነቱ ተቆጣ። ግን ደግሞ «አንተን ምፅዋ ከማድረስ የሚያግደኝ ሞት ብቻ ነው።» በማለት ቃሉን ሰጠው።

ሁለቱ ሰዎች የተገናኙት ያኔ ነው። በ1847 አዲሱ ንጉሥ ቴ ዎድሮስ ከወታደራዊ ባለሥልጣናቱ፣ ፕላውደን ደግሞ ከብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የሚያገናኘው ደብዳቤ ይዞ፣ በጋራ ተስፋ ነበር የተያዩት። የቴዎድሮስ የተሃድሶ እቅድ ዘርፈ ብዙ ችግር ባላቸው ጠላቶቹ ምክንያት ባለበት ተገትቷል። የፕላውደን ደብዳቤም የሚያስረዳው ያንን ነበር። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ተለያይተዋል።

ፕላውደን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1830ዎቹ የኢትዮጵያን ደጋማ አካባቢዎች ሲረግጥ ዓለም ሰፊ ስፍራ ነበር። የብሪታንያ ፍላጎት እጅግም ለድርድር አይቀርብም ነበር። በ1839 ፓመርስን የፕላውደንን አዲስ ግዛት ያውም ጥንታዊ እና የተረሳ መንግሥትን የመያዝ ሕልም ተጋርቶት ነበር። ንግድ እና ፈረንሳዮች አካባቢውን እንዳይቆጣጠሩ ማገድ የፕላውደን ጥንታቄ የራቀው ፕሮጀክት ዓላማውን እንዲያሳካ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ አደረገው።

ቴዎድሮስ ዘውድ ሲጭን በ1847 መሆኑ ነው፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ክላረንደን ፕላውደን በነገረው የቴዎድሮስ አነሳስ እና ወደፊት ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት በጣም ተደስቷል። በቀጣይ ዓመታት ግን ለፕላውደን ሀገሪቱን ለቅቆ ለመውጣት ሁሉ አደገኛ ሆነ። ይህ በእንዲህ እንዳለም ፈረንሳይ፣ ብሪታንያ፣ ግብፅ እና ኦቶማን ቱርክ የቀይ ባሕር አካባቢን ለመቆጣጠር ያሳዩት መነሳሳት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን ይበልጥ አደገኛ (አሳሳቢ) አደረገው። በውጭ ሃገራት ግዛቶች ውስጥ የሚደረገው ጣልቃ ገብነትም ትልቅ ዋጋ ይጠይቅ ጀመር። የሕንድ ነባር ዜጎች የብሪታንያ በሀገራቸው መገኘት እንደማያስደስታቸው በግልፅ አመለከቱ። ኢትዮጵያ እና ቴዎድሮስም በቀላሉ የሚፈቱ ምሥጢሮች አልሆኑም፤ እንደውም ትርፍ የማይገኝባቸው አደጋዎች ነበሩ።



በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የፕላውደን ጉዳይ ከዕይታ ተሰውሯል። በ1852 ክላረንደንን የተካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ራስል በንጉሡ እና ማለቂያ በሌለው ትግሎቹ ተሰላቹ። አምባሳደር ስለመቀበል መወራቱ ቆሟል። አካባቢ እያባከነ አስፈላጊ የሚለው ወደቡ ብቻ ነው። ፕላውደን ጊዜውን በደጋው አካባቢ እያባከነ ነው። «መደበኛ መኖሪያህ ወደሆነው ወደ ምፅዋ መመለስ ይኖርብሃል፤ እጅግ የተለየ ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር ከዚያ አትለቅም።» ተብሏል። ነገር ግን ምፅዋ መድረስ አልቻለም።

የብሪታኒያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያደረገው አንድ ነገር ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያን ካቶሊኮችን መክሰስ እንዲያቆሙ እንዲነግራቸው መልእክት ለፕላውደን ማስተላለፍ ብቻ ነው። እያቅማማ ፕላውደን ደብዳቤውን ለቴዎድሮስ ላከ። «በሀገርዎ ሁሉም ልክ እንደ እኛ ሰው የሃይማኖት ነፃነት እንዲኖረው እንዲያደርጉ ከልብ እንመክርዎታለን።»

ቴዎድሮስ በአውሮጳውያን ጉዳይ ሲደናገር ይህ የመጀመሪያው አይደለም። የቆየ ወዳጁ ፕላውደን ለጠላቶቹ ጥብቅና ቆሞ ሲናገር ምን ማድረጉ ነው? ፈረንሳዮች ንጉሤን በሰሜን በኩል እየደገፉት ነው፤ ንጉሤም በፋንታው ቴዎድሮስን በእነሱ ርዳታ ካሸነፈ በኋላ ወደሮማ ካቶሊክ ሃይማኖቱን ለመለወጥ ቃል ገብቷል።እናም በፕላውደን አማካኝነት ቴዎድሮስም ካቶሊኮችን እንዲቀበል እየተጠየቀ ነው። ፕላውደን ከፈረንሳዮች ጋር ግንባር ገጥሞ ይሆን? ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ዘመቻ ላይ እንዳለ አነበበው። ለረዳቱም ሰጠው። ከስድስት ሰዓታት በኋላ የጦር ሰፈሩ እንዲፈርስ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ለደብዳቤው ግን ምላሽ አልሰጠም።

ፕላውደን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያን ከረገጠ 17 ዓመታት ዓለፉ። «ለለውጥ እና ገደብ ለሌለው ነፃነት የነበረኝ ፍቅር፣ በመጀመሪያ ወደ አቢሲኒያ መራኝ፤ በመጨረሻም እስረኛነት እንዲሰማኝ ሆነ።» አሁን ጎንደር ላይ በሌላኛው የደጋው የዝናብ ወቅት በውለታ የተዘረጋለት አልጋ ላይ ተንጋሎ የቀደሙትን ጊዜያት ያሰላስላል። ከዝሆን ግዳይ በኋላ በብሩ የጦር ሰፈር የነበረው ፈንጠዝያ፣ ለጦርነት የነበረው ጥድፊያ፣ በጣና ሐይቅ ዳርቻ የሚካሄደው የጉማሬ አደን፣ አስደማሚው የፀሐይዋ ጥልቀት፣ በጥልቁ የአባይ ሸለቆ ሺህ ኦሮሞዎች ሲዋኙ............

ከኦሮሞ መሪው አህመድ ሁሩ ጋር በመጠነኛ የጦር ሰፈር ጥቂት ጊዜያት አሳልፏል።«እንዳንወጣ ዝናቡ ስላገደን ያለማቋረጥ ጠጃችንን ጠጣን፣ ለስድስት ቀናትም ምግብ ሳንበላ ቆየን። አህመድ ያለ ምክንያት በጥርጣሬ እየተመለከተኝ ልጄን እንዳገባት እንዲሁም ከግዛቱ ሰፋ ያለ ክፍል እንድወስድ ጠየቀኝ።»

ፕላውደን ዕድል የምትከተለው ሰው ነው። ምንኩሉ ላይ የነበረውን ቤቱን ለቅቆ በወጣ በሰዓታት ልዩነት ሠራዊት ደርሶ መንደሩን በመላ አቃጠለው። የተሻሉ

ሰዎችን ማግባባትም ተሳክቶለታል። ብሩ እና ውቤ እንዲሁም አቡነ ሰላማ ሌላው ቀርቶ አደገኛው ኃይሉ ሰይጣን እንኳን ወዳጆቹ ነበሩ።«አቢሲኒያ ውስጥ በነበረኝ መልካም ዕድል ወዳጅ አደረኩት።» በማለት ገልፆታል። ከቴዎድሮስ ጋር የነበረን ወዳጅነት ግሩም የሚባል ጊዜ እና ለሁለቱም ትልቅ ትርጉም ነበረው። ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ጦር ሜዳ ሊሄዱ ሲሉ ንጉሡ የፕላውደንን እጅ ይዞ፤ «ሰው ሟች ነው፤ አንድ ነገር ቢደርስብኝ ለልጄ ጥሩ ወዳጅ ሁን። ለሀገርህም በጣም የሚወድ ጓደኛ እንዳለህ፤ ለአንተ ወዳጅነት ሲል ኤምባሲ ለመላክ የተዘጋጀ ወዳጅ እንዳለህ ጻፍላቸው። ልጄን እንዲረዱትም ለምናቸው።» ብሎታል። ፕላውደን መስማማቱን ሲገልፅም ቴዎድሮስ፤ «አወድሃለሁ አምንሃለሁም፤ ደህና ሁን።» ብሎት ሄደ።

ፕላውደን በሀገሪቱ ምሥጢራዊ ባህል እና ሕግ እንዲሁም የጦርነት ልማድ ውስ...
የእንግሊዝን ታሪክ ነፀብራቅ ተመስክቶ...

ግዛቱ ከደቡብ ከአዋሽ ወንዝ አንስቶ ተራራማውን አካባቢ አጠቃልሎ ቀይ ባሕር ወደብ ደረሰ። ብዙዎች ቴዎድሮስ ላይ አሳድረውት የነበረው ተስፋ ዳግም አንሰራራ። ፕላውደንም አንዱ ነው።

ጎንደር ላይ ፕላውደን ጓዙን ሸክፎ ለጉዞው ተዘጋጀ። ወደ ትግራይ ሄዶ ቴዎድሮስን ያገኝ እና በዚያው ወደ ወደቡ ያቀናል። ብሪታኒያ ሲደርስ እግሩን በአግባቡ መታከም ይችላል። ከምንም በላይ ደግሞ ቴዎድሮስ የተቀዳጀውን አዲስ ስልታዊ ድል ምክንያት በማድረግም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዘገባውን በግንባር ያቀርባል። በቅሎው ላይ ወጣ፤ ከጎንደር ሲወጣም ሸኚዎች ተከተሉት።

የቀሐን ወንዝ ሲሻገሩ አራት መቶ የሚሆኑ ታጣቂዎች ጥቃት አደረሱባቸው። ታጣቂዎቹ በቴዎድሮስ የወንድም ልጅ ሆኖም ግን የንጉሤ ተከታይ በሆነው ጋረድ ... ፕላውደን ጎኑ ላይ በጦር ተወጋ። ከዘጠኝ ቀናት በኋላ ... አሸለበ።

# ምዕራፍ አስራ አራት

ቴዎድሮስ በ1847 ዘውድ ከጫነ በኋላ ከላካቸው ከመጀመሪያዎቹ ድብዳቤዎች አንዱ በኢየሩሳሌም የአንግሊካን ጳጳስ ለነበሩት ሳሙኤል ጎባት የጻፈው ነው። ጎባት ከ20 ዓመታት በፊት ገዳማ ወደ ኢትዮጵያ በሚስዮናዊነት መጥቶ ነበር። ነገር ግን አሳሳቢ በሆነው የሀገሪቱ አለመረጋጋት ምክንያት ለመውጣት ተገደደ። እንደ ሌሎቹ ሁሉ የቴዎድሮስን መነሳት ሲመለከት ዳግም ዕድል መጣ ብሏል። ዕድሉ ግን ለሁሉ ሳይሆን ለአዲሱ የወንጌላውያን ሠራተኞች ትውልድ ነበር። ቴዎድርስ ግን እሱን የጠየቀው የእጅ ሙያ አዋቂዎች እና ሠራተኞችን ነበር። ቄሶችን በእርግጥም አይፈልግም። «የሀገራችን ሁኔታ ያውቁታል፤ የኖሩበት ነው፤ አንዱ በአንዱ ላይ እየተነሳ አንዳንዴም በሶስት ጎራ የተከፋፈለ ነበር። አሁን በእግዚአብሔር ኃይል አንድ አድርጌዋለሁ፤ አሁን ሃይማኖት የሚያተራምሱ ቄሶች ሳይሆኑ ሠራተኞች ናቸው፤ ወደ እኔ መምጣት ያለባቸው። መሬትን በተሽከርካሪ ጎማ የሚያርሰው መሣሪያውን ይዞ ወደ እኔ ይምጣ፤ እንዲህ ያለነገር መኖሩን ሰዎች ነግረውኛል» ይላል የቴዎድሮስ ደብዳቤ።

ከስምንት ወራት በኋላ ሳሙኤል ጎባት በኢየሩሳሌም ፅዮን ተራራ ላይ በአንግሊካን ጉባኤ ፊት ቆመ። ሰባት አዲስ የሰለጠኑ ሚስዮናውያን እፊጠጡበት። «ወንድሞች ሆይ ለዓመታት ስትዘጋጁበት የነበረው ጊዜያችሁ መጥቷል፤ በሃይማኖት አብረዋችሁ ካደጉት ክርስቲያኖች የምትለያዩበት ሰዓት።» ጳጳሱ ጠንካራ እና ወፍራም ነው። ረጅም ነጭ ጺሙ ወደ ደረቱ ወርዷል፤ በንግግሩም እንዲህ ባለው ተልዕኮ ራሱ ያሳለፈውን ልምድ አቀረበ።

«አሁን በጨለማ በተሸፈነችው ሀገር እና በሞት ጥላ ስር በሚገኙት ሕዝቦች መካከል በድካማችሁ ሁሉ በጌታ ላይ ልትደገፉ ይገባል። ማለቂያ የሌለውን ደካማነታችሁን እና ረዳት አልባነታችሁን ከተረዳችሁ ወደ ልባችሁ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆናችሁ የምታዩበት የፀሐይ ጨረር ይገባል፤ ይህ ደግሞ በፊታችሁ የጉዟችሁ አስቸጋሪነት እና የምትገቡበት ሕዝብ ስብጥር በሚታሰባችሁ በአሁኑ ሰዓት ሁሉ ሊሰማችሁ ይገባል።» ሆኖም ግን ኢትዮጵያውያን የራሳቸው በሆነው የክርስትና መንገድ ሁሉም ያልዳኑ ናቸው ማለት አይቻልም። ቀጠለ ጎባት፤ «በራሱ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነበው የአሁኑ ንጉሥም ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡትን አባ ሰላማን ስንመለከት፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለማዳረስ የሚገጥማችሁ እንቅፋት አይኖርም፤ ከራሴ ልምድ እንዳየሁት አብዛኛዎቹ አቢሲኒያውያን መጽሐፍ ቅዱስን አመስግነው ይቀበላሉ»። ሆኖም ግን ተልዕኳቸውን በተመለከተ አደናጋሪ ነገር እንዳያሳዩ አስጠነቀቃቸው።

«የማዳን ተልዕኳችሁን ለማከናወን ሀገሪቱ ውስጥ መቀመጥ እንችላለንወይ የሚል ቀጥታ ጥያቄ ለንጉሡ እንዳታቀርቡ። ይህ ከሆነ የምታገኙት ወሳኝ ምላሽ ይሆናል። ይልቁን የሚበጀው ዕቅዱን አለማመላከት ነው፤ መዳኛትም አያስፈልግም፤ በቅድሚያ በመንፈስ እና በዓለም ፈጣሪ የሚመራ እውነተኛ ክርስቲያን በሚመስል ባህሪያችሁ ንጉሡን ልታግባቡ እና ልታሳምኑ ይገባችኋል። » ጎባት አፍሪቃ ውስጥ ታላቅ እና አዲስ የወንጌላዊነት ዓለም እየተከፈተ ነው ብሎ አምኗል። እሱና ኮሚቴው በኢትዮጵያና ግብፅ መካከል አስራ ሁለት «የሐዋርያዎች» ጣቢያ ለማቋቋም አቀዱ፤ ዋና ተግባሩም ለኢትዮጵያው ተልዕኮ አስፈላጊውን ማቅረብ እና የእግዚአብሔርን ቃልም ከአንዱ ጣቢያ ወደ ሌላው ማሰራጨት ነው።

«ከፊት ለፊታችሁ የተዘረጋው በረሃማ ስፍራ ወደ እግዚአብሔር የአትክልት ስፍራነት መቀየር ይኖርበታል። ማዳዋ በጣም ሰፊ እና የማይለካ ነው። አቢሲኒያ ብቻ ሳይሆንአጎራባቹ የኦሮሞ ጎሳ ግዛት፤ እንዲሁም ማዕከላዊ አፍሪቃንም ያጠቃልላል። አቢሲኒያ መግቢያ ነው፤ እዚያ ዲያብሎስ የራሱ ግዛት አለው፤ ለሺህዎች ዓመታትም በፀጥታ እና ሳይረበሽ የራሱን መንግሥት እንዲመራ ተፈቅዶለታል።»

በመጨረሻም በእጅ ሥራ ባለሙያነት መጋበዛቸውን እና የወንጌላዊነት ተልዕኳቸውን በዚህ መሸፈን እንደሚኖርባቸው አስታወሳቸው። «ምናልባት በመስበክ እና በማጥመቅ ፈንታ የእጅ ሥራ እየሠራችሁ በከፊልም ደመወዝ እየተቀበላችሁ መኖር እንዳለባችሁ ስትሰሙ ያልተለመደ እና እንደማትስማሙበትም ሊሰማችሁ ይችላል፤ ምናልባትም ዲያብሎስ ቢያንሾከሹክላችሁ የራሳችሁ ልብ ጮሆ ብሎ ቢታ፤ ሠርተን የላባችንን እናገኛለን፤ እንኖራለን እንሞታለንም፤ ረጅም ዝግጅት ሳናደርግ እና ወደ አቢሲኒያም ሳንጓዝ ጀርመን ውስጥም ልንሰራ እንችላለን ልትሉ ትችላላችሁ።» ጎባት ባደረገው የአቢሲኒያ ገለጻ ከተዘጋጁት ሦስቱ ከተልዕኮው ራሳቸውን አገለሉ። በሌሎቹም ላይ ማመንታት ታየ፤ ከሰባቱ መካከል ሁለቱ ብቻ ማየር እና ኪንስለን በጉጉት ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ተዘጋጁ።

# ምዕራፍ አስራ አምስት

ቴዎድሮስ በዘመቻ ... መሰናክል ሄደ። ቴዎድሮስ በዘመቻ ...ቀት ዓመታት ተልዕኮው ያለምንም መሰናክል ሄደ። ቴዎድሮስ በዘመቻ
...ቀት ዓመታት ተልዕኮው ያለምንም ... ትኩረት ለማድረግ አልቻለም። በ1850 ላይ ግን
መወጠሩ ሚስዮናውያኑ ላይ ትኩረት ለማድረግ አልቻለም። በ1850 ላይ ግን
...ለቤቱ ተዋበችን እንዲያከሙለት ጠየቃቸው፤ የተጠየቁትን አደረጉ፤ እናም
...ዚያን ጊዜ ወዲህ መቀራረብ ጀመሩ። የራሱ የቤተ ክህነት ሰዎች ጅላጅል
...መሆናቸውን ስላሳዩት ከደቡብ ጀርመናውያን ቄሶች ጋር ቴዎድሮስ ጊዜ ያጠፋ
ጀመር፤ በዚህም ለእነሱ እምነት አክብሮት ማሳየትን ጀመረ። እነሱ በፈንታቸው
አርሞ ላይ የሚወሰደውን የጭካኔ እርምጃ ወደ ጎን ብለው ያደንቁት ገቡ።

ኪንስለን እንዲያውም "አቢሲኒያ ውስጥ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው እሱ ብቻ ነው።" በማለት ጽፏል። በ1851 አዲስ ሚስዮናዊ መጣ። ትህትና እና እንደ ቅዱሳን ያለ በጎነት የተላበሰው ወጣቱ ስዊዛዊ ቴዎፍሎስ ቫልድማየር። ቴዎድሮስ ከውጭ ዜጎች መካከል በተለየ የሚወደው እያጣም። ዓመታት ሲያልፉም ቫልድማየር የጆን ቤልን ቦታ የሚተካለት ሆነ።

ቴዎፍሎስ ቫልድማየር በጥብቅ ካቶሊካዊ ሥርዓት ያደገ ነው። በሂደትም ትንሹ ቴዎፍሎስ «ከሕዝቡ ይልቅ ቀሳውስቱ ታላቅ ኃጥያተኞች» መሆናቸውን ተገነዘበ። የሴት አያቱ ይህን በማለቱ ምክንያት ስትገርፈው ከቤቱ ወጥቶ ሄደ። ካቶሊካዊነትን ትቶም ታዋቂ በሆነው የሚሲዮን ትምህርት ቤት ቅዱስ ክሪሾና ኮሌጅ ገባ። ከዚያ ደግሞ ሳሙኤል ጎባት መጥቶ ለኢትዮጵያው አገልግሎት መረጠው።

ወደ ኢትዮጵያም ከሌላኛው ሚስዮናዊ ዛልሙለር ጋር ሄደ። ከእነርሱ ጋርም ሁለት ጀርመናውያን ሚስዮኖች ማርቲን ፍላድ እና አዲሷ ሚስቱ ሲስተር ፓውሊና ነበሩ። ቴዎድሮስ ላቀረበው ከሃይማኖት የፀዳ ተልዕኮ ሽፋንም ሸሮት እና ልጁ አብረው ነበሩ። የጠብመንጃ ሰሪዎች ናቸው። በ1850 ማለቂያ ላይ ይህ የሚስዮናዊያን ቡድን በግብፅ በረሃ ጉዞውን ጀመረ። ረጅም የሚመል ሰልፍ ይከተላቸዋል። ከሠላሳ ሁለቱ ግመሎች አብዛኛዎቹ የተጫኑት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ጉዞው በራሱ ለወጣቱ ቫልድማየር አስደሳች ነበር። የፈርኦንን ሀገር እና የእስራኤል ልጆችም እዚያ በስደት የኖሩባት ግብፅን መመልከቱ ሰቦታል። በረሃው «በእግዚአብሔር ቁጣ የነደደውን ያለፈውን ዓለም» ይመስላል። የበረሃ ጉዞ አዳጋች ነው። በራሱ ገራገር አገላለፅ «የውኃ እጥረት አለ» ሲል አብረውት የሚጓዙትን አስጠንቀቀ።

ጉዞው እየከበደ አካባቢውም እየጋለ ሄደ። በጓዛቸው ውስጥ የከተቱት ሻማ እየቀለጠ በግመሎቹ ላይ ተንጠባጠበ። ከወ/ሮ ፍላድ በቀር ሁሉም ታመሙ እና ለቀናት በዚያ ሙቀት ውስጥ በተቆለለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥላ ስር ሰፈሩ። ሸሮት



እና ልጁ ሲሞቱ ሌሎቹ እነሱን ለመቅበር የተዳከመ አካላቸውን በግድ እንቀሳቀሱ። ሁሉም ታዲያ በቅርቡ እነሱ ወደ ሄዱበት መንገድ እንደሚከተሉ አልተጠራጠሩም። እግዚአብሔር ግን አተረፋቸው፤ በዚያም ሳይቆዩ በዱር አበቦች እና ንፁህ ውኃ ተከበው ወደ ደጋው ይወጡ ጀመር።

በዚያን ጊዜ ጆን ቤል ሊቀመኳስ ነበር እና በንጉሣዊው የጦር ሰፈር ተቀበላቸው። ወደ ቴዎድሮስ ፊትም አቀረባቸው፤ ቫልድ ማየር ንጉሡ የጦር ሰው አልመሰሉትም። በፈገግታ ስለጉዞው ጠየቃቸው፤ሸሮት እና ልጁ መንገድ ላይ በመሞታቸውም ሐዘኑን ገለፀ።

ቴዎድሮስ፤ «በኃጢአቱ ምክንያት ነው እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች የወሰዳቸው» ሲልም አከለ። ወደ መቅደላም ላካቸው፤ ለራሳቸው ደህንነት ነው ይህን ማድረጉ። ቴዎፍሎስ ቫልድማየር ተራራው እናት ላይ ባለችው ከሌሎቹ አምስት ሚስዮናውያን ጋር በሚጋራት ቤቱ ውስጥ በቀላሉ ተመቻችቶ ተቀመጠ። ሚስዮናውያኑ አማርኛ ቋንቋ ያጠኑ እና መሠረታዊ የሜካኒካዊ ዕውቀት የቀሰሙ ናቸው። ከንጉሡ ጸሐፊ ከደብተራ ዘነብ ጋር ረጅም የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክር ይከሄድ ነበር። ደብተራው በወቅቱ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ለማየት ነው የመጣው።

ቫልድማየር ለተልዕኮ በተጠራበት ሀገር ተደሰተ። ከዝናቡ ወቅት በኋላ መላ ሀገሪቱ ወደ ረጅም የአበባ አትክልት ስፍራነት ትለወጣለች በማለት ጽፏል። «ሕዝቡ የሚያምር እና ከተማረ በሁሉም ነገር ብልህ ነው።» ከእርሱ ቀድሞ ፕላውደን እንዳደረገው ሁሉ «መልካም አስተዳደር እና የጥንት ወደቧን ምፅዋን ካገኘች» ኢትዮጵያ እንደምታድግ እና ስለወደፊት ስኬቷ ያልማል። በቴዎድሮስ መልካም ሙከራዎችም እምነት አሳድሯል።

«ለመሆኑ ባለው ስልጣን እና ገናንነት የራሱን ምኞት ትቶ፤ በቅንነት እና ጥሩ መኖር ሲችል እንደ ድሃ የሚኖር ንጉሥ የት ነው የሚገኘው? መሸለም እና ንግሥናን እየሰጠ፤ በሕያው እግዚአብሔር ታምኖ ኢአማኒ እና ያልሰለጠኑ ሕዝቦችን ለመርዳትስ የሚጥር ማን ነው?» ሲልም ጠይቋል።

በፈንታው የቴዎድሮስን የተሰበሩ ጠብመንጃዎችን በመጠገኑ ቫልድማየር የንጉሡን ትኩረት ስቧል። እንዲያውም በታኅሣስ ወር ቫልድማየር የቴዎድሮስን ዘመድ አግብቶ ቤተሰብ ሆነ። መቅደላ ላይ ከሚኖረው ማሕበረሰብ ውስጥ የጆን ቤል ባለቤት የሆነችው የቴዎድሮስ የእከስት ልጅ ወርቅነሽ እንዷ ናት። ቫልድማየር የእነሱን የመጀመሪያ ልጅ ሣራን አገባ፤ ቆየት ብሎም ዛልሙለር እህቷን አገባ። ለሠርጉም ቴዎድሮስ በወርቅ የተጠለፈ ካባ፤ ውድ የሐር ሸሚዝ፤ ስማንያ በሬዎች እና አምስት መቶ በጎችን ላከለት። ድግሱ ለአንድ ሳምንት ሲበላ ሲጠጣ ሰነበተ።

እንዲያም ሆኖ ቫልድማየር መቅደላ ከመጡበት ወንጌላዊ ስራ እጅግ የተነጠለ መሰለው። ለእማቱ ጆን ቤል አንድ ሚስዮን ማቋቋም እንደሚያስፈልጋቸው ነገረው። ቴዎድሮስ ከመናገሻው ደብረታቦር ከተማው በስተሰሜን የሚገኘውን እነስተኛ ኮረብታ ጋፋትን ሰጣቸው። በዚህ ስፋራ ፕላውደን ለጥቂት ጊዜ ተቀምጧል። ቆንጆ ቦታ ነው። የጋፋት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ወጣቶቹ ጎጆ ወጪዎች ደኑን መንጠረው ጎጇቸውን ሲሰሩ፣ ለድሃ ልጆችም ትምህርት ቤቶችን ሲከፍቱ ሃይማኖታዊ ተልዕኳቸው መንፀባረቅ ጀመረ። በሂደትም ጋፋት ቴክኒካዊ ዕውቀት የሚገኝበት ማዕከል ሆነ። ሚስዮናዊያኑ የጉድጓድ ውኃ አዘጋጁ።

ቴዎድሮስም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በትዕዛዝ ወደዚያ ይልካል። «የአቢሲኒያ ብልህ ወንዶች ሁሉ በንጉሡ ትዕዛዝ ወደዚያ መጡ። ቴዎድሮስ ራሱ በተደጋጋሚ ቦታውን ይጎበኝ ነበር፣ እኔም አብዛኛውን ጊዜ ከንጉሡ ጋር በመቀመጥ ስለሃይማኖታዊ ውይይቶች፣ ስለሀገሩ እና ስለሕዝቡ ደኅንነት እናወራ ነበር።» በማለት ቫልድ ማየር ጽፏል።

ጆን ቤል ከተገደለ በኋላ የቴዎድሮስ ዓለም ይጨልም ጀመር። በበሰለ አዕምሮ ይካሄድ የነበረው ውይይት እየቀነሰ ሄደ። ንጉሡ ጋፋት ላይ ከሰፈሩት ሚስዮናዊያን የሚፈልጉትን ግልፅ አደረጉ። የጦር መሳሪያ እንዲሰሩ የሚፈለገው በጣም ትልቅ ፣ እጅግ ትልቅ የጦር መሳሪያ ነው።



## ምዕራፍ አስራ ስድስት

ቴዎድሮስ የጦር መሳሪያ ለመሥራት የሞከረው ንጉሥ ከመሆኑ አስቀድሞ ራስ አሊ ላይ የዘመተ ጊዜ ነበር። እንጨት ቦርቡሮ ዙሪያውን በመጠምጠም ድንጋይ ሞልቶ ያንን ተኩሷል። እርግጥ ነው ሙከራው ያን ያህል የተሳካ አልነበረም። የተቀዳጃቸው ድሎች ጥቂት የማይባሉ የጦር መሳሪያዎችን መማረክ አስቻለው። ተጨማሪ አራት ጠብመንጃዎችን ሰይድ ፓሻ ሰጠው፤ ሌሎች የጦር መሳሪያ ስጦታዎችን ግን ምፅዋ ላይ በነበረው የቱርክ ገዥ አዚያው ያዘበት። የባሕር ወደብ የጣው ቴዎድሮስ ደህና የጦር መሳሪያ ማግኘት ከፈለገ፣ እራሱ እዚያው መስራት እንደሚኖርበት ተገነዘበ።

በ1853 መሴ ገርኪ የተባለ ሰው ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ ተሰማ። ፈረንሳዊው እንግዳ የብረት ስራ አዋቂ የመሆኑ ወሬም ተናፈሰ። ቴዎድሮስ ጋፋት ወደ ሚገኙት መሰሎቹ እንዲሄድ ትዕዛዝ ላከበት። በዚያም ቴዎፍሎስ ቫልድ ማየር እና ሉሎቹ ፕሮቴስታንት ሚስዮናዊያን መድፍ በመስራቱ ያግዙታል። ሚስዮናዊያኑ ደግሞ የጦር መሳሪያ ሲሰራም የሚያስፈልገውን ሁሉ ለገርኪ እንዲያቀርቡ አዘዘ። «ይህን በጉልበትም ሆነ በሌላው የሚረዱትን እንዲያስተባብሩለት ተነገራቸው። መቃወም አንችልም።» ሲል ይቅር ባዩ ቫልድ ማየር ጽፎታል።

ገርኪ ጋፋት ሲደርስ ሚስዮናዊያኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰራተኞችን መለመሉለት። ከተመረጡት ገሚሱ የብረት ማዕድን ወደሚገኝበት ከነበቅሎቻቸው ሄዱ። ገሚሱ ካልሲዬም ካርቦኔት ያለበትን የድንጋይ ቋጥኝ እየናዱ ይፈጩ ጀመር። በቀናት ውስጥ ትልቅ ማንደጃ በእነስተኛ የጋፋት ኮረብታ ላይ ጎልቶ ታየ። የበሬ ቆዳ በአንድ ወገን ተያይዞ ተሰፋ። ከሰሉ ይነድ ጀመር። ገርኪ በጉጉት ስራውን እየተዘዋወረ ይቆጣጠራል። ስራው ተጠናቀቀ ብሎ ሲወስን ሁኔታውን ለመመልከት ሰው ተሰበሰበ።

ምድጃው ተቀጣጠለ። ወናፉ ከያለበት ሲነፋ እየሩ ሽከላውን ይሞላው ጀመር፣ በውስጡ እሳት ተንቦገቦገ፣ ድምፁም ይሰማ ጀመር፣ ገርኪ በመደናገር ቆሞ ይመለከታል። ወፋፍራሞቹ የበሬ ቆዳዎች ይለጠጣሉ፣..... ዳግም ይሚሸሻሉ ፣... ይለጠጣሉ፣.. ይሚሸሻሉ፣ የሙቀት መጠን ከፍ እያለ ሄደ። በውስጡ ያለው ባሩድ ወደ ቢጫነት ተለወጠ። እስካሁን ወናፎቹ ይሰራሉ። ሙቀቱ ጨመረ፣ ባሩዱ እየፈገገ ሄደ፣ .. ከዚያም ቀላ እያለ የምድጃው ውስጠኛ ግድግዳ መፈራረስ ጀመረ። ቫልድ ማየር እንዳስተዋለው ፈረንሳዊው ማዘንና ማልቀስ ጀመረ። «ወፈፍ አደረገው፣ ጮሆ አለቀሰ፣ በመጨረሻም ንጉሡ እንዲሄድ እንዲፈቅዱለት ጠየቀ። ሲፈቅድለት ሀገሪቱን ለቆ ሄደ።» ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቴዎድሮስ ራሱ ወደ ጋፋት መጣ። ሚስዮናዊያኑን ሰበሰበ እና ገርኪ የጀመረውን ስራ እነሱ በመቀጠል ትልቅ የጦር መሳሪያ መሥራት እንዳለባቸው ነገራቸው። የተከበሩ ጃንሆይ ስለዚህ ጉዳይ

ዕውቀትም ሆነ ልምድ የለንም፡ ፍፁም ደንቆሮዎች ነን፤ በማለት በአግባቡ ገለፁ።
«ይህ ችግር አይሆንም፤ ወዳጆቼ ከሆናችሁ ምክሩት፤ እግዚአብሔር እንዲሳካ ከፈቀደ መልካም ነው፤ ካልፈቀደም እንዲሁ መልካም ነው።» አለ ቴዎድሮስ። በዚህ አባባሉ ላይ ተቃራኒ ሊያነጋግር የሚችል ነገር ነበር። ከመሄዱ በፊትም ቴዎድሮስ እነሱን ለማበረታታት አገልጋዮቻቸው እንዲታሰሩ አዘዘ። ቫለድ ማየር እና ሌሎቹ ሚስዮናዊያን በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ተሰበሰቡ። ኅብት የላካቸው የጦር መሳሪያ በመገንባት ሕዝቡን ለማሸበር አይደለም። ነገር ግን በጋፋት ቆይታቸው ትምህርት ቤቱ፡ እንዲሁም በሙቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያስራጩት ትምህርት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ተስማሙ። የቴዎድሮስን ትዕዛዝ ማክበር አላባቸው፤ ግን እንዴት? መመሪያ ለማግኘት ጸለዩ። ተከራከሩም። ማቀጣጠያውን በጠንካራ በድጋሚ ጸለዩ። ገርኪ የተናገረውን ለማስታወስ ሞከሩ። ግን አልተሳካም። ምን ግድግዳዎች አጥብቀው ዳግም ለመገንባት ብዙ ጣሩ። ግን አገልጋዮቻቸው ሁሉ ታስረዋል። ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም። በዚያም ላይ አገልጋዮቻቸው ሁሉ ታስረዋል። ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም። በዚያም ላይ መንገድ ግንባታም ይሁን በመጨረሻም ሚስዮናውያኑ ወደ ንጉሡ በመሄድ መንገድ ግንባታም ይሁን በመጨረሻም ሚስዮናውያኑ ወደ ንጉሡ በመሄድ የሚላችውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁዎች ድልድይ! ማስተማር ጨምሮ አድርጉ የሚላችውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁዎች እንዲሆኑ ነገር ግን ይህ የብረት ስራ ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ ለማቅረብ ተስማሙ። በጣም አስቸጋሪ ነበር።

ቴዎድሮስ ጋሪ እንዲሰሩለት አዘዛቸው። ማየር ለስራ ተዘጋጀ። በበቅሎች የሚጎተት ተሽከርካሪ ሥራ ሆኖም ግን መንገድ በሌለበት ጎማዎቹ ምንም ጥቅም የሚሰጡ አልሆኑም። ከቦታ ቦታ ለመጓጓዝ እንዲያውም እየተበታተኑ ዳግም ለመግጠም የገበሬዎች መሳቂያ አደረገው። ቫልድ ማየር የጠብመንጃ ማቀፊያውን እንጨት ለመስራት ቀናት ቢፈጁበትም የተሰራው ማማሩን ያስተዋለው ቴዎድሮስ የሚስዮናምያኑ አገልጋዮች እንዲፈቱ አዘዘ። እንዲያም ሆኖ ለመስራት ገና አልተቃረበም።

ከኒኮላስ 1ኛ ጦር ከድቶ የሸሸው ሞሪትዝ ሃል ኢትዮጵያ ውስጥ ለጥቂት ዓመታት ተቀምጧል። ፕሮቴስታንት ሚስዮናዊያኑ ጋፋት ላይ መድፍ ለመስራት ሲታገሉ እሱ ደወል እየሰራ ይሸጥ ነበር። እናም በዚህ ወቅት ሃል በሌላኛው የቴዎድሮስ ግዛት ውስጥ አንድ ታምር ሠራ፣ ጠብመንጃ ። የሚያስገርም የደወል ቅርፅ ነበረው። ግዙፍ እና ኃያል ይመስላል። "ንጉሡ ሲመለከቱት በደስታ ዘለው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።" ብሏል ቫልድ ማየር። ለጥቂት ጊዜያትም ቴዎድሮስ ጠብመንጃውን በተመለከተው ቁጥር ተመሳሳይ ደስታ ይሰማው ነበር። እየቆየ ግን ቀስ በቀስ የተሰማው እርካታ ቀነሰ። ወደ ሃል መልዕክተኛ ልኮም የስራት ጠብመንጃ ትንሽ እንደሆነች እና እሱ ግን ትልቅ እንደሚፈልግ ነገረው።



«ብቻዬን ይህን የስራ ኃላፊነት ለመቀበል ይከብደኛል። ጋፋት የሚገኙት ኢትዮጵያውያን የሚረዱኝ ከሆነ ግን የግርማዊነትዎን ትዕዛዝ ለመፈፀም እችላለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።» አለ ሃል።

«ቫልድማየር እና አውሮጳውያኑ በሙሉ ከአንተ ጋር ይሰራሉ፤ በጋራ በመመካከር እናመፈ.ቃቀር ሥሩ።» ቴዎድሮስ አዘዘ። የንጉሡን ቡራኬ ተቀብሎ ሃል ወደ ጋፋት ሄደ። ምን መስራት እንደሚኖርባቸው ሲነግራቸው አውሮጳውያኑ ሁሉ ተርበተበቱ። በተደጋጋሚ የቴዎድሮስ መልዕክተኛ ወደ ጋፋት ሲመጡ ምንም ለውጥ እንደሌለ ለንጉሡ ይነግሯቸዋል። የንጉሡ ምላሽ «ግድ የለም፤ ከመጀመሪያው ጀምራችሁ እንደገና በጥንቃቄ ሥሩ» የሚል ነበር።

ባፕቲስት የተባለ ኦስትሪያዊ ወደ ቴዎድሮስ ችሎት ቀረበ። ስለ ንጉሡ የጸና ፍላጎት የሰማው ይህ አውሮጳዊ ከአካባቢው በተገኙ ንጥረ ነገሮች ባሩድ መስራቱን ተናገረ። ጥቂት በጥቂት እየቆነጠረ ሲያቀጣጥለውም ዱቄቱ በሚያምር ሁኔታ ሲፈነዳ ታየ።

ቴዎድሮስ ተደሰተ። ለሰውየውም ማር፣ በግ፣ ቅቤ እና ገንዘብ ሰጠው። እና በርከት አድርጎ እንዲያዘጋጅ ጠየቀው፤ ብዙም ሳይቆይ ግን የባፕቲስት ማንነት ተጋለጠ። ከአካባቢው ቀመምኩት በማለት ያቀረበው ባሩድ ከእንግሊዝ የመጣ ነበር። በድጋሚ ቴዎድሮስ እንዲያፈነዳ ሲጠይቀው ከእንግሊዝ የመጣው ባሩድ በማለቁ ከአካባባው ያሰባሰበው ንጥረ ነገር አልፈነዳ አለ። እሳት ውስጥ ሲወረውረው ፍንክች፣ .... የሆነ ነገር የለም። ባፕቲስት ሸሸ። ቆየት ብሎ ሚስዮናውያኑ መካ ውስጥ በነፍስ ማጥፋት ተከሶ መገደሉን ሰሙ።

ጋፋት ላይ አሁንም ሚስዮናውያኑ እና ሃል ስኬት እንደራቃቸው ነው። እነዚህ አውሮጳውያን እንደ ባፕቲስት አያታለሉ ነው የሚል ሹክሹክታ ከቴዎድሮስ ጆሮ ደረሰ። ንጉሡ በገሃድ ሕዝቡ ፊት አፈረ፤ ይህ ሁኔታም ለእነሱ አደጋ መሆኑን ሚስዮናውያኑ ተገነዘቡ። ተሰብስበው በጋራ ጸለዩ እና ለመጨረሻ ጊዜ በተፈጥሮ ያገኙትን ብረት አሰባስበው ማቀጣጠያውን አዘጋጁ። "ያለ የሌለ አቅማችንን አስተባብረን በመጨረሻ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳካ ሥራ ሠራን።" በማለት ቫልድማዬር ጽፎታል።

ወዲያው ሁሉም ነገር ተቀየረ። የአካባባው ህዝብ በእነሱ ላይ መሳቁን አቆመ። በሰሩት መሳሪያ በመገረም እንኳን ደስ አላችሁ አሏቸው። "ንጉሡ በትንሿ ብረታችን የተሰማቸው ደስታ ከፍተኛ ነበር፤ ሳመው እና አለቀሰ።" ብሏል ቫልድማየር በማስታወሻው፣ አያይዞም «አሁን ሐበሻ ውስጥ ማንኛውም ነገር መስራት እንደሚቻል አመንኩኝ፣ ጥበቡ ተገኝቷል፣ እግዚአብሔር በመጨረሻ ራሱን ገለፀ።» አለ ቴዎድሮስ።

ለሚስዮናውያኑ የቀለጠ ድግስ አዘጋጅቶም «ከዘውዴ እና ከግዛቴ ውጭ ምን ልስጣችሁ?» አላቸው።

« ግርማዊነትዎ ከዘላቂ ፍቅርዎ እና ወዳጅነትዎ ሌላ የምንመኘው የለም።» መለሱ ሚስዮናውያኑ። ቴዎድሮስ ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ሺህ የጀርመን የብር ገንዘብ(ታለር) ሰጣቸው ለተወሰነ ጊዜም በሁለቱም ወገን ደስታ ሆነ።

ቀጠለና ንጉሡ ተለቅ ያለ መድፍ እንዲሰሩ ጠየቀ። በድጋሚ ሚስዮናውያኑ ፍርሃት ዋጣቸው። ወደ ጋፋት ተመልሰው ደጋግመው ጸለዩ። ተሳካላቸው። ቴዎድሮስም ጥልቅ ምስጋና የተሞላበት እና ከላከላቸው ረዥም ደብዳቤዎች አንዱን ------- ጻፈላቸው።

« ወዳጆቼ እና ልጆቼ ! ሁሉን የሰራና ያደረገው እግዚአብሔር በሥራችን እንድናፍር አልፈቀደም። በዚህች ሀገርም ሆነ ውጭ የሚጠሉን ብዙ ሰዎች እንዳጠውናል ተሳቅለውብናል፣ ሆኖም/ አሁን ግን/ እግዚአብሔር በሚያምኑት ሰዎች ፀሎት በሁሉ ላይ ተገልጾ ስለረዳው አፈሩ። ሌሎች እንደ እውር አህያ ሲያበሻቅጡን እናንተ ግን የእኛን የአቢሲኒያውያን ዓይኖች ከፈታችሁልን» ። (ቴዎድሮስ ራሱ ለቫልድማየር ሀገሬ አህያ ሞላባት እንጂ ገነት ናትብሎታል) ። ጥንካሬ እና ቁርጠኝነት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውነን አስመሰገናቸው።

እግዚአብሔር አዳምን«በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ » እንዳለው በእንዲህ ያለ ውጥንቅጥ ውስጥ ላለችው ለዚህች ሀገር አለመታገል እና አለማሰብ ኃጢያት ነው። " ደብዳቤው ንጉሡ ለዘመናት ያሰበውና የተመኘው ሆኖለት በከፍተኛ የደስታ መንፈስ ላይ ሆኖ እንደጻፈው ግልፅ ነው።

" ሌሎች ነገሥታትን በብዙ ጠመንጃ እናመድፎች ድል ያደረገው የፈረንሳዩ ንጉሥ ናፖሊዮን በናፖርት በመጨረሻ ከነበረበት ከፍተኛ ሥልጣን ወድቆ ሞቷል የሩሲያው ንጉሥ ኒኮላይ ምንም እንኳን ጠንካራ ገዥ ቢሆንም በእንግሊዝ በፈረንሳይ እና በቱርክ ተሸንፎ በልቡ ያሰበውን እቅድ ሳያሳካ ብዙም ሳይቆይ ከዚህች ዓለም ተሰናብቷል። የእኛ ንጉሥ ሰናከሬም በኃይሉ በመታበይ በእራሱ ተመካ፡፡ በልቡ ኩራትም ፈጣሪውን ካደ ከሞት ግን አላመለጠም። የግብፁ ፈርኦን በጉልበቱ ተመካ፣ ልቡንም እግዚአብሔርን በመቃወም አፀና እና ቀይ ባሕር ውስጥ ሰጠመ። እንዲሁ ለእናንተ ከዚህ ሌላ ምን ልንገራችሁ? እራሳችሁ ተምራችሁታል ከመጽሐፍ ቅዱስም ትጠቅሱታላችሁ «ለአንበሳ አይመትሩ፣ ለብልህ አይመከሩ!»

እግረመ ንገዱን ቴዎድሮስ ስለእሱ የዘርሃረግ እና ቤተሰብ የሚባለውንም ቀጠለ። በመጨረሻም ሰዎች እኔ ተገቢው የዘውድ ወራሽ ሳልሆን የድሀ ገበሬዎች ልጅ እንደሆንኩ እየጠቀሱ ያማሉ። የእኔን የዘውድ ወራሽ ባለመብትነት ከአብርሃም



እስከ ዳዊት እና ሰለሞን ከዚያም ፋሲል እናም ከፋሲል ወደ እኔ መውረዱን ማረጋገጥ ይቻላል።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ንጉሡ ወደጋፋት ሄደ እና መሣሪያዎቹ እንዲፈተሹ ጠየቀ ሚሲዮናውያኑ ሳልሙለር ቤት ፊት ለፊት ተሰበሰቡ። ለቴዎድሮስ ምንጣፍ ተነጠፈ እግሩን አጥፍ አድርጎ በመቀመጥ ቦታውን ያዘ። ሌሎቹ ደግሞ አንድ ወገን እና ከኋላው ተሰበሰቡ። በቅርቡ የተሰራው መድፍ መጣ። ሚስዮናውያኑ ከሰሩት ትልቁ መሣሪያ መሆኑ ነው። የሚስዮናውያኑ አባት /የበላይ / ወንድም ቤንደር ለመተኮስ አጎነበሰ ለተወሰነ ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ። መድፉ ከማቀፊያው ወደኋላ ተንቀሳቀሰ ቤንደር ወደጎን ሸሽቶ ለጥቂት አመለጠ። ይተኩስ ጀመር። ቴዎድሮስ ይህ ሁሉ ሲሆን በፀጥታ ይመለከታል። በርካታ የመድፍ ተኩስ ቀጠለ። ቴዎድሮስ ይህ ሁሉ ሲሆን ትንፍሽ አላለም። ሚስዮናውያኑ ስጋት ውጧቸዋል። ከንፈሩን እየጨመቀ እና ዓይኖቹን ቦዘዝ እያደረገ ሲመለከት በሆነ ሃሣብ ውስጥ እንዳለ መሰለ።

የመጨረሻዋ ጥይት እንደተተኮሰች ከሚስዮናውያኑ ልጆች በአንዱ ትከሻ ላይ እጁን ጭኖ ስለወታደራዊ ስልት ለዛ ያለው ውይይት ጀመረ። የአውሮፖውያን ኃይል ምን ያህል እንደሚሆን፤ ስለመድፍ አጠቃቀም ይጠይቅ ገባ። በድጋሚ የተሰራውን የጦር መሣሪያ አድንቆ ሰራዎቹንም ካመሰገነ በኋላ አሁንም ግን ይህ መድፍም ትንሽ እንደሆነ እና በእግዚአብሔር ፈቃድ ተለቅ ያለ ሊገነቡለት እንደሚገባ አሳሰባቸው።

# ምዕራፍ አሰራ ሰባት

በ1856 ዓ.ም በጥቅምትር ወር፣ ፕላውደን ከሞተ ከሁለት ዓመት ተመንፈቅ በኋላ መሆኑ ነው ቴዎድሮስ ሚኒስትሮቹ የሐር ለምድ፣ የአንበሳ ጎፈር እንዲሁም ቢጫ የሆነ ሸማቸውን ለብሰው በድንኳኑ ሳሎን ውስጥ እንዲሰበሰቡ አዘዘ። ሰራቤት በሐር የተሸለመ ካባውን ለብሶ ባለመንታ አፈሙዝ ጠመንጃውን ከጎኑ አድርጎ ሌሎችም የጎረሱ ሁለት ሽጉጦቹንም በሌላኛው ጎኑ በኩል አስቀመጠ። 12 መድፎች።

የድንኳኑ መጋረጃ ሲገለጽ አዲሱ የብሪታንያ ቆንስል ወደ እነሱ ገባ። ታጣፊ እንዲቀመጥ ጠየቀ ። ቴዎድሮስ ወዲያው ከቤል እና ፕላውደን የተለየ ዓይነት ሰው እንደሆነ ተረዳ። ቻርለስ ዳንከን ፤ ካሜሮን ከእነሱ በእድሜ ጠና ይላል፡ ለበርካታ ዓመታት ታዛዥ ወታደር ነበር፤ በመቀጠልም በጥቁር ባሕር ላይ በሚገኘው የፖቲ ወደብ ቆንስል ሆኖ አገልግሏል። ለ18 ወራት ጉዞውን አዘግይቶ ለንደን ቆይቷል። ከሁለቱ ብሪታናውያን የቴዎድሮስ ወዳጆች በቀር ኢትዮጵያን የወደደ የለም። ለካሜሮን ሌላ የሥራ ምድብ ቢሆንም አልተመቸውም።

ቴዎድሮስ ከእርሱ ቀድመው እዚየ የነበሩት እንግሊዛውያን የገጠማቸውን ተረከለት የፕላውደንን እድለቢስነት እና ገዳዩ ላይ ያረፈውን ብቀላ። ቤል ከተገደለ በኋላም አምስት መቶ እስረኞች ደባርቅ ላይ አንገታቸው እንደተቀላ ዘረዘረለት። እናም ይህ ሁሉ የተደረገው የንግሥቲቱን ወዳጅነት ለማግኘት መሆኑንም ገለፀለት። ከቀናት በኋላ ደግሞ ካሜሮን ሰሌላ ጥያቄ ተጠራ የቴዎድሮስ ዋና ስጋት የቱርኮች ጉዳይ ማለትም ግብፅና ቱርክን በአንድ ላይ ይመለከታል። ከግብፅ ጋር የመሠረተው መልካም ወዳጅነት ተበላሽቷል። ትግራይን መገንጠሉ በቀይ ባሕር አካባቢ ካለው የኦቶማን ኃይል ተቃውሞን አስከትሏል። ግብጾችን ከቆላው አካባቢ አጥቅቶ በማስወጣት ወደምፅዋ ለመገስገስ ፈልጓል። ይህን ከማከናወኑ በፊትም በአውሮፓ የሚገኘውን የክርስቲያን ኃይል ድጋፍ ማግኘት ተመኝቷል።

ኢትዮጵያ በየአቅጣጫው በሙስሊም ኃይል መወረሯን ፤ ይህን ወረራ ለመመከት የሚቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ አፅንኦት የሰጠው ቴዎድሮስ ይህ ካልሆነ ግን ስከላከል እሞታለሁ በማለት ገለፀለት። ይህ ሁሉ የጦርነት እና የእልበገር ባይነት ወሬ ምስኪኑን ካሜሮንን ሲጋት ውስጥ ጣለው ። «ይህን ለማበረታታት አይደለም የተላኩት» በማለት የተላከበትን ለመግለፅ ሞከረ ። «የእርስዎን መልዕክተኛ ወደ ለንደን በሰላም እንዲያልፍ ማድረግ እንችላለን የምትዋጉ ከሆነ ግን እስቸጋሪ ነው» በማለት አከለ። ካሜሮን ወደ ድንኳኑ ተመለሰ። የበኩሉን ሥራ ሰርቷል፤ ዲፕሎማሲ ተገቢ መንገዱን መከተል አለበት።



በቀጣይ ቀናት ወደ ድንኳኑ የሚላከለት ምግብ የከፋ እና እንደውም በየጊዜው እንዳልሆነ አስተዋለ። ቴዎድሮስን ለማየት ቢሞክርም የሚቻል አልሆነም። እሱን እንዲንከባከቡ የተመደቡለት ጥቂት እና ግድየለሽ ሆኑ እንደውም ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ይጠይቁት ጀመር። ጥያቄው በየሰዓቱ ሲደጋገምበትም « ሥራዬን ለመፈፀም የሚያስችለኝ ከሆነ ስድስት ወር ድረስ እቆያለሁ በመንግሥቴ የተላኩት ይህን ላከናውን ነው » የሚል ምላሽ ይሰጣል። « ወደ ባሕሩ እንድያይህን ሂድ ! » ዲፕሎማት ቁጣው የነደደው ቴዎድሮስ ትእዛዝ ሰጠ። ካሜሮን ግን የንግስሥቷ ትዕግስቱም እንዲህ ባለው መንገድ እንደማይባረር ያውቃል። እናም ቆየ። ለንግሥት ቪክቶሪያ ውጤት አስገኘለት። ከወር ገደማ በኋላ ለመመለስ ሲነሳ ብሪታንያ ብቻ አይደለም የተጻፈ ደብዳቤ በእጁ ይዞ ነበር። ቴዎድሮስ ለታላቋ ከመንቀሳቀሱ አስቀድሞ የጻፈው። በግብፅ እና ቱርክ ላይ ርምጃ ለመውሰድ እንደሚፈልግ ነገረው። ለፈረንሳይ፣ «የክርስቲያን መንግሥታት ሁሉ» እንዲያውቁ ለኦስትሪያ እና ሩሲያም ጻፈ። ከነዚህ ሁሉ ሁለቱ ለጀርመን፣ ከተቻለም ለሆላንድ፣ ደብዳቤዎች ብቻ ናቸው የተረፉት። ሁለቱም የያዙት ፍሬ ሐሳብ እና የጋራ መልእክት ተመሳሳይ ነው።

ለንግሥት ቪክቶሪያ « ቱርኮች /ግብፆች/ የአባቴን ሀገር ልቀቁ ስላቸው ፈቃደኛ አልሆኑም። ስለዚህም በእግዚአብሔር ኃይል አሁን እዋጋቸዋለሁ። » ለናፖሊዮን 3ኛ « ቱርኮች/ ግብፆች/ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመቃወም የአባቴን አገር የማይሰጡኝ ከሆነ ልዋጋቸው ልወጣ ነው።» ለወዳጅነት ጥያቄ የጻፈው ደብዳቤ ትንሽ ልዩነት አለው። ለናፖሊዮን 3ኛ «የፈረንሳይ ንጉሥነትዎ እና የክርስቲያን ልዑልነትዎ እንፀባራቂ ክብር ደርሶናል በእግዚአብሔር ፀጋ በደስታ የወዳጅነት ሰንሰለት እንዲያስተሳስረን እመኛለሁ እንደ አንድ ዘመድዎም እንዲያዩኝ እንዲወዱኝም እሻለሁ።»

ለንግሥት ቪክቶሪያ፣ «ሚስተር ፕላውደን እና ሊቀ መኳስ ጆን ክርስቲያኖችን የሚወድ አንድ ታላቅ የክርስቲያን ንጉሥ እንዳለ እና ከርሱ ጋር ሊያወዳጁኝ እንደሚችሉ ይነግሩኝ ነበር። (የንግሥቲቱን ዖታ ያሳሳተው ፀሐፊው እንጂ ቴዎድሮስ አይደለም) ኤምባሲ ለመላክ እንደሚፈልግም ገልጿል። ፕላውደን በየጊዜው የሰላም ሁኔታው ሲፈቅድ ሁለቱ ሃገራት ልዑካን እንደሚለዋወጡ ስለዘገቡኝ ግልፅ ሲያደርግ ቆይቷል። « ቱርኮች ወደ ባህሩ የማለፊያ መንገድ ለናፖሊዮን ፤ ከካሜሮን ጋር የእኔን ልዑክ አብሬ መላክ አልቻልኩም።» እንደሁ «አምባሳደር ቼን መላክ እፈልጋለሁ። አባክዎ ግርማዊነትዎ ይቀበሏቸው እናም በአርጋታ አርግጡን ያሳውቁኝ።» ቴዎድሮስ አቤቱታውን አቅርቧል። ይጠብቅ ጀመር። ከግብፅ በኩል ስጋቱ እየለ፣ ሆኖም ግን በአውሮፓውያኑ ላይ ተስፋውን አድርጐ ሠራዊቱን ከጦር ሰፈሩ አላንቀሳቀሰም።

## ምዕራፍ አስራ ስምንት

ከአስር ወራት በኋላ ቴዎድሮስ በጥንታዊው የጎንደር ቤተ መንግሥት እንስተኛ ክፍል ተቀምጧል። በዙሪያው የብራና እና በቆዳ የተደጎሱ መጽሐፍት አስተኛ ከጀርባው መሥታወት የሌለው መስኮት ይታያል። ከበታቹ የቤተ መንግሥት ግቢ እና የግንብ አጥሩ ከዚያ አሻግረው ሲያማትሩ ደግሞ ከተማው እና የሠረገ ድንኳን ተንጣሏል። ወቅቱ መስከረም 28 ቀን 1863ዓ.ም፣ ዕለቱም የመስቀል በዓል ማግስት ነው። እውነተኛው የክርስቶስ መስቀል የተገኘበት መታሰቢያ ከሆ በዓል ደመራ ተለኩሶ ተከብሯል። እናም አሁን ከተማዋ አንቀላፍታለች።

ቴዎድሮስ ግን አላንቀላፋም። አውሮፓውያኑን ለስብሰባ ጠርቷል። ጨለም ካለ የቤተ መንግሥቱ የውስጥ ክፍል ቆንስል ካሜሩን ሰማያዊ የዲፕሎማቲክ የደንብ ልብሱን አድርጎ መጣ። እሱም እንደ ፈረንሳዩ ቆንስል መሴ ባርዴል ከሄደበት መመለሱ ነው። ቴዎፍሎስ ቫልድ ማየር፣ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን ሃይማኖት ለማስለወጥ ከሚሞክረው ሬቨረንድ ሄንሪ ሽተርን ጭምር ሚስዮናውያኑ አብረዋቸው አሉ። በግማሽ ክብ ቅርፅ ሁሉም ከንጉሡ እግር ሥር በታችውን ያዙ።

ቴዎድሮስ የአውሮፓውያንን ምላሽ እየጠበቀ ሳለ ከግብፅ ጥቃት ተሰንዝሮበታል። ሙሳ ፓሻ ሙተማን ዘርፎ ድንኩርን አቃጥሏል። ወደ ወህኒም እየገሰገሰ ነው። በዚህም የቴዎድሮስ ቆላማ ግዛት ወድሟል። የትውልድ ቦታው ቋራም ተወሯል። ያደረገው ነገር የለም። በጉብኝቱ ወቅት ካሜሮን እንዲህ ባለ ጥቃት ጊዜ ከአውሮፓውያን የሚገኘው ድጋፍ ማጣት እንደማይገባ ቴዎድሮስን አሳምኖ ነበር። ቴዎድሮስ ለደብዳቤው ምላሽ ይጠብቃል። ሆኖም በሰኔ ወር እንዳች የመጣ ምላሽ የለም። ካሜሮን ከዘናቡ ወራት አስቀድሞ ከሀገሩ ወደ ኢትዮጲያ የተመለሰው ባዶ እጁን ነበር።

«ግርማዊነትዎ ከሁለት ወራት በኋላ ለደብዳቤዎ ምላሽ ካልመጣ አንገቴን እሰጣለሁ።» ብሎ ነበር ካሜሮን። ቴዎድሮስ በካሜሮን ተናደዱ። ደብዳቤውን ራሱ ካሜሮን ማድረስ ሲገባው ለንደን ሲደርስ በመልእክተኛ ነው የላከው። የተጓዘውም ግብጾች በወረሩት በምስራቅ ሱዳን በኩል ነው። ከሁለት ወራት በኋላ ከፈረንሳይ ለደብዳቤው መልስ መጣ። አውሮፓውያኑን የሰበሰበው ደብዳቤው ሲነበብ እንዲሰሙ ነው። ወደ መሴ ባርደል ዞር አሉና ስለተልእኮው ጠየቀው፣ ቢያንስ ባርደል ፓሪስ ድረስ ተጉዟል።

« ግርማዊነትዎ ፈረንሳይ ያጋጠመኝ ደረጃውን የጠበቀ አቀባበል አይደለም።» ባርደል ቀጠለ።

« ለመሆኑ ማረፊያም ሆነ ምግብ፤ እንደው የሚያስፈልግህን ነገር ሰጡህ? »

« በፍፁም ጃንሆይ ለማረፊያ የሚሆን ቤት፣ ምግብ ሆነ የሚያስፈልገኝን የምገዛበት ገንዘብም እንኳን አላገኘሁም።»

« ለመሆኑ ንጉሡ ምን አሉ?» የቴዎድሮስ ጥያቄ ነበር። « « ደብዳቤዬን ስታቀርብ በአሽሙር ምላሽ ነው ያሰናበቱኝ፣ የተገገርዎቹን እጅ እና እግር ከሚቆርጥ ገዥ ጋር ቀጥሎ ግንኙነት አይኖረኝም ።» መለሰ ባርደል።ለሚያዳምጡት ለ ሌሎችም አሁን ነገሮች ሁሉ ተገለፁ። ባርደል ናፖሊዮን ሶስተኛን አላገኘም። ቴዎድሮስ ንጉሱን እየተቆጣጠረ ነው። ቆንስል ካሜሮን ከፈረንሳይ የመጣውን ደብዳቤ እንዲያነብ ታዘዘ። ደብዳቤው ከናፖሊዮን ሳይሆን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መሴ ድሮን ደ ሊዊ ሚያዝያ 23 ቀን 1855 ዓ.ም የተጻፈ ነው።

ልክ የብሪታኒያ መንግሥት በኘላውደን በኩል እንዳደረገው ሁሉ ፈረንሳይም ቴዎድሮስ ለካቶሊክ ሚስዮናውያን ጥበቃ እንዲያደርግ ይማፀናል። በዚያም ላይ እንደብሪታንያ ሁሉ ፈረንሳይም ስለጦርነት እቅድ ለቴዎድሮስ ትምህርት መስጠቱን አስፈላጊ አድርጋዋለች።

« ከኃያላን ጎረቤቶች ጋር ለመዋጋት ከመነሳት በፊት ያለውን ድል የማድረግ እድል በጥድፊያ ከማጣት አስቀድሞ ያላቸውን የኃይል መጠን መረዳት ያስፈልጋል። »

ቴዎድሮስ በአውሮጳ የክርስቲያን ኃይል ላይ ትልቅ እምነት አሳድሮ ነበር። ያገኘው መልስ ይህ ነው። አውሮጳውያንን በተመለከተ ቁጥር ብስጭቱ ናረ። በእነሱ ዓለም ግንባር በመፍጠር ረገድ ግልፅ ያለ ነገር የለም፤ ክርስቲያን እና ሙስሊም አንድ ጎራ ሆነው ይጓዛሉ። በየግል የፈረንሳይ ቆንስል አንድ፣ የብሪታንያው ደግሞ ሌላ ነገር ይነግሩታል። ድጋፋቸውን ሲጠይቅ ደግሞ ምላሻቸው ተመሳሳይ ነው፤ እናም ሁለቱን ቆንስላዎች ጠላቸው። የፈረንሳዩን እብድ፣ የእንግሊዙን ደግሞ አህያ እንደሚላቸው ይወራል። አሁን ከእግሩ በታች የተቀመጡት ሰዎች እንደ ታማኙ ጆን ቤልም ሆነ ዋልተር ኘላውደን ያለ ብቃት ያላቸው አይደሉም።

ከካሜሮን እጅ ላይ ደብዳቤውን መነጨቀው። « የደብዳቤዬ መልስ ይህ ነውን? ናፖሊዎን ታላቅ ነኝ ብሎ ያስብ ይሆናል። እኔ ግን አሁንም ታላቅ ነኝ የዘር ሐረጉም የትናንት ነው። የእኔ ግን እስከ ዳዊት እና ሰለሞን ድረስ ይዘልቃል።»

ከንጉሡ ፊት ለፊት የተቀመጡት ሁሉ አንዳች የተለወጠ ነገር መከሰቱን ተገነዘቡ። ወደ ኢትዮጵያ ለሥራ ፤ ለእረፍት ወደ ጅቡቲ ባጠቃላይ ለተለያየ ምክንያት ነው የመጡት። አሁን ሁሉም ወደየመጡበት የመመለሻው ጊዜ መሆኑን ተረዱ።

## ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

ቴዎድሮስ በራስ አሊ ላይ አምጾ ለንግሥናው እንፀባራቂ ዘመቻውን ከጀመረ ከአስር ዓመታት በላይ ሆነ። ራስ አሊን እና እናታቸውን መነንን፣ ደጃች ውቤ፣ እና ብሩን ሁሉ አሸነፈ። የየጁ ስርወ መንግሥት የለም፤ የዋግና ላስታ ግዛትም ከጁ ገብቷል። ሸዋና ትግራይም እንዲሁ። በአቡነ ሰላማ ድጋፍ ለመቶ ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን መከፋፈል አስወግዷል። ጥንታዊቷን ሀገር በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ለማስተካከልም አስፈላጊ ማሻሻልና ስውጦችን አምጥቷል።

በ1851 ዓ.ም ቴዎድሮስ አቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ተስፋ ካደረገው በላይ መርዘሙን ለፕላውደን አምኗል፣ ከዐራት ዓመታት በኋላ ግን ነገሮች ይበልጥ ጨልመው ታዩት።

« ራሴን ማታለሌ አርግጥ ነው ። ይህ አንገቱን ያደነደነ ሕዝብ ነው፣ እግዚአብሔር ለእነሱ በቸርነቱ ባበጃጀው በረከት ከመደሰታቸው በፊት ሊቀጡ ይገባል።» ሚስዮናዊው ሄነሪ ሸተርን በቴዎድሮስ ላይ የተመለከተው ለውጥ ድንገተኛ ነበር። እስከ ዛሬ ድንገተኛ ስሜቱን ሸፍነው የቆዩት የቅድስና መጋረጃዎች በድንገት ተገልጠው እውነተኛ ባሕርዩ ወጣ።

በተመሳሳይ በ1855 ዓ.ም የፈረንሳይ ምክትል ቆንስል ጊዮም ለዣ በአንድ ወቅት የከፋ አደጋ ላይ ከመድረሱ በፊት በሕሊናው ተመክሮ አደብ ሲገዛ አስተውሏል። እውነቱ የንጉሡ ባሕርይ ለዓመታት ፅንፍ የደረሰ ነበር። ስለ ቴዎድሮስ ጥሩ ጨዋታ አዋቂነት፣ ይቅርታ አድራጊነት ደግነት ፣ በዙሪያው ያሉትን ሁሉ የሚያስገርም ግርማ ሞገስ የተላበሰ ትህትና ይነገራል። ነገር ግን የሙካኔ ድርጊቶቹ ሲከተሉ ቀጣይነት ስለማይኖራቸው የሚያምነው የለም። ብዙዎች ኀዘን ያስከተለው ነው ይላሉ። የቆንስል ቤል እና ፕላውደን ሽምግልና አሁን የለም፤ ከታማኝዋ ባለቤቱ ተዋበች ጋር የነበረውን ቅርበት ማጣቱም ሌላው ምክንያት ነው።

በ1852 ዓ.ም ታዎድሮስ እንደገና አገባ። የቀድሞ ተቀናቃኙ የደጃዝማች ውቤ ልጅ ጥሩነሽን። ቴዎድሮስ ሁለቱም ቢያገባ የጠላቶቹን ልጆች ነው። ጥሩነሽ አለጋ ወራሹን ዓለማየሁን ስትወልድ ለደስታው ማድመቂያ አምስት መቶ እስረኞች ተለቀቁ። ትዳሩ ግን ደስታ አልነበረውም። ጥሩነሽ የአባቷን መንግሥት በመውሰዱ ቂም ይዛበታለች ። ስለ አብሮነት ጊዜያቸው የሚታወቀት ጥቂት ነው። ወደ ደንኳኑ ሲገባ አትነሳለትም። : «ከአንተ ከበለጠው ንጉሥ ጋር ነው የምነጋገረው» ትለው ነበር መዝሙረ ዳዊትን እያነበበች። ለቴዎድሮስ የማይነስት ሁለት ሰዎች፣ ጥሩነሽ እና አቡነ ሰላማ ናቸው።

ጥሩነሽ እና ዓለማየሁን ወደ መቅደላ ከላከ በኋላ በጦር ሰፈሩ ከሚገኙት ሴቶች የፈለጋትን ይወስድ ስለነበር « የእኔ ንግሥት ከሞተች ወዲህ የምመራው የፈለጋትን ክርስቲያናዊ እና ያልተረጋጋ ሕይወት ነው።» ይል ነበር።

ሸተርን እና ለዣ እንደሚሉት ከሆነ የቴዎድሮስ ውድቀት የጀመረው በ1855 ዓ.ም መጀመሪያዎቹ ወራት ነው። የካቲት 20 ቀን ንጉሡ ከደብረ ታቦር ወጥቶ ወደ ጎጃም ገሰገሰ። እዚህ የጥንቱ ገዥዎች ቤተሰብ የሆነው ተድላ ጓሉ የሸፍታ ቡድን አደራጅቷል። ግዙፍ ሠራዊቱን አስልፎ ከፊት የሚገሠግሰው የቴዎድሮስ ሁኔታ አሁንም ቀልብ የሚስብ ነበር። በዚህ ወቅት የተመለከቱት ተጓዦች እሱን እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል፤

« ግንባሩ ከፍ ያለ፣ እና ጎላ ብሎ የሚታይ ዓይኑ ጥቁር እና እሳት የሚተፋ፣ ፈጣን እና ሰርሳሪ። አፉ እንከን የሌለው እና ፈገግተኛ ፤ በንግግር ወቅትም ደጋግሞ ሲጫወትበት ይታያል እናም እንዳች መስሕብ ያለው ብንል ያስማማል፤ ሥርዓቱ ተስማሚ እና ትሁት አጠቃላይ እሱን ለመግለፅ ተክለ ሰውነቱ ቢቀር ከአስተዋዮች እና ደግ ሰዎች አንዱ ነው ።»

ለበርካታ ቀናት ሠራዊቱ ወደ ደቡብ ተጉዞ አባይን ሲሻገር፣ ቴዎድሮስ በአሮጌው ፖርቱጋሎች በሠሩት ድልድይ ላይ ቆሞ ሠራዊቱን ተመለከተ። ለሰዓታት በድንጋያማው ቁልቁለት ይተም ነበር። ከቴዎድሮስ ጋር ለዣ አብሮ ነበር። «ፈረሰኛው እና እግረኛው ጦር፣ ጓዝ እና ተከታዮች ሁሉ ወረዱ እንደውም እንደ ጥቅጥቅ ደመና ተግመለመሉ፤ በዚያም ላይ በሽዎች የሚቆጠር ባለጦር ሠራዊት ተከተለ» ።እንደ ለዣ ግምት በትንሿ ድልድይ የተሻገሩት 40 ሺህ ይሆናሉ። የማይሸነፈው ዘማች ቴዎድሮስም ቁልቁለቱን ተያይዘው፣ ለገርም ከኋላ ኋላ ይታገል ገባ።

የቴዎድሮስ ሠራዊት የተድላ ጓሉን ጦር በእንጅባራ ሸለቆ ገጠመው ። የንጉሡ ሠራዊት አሸናፊ ሆኖ 7 ሺህ ምርኮ ሲይዝ፣ ተድላ ጓሉ አመለጠ። ቴዎድሮስ ተቆጣ። ከዚህ የከፋ ወሬም መጣ። የግብፁ ሙሣ ፖ ሻ ጦር ቆላማውን አካባቢ እጥለቅልቆታል። ወዲያው ደግሞ ሸዋ ላይ ህገረ ገዥ አድርጎ የሾመው የከፍለ ሀገሩን ነጻነት አወጀ ራሱን ንጉሥ ብሎ ሰየመ።

ቴዎድሮስ ከሚገኝበት የሥልጣን ማማ ላይ ሆኖ ዙሪያ ገባውን አማተረ። ከእነዚህ ዓመታት ትግል ሁሉ በኋላ ዙሪያው በጠላት ተከቧል፣ ከድንበር ባሻገር ደግሞ ተስፋውን የጣለባቸው አውሮጳውያን ክርስቲያኑን ከመደገፍ ይልቅ ለግብፅና ቱርክ ሙስሊሞች ወገኑ።ቁርጥ ትእዛዝ አስተላለፈ፤ ሁሉንም ግደሉ፣

7, ዐዐዐዎቹን አስረኛችም ገደሉ። ከዚያ በኋላ በእሱ ሥር ያሉት ሁሉ ተቃውሞ ጀመሩ። የካቲት ወር ላይ በከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ የጦር አዛዦቹ የግድያ ሙከራ እንዳሴሩ ደረሰበት።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ጠዋት ሁሉንም ከፊት እንዲመጡ አድርጎ እጅ እና እግራቸው እንዲቆረጥ ወሰነ። ገሚሱ በደረሰባቸው ስቃይ ገሚሱ በጅብ ተበልተው ሞቱ። ከጥቂት ወራት በኋላ የተራበና ያመፀ ሠራዊቱ ዘርፎ እንዲበላ በመፍቀዱ ሁለት ችግር በአንድ ጊዜ አቀለለ። በአማፅያኑ መንደር ያገኙትን ሁሉ እንዲበሉ ፈቀደ። መጠራቱን ቢያምንበትም የጥሪው ን ምንነት አልተረዳውም። ለዓመታት ያለ ድካም ከወዲህ ወዲያ መሯሯጡ በሀገሪቱ አመፅን አስቁሞ ሰላምን ለማስፈን አልነበረም። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲቀጣ ነው የፈለገው።

ለገ እንደጻፈው ቴዎድሮስ ራሱን «የሀበሻ ምጽዓት » ሲል ሰይሟል። በ1855 የበልግ ዝናብ ወቅት ጋፋት ላይ የተሰራው መድፍ ወደ ጎጃም ሲጎተት በተሽከርካሪው ጋሪ ጎን ላይ እንዲህ የሚል ተጽፎ ነበር።

«የአመጸኞች ቀጪ ቴዎድሮስ»! እስከ አሁን ድረስ የቴዎድሮስ የቅጣት ርምጃዎች በራሱ ሰዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነበር። ሆኖም ከዕለታት በአንድ ቀን ወደ ተድላ ጓሉ በዘመተበት ወቅት በለገ በመናደዱ ለ24 ሰዓታት እሥሮ አቆየው። ቀድሞ ሲልም ንጉሡ ከግብፅ ጋር የነበረው ቅርርብም ሆነ ከባርደል ጋርመጨቃጨቁ ጥርጣሬውን በለገ ላይ አጠናክሮታል። አሁን ግን ቁጣውን ያጋለው ሌላ መሠረታዊ ነገር ነው። ይኸውም ለገ ለመሄድ ጥያቄ አቀረበ።



## ምዕራፍ ሃያ

1855 ጥቅምት 23 ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል ነው። ቴዎድሮስ ግማሽ ጨለማ በወረሰው የጎንደር ቤተ መንግሥት ውስጥ ሆኖ የውጭ ዜጎቹ ላይ ቁጣውን ሲገልጽ ሁለት ሳምንት ሆነው። ሚሲዮናዊው ሄንሪ አሮን ሽተርን ሀገሪቱን ለቀው ለመሄድ ከወሰኑት አንዱ ነው። በጠዋት ተነሳ ወዳጁ አቡነ ሰላማን ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበታቸው። እሱ የመሠረታቸው ተልእኮዎች «ጥልቅ እና ሰፊውን የአቢሲኒያዎችን የማይጨበጥ ክፉል ጨለማ በብርሃን ጨረር እና እውነትን በመፈንጠቅ ያረጋግጣሉ» በሚል ርካታ ተሰምቶታል። ቆንሲል ካሜሮን ከጎንደር ውጪ አብሮት ተጓዘ። ዋልተር ፕላውደን ወደ ሀገሩ ለመሄድ በመንገድ ላይ ሳለ ከፋኛ ከቆሰለበት ከቀሐ ወንዝ ዳርቻ ሲደርስ መሴ ባርደል አገኛቸው። ሦስቱ የውጭ ዜጎች በደስታ የጋራ ጉዟቸውን ቀጠሉ። በመንገዳቸውም የማስመሰል ጨዋታቸውን በመልካም ሁኔታ ያካሂዱ ነበር። ሀገሪቱ ወደፊት ስለሚኖራት መልካም ሁኔታ ስለውብቷ እና ስላለው እምቅ አቅም ይጨዋወቱ ጀመር።

ሽተርን፣ ካሜሮንና ባርደልን ተሰናብቶ ፈጠን በማለት ተሰብስበው የሚጓዙ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን ተቀላቀለ። ጓዙ ቀድሞ ሄዷል። መንገዱ የውጭ ዜጋ በሚጠሉት የቴዎድሮስ ወታደሮች ተሞልቷል። ሽተርን በቅሎውን በመካከላቸው ማሳለፍ ነበረበት። ሲያልፍም የስድብና ንቀት ቃላት እየወረወሩ በጥላቻ ተመለከቱት። መንገዱ አቀበት ሆኖ የእሱ ፍጥነት ሲቀንስ ፣ የእነሱ ጨመረ። ብዛታቸው እና ፀብ አጫሪነታቸው ተሰማው። እኩለ ቀን ሲሆን ከወገራ አውላላ ሜዳ ላይ ደረሰ። መንገዱ ከርቀት በስተሰሜን ወደ ትግራይ እና ወደ ባሕር ወደቡ አቅጣጫ ተዘርግቷል።

ከሜዳው በአንድ ወገን በርከት ያሉ ድንኳኖች ይታያሉ። ሽተርን ድንገት አንድ ነገር ታሰበው በድንኳኖቹ መካከል ነጩ የቴዎድሮስ ድንኳን ተተክሏል። በዚህ ስፍራ መቆም ግዴታው መሆኑን ያውቃል። ንጉሡ እና መኳንንቱ የጊዮርጊስን በዓል እያከበሩ ነው። ሽተርን አብረውት ካሉት ጋር ድንኳኑ ጋር ደረሰ። ድንገት በርከት ያሉ ወንዶች ብቅ አሉ፣ ጠጥተዋል። ሽተርን ላይ አተኩረው ጥቂት ቆሙ።

«በመድፍና ጠበንጃ ለምን ትዋጋላችሁ?» የሹፌት ጥያቄ ሰነዘሩ። ጎራዴ እና ጦር ምን ይጉድለዋል? ከዚያም የነጩ ድንኳን መጋረጃ ተገለጠ እና በርከት ያሉ የጦር አዛዦች ብቅ አሉ፣ ከመካከላቸው ቴዎድሮስም አለ። የሽተርን አገልጋዮች መሬት ላይ ተደፉ። ሽተርንም ዝቅ ብሎ ሰገደ። ቴዎድሮስ ምንም ሳይናገር አፈጠጠበት። «ምን ፈለግክ ? » « የግርማዊነትዎን ድንኳን በማየቴ በትሕትና ሰለምታዬንና አክብሮቴን ለእርስዎ ለግርማዊነትዎ ላቀርብ መጣሁ።» ተንተባተበ።

«ወዴት እየሄድክ ነው?»

«በግርማዊነትዎ ፈቃድ ወደ ምፅዋ ለመሄድ ነው»

የቴዎድሮስ ዓይን ሰርስሮት ገባ።

«መድፍ መሥራት ትችላለህ ?»

«በፍፁም »

« ውሸታም!»

ንጉሡ ሽተርንን ከተከተሉት ወደ አንዱ ዞረና፤ « የዚህ ነጭ አገሊጋይ ነህ ?» አለው። «አይደለሁም ግርማዊነትዎ እኔ የቆንስል ካሜሮን ተቀጣሪ ነኝ፤ ቤተሰቦቼን ለመጠየቅ ስለምሄድ ዐድዋ ድረስ ብቻ አሸኘዋለሁ» ሲል መለሰ። የሆነ ነገር ቴዎድሮስ ሽው አለበት። ርጋታው በአንዴ ጠፋ « አንተ ርኩስ... ባንዳ እንዴት ከንጉሥህ ጋር ለመነጋገር ደፈርክ ? በሞቴ ይህን ዋጋ ቢስ ጣልና በለው » ።ወዲያውኑ በርካታ ወንዶች ይዘው መሬት ላይ ጣሉት እና በዱላ ቀጠቀጡት።

«ሌላም አለ ግደሉት» አለና ሌላኛውን የሽተርንን ተከታይ አሳያቸው ፤ እነሱም ያዙት። የሁለቱም አስከሬን ተጋደመ።

ሽተርን በድንጋጤ ይመለከታል። ጣቶቹን በጥርሱ እየነከሰ ፊቱን መለሰ። ቴዎድሮስ ድንገት ወደእሱ መጣ ሽጉጡን ሚሲዮናዊው ፊት ላይ ደገነው፤ ሽተርን ከአሁን አሁን ተኮሰብኝ እያለ ሲጠባበቅ ንጉሡ ሽጉጡን መለስ ና « ጣለው!» ሲል ጮኸ።

ሽተርን መሬት ላይ ተጣለና ተገረፈ። አቅሉን ሳተ። በደረሰበት ድብደባ ያልሞተው ሚሲዮናዊ ወደ ጎንደር ተወስዶ በእግርና እጁ ሰንሰለት ገባ። «የበለዘው የቆሰለው እና የደማው ሚሲዮናዊ አቅሙ ተዳክሞ ተዘረጋ» ሲል የራሱን ገጠመኝ ጽፎታል። በዚህ የሥቃይ ሁኔታ ሆኖም የሌላውን ስቃይ አስቦ መጽናኛ አገኘ።

በዚያን ጊዜም ለራሴ እንዲህ አልኩ፤ «የተመታው ራስ፤ የተወጋው ጎን፤ የተቸነከሩት እግሮች እና ያ ለፍቅር የተከፈለ የመስቀል ከባድ ካሣ ፤ ፅናት የሚሰጥና ዝቅ ብሎ የሚወድቀውን መንፈስ የሚያበረታ ነው» ።



*ምዕራፍ ሃያ አንድ*

የሽተርን መያዝ ያልተጠበቀ ይመስል ነበር። በዚያ ማለዳ በቴዎድሮስ የጦር ሰፈር ዝር ባይል ኖሮ፣ ጉዞው ከጊዮርጊስ ዕለት ድግስ ጋር ባይገጣጠም ኖሮ ባመለጠ ነበር። ወይም በሌላ በኩል ትግራይን አቋርጦ ቢሄድ ቤቱ በገባ ነበር ። ውጦ አድሮ ግን በየትም በኩል ቢሄድ መያዙ እንደማይቀር ሄንሪ አሮን ሽተርን ተረዳ።

ሄንሪ አሮን ሽተርን ሀምበርግ፣ ጀርመን ውስጥ፣ ከአይሁድ ቤተሰብ ነው የተወለደው። በ19 ዓመቱ ሊባኖስ ውስጥ ሥራ አገኘ። ሆኖም ኩባንያው በመፍረሱ ሥራ አጥቶ ለወራት በጎዳናዎች ላይ ተርቦ ተንከራተተ። አንድ ምሽት ግን ሕይወቱን የለወጠ ነገር በፍልስጤም ፕሬስ የጸሎት ቤት ተከሰተ። በዚህም መሢሁ ለሁለተኛ ጊዜ የሚመጣው ፤ አይሁዶች የመጀመሪያ አመጣጡን ከተቀበሉ ብቻ እንደሆነ ተነገረው። ክርስቲያንም ሆነ። ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ተማረና በለንደኑ በአይሁድ መካከል ክርስትናን የሚያስፋፋ ማሕበረሰብ ሥር የሚስዮናዊነት ሥራውን ጀመረ። የብሪታንያን ዜግነትም ወሰደ።

ኢየሩሳሌም ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለጠፋው የአይሁድ ዘር የመስማት ፍላጎቱ ከፍ ስላለ በ1844 የአባይ ወንዝን ተከትሎ ወደ ደቡብ ተጓዘ። አፍሪቃ ውስጥ ያለው ታላቅ ስህተት በግልፅ ታየው። በተመለከታቸው የበረሃ ከተሞች የመሐመዳውያን እና እነሱን የሚቃወሙት እምነት የለሾች ስህተት ተደባልቆ ታየው። ኢትዮጵያውያንም የተሻሉ አልነበሩም። «ከመጀመሪያው ዕለት ጀምሬ ስህተት መሆናቸውን፤ አታላዮች እና ጋጠወጥ እንዲሁም በሃይማኖት እምነታቸውም በአስገራሚ ሁኔታ የማይጨበጥ፤ የህገር ውስጥ ግንኙነታቸውም በሚያስጠላ ሁኔታ የተበላሸ መሆኑን እስታውያለሁ» በማለት ጽፏል።

ከጎንደር ብዙም ሳይርቅ ተልእኮውን ጀምሮ ገንዘብ ለማሰባሰብ ወደ ብሪታኒያ ተመለሰ። በ1854 ከመመለሱ አስቀድሞም « በፈላሻዎች መካከል መዞር» በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጻፈ። ከዚያም ወደ ተልእኮው ተመለሰ። የቴዎድሮስ ቁጣ ያስከተለውን አዲስ ሥጋት ተመልክቶም «የተልእኮዬ ግብ በዚህ ወቅት ሙሉ ለሙሉ ተሳክቷል» ብሎ በመወሰን ወደ ወደቡ ለመጓዝ ተጣደፈ።

ተገቢውን ምላሽ ያላገኘው ቴዎድሮስ ጥላቻው እየተሰራ ጨ ነው ሁሉም በጥርጣሬ ነው የሚታየው ። በአንድ ወቅት ግሩም ወዳጅ የነበሩት አቡነ ሰለማ አሁን ጠላት ሆነዋል። አውሮጳውያንም ቃል የገቡትን ሁሉ ማድረግ አልቻሉም። : ሽተርን ለጥርጣሬ በሚያጋልጥ ሁኔታ የአቡነ ሰላማ ወዳጅ ሆነ። በሱ መድሐፋ ላይ ሽተርን፤ ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ ነው ብሎ ጽፏል። የንጉሡ አማካሪዎች ይህ የሀሰት ታሪክ ሁሉም እንዲያየው ብሪታንያ ውስጥ ታትሞ ይፋ መውጣቱን ነገሩት።

ነገር ግን አዲሱ ችግር ከሽተርን ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው ነገር የለም። እሱ ብሪታንያዊ ነው። ንጉሥ ቪክቶሪያ ደግሞ እስካሁን ለንጉሡ ደብዳቤ መልስ አልሰጠችም። የሁሉን አውንተኛ ትውልድ በተመለከተ የሚሰነዘረው ስላት እጅግ ከባድ ነበር። ቴዎድሮስ በገዛምታ የማብዕና ቁርከ ጠላቶቹ የሚያገናኛቸዉን ቤሬ ይገምታል። «ለመሆኑ እንዴት ነው ብሪታኒያውያኑ በእነሱ ግዛቶች ውስጥ እንዳሻቸው ገብተው የሚወጡት ? »

በአግር ብረት የታሰረው ሽተርን ድንኳን ውስጥ ተጋድሟል። ለሳምንታት በእግር ብረት የታሰረው ሽተርን ድንኳን ውስጥ በድንግዝግዝ ብርሃን እንደሚገባበት የሚገኝበት ከፍየል ቆዳ የተሰራ እስር ቤት በድንግዝግዝ ብርሃን እንደሚገባበት አውቋል። ከጠባቂዎቹ አንዳንዶች የእግር ብረቱን እያጠበቁ መቆም ወይም መተኛት ብቻ እንዲችል ከማድረግ አልፈው በቅርቡ እንደሚገደል ይነግሩታል። ቀረዎቹ ደግሞ ቁስሉን እያከሙ ሰንሰለቱን ያላሉለታል። ውሎ አድሮም ሁኔታዎች መሻሻል ጀመሩ። ቁስሎቹ ዳኑ እጁን ወይም ከንዱን እንደማያጣም አረጋገጠ።

እንዲሁም ቴዎድሮስ ስለጤንነቱ መጠየቁን የሚገልፅ መልእክት ደረሰው። ከቆንስል ካሜሮንም መልክም ዜና መጣ። ቴዎድሮስ ከብሪታኒያ የሚጠብቀውን ሁለት ደብዳቤዎች የያዘች በእንፋሎት የምትሰራ ጀልባ ምፅዋ ደረሰች። ኅዳር 11 ቀን ጠዋት / ከአምስት ወራት እስር በኋላ ሽተርንበአካባቢው የተሰበሰቡ ሰዎችን እንቅስቃሴ ሰማ። እኩለ ቀን ላይ ጠባቂዎቹ ወደ ድንኳኑ ገብተው እንዲነሳ አዘዙት።

ዓይኑ ብርሃን ለማየት ታገለ። በርካታ ሰዎች ከፊት ለፊቱ ተሰብስበዋል። ለንግሥቷ ደብዳቤ አቀባበል የተደረገ ስብሰባ ነው? የፈረንሳይ ምላሽ ሲነበብ እንደተደረገው በይፋ ሊነበብ ነው? እግሩን እየጎተተ በሁለት መስመር በተደረደሩት ሰዎች መካከል መራመድ ጀመረ። በገዛምታ ተመለከቱት የሸማቸው ንጣት ዓይኑን አጥበረበረው ። ባዙዎቹን ያውቃቸዋል። አንዳቸውም ግን ምንን አላሳዩትም። ከፊት ለፊት ራቅ ብሎ የጠመጠሙ ቄሶች በረድፍ ይታያሉ። ከመካከል በሁለት ሰፋፊ የሀር ጃንጥላዎች ስር ቴዎድሮስ ተቀምጧል። በአንድ ጎኑ በኩል ቆንስል ካሜሮን ፡ የጋፋት ሠራተኞችና ሚሲዮናውያኑ አውሮጳውያን ምንጣፍ ላይ ተቀምጠዋል። ሀሀይዋም የሽተርንን መሳጣ በሳቸው ፡ ቆሻሻ ላይ ሊወድቅ ተንገዳገደ።

ወደዙፋኑ ሲቃረብ ሌላኛው ሚሲዮናዊ ሮዘንታልም እንደሱ መታሰሩን አይቶ ደነገጠ ። ደብዳቤው ገና አልደረሰም። ስብሰባው የቴዎድሮስ ትልቁ የፍርድ ችሎት ነበር። «እናንተ አውሮጳውያን ወደዚች አገር መጥታችሁ እኔም እንደወዳጁ ጆን በል ሁልጊዜም እውነቱን ትናገራላችሁ ብዬ ወደድኳችሁ፣ አከበርኳችሁ፤ ሆኖም እናንተ ግን ውሸታሞች ናችሁ። » አለ ቴዎድሮስ።

ዐይን በሚወጋው የቀትር ብርሃን ከጸሐፊዎች አንዱ ከህዝቡ ፊት ቆመ እና ከፍትሐ ነገሥት ከተቀደሰው ሕግ የተሳቱ እስፍን አነበበ። በሽተርን ላይ የቀረበው ክስ የስም ማጥፋት ነበር፤ « የቴዎድሮስ አማካሪዎች ለሹመቱ አይመጥኑም፤ ንጉሱ በርካታ ቦታዎችን የኢትዮጵያውያን ጋብቻ በጊታ ፊት ቦታ የለውም፤ ቦታዎችን የሚሆኑ አቅም የሌላቸውን ዜጐች አርዷል፤ ዘርፏል፤ ከሰባት እስከ ስምንት መቶ የሚሆኑ አቅም የሌላቸውን ዜጐች አርዷል፤ ከዚህም ሌላ በመጽሐፍ ላይ የቴዎድሮስን የዘር ሃረግ ከጸጸሱ ጋር ወዳጅ ነበር፤ ከዚህም ሌላ በመጽሐፍ ላይ የቴዎድሮስን የዘር ሃረግ አዋርዷል» የሚል ነው።

ሮዜንታልም ተመሳሳይ አዋራጅ ድርጊት ፈጽሟል በሚል ነው የተከሰሰው። ከታሰበበት ሳይደርስ በመሃል በተያዘው ደብዳቤ ላይ፤ «ኢትዮጵያ በግብጽ ብትገዛ የተሻለ ሀገር ትሆናለች» ማለቱ ይፋ ሆኗል። ከጠመጠሙት ካህናት አንዱ ንግግር ጀመሩ። ቴዎድሮስ በምኒሊክ እና በአክሱም ታላላቅ ነገስታት ዘራ-ያዕቆብ፤ ልብነ ድንግል እና ሱስንዮስ በኩል ከዳዊት እና ሰለሞን ዘር መገኘቱን ዘረዘሩ። ሆኖም ግን ወደ 17 ኛው ክፍለ ዘመን እና ወደ ፋሲለደስ የሚለው ላይ ድምጻቸው ሰልሎ ማጉረምረም ተጀመረ።

ቴዎድሮስ፤ « ማንነቴን እንድታስታውሱ አስተምራችኋለሁ» ሲል ጮኸባቸው ፡ ቁሶቹም ዝም አሉ። ሽተርን የቴዎድሮስን ፊት በጥላው ስር ማየት ችሏል። በከፍተኛ ፍርሃት ውስጥም ያ «የንብር አስተያየቱ» ወደ እሱ ሲመለስ ተመለከተ።

« ሴት ካልሆንክ መሣሪያ ጦር ወይ ጎራዴ ፡ ሽጉጥ ወይም መድፍ መርጠህ ከእኔ ጋር ትዋጋለህ?» ጠየቀ ንጉሡ።

«እኔ ቄስ ነኝ አልዋጋም » መለሰ ሽተርን ።

ለመከላከልም ማብራራት ጀመረ። የስም ማጥፋት የተባለው በተርጓሚዎች ሆን ተብሎ የተሰራ ስህተት መሆኑን፤ ከመጽሐፋም ምንባቡ ከአውዱ ተቆንፅሎ መውጣቱን፤ ሙሉው ቢነበብ ግን ለግርማዊነታቸው ያለውን ከፍተኛ ክብር እንደሚያሳይ ተናገረ።

የዋና ዳኞኑቱ ኃላፊነት ቆንስል ካሜሮን ላይ ወደቀ። ተከሣሾቹን « ጥፋተኛ » ሲል በየነ። ሽተርን እና ሮዘንታል የሞት ፍርድ ተወሰነባቸው። ከድንኳኑ ጀርባ ተወሰዱ። ለቀጣይ አራት ሰዓታት ከአሁን አሁን ፍርዱ ይፈፀምብናል ብለው ጠበቁ ። የመጣ ግን የለም።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ከሁለት ቀናት በኋላ ከብሪታንያ መንግሥት የተላኩት ደብዳቤዎች ደረሰዉ. መጨረሻም ካሜሮን እጅ ገቡ። «ባለፈው ዓመት የላካቸውን ከቁጥር 18 እስከ ቁጥር 24 እንዲሁም ከዘንድሮው ከቁጥር 1 እስከ 7 ያሉት ዝርዝር ዘገባዎች ደርሰውኛል። ጥቅምት 31 የተላከው ቁጥር 18 ን በተመለከተ (የቴዎድሮስ ደብዳቤ የተካተተበትን ማለት ነው ) ለንግሥቷ ወኪል በአቢሲኒያ ጉዳይ ውስጥ መግባት የሚፈልግ እንዳልሆነ መግለጽ ይኖርብኛል» ።

ይኸው ነው በቃ። ቴዎድሮስ ለጠየቀው ድጋፍም ሆነ ኘላውደን በየጊዜው ቃል ሲገባው የነበረውን ኤምባሲ ለመላክ ስለመፈልጉ በቀጥታ አልተነሳም። እንደውም ሎርድ ራሰል፤ ካሜሮን ወደ ባሕር ወደቡ እንዲመለስ አዝዟል። ነገር ግን ቴዎድሮስ ከንግሥት ቪክቶሪያ ለጠየቀው መልስ እስኪመጣ መሄድ አልፈቀደለትም ። በ1855 ኅዳር 25 ቴዎድሮስ የጥፋተኝነት ብይን የተላለፈባቸው ሽተርን እና ሮዘንታል በአንድ ችሎት ላይ እንዲገኙ አዘዘ። ይህኛው የእነሱን ጉዳይ የሚመለከት ሳይሆን በቡድን የተከሰሱ ገበሬዎች ነበር። ተከሣሾቹ ጉዳያቸው ታይቶ ተፈረደባቸው እና ወዲያው ፍርዱ ተፈፀመባቸው፤ ፍርደኞቹ ለሞት የሚያደርሰው የጅራፍ ግርፋት ሲወርድባቸው ደማቸው በሚስዮናውያኑ ላይ ተረጨ ።

ቴዎድሮስ ዞር ብሎ « አሁንስ ፈራችሁ ? » አላቸው።

የታሳሪዎቹ ይዞታ አሁን በመጠኑ ተሻሽሏል። ሰንሰለታቸው ተፈቷል። መጽሐፍ ቅዱስም ተፈቅዶላቸዋል። ጠባቂዎቻቸው ቴዎድሮስ ከገበሬዎቹ ጋር ሲገድላቸው እንደነበረና በኋላ ግን እንደተወው ነገሯቸው። አሁን ሊለቃቸውም ይችላል።

በ1856 ታኅሣሥ 25 በድጋሚ ሽተርን እና ሮዘንታል ንጉሡ ፊት ቀረቡ። ዕለቱ ሰንበተ ክርስቲያን በመሆኑ ሚሲዮናውያኑ ቢያንስ በዚያን ቀን ጅራፍ እንደማይኖር አውቀዋል። ጠባቂዎቻቸው እንደሚ ለቀቁ እየነገሩ አበረታተዋቸው. ወደ ድንኳኑ ገቡ። ንጉሡ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ እግሮቹን ምንጣፍ ላይ ዘርግቷል። ካሜሮን እና ሌሎች 4 ወይም 5 አውሮጳውያን በአንድ ወገን በኩል ተቀምጠዋል። አስተያየታቸው ድርቅ ያለ ነበር። ሽተርን እና ሮዘንታል ከእነሱ አልፈው ቦታቸውን ያዙ። ቡድኑን አልፈው ሲሄዱም በሹክሹክታ መልእክት ደረሳቸው። የጠበቁት ግን አልነበረም። «አሁን ሁላችንም እስረኞች ነን » ወዲያው የሰንሰለት ኩሽኩሽታ ከፍ ብሎ ተሰማ፤ ጠባቂዎችም በየእግራቸው ውስጥ አጠለቁላቸው።



ሁለት ነገሮች ናቸው ቴዎድሮስ በአውሮጳውያኑ ላይ ርምጃ እንዲወስድ የገፋፉት። ከኢየሩሳሌም አንድ ካህን መጥተው ቅብጦች (ኮፕት) ኢትዮጵያውያንን ከቅዱሱ ከኢየሩሳሌም ቦታ ካላቸው ሕጋዊ ይዞታ አስወጧቸው። ኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ጠባቂ(ተከላካይ) የነበረው የብሪታኒያ ቆንስላ በዚህ ወቅት ምንም አላደረገም። ካሜሮን ደግሞ ከለንደን ኢትዮጵያን ለቅቆ እንዲወጣ ትእዛዝ ተሰጥቶታል።

« አስፈላጊው ፈቃድ እንዲሰጠኝ ስጠይቅ ማዕበሉ በሁላችን ላይ መጣ» ሲል ካሜሩን ጽፎታል። ቴዎድሮስ ብሪታንያ ከኢትዮጵያ ይልቅ ለቱርክ ታስባለች ብሎ ደምድሟል። በዚያም ላይ ለደብዳቤው እንኳን ምላሽ ለመስጠት አልሞከረም በእነዚህ በሁለት ግምቶቹ በእርግጥ ትክክል ነው።

ከአምስት ወራት በኋላ በእርሳስ የተጻፈ ማስታወሻ ለንደን ደረሰ። የቆንስል ካሜሮን ስም መነሻ ፊደል ያረፈበት ይህ ማስታወሻ ወደ ባሕር ወደቡ በድብቅ ነው ያለፈው። ጎንደር የካቲት 7 ቀን 1855 ዓ.ም (በችኮላ ዓመቱን በትክክል አልጻፈውም )፤ እኔ ሽተርን ሮዘንታል ፣ ኬርንስ ባርዴል፣ ማክ ክራቪና እና ማክ ኪልቪ በሙሉ በሰንሰለት ታስረናል። ፍላድ፣ ሽታይገር፣ ብራንዳይስ እና ኮርነሊዮስ ወደ ጋፋት ተልከው ለንጉሡ እየሰሩ ነው። ለንጉሱ ደብዳቤ የሲቪል ምላሽ እስኪመጣ መለቀቅ የለም።

የቴዎድሮስ ደብዳቤ ምን ሆነ ?

በቆንስል ካሜሮን እጅ ከንጉሡ የጦር ሰፈር ወጣ። ዐድዋ ላይ በመልእክተኛ በኩል ኤደን ውስጥ ለሚኖር ብሪታንያዊ እንዲደርስ ማስታወሻ ተጽፎበት ተላከ። ማስታወሻው « ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን መመልከት ጠቃሚ ነው። ያህል እንደማይሆን አገምታለሁ፤ ወይም ሲታላቋ ብሪታንያ ከሌሎች ሃገራት ከተላኩት አቤቱታዎች እኩያ ማለት ነው » ይላል ። ያም ሆነ ይህ ወደ ምፅዋ ተላከ፤ ከዚያም በጀልባ ቀይ ባሕርን ተሻገረ። ለመጀመሪያ ጊዜም ኤደን ወደሚገኘው የብሪታንያ ግዛት አስተዳደር ሰንሰለት ውስጥ ገባ። እዚያ ለመድረስም ብዙ ውጣ ውረድ አልፏል።

ወደ ቦምቤይ ከዚያም በሕንድ ውቅያኖስ ደግሞ ወደ ቀይ ባሕር ተጉዞ ምስዋን አልፎ ወደ ስዌዝ እስከንድሪያን አቋርጦ በመርከብ ወደ ማርሴይ ነጎደ። ጉዞውን ቀጥሎም እንግሊጣር (ኢንግላንድ) ገባ። ከቪክቶሪያ ጣቢያ ወደ ኋይትሆል ከዚያም ወደ ውጭ ጉዳይ። ፀሐይ በማይገባባቸው የሕንጻው መተላለፊያዎች ተንሸራትቶም የየክፍሎቹን በሮች እየተሳለመ የዓለምን ግሚስ ግዛት ወደሚያስተዳድረው አካል ወደብ ደረሰ። ዝግ ነበር። ከፀሐፊዎች አንዱ ፊርማውን እኑርበት ወደ ቆንስላ ዘርፍ አብረውት ከመጡት ሌሎች መልእክቶች ጋር ተላከ።

ለወራት የቴዎድሮስ ደብዳቤ እንደ በረዶ ኳስ እንዲህ ባለው ሂደት እና ጉዞ ከታሰበበት ለመድረስ ሲንገላታ ካሜሮን ሌሎች ዘገባዎቹን ከስር ከስር ይልክ ነበር። ደብዳቤው ለንደን ሲደርስም በጠቅላላ ከነአጃቢዎቹ አንድ መቶ ገጽ ሞልቶ ነበር። ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤድመንድ ሐመንድ፣ ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጀምስ መሪ፣ በፖርላማ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ኦስትን ሄንሪ ላያርድ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ራስል በሙሉ ከኢትዮጵያ የመጡትን መልዕክቶች ተመልክተዋል።

የሁሉም ድምዳሜ ተመሳሳይ ነበር። የጻፏቸው ማስታወሻዎች እና ቃላ ጉባዔዎች በሙሉ ያመለከቱት ቆንስል ካሜሮን እና የእሱ ተልዕኮ ምንም ዓይነት ጥሩ ነገር እየሠሩ አይደሉም የሚል ነው። «እንደሚመስለኝ ከሚገባው በላይ ሥራ እየበዛበትት እና በማያገባው እየገባ ነው። ቆንስላችን በማያገባው ጉዳይ ከሚገባው በላይ ጣልቃ እየገባ በመሆኑ በአቢሲኒያ ፖለቲካ ውስጥ በመግባትም ጥቅም ይገኛል ብለን አንጠብቅም» ።

ኢትዮጵያን በተመለከተ ካሜሮን የሚገባ ከሆነም አንድ ጠቃሚ ጉዳይ ብቻ ነው ያላቸው። ይኸውም በብሪታንያ ጥቅም ላይ የፈረንሳይ ጣልቃ ገብነት ችግር



ሊያመጣ እንደሚችል ማሳወቅ። ይህ ጣልቃ ገብነትም ከምፅዋ በኩል ግፋም በሆነ መልኩ መከናወን ይኖርበታል። ስለዚህ ወደ ባሕር ወደቡ እንዲመለስ አዘዙት።

ሎርድ ራሰል« የሕንድ ጽሕፈት ቤት» ብሎ አሽጉ ላይ ጻፈበት እና በ1855 ሚያዝያ 27 ተላከ። ምንም ትእዛዝ ስላልተሰጠበትም ለዓመታት እዚያው ሳይነበብ ተረስቶ ቆየ። በ1856 ግንቦት ወር ላይ ተስፋዋ የተሟጠጠው የካሜሮን ማስታወሻ ለንደን ደረሰች " ለንጉሡ ደብዳቤ መልስ እስካልተላከ ድረስ መፈታት አይኖርም። " በዚህ ጊዜ ሎርድ ራስል የረሳውን ድንገት እንደቁዛ ጠየቀ። « ከአቢሲኒያ ንጉሥ ተልኮ መልስ ያላገኘ ደብዳቤ አለ ? »

ደብዳቤው ወዲያው ከሕንዱ ጽሕፈት ቤት ተገኘ። አሁን የዲፕሎማሲ ቀውስ ተፈጠረ። የተደናገጠው ጀምስ መሪ ኃላፊነት ወሰደ። « ጨካኙ ሰዎቻችንን እንዲለቅ ያደርገዋል ያለውን ደብዳቤ ከንግሥቷ የተጻፈ አበመስሎ አረቀቀ»።

«ልዩ ኤምባሲዎን ወደ እኛ ለመላክ ከጠየቁት ሌላ ግርማዊነትዎ ስለ እኛ ያለዎትን አክብሮት የምናረጋግጥበት ተጨማሪ ማስረጃ አንሻም። ከአቢሲኒያ ጋር ያለን ርቀት ከፍተኛ ነው፤ በዚህም ምክንያት እምባሳደርዎ በጉዞው ላይ በሚገጥመው መንገላታትና ችግር ያልታወቀና ያልተጠበቀ ጎዘን ሊከተል ይችላል። ዘግይተው በደረሱን መረጃዎች መሠረት ግርማዊነትዎ በኛ ሠራተኛ ላይ የነበርዎ ፍላጎት ቀንሷል፤ በዚህም ምክንያት እርሱም ሆነ እኛ የምንደግፋቸው ሌሎች ሰዎች ከእርስዎ የማንጠብቀው እያያዝ ገጥሟቸዋል።

እናም ግርማዊነትዎ ለእኛ ያለዎትን እውነተኛ ስሜት ሆነ ወዳጅነት እና በጎ ፈቃድ የእኛን ሠራተኛም ሆነ ሌሎች ሀገርዎን ለመልቀቅ የሚፈልጉ አውሮጳውያንን በማሰናበት ሊያረጋግጥልን ይችላል» ።

በዚህ መልኩ የተዘጋጀው ደብዳቤ ግንቦት 16 ቀን 1856 ዓ.ም መልካም ወዳጅዎ ቪክቶሪያ ዲ በሚል ባልሞራል ላይ ተፈረመ። የራስልም ፊርማ አረፈበትና በጥድፊያ ሰኔ 9 ቀን ወደ ግብፅ ተላከ። ትርጉሙ በሌላ የብሪታንያ ቆንስል ፍሬድሪክ አይርተን ታየ፤ አይርተን ቃላቶቹን ሲመለከት አሉታዊ ጣጣ እንደሚኖራቸው አስተዋለ። ደብዳቤው ለንጉሡ ጥያቄ የያዘው ምላሽ ባዶ ሆነበት። ለቴዎድሮስ የኤምባሲ ጥያቄ ብሪታንያ ከእሱ ምንም እንደማትፈልግ ነው ያሳየው።

አይርተን ለሎርድ ራሰል ይህ ሊያስከትል የሚችለውን ጣጣ ዘርዝሮ ጻፈ። እንዲህ ያለውን ደብዳቤ መላኩ የንጉሡን በኢንግላንድ ላይ ያደረጉትን የመጨረሻ እንጥፍጣፊ ተስፋ የሚያጠፋ፤ በዚህም ምክንያት ወደፈረንሳይ ፊቱን ሊያዞር

እንደሚችል፣ የፈረንሳይ በቀይ ባሕር ላይ የምትከፍተው ኩባንያና ንግድ ወይሕንድ የሚያጓጉዘውን መስመር ሲያሳጣ እንደሚችል አብራራ።

ራሰል በመጨረሻም ለቴዎድሮስ ደብዳቤውን የሚያደርሰው የትኛው ም መልእክተኛ ቢቃል የኤምባሲው ጉዳይ ፈቃድ መኖሩን እንዲገልጽ ተስማሙ። ይህ ደግሞ ወደ ቴዎድሮስ የሚሄደው ሰው ላይ የሚጣል ከፍተኛ ኃላፊነት ሆኑ በመጨረሻ በኢራቃዊው ወጣት ክርስቲያን ሆርሙዝድ ራሳም ጫንቃ ላይ ወደቀ።

ምንም እንኳን መሣሪያ የተጠመደበት ጀልባ ወደ ቴዎድሮስ ግዛት አካባቢ መድረስ ባይችልም ምፅዋ ድረስ መሄድ ይችላል። የንጉሡ ሰላዮችም ከብሪታንያ ዲፕሎማሲ ጀርባ የጦር ኃይል መኖሩን ሹክ ማለታቸው አይቀርም። እንዳለመታደል ሆነና መሣሪያ የተጠመደበት ጀልባ የለም። የሕንድ የባሕር ኃይል ተሰርዟል። ወዲያው ግን አንድ ትልቅ የመጓጓዣ የእንፋሎት መርከብ ተገኘ እና 5 ጠመንጃዎች ተጠመደበት።

የቴዎድሮስ ደብዳቤ በምፅዋ በኩል አቋርጦ ከሀገር ከወጣ ዓመት ከመንፈቅ አለፈው። በ1856 ሐምሌ ማለቂያ ላይ መልሱ መጣ። ደብዳቤ ብቻ የጫነችው ዳልሃውሲ የተባለችው መርከብ በምፅዋ የባሕር ግዛት ላይ እየተንሳፈፈች መምጣቷን ለመጠቆም አምስት ጊዜ በተኩስ ሰላምታ ሰጠች።



## ምዕራፍ ሃያ አራት

በ1856 ጥር ወር ላይ ካሜሮን እና ግማሽ ደርዘን የሚሆኑት ሌሎች አውሮጳውያን ከታሰሩ በኋላ በንጉሡ የጦር ሠፈር ለወራት ሰነበቱ። ማለዳ ተነስተው ቡና ይጠጣሉ፣ በጠዋት ጸሎታቸው ተሰባስበው መዝሙረ ዳዊትን ያነባሉ። እኩለ ቀን ሲሆን በመሶብ የሚቀርብላቸው ገበታ ዙሪያ ከበው በአንድ ወቅት የፕላውደን ሠራተኛ የነበረችው ሴት ወጥ እያወጣችላቸው እንጀራ ይመገባሉ። እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው እግራቸው ላይ በተገጠመው እግረሙቅ ምክንያት አስቸጋሪ ነበር። በተለይ ካሜሮን ከፉኛ በመጎዳቱ ራሱን ከሌሎቹ አግልሎ ነበር የከረመው።

ምንም እንኳን እነሱ የሚገኙበት ድንኳን ከንጉሣዊው ማረፊያ የድንጋይ ውርወራ ያህል ባይርቅም ከቴዎድሮስ ጋር ፊት ለፊት የተያዩበት ጊዜ በጣም ጥቂት ነው። በዚህም በጣም ደስተኞች ናቸው። በ1856 ግንቦት 4 ቀን ግን በንጉሡ እና በአቡነ ሰላማ መካከል ክርክር ሰሙ። ቴዎድሮስ አቡኑ ለሽተርን እናቱ ኮሶ ሻጭ ነበረች ብለው ተናግረዋል፤ እሱም በመጽሐፉ ላይ ይህን ጽፏል ሲል ከሰሰ።

አቡነ ሰላማ ለረዥም ጊዜ ከቴዎድሮስ ጋር መልካም ግንኙነት ነበራቸው ። ከአሥር ዓመት በፊት ሁለቱ በጋራ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ይበጃል ያሉትን ለማድረግ ግንባር ፈጥረው ነበር። አቡኑን እና ፓትሪያርኩን በ1848 ቴዎድሮስ ባሰረበት ወቅት ግንኙነታቸው ሻከረ። ንጉሡ እምነት የሚጥልባቸው ሰዎች ስብስብ እየጠበበ በሄደ መጠንም አቡኑ ራሳቸውን ከዳር ወጥተው አገኙት። አቡኑ ቅብጥ ናቸው ፤ ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን ከተቀደሰው የኢየሩሳሌም ግዛት ያስወጡ ደግሞ ቅብጦች ናቸው። በዚያም ላይ ሰላማ ለተጠሉት እስረኛ የውጭ ዜጎች ለመከላከል የፈጠኑ መሰሉ፤ በተጨማሪም ለሽተርን ጥሩ ወዳጅ ነበሩ። ከክርክሩ በኋላ ካሜሮን ቴዎድሮስ ፈረሱ ላይ ወጥቶ «እንደ እብድ በሜዳው ላይ ሲጋልብ» አይቷል።

በዚያን ምሽት እስረኞቹ ጎራዴ ሲፋተግ ሰሙ፤ ከዚያም ቴዎድሮስ እና ጠባቂዎቻቸው ከድንኳናቸው አቅራቢያ መጡ። ንጉሡ ራሱ ሽተርንን አንቆ « ስለእኔ የዘር ሐረግ የነገረህን ሰው ንገረኝ ወይም ደግሞ እኔው ከልብህ ላይ ፍቄ አወጣዋለሁ » ሲል ጮኸበት።

ሽተርን፣ ሮዘንታል እና ካሜሮን መሬት ላይ ተደፉ። የሮዘንታል ሚስትም አብራቸው ነበረች። ግን እሷ አልታሰረችም። ትንሹን ልጃቸውን ሄንሪን እየከለለች ከመሸሿ በፊት ወደቀች። ወንዶቹ በአንድ ላይ በገመድ ከንድ፣ ደረትና ወገባቸው ታሰረ። ገመዱ ደማቸው በየጣታቸው ወርዶ የተቋጠረ እስኪመስል ድረስ ጥብቅ ተደርጓል።

« ሽተርን! » ጮኸ ካሜሮን ፣ « በቅርቡ መንግሥተ ሰማያት እንገባለን። » ጠባቂዎቻቸው ቀዝቃዛ ውኃ እስረኞቹ ላይ ረጩ ። የገመዱ ከሮች ተሸበሸቡ እና ይበልጥ ጠበቀ።

«ሽተርን ! ሽተርን ! አባክህ የምታውቀውን ሁሉ ተናገር» ካሜሮን ተማፀነ፣ ሽተርን ጸለየ።

ከዚያም ገመዱ ድንገት ተፈታላቸው፣ ጠባቂዎቹም ቁስላቸውን ጠራረጉላቸው። በተከታይ ቀን ጠዋትም እንዲሁ ተደገመ። አሁን በራሱ ጊዜ ሽተርን ያዞረው ጀመር እይታው ጨለመበት ፣ አእምሮው ተምታታበት ግራ ገባውም አበደ እናም ተናዘዘ።

«አዎ!» ጮኸ። «አዎ አቡኑ በየጊዜው ንጉሡ በጣም አስፈሪ ነው፣ ከቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች የበለጠ ኃይል አለው። ሆኖም ግን ልክ በሌለው ፍላጎቱ እና ጭካኔው የሀገሪቱን ሕዝብ ጨረሰው» ። ከዚያም ቴዎድሮስ ከአካባቢው ሄደ። ተጨማሪ የሰሙት ነገርም የለም። ሆኖም የአቡነ ሰላማን ቅሌት አረጋገጠ። እርግጥ ቴዎድሮስ እምነቱ ይዞት አልታሰሩም ነበር፣ እንዲያም ሆኖ ግን ነጻ አልነበሩም። የአውሮጳውያኑ የእጅ ሰንሰለት ተፈታላቸው እና በእግር ብረት ተተካ። የካሜሮን እግር ብረት በጣም በመጥበቁ እግሩ አበጠ። አቤቱታውን አቅርቦ እና አምኖ ተፈታለት። አንድ ቀን ሙሉ ግን እጅግ የከፋ ስቃይ አሳልፏል።

የዝናብ ወቅት ተቃርቧል። ቴዎድሮስ የጦር ሠፈሩን ነቅሎ ጎንደር አቅራቢያ ሰፈረ። አውሮጳውያኑም እዚያ ጥቂት ወራትን አሳለፉ። በሚያዚያው ምሽቱ ቁም ስቅል ወቅት ሸሚዞቻቸው ተቀዳደው እራፊው ብቻ ቀርቷል። ድንኳናቸውም ተበሳስቷል የየዕለቱ ቀለባቸውም እፍኝ ጥሬ ሆኗል።

«ተራቁተን እና ተርበን በሕመም እና ስቃይ ቀልባችንን ስተን የዝናቡን ወራት አሳልፈነው» በማለት ካሜሮን ገልጾታል።



## ምዕራፍ ሃያ አምስት

በ1856 ዓ.ም በሐምሌ ወር ኢጋማሽ በአንዲት ዕለት ምሽት ላይ ሆርሙዝድ ራሳም የተሳፈረባት SS ዳልሐውሲ መርከብ ከምፅዋ ወደብ ደረሰች። አካባቢው ከ300 ዓመታት በፊት በመጀመሪያ በኦቶማን ቱርኮች ተይዞ ነበር። በ18ኛው መቶ ከፍለ ዘመን ከእጃቸው ወጥቶ በግብጾች ተያዘ። ዳግም እንደገና በ1852 ላይ በቱርኮች ቁጥጥር ስር ዋለ። ያኔ ኘላውደን እዚያ ነበር የከተማው እነዚህ ለውጦቹ ሁሉ ታዲያ ጉልህ አልነበሩም ። ምፅዋ እጅግ ዘገምተኛ እና ያልደመቀች ቦታ ነበረች።

«ከምፅዋ ጋር ሲወዳደር ኤደን ምድረ ገነት ነው» ። ይላል ራሳም። በዚያች ምሽት እሱ እዚያ ሲመጣ ብቻውን አልነበረም። የመርከቧ ዘዋሪ ሌተናንት ፕሪዶ እና ዶ/ር ሔንሪ ብላንከም አብረውት አሉ። የምፅዋው ገገር የቱርኩ ካያም ማካም አልጋው ላይ እንዳለ ተቀበላቸው። ኦቶማኖች በተቆጣጠሩት በዚህ ውኃማ አካባቢ ለዓመታት መቆየቱ ዕናቱን አድቅቆታል። ግን ደግሞ ዶክተሩን ከነራሳም ጋር መመልከቱ መንፈሱን አነቃቃለት። ራሳም ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላከ ደብዳቤ ለቴዎድሮስ ሊያደርሱ መምጣታቸውን ነገረው።

«እኔ የእንግሊዝ ወዳጅ ነኝ!» ካያም ማካም ቀጠለ...« የብሪታንያ መንግሥት አድናቂ ነኝ፤ እናም ወደ ኢትዮጵያ እንዳትሄዱ ያለኝን ኃይል ሁሉ ተጠቀሜ እናንተን የማገድ ኃላፊነት አለብኝ። ንጉሡ እብድ ነው!»።

«ተልዕኮዬን እንደምንም አሳካለሁ፤» ራሳም በልበ ሙሉነት ተናገረ። «ለነገሩ እኔም ሆንኩ ዶ/ር ብላንክ ተልዕኳችንን በተመለከተ ያን ያህል የሚያጣድፈን ነገር የለም »።

ሐመምተኛው አገረ ገዥ ያሰበውን አሳካ። ያለውን አቅሙን አስተባብሮ እጅ ነሳቸው፤ «እንደዚህ ወደብ ባለሥልጣንነቴ እና እንደ ብሪታኒያ መንግሥት አጋርነቴ፤ እናንተን በሁሉም ረገድ ለመርዳት አቅሜ የሚችለውን ሁሉ በደስታ አደርጋለሁ»። ሆርሙዝድ ራሳም የኦቶማኖችን ስነልቦና ጠንቅቆ ያውቀዋል፤ እሱም ቢሆን በዚያው በሱልጣኑ ግዛት ነው የተወለደው። ዛሬ በሠላሳዎቹ አጋማሽ የዕድሜ ክልል የሚገኘው ይህ ሰው ሞሱል ከተማ ወጥቶ የተለወጠ ክርስቲያን ነው። በልጅነቱ ነነዌን በሚቆፈሩበት ወቅት፤ ኦስትን ሔንሪ ላያርድን በመርዳት ንበዝ ተማሪ መሆኑን አስመስክሯል። ለብሪታንያ ቤተመዘክር ተቀጥሮ በሚሰራበት ወቅት በ1846 ታላቁን የአሱርባኒፓልን ቤተመጽሐፍት እና ቤተመንግሥት እንዲሁም ብዙ የሚነገርላቸውን የአንበሳ አደን መሳሪያዎች ያገኘው እሱ ነበር። እነዚህ የዓለም ታሪካዊ ቅርስ ከሚባሉት ጥቂቶች የሚመደቡ

ናቸው። ከዚያም ላየርድ ራሳም መደበኛ ትምህርት እንዲያገኝ ወደ ኢንግላንድ ላከው። ራሳምም እዚያው ፕሮቴስታንት እና መፍቀሬ እንግሊዝ ሆነ። በርካታ ወዳጆችንም አፈራ። «ኢንግላድ ቤቱ ሆነች» ሲልም ጻፈ።

ይህች አባባሉም በኤደን የብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ተጠሪነት ሥልጣንን አጎናፀፈችው። ከዚያ ነው የንግሥት ቪክቶሪያን ደብዳቤ ለቴዎድሮስ እንዲያደርስ ትዕዛዝ የተሰጠው። በብሪታኒያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የምክር ቤት አባል የሆነው ላየርድ፣ ራሳም ታማኝ እና አስተዋይ እንዲሁም ከአረቦች ጋርም ጥሩ ግንኙነት ያለው ሰው እንደሆነ አረጋግጧል።

ሌሎች ግን የእሱን ሹመት ተቃውመዋል። ከማዕከላዊው ምሥራቅ አካባቢ ከተገኘው ሰው ይልቅ አንድ የብሪታንያ ዜጋ በስፍራው ቢመደብ ይሻላል የሚል መከራከሪያ አቅርበው ነበር። በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ከሚገኙ አንዳንዶች ደግሞ እንዲያውም የራሳም ትውልድ ስፍራ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ስሙም ቢሆን አንድ ነገር ኢጋጥሞ የሕዝብ ቁጣ ቢያስነሳ ብሪታኒያዊ ስላልሆነ የሀገራቸውን ስም ስለማያስነቅፍ እንደ ጥሩ ሽፋንነት ሊጠቅም ይችላል በሚል ድጋፋቸውን ሰጡት። ራሳምም ከብዙ አቅጣጫ ግሩም መሆኑን አረጋገጠ። ታጋሽ ፣ አዋቂ ፣ ደፋር እና እንደበተ ርቱዕ ። ተውኔቱም ሲጀመር ሊላሰው በእርሱ ቦታ ተመድቦ ቢሆን ኖሮ ስንትና ስንት ጣጣ ሊከተል ይችል እንደነበር ግልጽ ሆነ።

ከብዙ መጓተት በኋላ ራሳም ፈጣን ርምጃ መውሰድ እንደሚኖርበት አወቀ። ለቴዎድሮም ቢሆን ዕቃ የጫነች መርከብ ከወደብ መድረሷን የሚገልጽ ደብዳቤ መጻፍ ይችላል። የሚያስፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው። ደብዳቤውን የሚያደርስለት መልዕክተኛ። የታማሚው አገር ቸሸ ጥረት ምንም ያስገኘው ነገር አልነበረም። ምንም ያህል ዋጋ ቢከፈል መልዕክቱን ይዞ ወደ ቴዎድሮስ ለመሄድ የሚደፍር አልተገኘም። በመጨረሻ ግን ራሳም ራሱ ሁለት ሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ማግባባት ተሳካለት፤ ደብዳቤውን ለቴዎድሮስ ለማድረስ። ከዚያም ተረጋግቶ ውጤቱን መጠባበቅ ጀመረ። የምፅዋ የአየር ጠባይ ሕመም ማለት ነው። ዶ/ር ብላንክ ሁኔታውን ሳያሰልስ ይመዘግባል። ማታ ማታ አልፎ አልፎ የሙቀቱ መጠን ከ35 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ዝቅ ይላል። ራሳም እና ብላንክ በሙቀቱ ምክንያት ሰውነታቸው ሽፍ ሲል ሮጠው ከባህሩ ይገባሉ። ግን ደግሞ ሙቀቱ ተመሳሳይ በመሆኑ ሽፍታውን ያባብሰዋል። ከተማዋ በቀድሞው የብሪታንያ ልዑክ መንፈስ ተይዛለች። ዊሊያም ኮፈን ከሞተ ወዲህ እንደ አልባሌ የተጣለችው የልዑኩ ባለቤት ራሳምን ልታናግረው መጣች።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ራሳም ፕላውደን ይኖባት ወደነበረችው ሞንኩሎ ሄደ። በዚህ ስፍራ ፕላውደን የራሱ መኖሪያ ቤት ነበረው። በግቢው ውስጥም አትክልቶችን ተክሎ እንደነበር፤ ውኃውም ቢሆን ከሌላው አካባቢ የተሻለ እንደሆነ ነገሩት። እዚያ ሲደርስ የቀድሞው የፕላውደን መኖሪያ ዳዋ ወርሶታል።



ወደ ግቢ ለመዝለቅ ሲሞክር እርስ በእርስ የተጠላለፈው እሾሃማው ተክል ፀጉሩ ውስጥ ተሰገሰገ። አይጦችም በአካባቢው ይተራመሳሉ። በረሮችም ይንጿጿሉ። ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ እና ምፅዋ ከከተመ የብሪታኒያ ወኪሎች በሕይወት የተመለሰ የለም። ዊሊያም ኮፈን እዚያው ምፅዋ በኀዘን ልቡ ተሰብሮ ነው የሞተው። ልጁ ደግሞ የሞተው ውቤ ባደረሰበት ስቃይ መሆኑ ይነገራል ። ፕላውደን ጎንደር ውስጥ ተገደለ። ቆንስል ካሜሮንም ታስሯል። የራሳም ዕጣስ ምን ይሆን?

ራሳም እና አብረውት የመጡት ሁለት ሰዎች አካባቢውን አፅድተው ከፕላውደን ቤት ከተሙ። ከመርከቡ ይልቅ እዚህ ውበት አለ። የቀድሞውን ጉድጓድ ቆፍረው ንፁህ ውኃ አገኙ፡፤ እንዲያም ሆኖ የቀኑ ሙቀት ሊቋቋሙት የሚያዳግት ነበር። ከስሩ ቀዝቃዛ ውኃ ባለበት በዚያ ስፍራ እንኳን የሙቀቱ መጠን 40 ዲግሪ የሚደርስበት ጊዜ አለ።

ሁለት ወራት አለፉ። ከቴዎድሮስ ለራሳም ደብዳቤ ምላሽ የለም። አብዛኛው የምፅዋ ነዋሪ ከርቀት ባለው በእርሱ የአገዛዝ ጥላ ስር ነው የሚኖረው። የቱርኮች ግዛት ነው፤ በሚባለው በዚህ ስፍራ የተነገረች አንዲት ቃል ከቴዎድሮስ ጆሮ ትደርሳለች ተብሎ ይታመናል። የማይፈሩ ጥቂት ሰዎችም አሉ። ለምሳሌ አርመናዊው ማርቆስ (በቴዎድሮስ ለጥቂት ጊዜ ታስሮ የተለቀቀ ነው) ይህ ሰው የቴዎድሮስን ስም ሲያብጠለጥል አይፈራም። «ራሱን ንጉሥ ነኝ የሚለው ሰው በቆስጥንጥንያ የባሪያ ገበያ ለሽያጭ ቢቀርብ ብዙ ዋጋ አያወጣም» ሲል ተሰምቷል።

የፈረንሳዩ ምክትል ቆንስል ቴዎድሮስ ሌሎች እንደሚሉት መጥፎ ሰው እንዳልሆነ ለራሳም ነግሮታል፡፤ እሱ እንደሚለው አውሮጳውያን የሚገባውን ክብር አላሳዩትም። ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላከውን ደብዳቤ ሲመለከትም እስረኞቹን እንደሚለቃቸው እርግጠኛ ነው። ከአቶማኖች አንዱ እና ኃይለኛው የአካባቢው ባለሥልጣን ናይብ መሐመድ አብደል ራሒም የቴዎድሮስ አድናቂ ነው። በተፈጥሮ ደግ መሆኑን ያምናል። ነገር ግን ይህ መልካም ስሜቱ በሕዝቡ ደም ጥማት ተውጧል።

ለ41 ቀናት የቴዎድሮስ እስረኛ ሆኖ ያሳለፈው ናይብ ፈገግ ብሎ «ቀውስ ቢጤም ነው» ይለዋል። አንዳንዶች ለራሳም ቴዎድሮስ በአማፅያን እየተሸነፈ ነው ይሉታል። ሌሎች ደግሞ የለም አይናወጥም ብለው ያምናሉ። «ጌታዬ» አለው የ40 ዓመቱ የትግሬ ተወላጅ የሆነ የራሳም ምግብ አብሳይ፤ «እሱ እንዴ እስኪዘምትባቸው ነው እንጂ፤ እመነኝ ነፋስ እንዳገኘው ገለባ ብትንትን እንደሚሉ እርግጠኛ ነኝ።» ይህ ሰው ደስታ ጊዮርጊስ ይባላል፤ ኅበዝ ቋንቋ አዋቂ ነው፤ ራሳምም ለጥቂት ዓመታት ለአስተርጓሚነት ከእሱ ዘንድ አቆይቶታል።

ለምሥራቅ አቢሲኒያ ራሱን በጳጳስነት የሾመው ሞንሲኞር ቢያንቺሬ ቴዎድሮስ ሲያዘው መሆኑን ሲሰማ ምቹ የሆነውን የአየር ጠባይ እና በሀገር ውስጥ የነበረውን ቤቱን ትቶ ለመሸሽ ተገደደ። ራሳም ሲያገኘው እጅግ በቁጭት ተውጦ ነበር። ስለ ንጉሡ ሲናገር ጠሜውን ጨብጦ እርስ በእርስ እያጋጨ፤

«ኃይል ቢኖረኝ ይህን ደካማ ኢንዮቹ ብትንትኑን አወጣው ነበር» ይላል። ብዙም ሳይቆይ በሳምንታት ዕድሜ ውስጥ በልብ ድካም ሞት አሰናበተው።

በርከት ያሉ የባንያን ነጋዴዎች ራሳምን ሊጎበኙ መጡ እና አግረ መንገዳቸውን ቴዎድሮስ ራዕይ ያለው ሰው መሆኑን ነገሩት። ምዕዋ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የኖረው ካሆጃ በድሮስ ደግሞ መጣና ባንያን ነጋዴዎቹ እንደማይታመኑ ነገረው። «ምፅዋ ውስጥ የተነገረህን ሁሉ አትመን»ሲልም አስጠንቅቀው። ሌላው ሰውም መጣና ሌላ ነገር ስለ ንጉሡ ሹክ አለው። ሐጅ አደም ኮርማን በአንድ ወቅት የታወቀ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ ነበር። «ስለቴዎድሮስ ልንገርህ፤ በሀገሪቱ ውብ የተባለች ሴት አግብቼ ነበር፤ አሁን ግን ተሰድጃለሁ። ንጉሡ ገንዘቤን ወሰደ። ሚስቴን ወሰደ። ክርስቲያን አደረጋት እና በሙቶዎች ከሚቆጠሩት ሚስቶቹ ሁሉ የበላይ አደረጋት» ።

«ቴዎድሮስ!» ሲልም የብሪታንያውን ልዑክ አስጠነቀቀው፤ «ሰብአዊነት የሌለው... የሰው ዘር ጠላት ነው »። እርግጥ ነው ሃጅ አደም ለአማፅያን የጦር መሣሪያ በድብቅ የሚያስገባ ሰው ነበር። ቴዎድሮስ ንብረቱን ወርሰው እና ሚስቱን ምግብ አብሳይ አደረጋት። ጥቅምት ላይ የምፅዋ የአየር ጠባይ በረድ አለ። ራሳም ፣ ብላንክ እና ፕሪዶ እዚያ ከመጡ 3 ወራት ሆኗቸዋል። እስከ አሁን ከቴዎድሮስ በኩል የተሰማ ነገር የለም። ራሳም ድጋሚ ሌላ ደብዳቤ ጻፈ። ከንግሥት ቪክቶሪያ ለተላከው ደብዳቤ ምላሽ እየጠበቀ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤውን ለቴዎድሮ ላከ።

«ምላሽ እንዲሰጡኝ በአክብሮት እለምናለሁ....»



## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

ሽተርን እና ሮዘንታል የሞት ፍርድ በተፈረደባቸው ጊዜ ቴዎድሮስ የምሕረት ጥያቄ ቀረበለት። ቴዎፍሎስ ቫልድማየር ከፊቱ ተንበረከከ። እያነባም ሁለቱ ሚሲዮናውያን ጓደኞቹ ምሕረት እንዲደረግላቸው ለመነ። ቴዎድሮስ ትኩር ብሎ ቫልድማየርን ተመለከተና እጁን ይዞ፤ «አትፍራ የእኔ ወዳጅ ፣ የእኔ ልጅ፤ ስላንተ እና ስለ ሚስተር ቢል ስል አልገላቸውም» በቴዎድሮስ እና ቫልድማየር መካከል የተመሰረተው ወዳጅነት ወደር የሌለው እና ልብ የሚነካ ነበር። የቴዎድሮስ ንዴት ሲንር ፣ ስዊዛዊው ሚሲዮናዊ በእምነት ጠጋ ብሎ ልክ እንደ አሁኑ ማረጋጋት ይችላል። በአማላይ እና ሁለት ገፅታ ባላቸው የውጭ ዜጎች የተከበበው ንጉሥ ለቫልድማየር በግልጽ ታማኝነት መልስ ይሰጠዋል።

«አንተ እውነተኛ ነህ፤ እኔም እወድሃለሁ» አለው ቴዎድሮስ ቫልድማየርን። ከጥቂት ዓመታት በፊት ቴዎድሮስ ለቫልድማየር ስጦታ ልኮለት ነበር። ከንጉሡ በቀር ማንም ሰው አንበሳ በግሉ እንዲኖረው አይፈቀድም፤ አንድ ወታደር ጋፋት ድረስ የአንበሳ ደቦል ታቅፎለት ሲመጣ ቫልድማየር በጥርጣሬ ነበር የተመለከተው፤ ቫልድማየር ወተት ሰጠው፤ እየቆየም አደገ። በዚያው መጠንም የምግብ ፍላጎቱ ከፍ አለ። ሥጋ ይፈልግ ጀመር። በየቀኑ አንድ በግ ቀለቡ ሆነ፤ ይህም በቴዎድሮስ በራሱ ይቀርብለት ነበር። ቫልድማየር እና ሚስቱ ሣራ ለአንበሳው "ሐጎስ" ብለው ስም ሰጡት። ደስታ ማለት ነው፤ ትርጓሜው። በጋፋት ኮረብታ ላይ በሰለንሰለት አስረውት ቢቀመጥም በየዕለቱ ግን በአካባቢው እንዲሯሯጥ ነፃነት ሰጥተውታል። ልጃቸው ሮዛ እሱን መጋለብ ትወድ ነበር። እንዲያም ሆኖ ይላል ቫልድማየር በጻፈው ማስታወሻ፤« እንደ አባትነቱ ዘወትር ከሥራ መሆን ግዴታዬ ነበር፤ እሷን በቀኝ እሱን በግራ እጄ እመራቸው ነበር።»

ከዚህም ሌላ ቫልድማየር ሐጎስ እጅግ ውብ እና ጥሩ ለማዳ አውሬ እንደነበር ጽፏል። «በሚያስገርም አተያይ ቴዎድሮስን የሚገረምመው አንበሳ እንደ ንጉሥ ይመስለኛል። ጨኸቱም አየሩን የሚያሸብር ግርማ አለው። ሐጎስን የሚያስቆጣው አንድ ነገር ነው። እሱም ሲበላ ሲያዩት አይወድም።»

የ1848ዓ. ም የዝናም ወቅት ሲያበቃ አውሮጳውያኑ እሥረኛ ከጋፋት 1 ሰዓት በእግር ወደ ሚያስኬደው ደብረ ታቦር ተወሰዱ። በዚያም የቫልድማየርን እና የማኅበረሰቡን ድጋፍ የማግኘት ተስፋ ሰንቀዋል። እጅግም የታየ ነገር የለም። እስረኞቹ የቴዎድሮስን ቆምጠጥ ያለ ስሜት ሲያዩ ሞት ሞት ይሸታቸው ጀመር፤ ቫልድማየር እና ሌሎቹ በሙሉ የሚችሉትን ያደርጉ ነበር። ድንች ፣ ዳቦ እና ወተትን ጨምሮ የእስረኞቹን ፍርሃት የሚያረጋግጥ መልእክት ይላክላቸዋል።

ቴዎድሮስ ጋፋት ሄዶ ስለታሳሪዎቹ ምንም አለማንሳቱንም ነገሯቸው። እስረኞቹ በሰንሰለት እንደታሰሩ ድንኳናቸው ውስጥ በፍርሃት ሰነበቱ። ዕጣ ፈንታቸው ከእነሱ ቁጥጥር ውጭ በሆነ አጋጣሚ ላይ የተመሰረተ ነው። ዕድል የሚያመጣ አስተያየት ፣ ወይም በቴዎድሮስ ድንኳን ውስጥ መጠጥ ሲጠጣ ፣ ወይም ደግሞ ከምፅዋ የሚጠበቀው ደብዳቤ ከመጣ ጥቅምት ወር ማለቂያ ላይ ቴዎድሮስ እነሱን ወደ ጋፋት ለመላክ ከንቲባ ኃይሉን ፣ የቀድሞውን የጎንደር አገረ ገዥ እና የንጉሡን ታማኝ ሚኒስትሮች እንዲሸኟቸው ሊልክ መሆኑን ሰሙ ፣ በዚያ ነፃነታቸውን ሊያገኙ ይችላሉ፤ የታሰሩበት ሰንሰለት ተፈታ እና የከንቲባ ኃይሉን መምጣት ይጠባበቁ ጀመር።

ሆኖም ግን ቴዎድሮስ ሐሳቡን መቀየሩን ሊጎበኛቸው የመጣ ሌላ ሰው አረዳቸው። የብሪታንያ ጀነራል እና ወታደሮቹ ምፅዋ ደርሰዋል የሚል ጭምጭምታ ሰምቷል። በስናር በኩልም ሌላ የአውሮጳ ኃይል ስለመምጣቱም እንዲሁ፤ ቀጠለና ደግሞ የመቅደላ ስም ተሰማ። «ወደዚያ ድንጋያማ ተራራ ከነሰንሰለታችን መወሰዳችንን ሳስብ ሰውነቴ ራደ።» በማለት ሽተርን ጽፏል።

ከዚያ እንደሄዱ ቴዎፍሎስ ቫልድማየር እነሱን ለማየት ገሰገሰ። ወደ ግቢው እንዳይገባም ተከለከለ። መነጋገር አልቻሉም፤ የፈረሱን ጋማ እያሻሸ ሽተርን ከአሾሁ አጥር አሻግሮ ተመለከተው። ከስሩ ያለው እንስሳ ወደፊትና ወደ ኋላ መቁነጥነጡን ሲመለከት ሽተርን የነፃነት እና እርነት ራዕይ በእጆቹ ላይ ያለውን የብረት ሰንሰለት እንደ እሳት ሲያቀልጠው ታሰበው።

አሁን የአውሮጳውያኑ እስረኞች ቁጥር ጨምሮ ከደርዘን አልፏል፤ በዚያ ላይ የሁለቱ ሚስቶቻቸው እና አራት ልጆቻቸው ታክለዋል። ከሌሎቹ እስረኞ ጋር ተቀላቀሉ። የአማፅያን መሪዎች ፣ ከሥልጣን የተነሱ ባለሥልጣናት ፣ ነፍሰ ገዳዮች እና ሌቦች ከሚገኙበት የእስረኛ ስብስብ ጋር በመሆን የመቅደላ ጉዟቸውን ጀመሩ። ቴዎድሮስ እና የእሱ ሰዎችም አብረዋቸው አሉ። ለሰባት ቀናት በስተምስራቅ በኩል ሜዳውን ይዘው ተጓዙ። በሚያዳፈው ሰርጥ እየወረዱ፤ በወርቅ ውኃ አቀበት እየወጡ ተራራውን ተያያዙት። በመጀመሪያው ዕለት ምሽት ሌሎቹ እሥረኞች ወደ ጎጆዎቹ ሲገቡ አውሮጳውያኑ ውጭ አደሩ። አዲስ ለመጡት እስረኞች ሰንሰለት ለማጥለቅ የአካባቢው ቀጥቃጮች ሦስት ቀን ፈጀባቸው።

በአደገኛነት ከተፈረጁት እስረኞች መካከል ካሜሮን ፣ ሽተርን እና ሮዘንታል ይገኙበታል። እንዲያም ሆኖ ከተጨናነቀው እስር ቤት ተርፈው ከንጉሡ አቅራቢያ ጎጆ ተሰጣቸው። የአምባው ሜዳ በስተደቡብ በኩል በመቶዎች የሚቆጠር ሜትር ሰፍቶ ወደገደሉ ጠርዝ ይደርሳል። የውጭ ዜጎቹ ከታሰሩበት 20 ሜትር ገደማ ራቅ ብሎ በስተጀርባ ያለው ገደል የባሰ ነው። ወደ አምባው የሚያስገባው መንገድ የድንጋይ ንጣፍ ሲሆን እስከ ዋናው መግቢያ ድረስ

ይዘልቃል። ጠባቂዎቻቸው፤ «ንጉሡ እናተን እንድንጠብቅ እንጅ ስለጤናችሁም ሆነ ስለምቾታችሁ ኃላፊነት አልሰጡንም። ብትሞቱ አንጠየቅም፤ ብታመልጡ ግን እናታችን ይፈርሳል» በማለት አስጠንቅቀዋቸውል።

ሽተርን ስለስፍራው «እሥረኞች ከአምባው ለመውጣት ክንፍ የላቸው አይበሩ፤ ቀጥ ብሎ በተሰደረው ገደል ለመውረድም እንደ ወፍ የሚቆነጥጥ ጥፍር የላቸውም" ሲል የከተበውን አላዩትም።

## ምዕራፍ ሃያ ሰባት

በ1856 እና 1857 ዓ.ም ራሳም ፣ ብላንክ እና ፕሪዶ ወደቡ ላይ ተቀምጠው ይጠብቃሉ። «ሙቀቱ ከፍተኛ በመሆኑ አንዳንዴ መተንፈስ ሁሉ ያስቸግረን ነበር።» በማለት ወቅቱን ያስታውሰዋል። በዚያም ላይ ርሃብ ነበር። ድርቅ እና የገበያ ስፍራዎች ባዶ ነበሩ። ሕዝቡ ከብቶቹም ሆኑ ግመሎቹ ሲሞቱ ወዲያው ሥጋቸውን እየቆረጠ ይከፋፈላል፤ ቆዳ እና አጥንታቸውንም ይቀቅላል፤፤ በባህሩ ዳርቻም እጅግ በርካታ ሕዝብ ጥልቀት ከሌለው የውኃ አካባቢ ቀንድ አውጣ ለመልቀም ይሻማል።

በርካቶች ይህን በመመገብ ሞቱ። ለሀጅ ከሄዱት አብዛኞቹ አልተመለሱም። መካ ውስጥ የኮሌራ ወረርሽኝ መቀስቀሱ ተነግሯል። ምፅዋ ለሞተው ቱርካዊ ገዥዋ አለቀሰች። ስፍራው የጦጣዎች እና ጅቦች መናኸሪያ ሆነ። ራሳም ወደ ቴዎድሮስ ለላካቸው ለመጀመሪውም ሆነ ለሁለተኛው ደብዳቤዎቹ ምላሽ አላገኘም። ለሶስተኛ ጊዜ መጋቢት ወር ላይ እስከ አሁን መልስ አለማግኘቱን ጠቅሶ ደብዳቤ ላከ። ምናልባት ጃንሆይ ደብዳቤዎቹ አልደረሰዎትም ይሆን? (ራሳም ቢያንስ አንደኛው ደብዳቤው ከንጉሡ መድረሱን አረጋግጧል) ምናልባት የእሱ ተልዕኮ ምንነት ጥርጣሬ አሳድሮበት ይሆን? «የብሪታንያ መንግሥት ለእርሶ ማዘት ደህንነት እንደሚያስብ በሙሉ ልብ አረጋግጥልዎታለሁ።» እናም ራሳም ያለው ጊዜ ውሱን መሆኑንም ግልጽ አደረገ። «ግርማዊነትዎ ምላሽ የማይሰጡኝ ከሆነ ወደ ኤደን ለመመለስ እገደዳለሁ።»

ዶ/ር ብላንክ እንዲህ ያለውን ድርድር ለራሳም ተወለት። እሱ እና ሌተና ፕሪዶ እዚያ የተገኙበት ምክንያት፣ ዶክተር ፡ ወታደር እና ዲፕሎማት እንዲህ ላለው ተልዕኮ የሚያስፈልጉ በመሆናቸው ነው። ብላንክ ጊዜውን በሳይንስ ምርምር ያሳልፋል። በየዕለቱ ሳያሰልስ የአየር ፀባዩን ይመዘግባል፤ በምፅዋ ገበያ እና በአካባቢውም ለየት ያሉ ባሕላዊ ለውጦችን አግኝቷል፤ የተለያዩ በሽታዎችንም መዝግቧል፤ ቅኝቱ ግን ለውትር ከለመደው አካሄድ የተለየ ነበር። አልፎ አልፎ ከሚዘንበው ዝናብ በኋላም ትኩሳት በየጊዜው የሚያጋጥም ችግር መሆኑን አያቷል። በተምቤ የአባላዘር በሽታ እጅግ የተስፋፋ ነበር። ፈንጣጣም ድንገት በአሰከፊ ወረርሽኝ መልክ ተነሳ። ከተባት በመያዝም በበሽታው ከመጠቃት አመለጠ። ሌላው በአካባቢው ከፍተኛው የሞት ምክንያት ወሊድ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ራሳም ከእስረኞቹ አመርጿውያን መልእክት ደረሰው። ከመቅደላ ደብዳቤ በሰውር መላክ ቻሉ፤ ካሜሮን ሌሎቹንም እስረኞች በተለይም አኑ ፍላድ እና ሮዘንታልን እንዳማከረ በገለጸበት መልእክቱ ወታደራዊ ርምጃ ብቻ



ቴዎድሮስ አንድ ነገር እንዲያደርግ እንደሚስገድደው እንደሚያምኑ ገልጿል። በመጨረሻም «ስለ እግዚአብሔር ብለህ ወደዚህ ለመምጣት እንዳትሞክር፤ እንደ ጠበመንጃ ነው የሚተኩስህ» አለው። ጥርጣሬ ለሚያናውዘው ራሳም መጠበቁ በራሱ ትዕግስት አሳጥቶታል፤ ምክር የሚሰጠው አላጣም። » የነገርኩህን መስማት ነበረብህ፤ ቴዎድሮስን እንደሰው ለመንከባከብ መፈለግህ ተሳስተሃል፤ እንደ አህያ ብትይዘው .... በዱላ ማለቴ ነው፤ ያኔ አንድ ነገር ያደርጋል» አሉት ሀጂ ኢደም። ናይብም ሁለት እጅግ ጠቃሚ ደብዳቤዎችን ለቴዎድሮስ ልኮ መልስ አለማግኘቱን ነግሮታል። ሦስተኛውንና ተራ ደብዳቤ ሲልክ ግን መልስ መጣ። « እንደ ቀበጥ ልጅ ተስዋዋጭ ነው» አለ ናይብ።

ተልዕኮው ሁሉ ተሳሰረ፤ ሳምንታት ነጎዱ፤ ወቅቱ እጅግ ሞቃታማ ወራት ነበር። በርከት ያሉ ደብዳቤዎች ከእስረኞቹ መጡለት። ሦስቱ የእንግሊዝ ልዑካን ከወደቡ ገባ ብሎ ወደሚገኘው አካባቢ ገብተው ሰፈሩ። እዚያ ግን ሙቀቱ ጠናባቸው፤ የጨውን ከምር አልፈው ራቅ ብለው ወደ ኮረብታው ዘለቁ፤ እዚህ ትንሽ እፎይታ አገኙ። ነሐሴ መባቻ ላይ ወደ ወደቡ ተመለሱ። ጭንቅላታቸውን በእርጥብ ፎጣ ጠቅልለው ድንኳናቸው ውስጥ ተቀመጡ። ዶ/ር ብላንክ እንገላቸው ከመጠን በላይ በሆነ ሙቀት ውስጥ ሲቀመጡ ሊገጥመው ስለሚችለው አደጋ ማብራሪያ ሰጠ። ድንገት ከውጭ ጩኸት ተሰማ። ኤል በሽራ! መልካም ዜና! መጋረጃውን ሲገልጡት የናይብ የእህት ልጅ ከግመል ላይ እየወረደ «የምስራች ንጉሥ ቴዎድሮስ ጻፈ!» አላቸው።

## ምዕራፍ ሃያ ስምንት

ላለፉት ጥቂት ዓመታት ቴዎድሮስ ቀድሞ በቀላሉ አግኝቶት የነበረውን አካባቢ ፣ ጀነራሎች ፣ ወታደሮች ፣ ተኳደኞች እና ደጋፊችን ቀስ በቀስ እያጣ ሄዷል። አሁን ደግሞ በዘመቻ ድል አጣ። በ1850 የክረምቱ ወራት ከመግባቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ወደ ደቡብ ዘምቶ ነበር። ራሱ የሾመው የሸዋው ሀገረ ገዢ በዛብህ አመጸበት። በዚህ ጦርነት አልቀናውም።ወታደሮቹ በጦርነት ድል በመነሳታቸው አንገታቸውን ደፉ፤ ረሃብና ድካምም ፈተናቸው፤ ወደ ጎንደር እንዳይመለሱ አመፀኛው ጥሶ(ጥርሶ) ጎበዜ ተቆጣጠረው፤ ወደ ደብረ ታቦርም መግባት የማይታሰብ ሆነ።

እናም ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ መራቸው፤ ይህ ተራራ የእሱም ሆነ የሀብት ንብረቱ መሸሸጊያ እንዲሆን መርጦታል፤ «የአቢሲንያ ንጉስ የገገር መደብ እዚህ ነው » ሲል ካሜሮን ጽፎታል። ከአንድ ዓመት በፊት ቴዎድሮስ ዙር አምባ የነበሩትን የፖለቲካ እስረኞቹን አውሮጳውያን ወደ መቅደላ አዛውሯል። በዚህ ስፍራ በመቶዎች ከሚገመቱ አብያተ ክርስቲያናት የተዘረፉ ንዋየ ቅድሳት ይገኛሉ። ስንክሳር፣ ገድለ ቅዱሳን፣ ሃይማኖተ አበው የከብረ ቅዱሳን ቅጂ ሁሉ እዚያ አለ። የንጉሡ ባለቤት እቴጌ ጥሩነሽ እና ልጃቸው ሕፃኑ ዓለማየሁም እዚያ ናቸው። ከፊል እስር ላይ የሚገኙት የእስረኞች ሚስቶች ፣ አቡኑ እና ከሰለሞን ዘር የመጨረሻው ገዥ ሞኙ ዮሐንስ ( ንጉሥ ዮሐንስ ሦስተኛም) በእዚያ ይገኛሉ ፤ በተጨማሪም ቴዎድሮስ የየግዛቱን መንግሥታት ወራሾች በዚያ ሰብስቧል። የኦሮሞው ልዑል አህመድም እዚያው ነው፤ ከኦሮሞዋ ንግሥት ከአህመድ እናት ወርቂት ጋር ድርድር ላይ ነበር። ካሜሮን በማስታወሻው እንዳሰፈረው ከሆነም «የአቧ ወታደሮች የንጉሡን ወታደሮች እጅ ቆርጠዋል። ሰቅለዋቸዋልም»።

መቅደላ ላይ ከነበሩት ወራሾች መካከል ምኒልክም አንዱ ነው። ቴዎድሮስ መጀመሪያ ወደ ሸዋ ዘምቶ የሸዋን ግዛት ሲቆጣጠር ነው፤ የ11 ዓመቱ ምኒልክን ይዞ ወደ ጎንደር በማምጣት ከመጀመሪያው ትዳሩ ካፈራው ልጁ መሸሻ ጋር አብሮ ያሳደገው፤ ለሁለቱም ተመሳሳይ ፍቅር ያሳያቸው ነበር። ምኒልክም ቢሆን ቴዎድሮስ ልክ እንደ ሁለተኛ አባቱ አንደ ነበር ገልጿል። በመቅደላ ቆይታውም የቴዎድሮስን ልጅ አልጣሽን አግብቶ ነበር። ሆኖም ግን በዛብህ ቴዎድሮስን ድል ማድረጉን ያወቀው የምኒልክ መንፈስ እረፍት አጣ።

በዛብህ ራሱን የሸዋ ንጉሥ ብሎ ሲያውጅም ርምጃ መውሰድ አለብኝ ብሎ ወሰነ። በ1850 ሰኔ ወር ማለቂያ አንድ ምሽት እናቱን ጨምሮ ሌሎች ሸዌዎችን ሰበሰበ እና ከተራራው ላይ ሾልኮ አመለጠ። አልጣሽን ግን አላስከተለም።

በማግስቱ ጠዋት ቴዎድሮስ በተራራው ገደል ላይ ሆኖ በቴሌስኮፕ ሲመለከት አነምኒልክ ከንግስት ወርቂት የጦር ሰፈር ደርሰዋል። ቴሌስኮፑን ዘጋው፤ «ወርቂት አሁን ነፃ የሆነ ልጅ አግኝታለች ፤በታሠረው ግን ዋጋ ትከፍላለች» አለ። ፈረሱ ላይ ወጥቶ በተራራው እናት ሽምጥ ወደ እስር ቤቱ ጋለበ።

«አህመድ የት አለ?»

«እዚህ ነኝ ግርማዊነትዎ!» በትሕትና መለሰ ልጁ።

በዚያን ጠዋት ፍቅርም ሆነ ርኅራኄ በቴዎድሮስ መንፈስ ውስጥ አልነበረም። አህመድን እና በረከት ያሉ የኦሮሞ ባለስልጣናትን ወደ መቅደላ አፋፍ ላካቸው። ሰንሰለት ያለበት እግራቸው እየተቆረጠ ወደ ገደሉ በጦር እየተወጉ ተጣሉ። ቆየት ብሎ ቴዎድሮስ ዞር ሲል አቡኑ ከታሰሩበት ጎጆ ደጃፍ ተቀምጠው ተመለከተ።

«ለምንድነው መጥተው ያልገሰፁኝ? » ሲል ጮኸባቸው።

«ፊትዎ ደም ለብሶ ስለተመለከትኩ ነው!» አሉ።

ቁጣው የነደደው ቴዎድሮስ ጦሩን ሰብቆ ተጠጋ፤ አቡኑ የተከናነቡትን ከጭንቅላታቸው አውርደው «ይኸው ግደሉኝ!» በማለት አፈጠጡ። ቴዎድሮስ የሰበቀውን ጦር ጣለው፤ አብረውት ለነበሩትም፤ «መሞት ከፈለገ፤ መኖር አለበት» አላቸው።

መቅደላ ላይ የሚኖረው ማኅበረሰብ ከዚህ ድንጋጤ ብዙም ሳይወጣ ከወደቡ የመጡ ሁለት ነጋዴዎች እዚያ ደረሱ። አንደኛው ቴዎድሮስ ምፅዋ የሚገኘውን የእንግሊዝ ልዑክ ሆርመዝድ ራሳምን ምንነት እንዲያጣራ የላከው ወልደ ስላሴ ገበዜ ነበር። «ጥሩ ሰው ነው» እያለ ወልደ ስላሴ ለንጉሡ ሞቅ ያለ ዘገባውን ሲያቀርብ አብሮት የተጓዘው ጓደኛው ባለመስማማት፤ «ዋይ ዋይ! ከፈረንጆቹ ጉቦ ተቀብለሃል መሰል ወልደ ስላሴ?» በማለት አናጠበው። ወልደ ሥላሴ ዞር ብሎ ጓደኛውን ጎሸመው፤ ቴዎድሮስም ሳቀ።

እስከዚያን ጊዜ ድረስ ቴዎድሮስ ራሳም ወደ መቅደላ ብቅ እንዲል ፍላጎት አልነበረውም፤ እንዲያም ሆኖ ልዑኩ ያገኘው መልካም አጋጣሚ የሸዋው ሽንፈት እንዲሁም የምኒልክ ማምለጥ ተደማምሮበት የእስረኞቹን ጉዳይ ለማፋጠን ረድቷል። ቴዎድሮስ ሁለቱን ጸሐፊዎቹን ጠራ።

## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ራሳም ከአንድ ወር በኋላ ከቴዎድሮስ በአረብኛ የተላከለትን ደብዳቤ አግኝቶ አነበበ። አጋጣሚውም ይህ ሰው ከርቀትም ቢሆን የእሱን ሕይወት መቆጣጠር እንደሚችል ያመለከተ ነው። ደብዳቤው ፊርማም ሆነ ንጉሣዊ ማሕተም የለውም።

«ስሜን ያልጻፍኩልህ ፣ አቡነ ሰላማ ፣ ፈላሻው ኮከቤ (ሽተርን) እንዲሁም እናንተ ቆንስል አድርጋችሁ ሾማችሁ የላካችሁት ካሜሮን የእንግሊዝን ወዳጅነት በመፈለጌ ምክንያት በእግዚአብሔር ኃይል በራሴ ከተማ በወዳጅነት ተንከባከቤ ባኖራቸው ስለ ሰደቡኝ ነው። እንግሊዛውያኑ ፕላውደን እና ጆን ቤል በገዛ ሀገሬ ጥቃት ሲደርስባቸው በእግዚአብሔር ኃይል የእነሱን ደም በመበቀሌ ጨካኝ ሲሉ ሰደቡኝ» ።

ደብዳቤው ቴዎድሮስ ካሜሮን ላይ ያደረበትን ቅያሜ ይዘረዝራል። «እኔ እና ንግሥቲቱ መካከል ወዳጅነት እንዲመሠርት ቢላክ ከቱርኮች ጋር ከርሞ መልስ ሳይዝ ተመለሰ። ምን ባደርጋቸው ነው የጠሉኝ ብዬ በመገረም በፈጣሪዬ ኃይል ዝም አልኩ»።

እንዲህ እንዲህ እያለ የቴዎድሮስ ደብዳቤ ከግብግቡ ይልቅ ወደ እሱ መምጣት ከፈለገ ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ በመምከር ተቋጨ ። «ትግራይ ውስጥ አማፅያን ስለተነሱ በእግዚአብሔር ኃይል መንገድህን ለውጠህ በመተማ በኩል ዞረህ ና፤ መተማ ስትደርስ አሳውቀኝ፤ በእግዚአብሔር ኃይል ሰዎች እንዲቀበሉህ እልክልሃለሁ»።

ራሳም ግራ ገባው ይሂድ? ካሜሮን እንዳይሞክረው አጥብቆ አስጠንቅቆታል። በዚያም ላይ ፊርማ ስለሌለው ጥርጣሬ አድሮበታል። የቴዎድሮስ ሁኔታም ቢሆን «አክብሮትም ሆነ ግብግቡ» የተላበሰ አልነበረም። ነገር ግን መልዕክተኞቹ ካሜሮን መፈታቱን ነገሩት። (ይህ ግን እውነት አልነበረም) ። የተፈጠረውን ቀውስ ለመፍታት ዓመት የጠበቀው ራሳም ሁሉንም ለማየት ፈለገ። ከለንደን ምክር ፈልጎም ጥቂት ቆየ።

አንድ ቀን አመሻሽ ላይ በጀልባ ለመንሸራሸር ወጣ። ምፅዋ ላይ ፀሐይ ስትጨልም እና በአቧራ ተሸፍና ስትጠፋ ተመለከተ። በፍጥነት በአቅራቢያው ወዳለው የባሕር ዳርቻ ቀዘፈና ወርዶ ከጀልባው በታች ተሸሸገ። ነፋሱ ከበረሃው ያመጣውን አሸዋ ከባህሩ ዳርቻ እያላጋ ጮኸ። ከጨለመ በኋላ ነበር ራሳም ከተሸሸገበት መውጣት የቻለው። ከዚያም ጨለማውን ገፎ ቀን የሚያስመስለው የመብረቅ ብልጭታ ተደጋግሞ አየ። ራሳም በጻፈው ማስታወሻው ይህን



አስፍሯል። «ከአንድ ዓመት በላይ ስንቆይ ለመጀመሪ ጊዜ ያየነው ጠንካራ ነፋስ ነበር» ። ወደ ደሴቱ ሲመለስ ሲቀዝፍባት የነበረችው ጀልባ የታችኛው ክፍል በአሸዋ ተሞልቶ ነበር።

ከጥቂት ቀናት በኋላ መጥፎ ዜና ደረሰው፤ በእሱ ሹመት ምክንያት ጉርምርምታን ሲያስተናግድ የነበረው የብሪታንያ መንግሥት ቴዎድሮስን እንዲጎበኝ ሌላ ሰው መደበ። ይህ ሰው እንግሊዛዊው ዊልያም ፖልግራቭ ነ በር። ራሳም ወደ ግብፅ ሄደ፤ ከስዊዝ በባቡር ተሳፍሮ ወደ እስከንድሪያ ተጓዘ እና ምቾቱ በተሟላለት ሆቴል ደ ኢውሮፕ ተቀመጠ። በፈጣኑ አዲስ ቴሌግራፍ አማካኝነትም በየዕለቱ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጋር ይገናኝ ጀመር። በእስከንድሪያ እና ለንደን መካከል የቴሌግራፍ መልእክት ልውውጡ ቀጠለ። በመልሱ ፍጥነትም ተፈጥሮ የነበረው ጥርጣሬ እና አለመግባባት ሁሉ ተነነ። ፖልግራቭ ከተላከበት ተጠራ። ራሳም ወደ ገበያ ወጥቶ ለቴዎድሮስ ስጦታዎች ገዛ። ከሳምንታት በኋላ መስከረም 9 ቀን ወደ ምፅዋ ተመለሰ። ግልጽ መመሪያ ከለንደን ተቀብሷል። ትክክለኛ ፈቃድም ከካይሮ፤ አግኝቷል፤ በዚያም ላይ ስጦታዎችን ጭኗል። ከበታቹ መርከቧ የቀይ ባሕርን ውኃ በልበ ሙሉነት እየሰነጠቀች ወደ ደቡብ አቅጣጫ ትፈሳለች። ራሳም በጥሩ ስሜት ላይ ነው። እየሩ ግሩም ነፋሱም ከኋላው ነው።

«ደስ የሚል ስሜት ነበር፤ እንደ ምኞቴ ፣ የአቢሲንያ ጉዳይ ለእኛ በሚጠቅም መልኩ ተሰወጠ፤ ወደፊት የተረጋጋ ቀዘፋ ብቻ ይሆናል»።

## ምዕራፍ ሠላሳ

በ1857 ጥቅምት አምስት ቀን የኮሌራ ወረርሽኝ በርካቶችን በከፍተኛ ፍጥነት ሲጨርስ የብሪታንያ ልዑካን ምፅዋን ለቀው ወደ ቴዎድሮስ ጉዞ ጀመሩ። በአማፅያን የተያዘችውን ትግራይን ወደጎን ትተው በስተምዕራብ ወደ ሱዳን አቅጣጫ ተጓዙ፤ ከራሳም፣ ዶ/ር ብላንክ እና ሌተናል ፕሪዶ ጋር መደበኛ ያልሆነ የቱርክ ጠባቂዎች ፣ ጥቂት ፓርቱጋሎች እና የሕንድ አገልጋዮች ፣ የናይብ የእህት ልጅ እንዲሁም ዕቃና ስጦታዎችን የጫኑ 60 ግመሎች ተከትለዋል።

ምፅዋ ላይ ማብራሪያውን ሲያወርደው የከረመው ዶ/ር ብላንክ አሁን የአየር ንብረቱ ይለዋወጥበት ገባ። አዲስ የአየር ጠባይ ማለት ደግሞ አዳዲስ የበሽታ ዓይነቶችን ማጥናት ማለት ነው። የልዑኩ ወታደራዊ ሰው ፕሪዶ በመጨረሻ ወደ ዘመቻው በመግባቱ በጥንቃቄ ጉዞውን ተያይዞታል።

ለዓመታት በደረሰበት ድርቅ ምክንያት በወደመው አካባቢ ማለፍ ጀመሩ። የአንበጣ ው መንጋ ከዚያ ሁሉ መዓት ተርፈው በያለበት ብቅ ብቅ ያሉትን አረንጓዴ ተክሎችን እያደነ ያወድማል። ግመሎቹ ይጥመለመሉ እና ይንገዳገዱ ጀመር፤ አጅግ የደከሙትን ሸክማቸውን እያራገፉ በጠንካሮቹ ላይ በመደረብ ለጅብ ተዋቸው። በተለይ ከሰላ እና ቀርታለች። የአካባቢው ወታደሮች በኃላፊዎቻቸው ላይ በማመፃቸው 2,000 የሚሆኑት ተገድለዋል፤ ቀሪዎቹን በየእስር ቤቱ በሽታ ፈጃቸው።

«ከተማዋ ጥቂት በቀሩት መናፍስት መሰል የደቀቁ ዜጎቿ መንፈስ ተሞልታለች» ሲል ዶ/ር ብላንክ በወቅቱ ያስተዋለውን በማስታወሻው ከትቧል። ለአንድ ወር በዚያ አሸዋ ላይ ሲንፏቀቁ የታመመም ሆነ ጤነኛ ነፍስ ብዙም አላጋጠማቸውም። "እጅግ ደረቅ እና አድካሚ። ሲል ዶ/ር ብላንክ ጊዜውን ገልፆታል። ሕዳር ወር ማለቂያ ላይ መተማ ደረሱ። ቴዎድሮስ ከዚህ ስፍራ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ይገኛሉ እንደታዘዘው ራሳም ደብዳቤ ላከ። አንድ ሳምንት አለፈ። ቴዎድሮስ ጋር የነበረ ከተማው ውስጥ የሚገኘው ጀርመናዊ ወደ ቴዎድሮስ እንዲሄዱ አበረታታቸው፣ ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላከውን ደብዳቤ ማድረሱ የእስረኞቹን መፈታት ሊያመቻች እንደሚችልም ነገራቸው። መጠበቃቸውን ቀጠሉ። ዶ/ር ብላንክ ብዙ የሚሰራው ነገር አገኘ። ለከባድ ተቅማጥ (የጉሎ ዘይት ፣ በአፒየም እና ታኒክ አሲድ) እያለ ይመራመር ጀመር። ሌተናል ፕሪዶ የሰዎቹን አቋም ተመልክቶ ጠንካራ እና ደፋር እንዲሁም ግሩም ፈረሰኞች ናቸው ሲል ገምግሟል። ለራሳም ደግሞ ወደ ምፅዋ መልእክት ለመውሰድ እምቢ ስላሉት ሰነፍ እና ፈዛዛ ዘር ሆነውበታል።



ቴዎድሮስን ጎብኝቶ የተመለሰው የአካባቢው ሼክ በከተማዋ አስገራሚ ስሜት ነው ያዘመተው። ራሳምን በፍቅር እቅፍ አድርጎ «ቴዎድሮስ ታላቅ ሰው ነው ፣ እዎ ታላቅ ሰው!» ሲል ጮኸ። «መልካም ሰው!» ። ከዚያ ሊጠጣ ሄደ።

አንድ ደብዳቤ ከራሳም እጅ ገባ፡፤ እስረኛው ቆንስል ካሜሮን ነበር ከመቅደላ የላከው፡፤ አሁን አጣዳፊ የሆነ ግፊት እስረኞቹ እንዲደረግ ይፈልጋሉ። ጋፋት የሚገኙት አውሮጳውያን ራሳም ካልመጣ መቅደላ ያሉት እስረኞች አለቀላቸው ነው የሚሉት። እስረኞቹ መቅደላ ላይ አሁንም እጅና እግራቸው በሰንሰለት እንደታሰረ፤ ርምጃቸው የእንቆቅቅ ቢሆንም ቴዎድሮስ ለእያንዳንዳቸው ላም ላከላቸው። መልካም ምልክት። ሌላ ሦስት ሳምንት አለፈ።

«አሁን ስጋት ገባኝ። ምፅዋ ላይ እንዳደረገው ቴዎድሮስ እዚህ መተማም ሆነ ብሎ እንድጠብቅ ያደረገኝ መሰለኝ» ። ይላል ራሳም፤ የልደትን በዓል እንዲህ ባለው ሁኔታ ማሳለፍ ከባድ ነበር። ከርስትናን ተቀብሎ በማደጎ ያደገበት ኢንግላንድ እንደለመደው በዓሉን በዓል የሚያስመስሉት አስፈላጊ የጣፋጭ መቀመሚያዎች እዚህ አይታሰቡም። ሕንዳውያን አገልጋዮቹ ተሟሙተው የተወሰነ ነገር ማቅረብ ቻሉ። በገና በዓል ማግስት በኢንግላንድ ስጦታዎች በሚከፈቱበት ዕለት በአረብኛ የተፃፈው የቴዎድሮስ ደብዳቤ ከተፍ አለ።

«ለተወደደው እና አዲሱ ሁሩገ ራሳም! ከሠላምታችን ቀጥሎ ያንተን ጤናና ደህንነት እንጠይቃለን፤ እኛ ሺህ ጊዜ እግዚአብሔር ይመስገን ለጤናችን ደህና ሆነን በሰላም አለን። ለክቡርነትዎ ለመግለጽ የምንፈልገው በኅዳር ወር የላኩት ደብዳቤ ደርሶናል። ቃል በቃልም ተረድተነው ለወዳጅነትዎ ፈጣሪያችንን እመሰግነናል» ።

ከጥልቅ ሠላምታው በቀር ይህ ደብዳቤም የቴዎድሮስን ንዴት የሚያንፀባርቅ ነበር፡፤ ማንበቡን ሲቀጥል ራሳም መረጋጋት አልቻለም፡፤ አሁንም ደብዳቤው ፊርማም ሆነ ማኅተም አልነበረውም። «እናም አሁን የተወደድከው ሆይ እንደገለጽንልህ በነዚያ በምወዳቸው እና በሥልጣኔ ስር በየዕለቱ እንዲኖሩ በፈቀድኩላቸው ሆኖም ግን እነሱ ባጋለጡኝ ሰዎች ስሜ ስለተጣለ ይህ ደብዳቤም ስሜን አልያዘም» ። ቴዎድሮስ ይህን ደብዳቤ ከጻፈ ከአንድ ቀን በኋላ ሐሳቡን ለወጠ። «ከእኔ ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ተስፋ ባለመቁረጥ ያን ሁሉ ጥረት አድርጎ እንዴት ራሳምን በመጥፎ ሁኔታ እስተናግደዋለሁ?» ሲል ንጉሡ ለችሎቱ ገለጸ እና ጸሐፊውን ጠርቶ ሁለተኛ ደብዳቤ አጻፈ።

«እነዚያ ደካማ ሰዎች እኔን ቢያጋልጡኝም ውዱ ሰው ሆይ አንተ ምን መጥፎ ነገር እኛ ላይ አደረግህ?» ሁለቱም ደብዳቤዎች በአንድነት ከራሳም ዘንድ ደረሱ። በዚህኛው ደብዳቤ ራሳም መፈለጉንም ሆነ የንጉሡን ማሕተም እና ስም አየ።

ለመጀመሪያ ጊዜም ራሳም የቴዎድሮስን የዲፕሎማሲ አካሄድ አስተዋለ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ልዑካኑ በረሃውን አልፈው ዳገቱን ተያያዙት፤ በተደጋጋሚ ከበቅሎቻቸው እየወረዱ ገደሉን ለመውጣት ተፍጨረጨሩ። በየመሃሉም እየሩ ትንፋሽ ይወስዳሉ።

«እንደተስፋይቱ ምድር ከናፈቅናት ሥፍራ ወደታች እንፈጠፈጣለን የሚለው ስጋታችን ተወግዶ ስንደርስ እርስ በእርሳችን እንኳን ደስ አለን ተባባልን» ሲል ብላንክ ጽፏል። ራሳም ለአጭር ጊዜም ቢሆን የተልዕኮው ክብደት ከትከሻው ወረድ አለለት፤ ዙሪያ ገባውን በአድናቆት ተመለከተ።

«በጣም አስገራሚ ት ዕይንት ... እንዲህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም። ከፊት ለፊቱ 160 ኪሎ ሜትር ገደማ የሚሆን በሰሜን እና በምዕራብ በኩል ተንጣሏል። በዳሩ ላይ የተለያዩ ቁልቁለት እና ጉድባዎች ያሉባቸው ተ ራራዎች አሉ። አንዱ ከሌላው ጋር መሳለመሳ ወርዶ ይታያል ፣ አንዱ ሌላኛውንም ያቋርጣል» ። ሌተናል ፕሪዶ ግን ተራራውን ስለመውጣትም ሆነ አናቱ ላይ ስለመድረስ ትንፋሽ ያለው ነገር የለም።

ሦስቱ ሰዎች ጉዟቸውን ወደ ጣና ሐይቅ ዳርቻ እና ወደ ንጉሡ መንደር ቀጠሉ። ከየደረሱበት አውራጃ ዕቃ የተሸከሙ ተጓዦች ከእነሱ ጋር እየተደመሩ ይጓዛሉ። የራሳቸውን ሸኚዎች ጨምሮ ሌሎች 1,200 ሰዎች ተከተሏቸው። በመንገድ ያስተዋለውን ራሳም እንዲህ ጽፎታል። «እጅግ ጠንካራ ወንዶች ትንሽዬ መቀመጫ ለሁለት ይዘው መሄዳቸውን፤ ሌሎች ደግሞ ዱላ ብቻ መሸከማቸው፤ ሁለት ወይም ሶስት የድንኳን ማያያዣ ወይም ቀንጨራ ብቻ ይዘው ሲጓዙ ማየት በጣም አስቂኝ ነበር» ። የልዑካኑ መምጣት ቀድሟቸው በየአካባቢው ዜናው ተሰራጭቷል። ከምንም በላይ ከመካከላቸው አንድ ፈረንጅ ሐኪም መሆኑ አገሩን አዳርሷል።



# ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

መቅደላ ላይ ቀናት እስረኞቹን አዚያው ጥለው ይከንፋሉ። በ1857 ዓ.ም የክረምቱ ዝናብ ዘግይቷል። ሌላው ቀርቶ በሐምሌ አጋማሽ እንኳን የወረደው ጥቂት ነው። እንዲያም ሆኖ በመስከረም የመቅደላ አናት እና የድንጋይ ስብስቡ በትናንሽ አበባዎች ተዋበ። ከታች ባሻገር ደግሞ በወራጅ ውኃ ታጅቦ የጎብስ ፣ የጤፍ እና የስንዴው እርሻ በማለዳዋ ፀሐይ አረንጓዴ ለብሶ መታየት ጀመረ። በኮረብታው ዙሪያ የወረደው ድንጋያማ ገደል ከወትሮው የበለጠ ጠቁሯል። ወጣቱ ምንሊክ በዚሁ ዓመት ሐምሌ ወር ከመቅደላ ካመለጠ በኋላ ቴዎድሮስ አውሮጳውያን እስረኞቹን በተመለከተ አዲስ ትዕዛዝ ሰጠ። በታሰሩበት ሰንሰለት ላይ ሌላ ማያያዣ ተጨምሮ ከወገባቸው ወርዶ ቁርጭምጭሚታቸው ላይ በ8 ኢንች(እጅቅ) ሰንሰለት እንዲያያዝ ተደረገ። ተጨማሪው ማያያዣ 9 ኪሎ ገደማ ይመዝናል። መራመድ የሚችሉት አጎንብሰው የመንፏቀቅ ያህል ነበር። ካሜሮን እና ሽተርን አከርካሪያቸው ላይ ከባድ ሕመም አደረባቸው። ሕይወታቸውም መከራና መዘዙን ያስተናግድ እንደነበር ሽተርን ጽፏል። እንዲያም ሆኖ በየራሳቸው ጎጆ እንዲኖሩ እና አገልጋዮችም እንዲረዷቸው ተፍቅዶላቸዋል። ኢትዮጵያውያኑ እስረኞች ግን ከአምባው በስተምሥራቅ በኩል አንድ ላይ ታጉረዋል። ቴዎድሮስ ሲበሳጭም አንድ ወይም ሁለቱ ይገደላሉ። አብዛኞቹንም በሽታ ይፈጃቸዋል።

የዝናቡ ወራት ሲያበቃ ቴዎድሮስ ሠራዊቱን አስከትሎ እንደ ፀደይ አበባ በያለበት የፈሉትን መለስተኛ አማፅያን ልክ ሊያስገባ ተነሳ። በዚያም ላይ እሮሞ እስረኞን ከፈጀ በኋላ አምባው ላይ ሰፍሮ የነበረው ከባድ የፍርሃት ድባብ ለጊዜው ገለል አለ። በዚህ ወቅትም አውሮጳውያኑ ቴዎድሮስ ከንግሥቷ የተላከውን ደብዳቤ እንዲያደርስለት ለራሳም ፈቃድ መስጠቱን አውቀዋል። በአንድ በኩል ይህ ዜና መጠነኛ ተስፋ ሲሰጣቸው በሌላ ወገን ደግሞ በርከት ያሉ የውጭ ዜጎች ወደዚህ እየመጡ የቴዎድሮስን ንዴት ማባባሳቸው ስጋት ፈጠረባቸው። ጊዜያቸውን በጎጆአቸው ዙሪያ ሲንቆራጠጡ፣ ባሻገር ያሉ አካባቢዎችን እና ሰማዩን ሲቃኙ ማሳለፍ ግድ ነበር። ከመካከላቸውም ሚሰስ ሮዘንታል ብቻ የ3 ዓመቱን ወንድ ልጇን ሄንሪን አስከትላ ረኸርም ቀሚሷን እያንጓተተች በነፃነት ትዘዋወራለች።

እሷና ልጇ ላለፉት 21 ወራት ቢጤዎቻቸው ሲታሰሩ፣ ሲሰቃዩ ችሎት ሲቀርቡ እስር ቤታቸው የንጉሡን የጦር ሰፈር እየተከተሉ ከከተማ ከተማ ሲቀየሩ እና አሁን ደግሞ መቅደላ አናት ላይ ከፍ ብለው ሲታሰሩ ሁሉ ይከተሏቸዋል። የሮዘንታል ቤተሰቦች በ1856 ዓ.ም ነው፣ በሚሲዮናዊነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት። ከኢንግላንድ በጀመረው ረዥም ጉዟቸው ሚስስ ሮዘንታል ነፍሰ ጡር ነበረች። ሔንሪ አባቱ ከመታሰሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ተወለደ። ባለቤቱ እና ልጆቹ ለንደን የሚገኙት የሽተርን ብዕር ሔንሪ ላይ አትኩሯል። «ተወዳጁ ፍጥረት የእናቱን የፍቅር ፈገግታ መረዳት ጀምሯል፤ ከቤት ወደ ቤት ሲዘዋወርም የሚመገበው

እያለቀሰ ነበር። እብዛኛውን ጊዜም ልብን የሚነካ ሰቀቀን ይታይበታል» ። አባቱ
እንደሚለው ሔንሪ ሮዘንታል ያሳለፋት አጭር አስቸጋሪ ሕይወት በዕድገቱ ላይ
የራሱን አሻራ ጥሎበት አልፏል። ከዕድሜ አቻዎቹ ጋር ሲነፃፀር በሰውነት ዕድገቱ
ብዙም ያልተለወጠ እና የማይናገር ነበር፡፤ ከሁለት ወራት በፊት በጣና ታመመ፤
አባቱ ሰንሰለቱን እንዳጠለቀ ከሚስቱ ጋር ሌሊቱን ሳይተኛ ከአሁን አሁን ተሰናበተ
በሚል ስጋት ይጠባበቃል። ልጁ ከሕመም ሲያገግም ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን
እንደሆነ ሸተርን ያውቅ ነበር።«የሳይንስ ሰዎች በሌሉበት ታላቁ ሐኪም እዳነው»

ሄንሪ አገግሞ አቅሙ መመለስ ሲጀምር ተመልከቱም፤ «ከጨካኝ ወጥመድ
እንዳመለጠች ወፍ ዘወትር እንቅስቃሴ ላይ ነበር፤ በጠባቂዎች ሳይከለከል
መሮጥ» ወጣቶቹ ኢትዮጵያውያን እስረኞች አብረውት ይጫወታሉ፡ ሳሩን
ሙጎንጎን ወይም እራፊ ጨርቆችን በመሥፋት ኳስ ሰርቶ ሜዳው ላይ መጫወት
ያስተምሩታል። መቅደላ ላይ እስረኞችም ነፃ ሳይሆኑ የሰፈሩት ማኅበረሰቦችም
ወደየመኖሪያቸው እንዲመጣ ያበረታቱታል። የራስ ዓሊ እናት የቴዎድሮስ ዋነኛ
ተቀናቃኝ እቴጌ መነን ሕፃኑን ተቀበሉት። አቡነ ሠላማም የሚያንፀባርቀው
መስቀላቸውን እና ደማቅ ልብሳቸውን እንዲመራመርበት ፈቀዱለት። ቀን ቀን
በሙቶዎች የሚቆጠሩት እስረኞች በተራራው እናት ላይ እንዲዟዟሩ
ይፈቀድላቸዋል። ማታ ማታ ግን እየተቆጠሩ መኝታ ለማግኘት ወደሚያስቸግረው
ጎጆዋቸው ይገባሉ።

እራፊ ሱቲ ከተሰቀለባቸው የሳር ከዳን ጎጆዎች ሽረሪቶች ይንጠባጠባሉ። አይጦች
በቡድን ሆነው በመምጣት የተጠቀለሉ እስከሬኖችን ይቀራመታሉ። በየሳምንቱ
በሚባል ደረጃ አጭር የቀብር ሥርዓት ይፈፀማል። ተራራው ላይ የሰፈሩትን
እስረኞች በማከማቸው አውሮጳውያኑ እስረኞች የብዙዎችን አከብሮት እና ውዴታ
አትርፈዋል። እርግጥ ነው ከመካከላ ቸው ያን ያህል በቂ የሚባል የሕክምና
ባለሙያ አልነበረም። ነገር ግን በቂ መረጃ የሚሰጥ የመድሃኒት ቅመማን
የሚጠቁም የሕክምና መጽሐፍ አላቸው፤ ሸተርን እንደሚለው ወደ 300 የሚሆኑ
የዓይን ሕሙማንን ማዳን ችለዋል፡፤ ሸተርን ራሱም ከአንድ የአየርላንድ ተወላጅ
ወዳጁ ጋር በመሆን አንድ መድኃኒት ቀምሟል። የዚህ አየርላንዳዊ የሎረንስ
ክሬንስ አባት በሀገሩ የታወቀ ቀዶ የሚጠግን ሀኪም ነበር። በ1856 ወደ
ኢትዮጵያ የመጣው ከምፅዋ ገደቢሷን የሎርድ ራሰልን ደብዳቤ ለካሜሮን
ለማድረስ ነው። ክሬንስ ለቴዎድሮስም የምንጣፍ ስጦታ አምጥቷል። ስጦታው
ቴዎድሮስን ሊያስደስት ይችላል በሚል የተመረጠ ሲሆን፤ ታዋቂው ፈረንሳዊ
አዳኝ ጁል ጌራ አንበሳ ሲገድል ሲል ያሳያል። ቴዎድሮስ ግን ፈረንጆቹ ያሰቡት
ብሎ የተረዳው በተለየ መንገድ ነው። ሰለባ የሆነው አንበሳውን በራሱ መሰለው
እና በግብፆች ሲወረር እንደሆነ አሰበው። በዚህ ክብረ ነክ ገጸ በረከት ምክንያትም
ክሬንስ ከሌሎቹ ጋር አብሮ ታሰረ። በ1857 ሐምሌ ወርም ከመቅደላ
የሚከተለውን ግሩም ማስታወሻ ጻፈ።

«ውድ እናትና አባቴ አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንደምገኝ ለማወቅ እጅግ
ጓግታችኋል። በቅድሚያ ከታሰርኩ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሆነ። 9 ኪሎ
የሚመዝነው ሰንሰለት እግሬ ላይ ታስሮ ነበር አሁን ደግሞ ቀኝ እጄም አብሮ
ተያይዟል። በየዕለቱ እንዴት ባለ የፍርሃት ስቃይ ውስጥ ማለፍ እንዳለብኝ
መገመት አትችሉም። ቀደም ሲል እንደውም ሁኔታው ከዚህ የከፋ ነበር፤ ሆኖም
አሁን ያው አዳጋች ነው። ቶም የሙቶ አለቅነት ማዕረጉን ማግኘቱን መስማቴ
አስደስቶኛል።» መቅደላ የሚገኙ በሽተኞችን ከቤተሰብ የቀሰመውን የቀዶ ጥገና
ሕክምና ጥበብ ተጠቅሞ ክሬንስ ሲያክም ካሜሮን በመገረም ይመለከተዋል።
ጥርስ ይነቅላል፤ ብርቱካን የሚያካክሉ ዕጢዎችን በጥበብ ያወጣቸዋል። እንዲያም
ሆኖ ግን አውሮጳውያኑ በፀደይ ወራት መቅደላ አፋፍ ላይ ለደረሰው የኩፍኝ
ወረርሽኝ እስከ አሁን መላ ማግኘቱ አልተሳካላቸውም። እስር ቤቶቹ ውስጥ
ያሉትን ሲያዳርስ ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ በየምሽቱ የሚከሰተው ሞት
አካባቢውን ቀውስ ውስጥ ከተተው። ውሎ አድሮ ወረርሽኙ በረድ ሲል ቀናት
ሳምንታቱ እንደተለመደው ይነጉዱ ጀመር። ሸተርን መድኃኒት ለማቅረብ በጎጆ
አካባቢ ሲንጎዳጎድ በሽተኞቹን በቀዶ ሕክምና የሚረዳው ክሬንስ ሰንሰለትም
እንቅስቃሴውን ተከትሎ ሲንሿሿ ይሰማል።

ከእስረኞቹ ግቢ ውጭ በነፃነት የሚንቀሳቀስ በየሁሉም ጎጆ የሚገባው ኳሱን
የሚያባርረው እና የሚጯጯጠው ትንሹ ሔንሪ ሮዘንታል የእነሱ መልዕክተኛ
ነበር። ከዕለታት በአንዱ ቀን አቡነ ሰላማ አቧራ እያቦነነ ሲጫወት እየተመለከቱት
እንዲህ አሉ። «ይህ ልጅ ከገነት ተጠርቷል፤ በዚህ ዓለም ብዙም አይቆይም»
አባቱ እና ሌሎቹ ጓደኞቹ ጸሎታቸውን ጨርሰው ብዙም ሳይቆዩ ሔንሪ በቆመበት
ድርቅ አለና፤ መተንፈስ ተስኖት ይታገል ጀመር። አለቀሰ። ከጥቂት ቀናት በኋላ
ሚሲዮናውያኑ ባልታሰረው ግራ እጃቸው ጉድጓድ ምሰው ቀበሩት። በዚያን
ሰሞን ነበር በጠባቂዎቹ እና ጎብኝዎቹ ዘንድ አንድ ቃል በያለበት መሰማት
የጀመረችው። ለጤናቸው ባደረባቸው ስጋት ምክንያት በመላው ተራራ ላይ
የሚገኘው ማሕበረሰብ ሁሉ «ሀኪም! ሀኪም!» ማለት ጀመረ።

በስተምዕራብ በኩል ከወደ ሱዳን አቅጣጫ አንድ ዶ/ር ወደ ኢትዮጵያ መጣ።
የማዳኑ ዜናም ከመንደር መንደር ፣ ከሸለቆ ወደ ሸለቆ ተዛመተ። ያንን ሁሉ
አቋርጦም መቅደላ እናት ላይ ደረሰ።

«በነጠብጣብ የጀመረው ወንዝ ሆነ። የራሴ የምለው ነገርም ሆነ አረፍት አጣሁ።» በማለት ዶ/ር ብላንክ ጽፏል። ሦስቱ ልዑካን ቴዎድሮስ ጋር ለመድረስ ሲጣደፉ የዶ/ር ብላንክ ፈላጊዎች በረከቱ። ታማሚዎችን ይፈልግ የነበረው ሀኪም አሁን ተፈላጊ ሆነ። በርካቶች በቆዳ ችግር እና በዓይን ሕመም ይሰቃያሉ። እሱ ሊያድናቸው ያልቻለ ሌሎች ታማሚዎችም ነበሩ። ሆኖም ግን እንግሊዛዊው ዶ/ር ተዓምሩን እስኪሰራላቸው ተስፋ ሳይቆርጡ ይጠብቁታል።

«አቤት፣ አቤት ሀኪም !» ልዑካኑ ባለፉበት በስተምስራቅ ከዚያም በስተደቡብ ወደ ጣና ሐይቅ አቅጣጫ በሄዱበት ሁሉ ሕዝቡ ተጠራራ። በየዕለቱ በርካታ ታማሚዎች መንቀሳቀስ የማይቻሉ፣ ዕጢ ያለባቸው ፣ የጠና ጨብጥ እና ፣ የሚጥል በሽታ፣ በዝሆኔ የተነረተ ቁርጭምጭሚት፣ ሥጋ ደዌ የጎመደው ጣት፣ እንቅርት፣ በተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና በሌላ ምክንያት የተጎዱ ሁሉ መንገዳቸውን ያጣብቡ ነበር።

እያደር ዶ/ር ብላንክ ከድንኳኑ መውጣት ሁሉ አቃተው። ከወጣም ሀኪም ፈላጊዎች ይከቡታል። ከዚያም ኢትዮጵያውያኑ ጠባቂዎች አቁመው ህመምተኞቹን ገለል ያደርጉለት ጀመር። ቀጠሉና ጠባቂዎች ራሳቸው ቤተሰቦቻቸው እና ጓደኞቻቸውን ወደ ዶክተሩ መላክ ሲጀምሩ የዶ/ር ብላንክ ድንኳን ዳግም ይከበብ ጀመር። ቀስበቀስ የሚከባቸው ሰው ገለል አለ። ከዚያም ልዑካኑ ብቻቸውን ሆኑ። ያልተለመደ ጸጥታ በአካባቢው ሰፈነ። ሰብሉ እየሳሳ ከብቶችም ተበታትነው ይታዩ ጀመር። ወደ ጣና ሐይቅ ሲወርዱም ዳሞት ውስጥ ሁሉም ነገር ወድሞ ተመለከቱ።

ጎጆዎች እና ናቸው።መንገዶች ባዶ ሆነው መሬቱም ተቃጥሏል ። በቀድሞዋ መንደር ፍርስራሾች ውስጥ አልፎ አልፎ ገሚሱ፣የተራበ፣ገሚሱ እርቃኑን የቀረ ገበሬ አመድ በሆነው አባቶቹ መሬት ላይ ቤት ለመቀለስ ደፋ ቀና ይላል። ወደ ቴዎድሮስ የጦር ሰፈር እየተቃረቡ ነው። በ1858 የጥር ወር ኢጋማሽ ላይ የብሪታንያ ልዑካኑ እና 1,400 ጓዝ ተሸካሚዎቻቸው ቃጠሎው ገና ካልበረደ ባት፣ ሰውም ሆነ አውሬ ከሌለባት እንዷት ሥፍራ ደረሱ። በአንዱ ቀን ከቀትር በኋላ ማረፊያቸውን አመቻችተው ፀጥ ባሉበት ከሩቅ አንድ መንደር በመመልከቻቸው የግርምታ ድምጽ አሰሙ። ራሳም ከፍ ወዳለው ሥፍራ ወጥቶ አሻግሮ አማተረ። በሺዎች የሚገመቱ ድንኳኖችን ተመለከተ። ነጭ ድንኳን በጥቋቁሮቹ መካከል ጎልቶ ይታያል። መንገድ መሪው ያ የቴዎድሮስ መሆኑን አመላከታቸው።





ራሳም እንቅልፍ እንቅልፍ የሚያስኘውን ኤደን የሚገኘውን ቢሮውን ትቶ ከወጣ 18 ወራት አለፉ። ድካም ብሎታል። የተግባር ሰው ያልሆነን ሰው መልስ በመጠበቅ ታክቷል። እንደያም ሆኖ እጅግ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው የተልዕኮው ዋና ክፍል ገና ከፊቱ እንደሚጠበቀው ያውቃል።

እያንዳንዱ አቀራረቡም ሆነች በሚሰነዝረው አስተያየት ላይ የሚፈጠር ትንሽ ስህተት ተልዕኮውን ማስናከል ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን በርካታ አውሮፓውያን ሕይወት ለአደጋ ያጋልጣል።

ፕላውደን ዋሸንት ተሟዋቾች እና ጀኔራሎች ተቀበሉት፣ ካሜሮን ደግሞ ለክብሩ 12 ጊዜ መድፍ ተተኩሶለት ነበር። ቴዎድሮስ ለሶስተኛው የብሪታንያ ልዑክ ያደረገው አቀባበል ረዘም ያለ ነው። በ1858 ጥር 20 ቀን በጠዋቱ ወደ ቴዎድሮስ የጦር ሰፈር ሲቃረቡ ራሳም እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በማይታይ እጅ በሚደረግ ቁጥጥር በሥርዓት መንቀሳቀሱን አስተዋለ።በመጀመሪያ የቴዎድሮስን ሰላምታ የያዘ መልእክተኛ መጣ። «ለጤናዎ እንዴት ነዎት? አብረዎት የመጡትስ ለጤናቸው ደህና ናቸው?›› ። ከሰዓታት በኋላ ሌሎች ሁለት መልዕክተኞች መጡና ተመሳሳይ ጥያቄያቸውን አቀረቡ ባለስልጣናት ወደ ሰፈሩ ሲያደርሷቸው መጡ። መንገዱ በጦር መሪዎች እና መኮንኖች ተሞልቷል፤ እያንዳንዳቸው እንደ ደረጃቸው ለብሰዋል። በየተራ እየመጡ «ለጤናዎ እንዴት ነዎት?›› ‹‹አብረዎት ያሉት እንዴት ናቸው?›› ይላሉ።

ከንጉሣዊው የጦር ሰፈር በሶስት ኪሎ ሜትር ርቀት ገደማ በሚገኘው ጎጆ ቸው ውስጥ የውጭ ዜጎቹ ልብሳቸውን ሲቀይሩ ይታያሉ። ራሳም ሰማያዊ የዲፕሎማት የደንብ ልብሱን ለበሰ፣ ዶ/ር ብላንክ የሕንድ የህክምና ቡድን የሚያደርገውን የሀኪም መለያ ለብሷል፤ ሌፍተናንት ፕሪዶ ደግሞ የቦምቤ የባሕር ኃይል ልብሱን ለወጠ።

በዕኩለ ቀኑ ሙቀት ከድንኳናቸው ወጥተው መንገድ ሲጀምሩ ከፊት ለፊታቸው ሁለት ኮረብታዎችን ተመለከቱ። በአንደኛው ላይ ጠመንጃ እና ጦር ያየዙ ሰዎች አሉ። ሁሉም የለበሱት ነጩን ሸማ ነው። የያዙት መሣሪያ በጸሐይዋ ብርሃን ያንጸባርቃል። በሌላኛው ኮረብታ ላይ ጥቋቁር ድንኳኞች እና ነጩ የቴዎድሮስ ድንኳን ይታያሉ። በሁለቱ ኮረብታዎች መካከል በርካታ መደበኛ ወታደሮች ሰፍረዋል። የፈረሶቹ ጭንቅላት የተጌጠበት ብርማ ልጓም ያንጸባርቃል። የጋሻቢዎቻቸው ጋሻ እና አምባራቸው ደምቆ ይታያል። ራሳም እና ብላንክ መደበኛውን ጦር እስከ 10,000 እንደሚደርስ ገምተዋል።

ከሠልፉ ራቅብሎም ከፊት ለፊታቸው ኢትዮጵያውያን ባለሥልጣናት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ እንግዳ እና በአቶ ሳሙኤል እየተመሩ ወደ እነሱ መጡ። ሁለቱ ወገኖች ተቀራረቡ። መነጋገር በሚችሉበት ርቀት ላይ ሲደርሱ ሁሉም ባሉበት ቆሙ። ራስ እንግዳ፤ « ግርማዊነታቸው ለጤናዎ እንዴት ነዎት? ጋደኞችዎስ እንዴት ናቸው? ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? ሲሉ ጠይቀዋል » በማለት ሰላምታ አቀረቡ። ከዚያም ለራሳም በቅሎ አቀረቡ። በቅሎዋ በተጌጠ ኮርቻና ልብስ ተውባለች። በንጉሡ ስም ከዚህ የበለጠ ነገር መስጠት ባለመቻላቸው ይቅርታ ጠየቁ።

የንጉሡ ድንኳን ካለበት ኮረብታ ስር ደረሱ። ራስ እንግዳ ከበቅሎ እንዲወርዱ አዘዙ እና ተይ ጨርቅ ወደ ተነጠፈበት ድንኳን መሯቸው።ከዚያም እንዲቀመጡ ጋበዟቸው። በዚህ ጊዜ ራሳም ፤«የለም የሀገሪቱ ሚኒስትር ቆሞ እኛ ልንቀመጥ አንችልም» አለ።

‹‹ ኧረ በንጉሥ ቆሙ በሉ፣ ደከሚችኋል፤ በዚያም ላይ እንግዶቻችን ናችሁ» አሉ ራስ እንግዳ በአርጋታ። ሲቀመጡም ራሳም ስለደከማቸው ሳይሆን የእሳቸውን ትዕዛዝ በማክበር መሆኑን ገልጾ፤ ራስ እንግዳ ትተዋቸው ወጡ። አሥር ላም፤ አሥር በግ፤ እንዲሁም ምግብ እና ጥቂት ጥቂት እንሥራ ጠንካራ ጠጅ መጣላቸው ። የጠጁ መዓዛ ብቻ እንዲጠጡት ይጋብዛል። ተጎነጩለት። አንድ ሰዓት አለፈ። ሁለተኛውም ተደገመ። ከሰዓት በኋላ ሲጋመስ በአረብኛ እና በአማርኛ ተጽፎ ንጉሣዊ ማሕተም ያለበት ደብዳቤ መጣላቸው።

‹‹ በስመ አብ ወወልድ ወመንፍ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ምስጋናለዘለዓለም ለእርሱ ይሁን አሜን ። ከነገሥታት ንጉሥ ሱልጣን ቴዎድሮስ የእኛን ወዳጅነት ለመሻት ከጠየቅከው ከተወዳድከው ሆርሙዝድ ራሳም በእግዚአብሔር ኃይል ይድረስ። መኖሪያ እና እረፍት ቅድሚያ ተሰጥቶ ንግግራችን በሚቀጥለው ቀን መሆን ነበረበት። ሆኖም ባለንበት ተወስነን ያለንን እየተመገብን የእናንተን መምጣት ስንጠባበቅ ነበር። ወታደሮች ተርበዋል፤ አልታዘዝም ብለዋል። በዚህም ምክንያት ሰብሰባው ለዛሬ ተወስኗል። እናም ነገ መንገዳችንን እንጀምራለን። ስለዚህ አሁን ወደእኔ ኑ» ።

ድንኳናቸውን ለቀው ሲወጡ አቶ ሳሙኤል ‹‹ ቁሙ ንጉሡ የትኛውንም የውጭ ዜጋ ከነመሣሪያው ተቀብለው አያነጋግሩም» ሲሉ አ ዘዙ። ራሳም፤ የደንብ ልብሱ ይህ ከጎደለ ሙሉ አይሆንም በማለት አስረዳ። ወደ ኮረብታው እናት ሊቃረቡ ጠብመንጃ ያነገቱት ሰልፈኞች ቀጥራቸው በእጥፍ ጨመረ። አንድ የጦር መኮንን ወደ ራሳም ጢጋ ብሎ፤ ግርማዊነታቸው ለመሆኑ ለጤናዎ እንዴት ነዎት በማለት ጠይቀዋል» አለው።



ጠብመንጃ አንጋቾች መሳሪያቸውን ወደ ላይ አቅንተው ተኩሱ። ደጋገሙት። ሦስት የውጭ ዜጎች አቶ ሳሙኤልን ተከትለው በመከከላቸው አለፉ።ተኩሱ ልክ ድንኳን ውስጥ ሲገቡ ቆመ። ሞቅ ያለ ነው። በሐሩ መጋረጃ ላይ ብርሃን አርፎበታል። ቴዎድሮስ በግርማ ቆሞ ብሏል። በግራ እና በቀኝ ሚኒስትሮቹ ቆመዋል። ጠባቂው በሁለት እጆቹ ባለመንታ አፈሙዝ ሽጉጦችን ደቅኖ ቆሟል። ንጉሡ ነገሥቱ ተራ ሸማ ለብሷል። ራሱንም ተከናንቦ አይኑ ብቻ በከፊል ይታያል።

‹‹ ለግርማዊነትዎ ይህን ከተከበሩት የኢንግላንድ ንግሥት የተላከ ለእርሶ ያላቸውን የወዳጅነት መንፈስ የሚገልጽ ደብዳቤ ሳቀርብ ክብር ይሰማኛል» አለ ራሳም።

‹‹ በደስታ ተቀብያለሁ። እናንተን በማየቴም ተደስቻለሁ» የሚለውን ምላሽ ቴዎድሮስ ለመስጠት አፉን ሲያንቀሳቅስ ሸማው ተገለጠ። ደብዳቤውን ሳያነብ ከጎኑ አስቀመጠው፤ ልዑካኑን እንዲቀመጡ ጋበዛቸው። ራሳምም ብላክን እና ፕሪዶን አስተዋወቀ።

ቴዎድሮስ መናገር ጀመረ። በካሜሮን እና ሽተርን ላይ ያደረበትን ቅሬታም ዘረዘረ። እንዴት በክብር እንዳስተናገዳቸው፤ በተቃራኒው እነሱ ደግሞ እንደከዱት ገለጸ። የራሱን ሕዝብም ተቸ። ሰላም ሊሰጣቸው እንደሞከረ፤የሰለጠኑ ሰዎች ወደሚኖሩበት የጉሮ ሥርዓት ሊያሻግራቸው እንደጣረ፤ ለልጆቻቸው ተስፋ ለማቆየት እንደሞከረ ገለጸላቸው።

ራሳም የተወሰኑ አስተያየቶችን ከመስጠት በቀር ጸጥ ብሎ አደመጠ። ስለ አባ ሰላማ፤ ካሜሮንም ሆነ ሽተርን በተመለከተ ሲናገር እርምት ለመስጠት አልሞከረም እንደዩም ሆኖ ዝምታ ጥርጣሬን ከመፍጠር ባሻገር የድክመት ምልከት ተደርጎ ለወሰድ እንደሚችል ተረድቷል። ምን ማለት ይችላል። የታሳሪዎቹን ጥፋትና ስህተት በማረጋገጥ የእስራት ጊዜያቸውን ማራዘም የማይታሰብ ነው። ስህተታቸውን በማስተካከልም ቴዎድሮስን በኢፍትሓዊነት ጭካኔም ሊከስ አይችልም። ከሁሉም የቴዎድሮስን ስጋቶች መሰረት በማድረግ በአከባቢው ያለውን ችግር በመዘርዘር ሐሳቡን እንዲህ አቀረበ።

‹‹ በግርማዊነትዎ ቦታ የሚገኝ ንጉሥ እጅግም ለነገሮች ስሱ መሆን አያምርበትም ይልቁንም ታጋሽና ጥንቁቅ መሆን ይኖርበታል። ግለሰቦች ናቸው፤ ግላዊ ጉዳያቸውን መከታተል ያለባቸው። ነገሥታት ግን የሚሊዮኖችን ጉዳይ ነው መመልከት የሚኖርባቸው እናም በሺዎች ለሚገመቱ ከባድ ወንጀለኖችን ለፈጸሙ ሁሉ ምሕረት ያደርጋል። ግርማዊነትዎ ሉዓላዊ አባት አይደለም እንዴ? መልካም አባት ለልጆቹ ታጋሽ ሆኖ የትኛው ትክክል እንደሆን ማስተማር የለበትም? የንግሥታችንን ደብዳቤ ካነበቡ በኋላ ግርማዊነትዎ እኔ የተላኩበትን

ወዳጃዊ ተልዕኮ በመቀበል የበፊቱን ረስተው ከኢንግላንድ ጋር መልካም ወዳጅነት እንደሚመሠርቱ እተማመናለሁ፤ እኔም እንደንግሥቷ አገልጋይ ይህን ለማሳካት የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ»።

የቴዎድሮስ ፈገግታ ብልጭ ብሎ እንደገና ድርግም አለ። የንግግር ምልልሱ ከማብቃቱ በፊት ራሳም አንድ ነገር ለመነ።

‹‹ እኔና ባልደረቦቼ እንግዶች መሆናችን አባክዎ ያስተውሉ። የሀገሪቱን ወግም ሆነ የችሎቱን ስርዓት አናውቅም። ስለዚህም በቆይታችን ባለማወቅ ስህተት ብንፈጽም እንዳላየ ግርማዊነትዎ ይለፍን።

‹‹ እሺ እሺ በሚገባ›› በማለት ቴዎድሮስ ሳቀ። የሳቁ ውበትም በመካከላቸው ሰፍኖ የነበረውን ውጥረት አረገበው።›



## ምዕራፍ ሠላሳ አራት

በዚች ዕለት ምሽት ቴዎድሮስ የተሰማው ደስታ እንቅልፍ ነሳው። ሲነጋጋ ጸሐፊውን አለቃ እንግዳን አስጠራ። በትሕትና የተሞላው የዚያን ጠዋቱ ደብዳቤ ምናልባት ሐሰት ይሆናል የሚያስብል ነው፡፤ ሆኖም ግን እውነት ሆነ በርቀት ለሚገኙ የተከበሩ ንግሥት የቀረበ ውዳሴ፤ ‹‹ የእግዚአብሄር ፍጡር እና ባሪያ ከዳዊት ልጅ ሰለሞን ነገድ የነገሥታት ንጉሥ የተላከው ይህ ደብዳቤ እግዚአብሔር ከወንዶች መርጦ ንግሥት ወደዳረገዎት ጓደኝነት እና ሃይማኖት ወዳድ እና የተጨቆኑ እና የድሆች ተሚጋች ቪክቶሪያ ይድረስ።

እንደነገሩኝ ሆርዝሙድ ራሳምን በካሜሮን ምክንያት ስጋት አድሮብዎት ወደእኔልከዋል እንኳን እርስዎ የባሪያዎ ባሪያስ ቢጽፍልኝ እንዴት እምቢ ማለት ይቻለኛል፤ ታላቅ ከሆኑት ከእርስዎ ጋር ደብዳቤ መለዋወጥ አይገባኝም። ነገር ግን ታላቅ ሰው እና ባሕር አንድ ናቸው። ማንኛውም ነገር መሸከም ይችላሉ። ስለ እግዚአብሔር ሲሉ እኔን የማልረባውን ኢትዮጵያዊ ታገሱኝ። ሰዎቹን በማሰሬ የተዋረድኩት እና የተጋለጥኩት እኔ ነኝ። እኔ የእሥራኤላዊቱ ልጅ በኦሮሞ አገዛዝ ምክንያት ድሀ ሆንኩ፤ የእሥራኤል ልጆች ምንም አልነበራቸውም ማከከና መለመን ብቻ ተረፋቸው ፤ ሆኖም እግዚአብሔር ኃይል ሰጠኝ እና የአባቴን ግዛት አስከበርኩ ። የእኛ የኢትዮጵያውያንን አለማወቅ እና እውርነት ሰምተው ይሆናል። ተገቢ መስሎኝ በግልጽ የጣፈኩት እስነዋሪ ሆኖ ቢያገኙት አይዘኑብኝ ባይሆን እግዚአብሔር የመረጥዎት እና የተከፈቱ ዓይኖች ያደለዎት ንግሥት ይምከሩኝ»።

ዓለም ከተፈጠረ ከ7358 ዓመት በኋላ በጥር 22 ቀን ጌታችን ከተወለደ ከ1858 ዓመት በኋላ ተጻፈ።

በዚያን ቀን ጠዋት ትንሽ ረፈድ ሲል ወደ ራሳምና ወደሌሎች መልእክት ተላከ። ቴዎድሮስ ከድንኳኑ ውጪ ቆሞ አገኙት። ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጣቸው። ውስጥ የነበሩትን እና ባለሥልጣናቱን ዞር እንዲሉ አዘዘ« ወዳጄ ስለሆኑት ስለንግሥቷ እና በሚስተር ካሜሮን ምክንያት ችግር ላገኛችሁ ለእናንተም ስል፤ ለአውሮፓውያን እስረኞች ሁሉ ምሕረት አደርጋለሁ»። እንዲፈቱም ወድያው ትዕዛዝ ሰጠ። ከመቅደላ ተፈተውም በነጻነት ከሀገር እንዲወጡ ለራሳም እንደሰጡ ነው የወሰነው። 18 ወራት የፈጀው የራሳም ድጅ ጥናት በመጨረሻም ከ24 ሰዓታት ባነሰ ጊዜ ፍሬ አፈራ። ቅድመ ሁኔታ አልተነሳም፤ሌላው ቀርቶ ብዙ የተደከመበት የኤምባሲ ነገርም አልተጠቀሰም።

በዚያኑ ዕለት ከቀትር በኋላ ራሳም ይዞ የመጣውን ስጦታ ለቴዎድሪስ አበረከተ። ንጉሡ ስጦታዎቹን እየከፈተ ሲመለከት ልዑካኑ ከድንኳን ውጪ ተቀምጠዋል። ራሳም ቴዎድሮስ የጦር መሣሪያ ላልሆኑ ስጦታዎች የሚኖረውን ስሜት

አያውቅም። የናፖሊዮን 3ኛን ሀር አሽጉን በከፊል ከፍቶ እንደተመለከተው ለሴቶቹ ላከላቸው ። ካሜሮን ያመጣለትን አነስተኛ ኦርጋን ተመልክቶ‹‹ እንዲህ ያለውን ትርጉም አልባ ነገር አውሮውያን ለእኔ መላካቸው ምን ጥቅም አለው›› ብሎት ነበር።

አሁን ግን ቴዎድሮስ በአድናቆት ነው የተቀበለው። «ይህን ሁሉ ከባድ እቃ ተሸክማችሁ ለገጠማችሁ ችግር አዝናለሁ»። እያንዳንዷን ስጦታ በጥንቃቄ እየተመለከተ ከሳሩ ላይ ደረደራቸው። ራሳም አንድ መስታወት አነሳ እና ለንገሥትዎም አለው። ቴዎድሮም በረዥሙ ተነፈሰና «መልካሟ ንግሥቴ ከሞተች ወዲህ ኢክርስቲያናዊ እና የተዛባ ሕይወት እየገፋሁ እገኛለሁ» በማለት ስለጥሩነሽ ምንም ሳያነሳ ስጦታው ለሚወዳት ዕቁባቱ ለየተመኙ እንደሚላክ ለራሳም ነገረው።



## ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

በሚቀጥለው ቀን በማለዳ 45 ሺ የሚሆነው የቴዎድሮስ ሠራዊት ጦር እና ጠብመንጃውን እንግቦ ሽማውን በአንድ ወገን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ወደ ሰሜን ለመጓዝ ተዘጋጀ። ትተውት የሚሄዱትን ጊዜያዊ የሳር ጎጆ እያፈራረሱ እሳት ለቀቁበት። ሠራዊቱን ተከትሎም በሺህ የሚገመተው ዕቃ ጫኝ፣ በቅሎ አስጋሪ፣ ውኃ ቀጂ፣ ሽቀጥ አቅራቢ፣ ምግብ አብሳይ እና ዕቁባቶች ይጓዛሉ።

ወሎ እና ሸዋ፣ ስሜን እና ወገራ ከቴዎድሮስ ቁጥጥር ውጭ ሆናዋል። ተድላ ጓሉ ሸፍቶ ጎጃምን በግዛቱ ስር አውሏል። ትግራይን ደግሞ ዋግ ሹም ጎበዜ ይዟል። ሰሜን ጎንደርን ጢሶ ጎበዜ ተቆጣጥሯል፤ በወቅቱ የወጣው መረጃ የንጉሡ ግዛት በጌምድር ብቻ እንደነበር ያመለክታል። ወታደሮቹ እየከዱ በመሄዳቸው የንጉሡ ኃይል ተዳክሟል። በግዛቱ አከባቢ ግን አሁንም የበላይነቱ እንደተጠበቀ ነው ። «ጉዞው ባማረ ሥርዓት የሚከናወን በመሆኑ ከንጉሡ ሠራዊት ጋር መጓዙ ያስደስታል» ብሏል ራሳም። እንደ እርሱ ምስክርነት ቴዎድሮስ በደካማ አስተዳደር እና በጭካኔ ቢኮነንም የሚደሰትባቸው በርካታ ነገሮች መኖራቸውን አልሸሸገም።

ሠራዊቱ ጠባብ ሸለቆ ውስጥ ሲደርስ ሥርዓቱ ፈረሰ። ሁሉም ቀዳሚ ለመሆን ይጣደፍ ገባ። ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑ እግሮች የተረባረቡበት ምንጭም ወደ ሀይቅነት ተለወጠ። የበልግ ዝናም ጀምሯል። እያለፉ የሄዱባቸው መንደሮች አብዛኞቹ ነዋሪ አልባ ነበሩ። የመንደሩ ነዋሪዎች የወታደሮችን መምጣት ሰምተው አስቀድመው አከባቢውን ለቀዋል። እግረኛው ሠራዊት በሰልፍ እየተጓዘም መንገደርተኛው በማሳው ላይ ዘርቶት የነበረውን ሰብል ሰብል በጎራዴ ቀነጣጠሰው።

በአንድ ቀን ጠዋት ቴዎድሮስ የብብሪታንያ ልዑካን ወደ እርሱ እንዲመጡ አስጠራ። ለዕለቱ ጉዞ እየተዘጋጁ ቆይተዋል።« ሌሊቱ እንዴት ነበር? ጤናችሁስ እንዴት ነው? አብረውህ ያሉትስ? ምሽቱን እንዴት አሳለፉ? ደህና ናችሁ? በእርግጥ ደህና ናችሁ ወይ?›› ብሎ ከጠየቃቸው በኋላ ለእነሱ ምቾት ሲባል ምስቱ ልዑካን ከእርሱ ጋር እንደሄዱ ሐሳብ አቀረበ» ።

ሠራዊቱን ከበስተኋላው በመተው ቴዎድሮስ ወደፊት ገሰገሰ። ራሳም የሰጠውን ሸሚዝ ለብሷል። ተከታታዮቹ ጋሻ፣ ጠብ መንጃ እና ቴሌስኮፕ ይዘው በቅርብ ርቀት ይከተላሉ። ከቴዎድሮስ ተከታዮች ቀጥሎም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ እንግዳ ከዚያም ራሳም ብላንከ እና ፕሪዶ ተራቸውን ይዘው ይጓዛሉ። ሌሎች ሚኒስትሮችም በተዋረድ ከኋላ ሲከተሉ ከእነርሱ ጀርባ የሚተመው ሠራዊት ከርቀት ሲታይ የጭንቅላት ወንዝ ይመስላል።

ከንጉሡ ጋር የሚጓዘው ቡድን ሞቃታማው ዕለት ከቀትር በፊት ሲጋመስ ከጉዞው ቆም አለ። ሰፊ ሜዳ ላይ ነበሩ። አንድ መልእክተኛ በአቅራቢያው አማጺ ኃይል መኖሩን ነገረ። ከዚያም ተዋጊውን ሠራዊት ወደ አቅጣጫው እየመራ ወሰዶ፤ ወዲው በሜካው አካባቢ ያለው አየር በጥቁር ጭስ ተሞላ። ወደፊት መግፋቱን ቀጠለ፣ እየተሰበሰበ ወይተለያየ አከባቢ ይበተናል። ዙሪያ ገባውን አጥለቅልቆ የጀመረውን እንቅስቃሴ የሚገታው አልነበረም። ሁኔታውን የሚግጡትን በርካታ ሚዳቋዎች በጠበጣቸው ፤ እንስሳቱ ጭንቅላታቸውን አድርገው ዙሪያውን ከማተሩ በኋላ ወደ ሜዳው ሸሹ። ሆኖም ሽሽታቸው ተዛዥነታቸውንና አልተሳካም ከዚያም ሰዎች ነበሩ። በዛፎች መካከል ለመሸሽግ ሞከሩ፤ እንዲያም ሆኖ የሚሸሽጋቸው አላገኙም። የሰዎቹ ሰልፍ ማለቂያ አልነበረውም። ከከበባው ነጻ መውጣት ስላልቻሉም ተደናግጠው በሠራዊቱ መካከል ወዲህ እና ወዲያ ይራራጡ ጀመር ። በመጨረሻም ተዳክመው ሞቱ። የሞቱት ሚዳቋዎች ተወስደው ከቴዎድሮስ እግር ስር ተዘረጉ፤ ቴዎድሮ ሥጋቸውን ለራሳም ላኩ

በቀጣዩ ቀን ብዙም ሳይጓዙ አባይ ወንዝ ደረሱ።

## ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

ከዕለታት በአንዱ ከቀትር በኋላ ቴዎድሮስ ራሳምን ጠራው ፣ ቴዎድሮስ ከቤል እና ፕላውደን ጋር ያደርግ እንደነበረው ስለዓለም ጉዳዮች አወሩ። ንጉሡ በተለይ ስለተለያዩ የጦርነት ምሥጢሮች ለማወቅ ይጓጓ ነበር። በቅርቡ ስለተቋጨው የዩናይትድ ስቴትስ የእርስ በርስ ጦርነት፤ ስለቀጠለው ብሪታንያ እሽንቲ ላይ ስለወሰደችው ርምጃ ተጨዋወቱ። ከዚያም ቴዎድሮስ ስለሚወደው ስለክሬሚያ ጦርነት ያወጉ ጀመር።

‹‹ ብሪታኒያ ዛር ኒኮላስን ገደለችው››

‹‹ በፍጹም›› መለሰ ራሳም፤ ተሸናፊ ሰላም እንዲወርድ መጠየቁ የተለመደ ነው››

‹‹ እንዲህ ላሉ ጦርነቶች የሚከፍለው ማን ነው?›› ቴዎድሮስ መጠየቁን

እንዲያም ሆኖ እስረኞቹ ከተለቀቁ በኋላ የብሪታንያ መንግሥት ከእሱ ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር የሚኖረው ፍላጎት ሊያበቃ እንደሚችል ግን ራሳም ለመገ[ን]
አልደፈረም።

«የኢትዮጵያን ዘውድ ከተቀዳጀሁ ጀምሮ ይህ እንዲሆን አስብ ነበር። ዳሩ ግን ሚስተር ካሜሮን ሁሉንም ነገር አበላሸው» በማለትም ስሜቱን አጋለው። በቀጣ[ዩ] ቀንም ውይይታቸው ቀጠለ። በአንድ ወቅት የሀገሩ ሰዎችን ችሎታ እና ባህል የሚያሳይ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ለንግሥቲቷ እንዲላክ ትእዛዝ ሰጥቶ እንደነበር አሜዉተው ። በእርግጥ ይህ በእንግሊዞች ፊት ጥቅም የለውም። ራሳምና ሌሎች ጓደኞቹ ከጣና ሃይቅ ዳርቻ ወዳለችው ቆራጣ እንደሚሄዱ. በዚያም ወደ ሀገራቸው ለመጓዝ ታሳሪዎቹ እስኪመጡ መጠበቅ እንደሚኖርባቸው ነገቻራው። እሱ ግን ማቆሚያ ወደሌለው አማጽያንን የማጥፋት ዘመቻው መግስገሱን ይቀጥላል።

ከመለያየታቸው በፊት ቴዎድሮስ ለመጨረሻ ጊዜ ራሳምን አስጠራው። ከመጣበት ጊዜ አንስቶ መልካም ነገሮች እየተሳኩት የሄደው ራሳም ከቴዎድሮስ ጋር የሚኖረውን እንዲህ ያለውን ጊዜ ይወደው ጀምሯል። ቴዎድሮስ ሁለት ጆንያ መሬት ላይ ተራርቆ እንዲነጠፍ አዘዘ። በአንደኛው ላይ ንጉሡ፣ በሌላኛው ራሳም ፣ብላንክ እና ፕሪዶ ተቀመጡ ። ቴዎድሮስ በድጋሚ ለእንግሊዝ ያለውን ፍቅር እና ወዳጅነት መመስረት እንደሚፈልግ አጽንኦት በመስጠት ገለጸ። ከልጅነቱ ጀምሮ የተሳካለት የጦርሰው እንደነበር ነገራቸው። በቱርኮች ተይዞ የነበረውን ምዕራባዊ አከባቢ ነጻ አድርጎ ወደሰዳን እንደገፋቸው ፣ ፈረሶች ስለሁ ከመድፋቸው ጀርባ ባይሸሽጉ ኖሮም ድል ያደርጋቸው እንደነበር ዘረዘረላቸው።

‹‹ እናንተ ለእኔ ልክ እንደ ወንድም ናችሁ›› አላቸው ድንገት ከዚያም ሚሲዮናውያኑ የሰነዘሩብትን በደል በድጋሚ አስተወሰ። ሮዘንታል ስለጻፈው ድብዳቤ ነገራቸው።

‹‹ በደብዳቤው ፣ የዱር አውሬዎች ንጉሥ አለኝ፣ ታውቁታላችሁ ? ጠየቀ።ራሳም ፈጠን ብሎ እንደማያውቁት ተናገረ።

ቴዎድሮስ እጁን ከመሬት ጥቂት ከፍ አድርጎ ዘርጋ እና ‹‹ የዱር አውሬዎች ንጉሥ ያለኝ ሰው ከዚህች በላይ እንኳን ከፍ ያለ አይደለም» ሲል፣ አስተርጓሚ አቶ ሳሙኤል «አይደለም ግርማዊነትዎ እጅዎን ጥቂት ከፍ ያደርጉት» አሉ። ቴዎድሮስም ጥቂት ከፍ አደረገ።

‹‹ በድጋሚ ትንሽ ከፍ ግርማዊነትዎ» ጥቂት ከፍ አደረገ ።

‹‹ ትንሽ ከፍ››



‹‹ አቶ ሳሙኤል ከዚህ በላይ እጄን ከፍ ማድረግ አልችልም። ራሳም ፣ ከዚህ በላይ ከፍ እንደማይል አረጋግጥልሀለሁ» ። ወዲያው ስሜቱ ድፍርስ አለ። ራሳም ያጅን ቅጽበት ያስታወሳል።

‹‹ አንዳች የከፋ ጥፋት ሊከተል ይችላል ብዬ ፈራሁ። ፊቱ ድርቅ ብሎ እጁ ይንቀጠቀጥ ጀመር» ። ከዚያም ሊያረጋጋው ሞከረ። «ታላቅ ሉዓላዊ የሆኑት ግርማዊነትዎ ተራ ቁሶች በተናገሩት ለምን እንዲህ ይበሳጫሉ?» ።

ቴዎድሮስ ፈገግ አለ፤ «ስላለፈው ግድ የለኝም የሚያሳስብኝ የእናንተ የንግሥታችሁ ወዳጅነት ነው» ።

ጋርለኛ ዐሐይ ነበር። ቴዎድሮስ በጨዋታው በመመሰጥ ጥላ እንኳ እንዲዘረጋለት አልጠየቀም። እየገረረ በሄደው ሙቀት ለሁለት ሰዓት ያህል ተቀምጠዋል። ቴዎድሮስ በ1848 ዓ.ም ፕላወደን ያቀረበለትን ውል አስታወሰ። ስምምነቱ ከራስ አሊ ጋር ነበር የተደረሰው እናም ፕላውደን ቴዎድሮስን ጎንደር ላይ የብሪታንያን በንደት ዓላማ መትከል ይቻል እንደሆነ ጠየቀው። ‹‹ ምን አልከ ? ለመሆኑ እንደ ራስ አሊ ገልተ ባሪ ያ መሰልኩህ እንዴ ፣ ከእኔ ጋር እንዲህ ለመነጋገር የደፈርከው? ለመሆኑ የማንም መደዴ ባሪያ ከውጭ ሃገራት ጋር እንዲህ ያለ ስምምነት ማድረግ ይችላል?!» ሲል ነበር ያኔ ፕላውዴንን የጠየቀው።

አሁን ግን ቴዎድሮስ አዲስ ውል ራሳምን ጠየቀው። ራሳም ይህን ለማድረግ ሥልጣን እንደሌለው ገለጸ። ‹‹ ወደ እንግላንድ ስመለስ ግርማዊነትዎ ምን ያህል ይህን ለማድረግ ዝግጁ እንደሆኑ ለንግሥቲቷ አቀርባለሁ። ይህን ከግምት በማስገባትም ግርማዊነትዎ ያቀረቡት ጥያቄ ሁሉ ቦታ ይሰጠዋል» ።

ከመለያየታቸው በፊት «ለንግሥቲቷ ከእሳቸው ጋር መገናኘት መቻል ለእኔ ትልቅ ነገር መሆኑን እንድትገልጽላቸው እፈልጋለሁ። በርካታ አገር ገዥዎች ሕንድ ውስጥ እንዳለችው ሰምቻለሁ፣ ከእነሱ አንዱ ከእኔ ጋር እንዲጻጻፍ ያደርጉታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አለ ቴዎድሮስ። ብሪታኒያዎቹ ልዑካን ከገመቱት በላይ በፍጥነት ማሳካት ችለዋል። ቴዎድሮስ በደመቀ ክብር በመቀበል የሚፈልጉትን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገባላቸው ። እስረኞቹን መልቀቅ እና ከሀገር መውጣትን ጭምር። አሁን እስረኞቹ ከመቅደላ እስኪመጡ እየጠበቁ ነው።

በቀጣዩ ቀን የቴዎድሮስ ስሜት ተለወጠ። ከሰዓት በፊት ብቅ አላለም። ስለዚህ የብሪታኒያ ልዑካን ቆራጣ ከተማ ለመሄድ ወደ ጣና ሐይቅ አቀኑ።

# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

ልዑካኑ ቆራጣ ላይ ሁለት ወራት በጣም ምቹ ጊዜ አሳለፉ። በውኃው ዳርቻ መኖሪያቸውን አደረጉ። ሰማያዊው የጣና ሐይቅ ውኃ ወደ ሰማኒን ከ64 ኪሎ ሜትር በላይ ተንጣሏል። እነሱ የሰፈሩበት የውኃው ዳርቻ ድንጋያማ እና በዛፎች ተከቦ በአዕዋፍ ድምጽ የተሞላ ነው። ሊተናንት ፕሪዶ ከድንኳኑ ሆኖ አንዲት ዳከዬ መትቶ ጣለ። ያሉበት ሥፍራ ዝዬ ቢሉ ኸፕግራ ቆቅ ቢ ሉ አምባራይሊ አማርጠው መመገብ የሚያስችል ነው። የዶ/ር ብላንክ በሽተኞች በሥርዓት ወደ ማረፊያቸው ሁሉትም ሶስትም እየሆኑ እየገቡ ይወጣሉ።

ከውኃው በስተምዕራብ በ 13 ኪሎ ሜትር ርቀት ገደማ በደን የተከበበው የዚጊ ሰላጤ ይገኛል። እዚህ ከሚገኘው የቴዎድሮስ ከፊል ቋሚ የጦር ሰፈር እሳት ይታያቸዋል። በየጊዜው የነጋሪት ድምፅ ይሰማል። ቴዎድሮስ ሠራዊቱን ወደ ውጊያ ይልካል ። እንዲያም ሆኖ ቆራጣ ያሉትን የብሪታንያ ልዑካን አልዘነጋቸውም። የራሳም አቀራረብ ስቦታል። በእሱ ግዛት የሌለውን ዓለምን የወከሉ የብሪታንያ ልዑካን አሳይተዋል፤ እርጋታ፣ ኃይል፣ ፈጠራ እና ቴክኒዎሎጂ።

ሳምንታት ሲያልፉ የተለመዱት የጣና ላይ መጓጓዣ ታንኳዎች ሐይቁን እያቋረጡ ከንጉሡ ሰፈር ወደ ልዑካኑ አቅጣጫ መጡ። ስጦታ ጭነዋል። አንድ ባለአንድ አፈ ሙዝ ጠብመንጃ፣ 4 ባለ ጥንድ አፈሙዝ ጠብመንጃዎች፣ አምስት ባለጥንድ አፈሙዝ ሽጉጦች፣ 5000 የጀርመን የብር ገንዘብ፣ ሁለት የአንበሳ ደበሎች፣ አንድ ሚዳቋ እና በርካታ ደብዳቤዎች። ደብዳቤዎቹ የተለያዩ ናቸው። ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያን አገልጋዮቹ ሁሉ የሚለብሱትን ሸሚዝ እንዲያስጌጥ ለራሳም በአክብሮት ዕድሉን ሰጠው። እውቀትን የሚፈልገው ቴዎድሮስ በጣና ሐይቅ ላይ የሚንቀሳቀሱ አዳዲስ ጀልባዎችን በመሥራት ግሩም ጥረት እያደረገ ነበር። ቴዎድሮስ እጅግ ያቀረበውን ራሳምን «እውነተኛ ወዳጅ፣ . . . የታላቋ ንግሥት ታላቅ ሰው . . . በሉዓላዊዎች ላይ እግዚአብሔር ከፍ ያደረጋት እና በልዑላን እና ህዝቦች ላይ ያላቃት፣ የክርስቲያን እምነት ጠባቂ ያደረጋት፣ እንዲሁም የድሀና የተጨቆኑ እናት የሆነችው ንግሥት አገልጋይ፤ ሆርሙዝድ ራሳም፤ በእግዚአብሔር ኃይል ጥበብ እና ቀና ልብ የተሰጠው » በማለት ነበር እየቀያየረ የሚጠራው።

ቴዎድሮስ ጋፋት ወዲሚገኙት ወደ ቫልድማየርና ሌሎቹ «የጦር መሣሪያ መሥራታችሁን ተውት እና ወደ ቆራጣ በመሄድ ከተከበሩት የብሪታንያ ልዑካን ጋር ቆዩ» የሚል መልእክት ላካባቸው። ከጥቂት ቀናት በኋላም «አውሮጳውያን ሴቶች መታጀብ እንደሚያስደስታቸው ስለሚያውቅ ሚስቶቻቸው ወደዚያው እንዲሄዱ አደረገ» ።

እመከናኛዊው ዶ/ር ብላንክ እንኳን ግማሽ ደርዘን የሚሆኑት ዝቅተኛ ቤተክርስቲያን ልዑካኑን አመጣጥ እጅግም ቦታ አልሰጠውም ነበር። ነገር ግን ከሚዳው በሻገር ሲመለከት እየተቃረቡ ሲመጡ በማየቱ ተገረመ። አውሮጳውያኑ በበሱት ደማቅ ቀለም ያላቸው ልብሶች ነበር። ራሳም እንደጻፈው ሴቶቹ ከወንዶቹ በተለየ የሚያምሩ ልብሶችን ለብሰዋል።

ከጋፋት ከመጣው ማሕበረሰብ መካከል ኢትዮጵያ ውስጥ ለዓመታት የኖረው ጀርመናዊ ቪልሐልም ሺምፐር ይገኛል። ቴዎድሮስ ለራሳም ምን ያህል እንዳደላ ያውቃል። ከዕለታት በአንዱ ቀን ራሳምን ሰዎች ካሉበት አካባቢ ዘወር አድርጎ አስጠነቀቀው። የእጁን መዳፍ እያሳየው፦ «አቢሲኒያውን ልክ እንደዚህ ናቸው» ብሎ እጁን ገለበጠው እና ዙሪያ ገባውን አማተረ።

በዚያን ቀን ከቀትር በኋላ የቴዎድሮስን ሶስት ስጦታዎች የጫነች ታንኳ ወደእነሱ መጣች። በላይዋ ላይ እየጮኹ የተጫኑበትን መሻገሪያ የሚቧጥጡ ሁለት ጦጣ እና ዝንጀሮ ነበሩ።

# ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

የካቲት 17 ከቀትር በኋላ በተቆጪነታቸው የሚታወቁት አንድ ዓይናው ኢጋፋሪ ጎለም(ገልሞ) መቅደላ ተራራ ላይ መልእክት ይዘው ከተፍ አሉ። ዓይናቸውን ፈንጣጣ ያጠፋባቸው ኢጋፋሪ የመጡት የንጉሡን የምሕረት ቃል ለእስረኞቹ ሊያደርሱ ነበር። ካሜሮን፣ ሽተርን፣ ሮዘንታል እና ሌሎቹም ሁሉ በፊታቸው እጎንበሱ። ካሜሮን ደሙ ምጥጥ ያለ ገመምተኛ መሰሏል።

«ጌታዬ ንጉሡ» አሉ ኢጋፋሪ፣ «ከንግሥታችሁ የተላከ ደብዳቤ በልዑካቸው በሚስተር ራሳም አማካኝነት እንደደረሳቸው እንድነግራችሁ አዝዘውኛል። በደብዳቤው ላይ በተጠየቀት መሠረትም የእናንተን ከእሥራት ነፃ መሆን እንዳበሥራችሁ ሲያዙኝ በደስታ ነው» ።

እሥራቱ የውጭ ዜጎቹን በቴዎድሮስ ግዛት ደንብ እንዲገፉ አድርጓቸዋል። ሽተርን ከንጉሡ መልዕክተኛ ሥር ተንበርከከ፤ ካሜሮን ራሱን ዝቅ ለማድረግ ታገለ። ብረት ቀጥቃጮች ወዲያው ሰንሰለታቸውን በመፍታት ሥራ ተጠመዱ። ብረቱ የእስረኞቹን ሥጋ እየገዘገዘ ቆርጧል። እጥንትና ብረት ሲፋተግ ከርሟል።

«እግረ ሙቅሲፈታ» ይላል ሽተርን በጻፈው ማስታወሻ «እብዝቶ ጠጥቶ እንደሰከረ ሰው ዓይነት ነበር የሆነው። ለመራመድ ተውተረተርን፣ ሚዛናችንን እየሳትን ተንገዳገድን ከዚያም ቁጭ አልን። ሁሉም ነገር ኽርው እያለ በዓይናችን ላይ ይዳዛል ወይም ወደ ታች ወደ እግራችን የወረደ ይመስላል። እንደወትሮው መራመድ የሚቻል አልነበረም»። ከተራራዎቹ ወደ ጣና ሐይቅ የሚደረገው ጉዞ አዝጋሚ ነበር።

በየዕለቱ የምናደርገው እንቅስቃሴ ረዥምም እና አድካሚ ነበር። ሆኖም በእነዚህ አሰልቺ ጉዞዎች የምናደርገው ርምጃ በነዚያ ገጽታዎች እና በእኛ መካከል ያለውን ርቀት እስከቀነሰልን ድረስ ማን ግድ አለው? ፈገግታ፤ሰንሰለት እና እሥራት፣ ቴዎድሮስ እና አቢሲኒያ ሊረሱ ይችሉ ይሆን?»

መጋቢት 3 ቀን ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ የመቅደላ እስረኞች ቡድን በመከራ ተጉዞ ቆራጣ ሠፈር ደረሰ። ሁሌም ትክክለኛ ንቁ እና አስተዋይ የሆነው ራሳም የቴዎድሮስ ትኩረት ቀገዘቀዝ ማለቱን አስተዋለ። ቫልድማየር «ራሳም ከየትኛውም የውጭ ዜጋ በተሻለ» ከንጉሡ ጋር ማድረግ የሚገባውን ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ይናገራል። እናም አሁንም ራሳም የተጠሉት እስረኞቹ ወደ ቆራጣ መምጣት የቴዎድሮስን ስሜት ሊረብሽ እና ተልዕኮውንም ሊያከሽፍበት እንደሚችል ተረድቷል።በመካከላቸው የመተባበር ነገርን ካስተዋለም ቴዎድሮስ ወደ ሀገራቸው እንዲሄዱ ላይፈቅድ ይችላል።



ስለዚህ ራሳም የተጠበቀው ቡድን እዚያ ሲደርስ ከድንበር ጠባቂዎቹ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ተቀበላቸው። የሃያ ሶስት ሰዎች የስም ዝርዝር ከነማንነታቸው የሚያሳይ የራሱን ቅፅም አዘጋጀ።

ከሁለት ቀናት በኋላ ከዘጌ ደሴት ሐይቁን አቋርጦ መጣ። በቴዎድሮስ ምትክ ራሳም የእስረኞቹን ጉዳይ በችሎት እንዲዳኝ ተሰየመ። የይስሙላ በተሰየመው ችሎት ፊት በእግሮቹ ለመቆም ያልቻለው ካሜሮን የቴዎድሮስን መልእክት ወደ ንግሥት ቪክቶሪያ ባለማድረስ ጥፋተኛ ተብሎ፣ ከንጉሡ ጠላቶች ተደመረ፤ ሌሎቹ ደግሞ የቴዎድሮስን ወዳጅነት አግኝተው ሳለ በማበላሸታቸው ጥፋተኛ ተባሉ። ከዚያም ራሳም ለቴዎድሮስ ሁሉም ጥፋተኛነታቸውን ማመናቸውንና ጸጸታቸውን በመግለጽ በክርስቲያን ደንብ ይቅርታ እንደሚጠይቁ ጻፈ። ቴዎድሮስም ይህን ተቀብሎ ይቅርታ አደረገላቸው፤ ራሳምንም «ጎንበስ ብዬ እጅህን እና እግሮችህን ብስም እወዳለሁ» አለው።

ለራሳምም 50 ጥገት ላሞች እንዲሁም 5 ሺህ የጀርመን ከብር የተሰሩ ሳንቲሞች ሁለት፡ የወርቅ ኮርቻ፣ ጋሻ እና ሜዳልያም ሊሰጠው ፈለገ። መስቀል እና በለሙን ማሕተምም ሦስቱ የብሪታንያ ልዑካን ወደ ባሕር ወደቡ ከመሄዳቸው በፊትም እንዲዘጋጅላቸው አዘዘ። እንዴት ያለ ቅርፅ እንደሚኖራቸው ለማማከርም አንጥረኞቹን ወደ ራሳም ላካቸው። እቅዱ በዳዊት ኮከብ ውስጥ ባለው ሶስት ማእዘን ላይ መስቀል እንዲደረግ፣ ከፊት ለፊት በኩል «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ከጀርባው ደግሞ «ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት» ተብሎም እንዲጻፍበት ተወሰነ። ቴዎድሮስ ሁሉም ነገር ያበቃ መሰለው። እንዲሠራ የታዘዘው ሜዳልያ ሦስት ደረጃዎች አሉት። ወርቅ፣ የወርቅ እና ብር እንዲሁም የብር ብቻ። ራሳም፣ ራስ እንግዳ እና የቴዎድሮስ የመጀመሪያ ልጅ አንደኛ ደረጃ ብላንክ እና ፕሪዶ እንዲሁም የፍጠኛው ጦር የበላይ አዛዥ ራስ ተጋ ሁለተኛ ደረጃውን ሜዳልያ ይሸለማሉ፤ ለሶስተኛው ደግሞ ተሸላሚዎች ይመረጣሉ።

ቴዎድሮስ ከአውሮጳውያኑ ጋር ለመሄድ እንዲዘጋጅ ለራሳም ነገረው። ሜዳልያዎቹ እና የወርቅ ኮርቻው ብቻ ተዘጋጅቶ እንዳበቃም የንግሥቷ ባሪያ ለሆነው ወዳጁ ታስረው ከነበሩት ጋር ሁሉ ሀገሩን ለቅቆ እንዲወጣ ቃሉን ይሰጠዋል።

እንዲያም ሆኖ ራሳም እያንዳንዱ ዕለት የንጉሡን አእምሮ የሚያነቃ ጭምጭምታ ወይም መልእክት አምጥታ ሁሉንም ነገር አደጋ ላይ ልትጥል እንደምትችል ያውቃል። ቴዎድሮስ ጋር አግባብ ያለው ሥርዓቱን ማሳየቱን ቢቀጥልበትም በልቡ ግን ሜዳልያ እና ኮርቻውን ሰብስቦ ባሕር ውስጥ ቢጥላቸው ይመኝ ነበር።

## ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

ታላቁ የሁዳዴ ፆም እየተገባደደ ትንሣኤም እየደረሰ ነው። ቴዎድሮስ ወደ ሴቶቹ መልእክት ላከ። ከሁሉም የበላይ እና ምንም እንኳን እውነተኛዋ እቴጌ ከልጅ ዓለማየሁ ጋር መቅደላ ቢሆኑም፤ ቴዎድሮስ እቴጌ የሚላት የተመኙ ናት። ግዜና የተመኙ ከሰንበሌጥ በሚሰራው ታንኳ ተሳፈረች። ሌሎቹ ሴቶች ደግሞ በሌላ የእዛገሮቹ ሴቶችም ተከተሏቸው። በነጭ ሸማ የተሸፈኑት ታንኳዎች ንጉሣዊው መንደር ወደተተከለባት ወደ ዘጌ ደሴት ተጓዙ።

ፈረሶችም እንዲመጡ ቴዎድሮስ በማዘዙ ቢታንኳ መጫን ስለማይቻል በስተደቡብ በሐይቁ ዳርቻ አማፅያን እጅ በማይገቡበት መንገድ ተወሰዱ። ከሴፈ ከመነሳቱ በፊት መጋቢት 13 ቴዎድሮስ ለራሳም እንዲህ ሲል ጻፈለት ፤ «እንተን ለማየት እና ለማግኘት ስናፍቅ ቆይቻለሁ። አሁን ለጉዳይ ወደሌላ ቦታ ሄጃለሁ፤ በእግዚአብሔር ኃይል ስመለስ አሳውቅሃለሁ ወዳጅነትህን እናፍቃለሁ »።

በእርግጥም አድርጓል። ራሳም ቆራጣ በነበረበት ወቅት ቴዎድሮስ 23 ደብዳቤዎችን ጽፎለታል። የውጭ ዜጎቹ የመሄጃ ጊዜ ሲቃረብ ቆራጣ በሰፈሩት አውሮጳውያን መንደር ውጥረት ማንገርበብ ጀመረ። ራሳም ከቴዎድሮስ በኩል ያተረፈው ውዴታ በራሱ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል አውቆታል። ቴዎድሮስም የራሳምን መመለስ ሲያስበው ምቾት አልተሰማውም። ራሳምን ወደ ዘጌ አስጠራው ። ብላንክ፣ ፕሪዶ፣ ቫልድማየር እና የጋፋት እጅ ሙያተኞችን ሁሉ አስመጣ። ከሐይቁ ዳርቻ ድረስ ሄዶ ተቀበላቸው። የብሪታንያን የባለስልጣናት የደንብ ልብስ ለብሰው ሲመለከትም ፈገግ አለና፤ «ንግሥቷን እንደጎበኘሁ ያህል ደስታ ተሰማኝ» አላቸው።

ግቢውን አቋርጠው ወደ እዳራሹ ሲሄዱ ቴዎድሮስ የራሳምን እጅ ያዘው። ወደ ውስጥ ሲዘልቁም በዙፋኑ ዙሪያ ምንጣፎች በየአቅጣጫው ተዘርግተው የቴዎድሮስ የቅርብ ሰዎች ተቀምጠዋል። ቤተሰቦቹም ጭምር። እየተቀመጠም ንጉሡ አንድ ወጣትን ጠራ።

«መሸሻ ቀረብ በል» አለው። የመጀመሪያ ልጁ ነው ራስ መሸሻ። ራሳም ለቴዎድሮስ ካቀረባቸው ገፀ በረከቶች ከሀር የተሠራ ሸሚዝ ለብሷል። «በእንግሊዞች ስልት እነዚህን እንግሊዛውያን ወዳጆቼን ሰላም በላቸው እንደእነሱ እንድትሆን እፈልጋለሁ»። ወደራሳም ዞር ብሎም፤ «ይህ ልጅ እና መቅደላ የሚገኘው የአራት ዓመቱ ዓለማየሁ የእንግሊዝ ማደጎ ቢሆን አመኛለሁ። ወደ ሀገርህ ስትመለስ ለንግሥቷ ንገርልኝ፤ ስሞት በመጥፎ አስተዳደር ስር ከሚወድቁ እንግሊዝ እንድታሳድጋቸው»። አለው።



ከዚያም ፕላውደን እና ንግስት ቪክቶሪያ የሰጡትን የሚወዳቸውን ጠብመንጃዎች፣ ሽጉጦች፣ ዲሞትፈሮች... አሳያቸው። በመቀጠልም ስጦታዎቹን ሁሉ እና እነዚያ ታስረው የነበሩ ሰዎች ምን ያህል እንደከዱት አስታወሰ።

በሚቀጥለው ቀን ታላቅ ስብሰባ ተደረገ። 85 ሹሞች ወደ አዳራሹ ገብተው ከራሳም እና ከልዑካኑ እንዲሁም ከጋፋት ከመጡት ጋር ቦታቸውን ያዙ። ቴዎድሮስ ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላከለትን ደብዳቤ ከፊት ለፊቱ ዙፋኑ ላይ አስቀመጠ እና ታማኙ የሆኑትን አቶ ሳሙኤል እና ወልደ ጋብርን« እነዚህ ሰዎች ወደ ባሕር ወደቡ እንዲሄዱ ይፈቀድላቸው?» በማለት ጠየቃቸውና «ግርማዊነትዎ ወደሀገራቸው በደስታ ቢሸኟቸው ይሻላል» ሲሉ ምክራቸውን ሰጡ።

የሚፈልገው መልስ አልነበረም፡ ተመሳሳይ ጥያቄ ለቫልድማየር አቀረበ። አውሮጳውያኑ እንዲሄዱ እንዲፈቀድ እሱም ሐሳቡን ሰጠ። ብረት አቅላጩ ሀገር ወደዙፋኑ ተጠግቶ የንግሥቷን ደብዳቤ አነሳና ማሕተሙን በጥንቃቄ ተመለከተ።

«ግርማዊነትዎ ይህን ሊያምኑ ይገባል፤ የንግሥቷ ትክክለኛ ቃላት መሆናቸው ያስታውቃል፤ ቃሏንም አታጥፍም» አለ። ከዚያም ቴዎድሮስ አውሮጳውያኑን አሰናበታቸው ። ወደ ባለስልጣናቱ ፊቱን አዞረ። ሁሉም እንዲለቃቸው ጠየቁት።

«ከዚህ ምን አገኛለሁ?»

የሥራዊቱ አዛዥ ራስ ተጋ ሌሎቹን ወክለው ተማፅኖ አቀረቡ። «ግርማዊነትዎ በሰላም እንዲሄዱ እንዲፈቅዱላቸው እንማፀንዎታለን። ራሳም ከሄደ በኋላ ከዋሸ በመካከላችሁ እግዚአብሔር ይፍረድ። እግዚአብሔርን ይመኑ .... እርሱ ይበቃናል»። ሌላኛው ምክሩን ደገመው። «ግርማዊነትዎ እንግሊዞችን ካላመኑ ራሳም መጽሐፍ ቅዱስ መትቶ እንዲምል ያድርጉት። እንግሊዞች መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ለሚምሉት መሐላ ታማኞች ናቸው»።

የተሰበሰቡትን በተነና ንጉሡ ራሳምን እና ጋፋት የሚኖሩትን ሚሲዮናውያን አስጠራ። ድንኳኑ ውስጥ እንደገቡ ቴዎድሮስ መናደዱ በግልፅ ይታይ ነበር። በእሱ ላይ የተነገሩትን ዘለፋና ስድቦች በሙሉ ዘረገፋቸው። አቡኑንና እና እቴጌን ለመጎብኘት ወደ መቅደላ የመሄዱ ጉዳይ የጋለሞታ ወዳጅ እንዳደረገው፤ ፈረንሳዊው ለገ ብዙ እንደሰደበው፤ የቅብጥ ፓትሪያርክ ዘውዱን መጠየቃቸው፤ በሻ ፈለቀ የሚል ቅፅል የተሰጠው እንግሊዛዊ ጅብደኛ ካፒቴን ቻርለስ ስፒዲ ከጉብኝቱ ሲመለስ ኢትዮጵያውያንን «እህዮች» ማለቱ .....።

«እና እናንተስ ከእነዚህ እንደማትለዩ በምን አውቃለሁ» ቴዎድሮስ ራሳም ላይ
አምባረቀበት። ራሳም ለመመለስ ይንተባተብ ገባ። ቴዎድሮስ በዚህ ጊዜ
ፀጥታውን መልሶ ለስለስ ባለ ድምፅ ሰበረው። «ከሀገሬ ስትወጣ አትሰድበኝም
ይሆናል ግን ልትረሳኝ ትችላለህ»። «ከሌሎቹ የተሻልኩ ነኝ ብዬ ራሴን ማወደስ
አልችልም ግን ፈትኑኝ» አለ ራሳም።

ቴዎድሮስ አማካሪዎቹን ሁሉ አነጋግሮ ጨርሷል። እያንዳንዳቸው የተናገሩት
ተመሳሳይ ነው። የማንንም ምክር ሳይሻ የዳዊትን ርምጃዎች መሠረት አድርጎ
በራሱ ውሳኔዎችን ያሳለፈባቸው ጊዜያት አሉ። አሁን እነዚያ ግዜያት የሉም።

«እሺ» ድምፀቱ ምጥን ነበር። ንዴቱ አብቅቷል።«መልካም አፈትንሀለሁ።
ሀገራችሁ በሰላም ግቡ»።



# ምዕራፍ አርባ

በስለተ ዓርብ በሚያዚያ መባቻ ቀናት በ1858 ዓ.ም የቋራ መንደር በሰዎች
ተሞላ። የመቅደላ እስረኞችም ወደ ባህሩ ጠረፍ ጉዟቸውን ጀመሩ። በጣና ሐይቅ
በስተምስራቅ ዳርቻ በበጋው ወራት በደረቀው የውኃ መንገድ ተጓዙ። ሳምንታት
የሚፈጅ ከባድ መንገድ ከፊታቸው ተዘርግቷል። እንዲያም ሆኖ በዚያች ዕለት
የነፃነታቸው ነፃ የመውጣት መንፈስ ስሜታቸውን ሞላው።

ሸተርን በማስታወሻው፤ «በደስታ የተሞላው ስሜታችን እያንዳንዱን ነገር የተዋበ
ቀለም አለበሰው። እጅግ ውብ በሆነ ሀልማችን ተውጠን በጉድጓድና በጉድባው
ላይ እየዘለልን፣ አረም እና ጫካውን እየታከከን ተጓዝን» ሲል ጽፎታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሦስቱ ልዑካን ለመጨረሻ ጊዜ ሐይቁን አቋርጠው ወደዘጌ
ሄዱ። ራሳም፣ ብላንክ እና ፕሪዶ ንጉሡን ተሰናብተው ከቡድኑ ጋር በመሆን ወደ
ሀገራቸው ለመጓዝ ነው የፈለጉት።

ዘጌ ሲደርስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ እንግዳ ሦስት የተጌጡ በቅሎዎችን ይዘው
ተቀበሏቸው። በፀሐይ ብርሃን በተዋበው ቀን በ ዛፎቹ መካከል አልፈው
ወደቴዎድሮስ ግቢ አቀኑ። በሁሉም ልብ ፀጥታ ነግሧል። ለእንግድነታቸው
የተዘጋጀ ድንኳን የለም። በጦር እና በጠብመንጃ ሰላምታ ከበቅሏቸው ወረዱ።
ራስ እንግዳ ወደ አዳራሹ ዘልቀው ከመግባታቸው በፊት ለጥ ብለው እጅ ነሱ።
ውስጥ አራት መቶ የሚሆኑ ባለስልጣናትን ተመለከቱ፤ ራሶች፣ ደጃዝማቾች፣
ግራዝማቾች እና ቀኝ አዝማቾች ሁሉም የሀር ሸማዎቻቸውን ለብሰዋል።
በመካከላቸው ራቅ ብሎ ዙፋኑ ተቀምጧል። ራሳም ቦታው ባዶ መሆኑን
ተመለከተ። ነገር አለ።

በዚያች ቅፅበት የሆነ ሰው ከንዱን አፈፍ አደረገው። ሌላኛውንም ደገመው።
ሶስተኛው መኮንን የኮቱን ጫፍ ያዘ። ዙሪያ ገባውን ተመለከተ። ብላንክም
ተይዟል፤ ፕሪዶ ሲወሰድ ወታደራዊ ሊሻኑ ተመንጥቆ ተሸቀንጥሮ ራቅ ብሎ
ወደቀ። ብላንክ ንዴቱን መቆጣጠር ተሳኖት ጥርሱን አፋጨ። ራስ እንግዳ ወደ
እነሱ ዞር አሉ። የተገረሙ ይመስላል። «አይዟችሁ አትፍሩ» አሏቸው።

በተመሳሳይ ሰዓት በ64 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነፃ የወጡትን ሚስዮናውያን
እስረኞች ይሸኙ የነበሩትም የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ተግባራዊ አደረጉ። የውጭ
ዜጎቹን ዳግም አሰሯቸው። እንደገና የሁለት ቀናቱን መንገድ ወደዘጌ መመለስ
ጀመሩ። ቴዎድሮስ ስለራሳም ጉዞ ለወራት ሲያስብበት ቆይቷል። 56 ቀናት
የሚቆየው የሁዳዴ ፆም ሲጠናቀቅ ድል ባለድግስ ሽኝት ለማድረግ እና በማይረባ
ምክንያት የተበላሸውን ግንኙነት ለማደስ አስቧል። በዚህም ደግሞ የእንግሊ

ኢትዮጵያን ግንኙነት አጠናክሮ በታላቁ የክርስቲያኖች ሕብረት ሙስሊሞችን ወ፣ በረሃው መልሶ ለማባረር እና ከደቡብዊ የቀይ ባሕር ዳርቻ ለማስወገድ አልሟል፡

ቴዎድሮስ ወርቃማ ሊሻኖችን ለራሳም ለማበርከት ፈልጓል። ለዚህ በዓል ሲባል የተዘጋጀው ከፍተኛውን መስቀል እና የሰለሞን ማሕተም ያለበትን ሜዳልያ እራሱ ደረቱ ላይ ያደርግሊታል፣ በተጨማሪም ከንጉሣዊው ቤተሰብ በቅሎዎች እና ፈረሶችንም ቴዎድሮስ ለራሳም ለማበርከት መርጦ አዘጋጅቷል። አነሱን እና ከ የወጡትን እስረኞች ከዘጌ አንስቶ ከግዛቱ እስኪወጡ ድረስ የሚደረገው የሽኝት ዝርዝር መርሃ ግብር ተነድፏል። የመጀመሪያውን ደረጃ የሚመሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ እንግዳ ናቸው። ንጉሡ ባለስልጣናቱን ሰብስቦ ሲድግሱ ድንኳኖች እንዲተከሉ አድርጓል። ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ወደ አዳራሽ ሲገቡ እና ራስ እንግዳ እነ ራሳም የደንብ ልብሳቸውን ለብሰው እስኪመጡ ሲጠባበቁ እንኳ የሚያስቡት አሸናንት ይደረግላቸዋል በሚል ነው። ሆኖም ቴዎድሮስ ውስጡ ባገረሸው ቁጣ ምክንያት የራሳም መሄድ ሊያመጣው የሚችል ነገር የለም የሚል ጥርጣሬ አደረበት። እናም በጠዋቱ ቢትወደድ ተድላ ጣናን ተሻግረው የተለቀቁትን የመቅደላ እስረኞች መልሰው እንዲያስሩ አዘዘ። «ወደ ሀገራችን ልንሄድ ነው ባሉት በወዳጆቻችን እና በአውሮጳውያን ተቆጥተናል፤ ገና እርቅ አላወረድንም ምን እንደምናደርግ እስከንመክር ድረስ ያዟቸው»።

ቴዎድሮስ ሌሊቱን በዐይኑ እንቅልፍ አልዞረም። አንድ ቀን ቀደም ብሎ የታዘዘው ሜዳልያ ሆነ መስቀልና የሰሎሞን ማሕተም ያለበት ሽልማት እንዳልደረሰ ተነግሮታል። በዚያም ላይ ራሳም ከመቅደላ ለተለቀቁት እስረኞች የጦር መሣሪያ ሲያድል ነበር የሚል መረጃ ደርሶታል።

ሰው ጥቅጥቅ ባለበት አዳራሽ ራሳም፣ ብላንክ እና ፕሪዶ እየተዳፉ እና የደንብ ልብሳቸው እየተጎተተ ከባዶው ዙፋን ፊት ተገተሩ። ጸሐፊው ተነስቶ የቴዎድሮስን የዘር ሐረግ ከሰሎሞን እና ሳባ እስከ ንጉሥ ዳዊት ድረስ ዘረዘረ። ራሳም የጥያቄ መዓት ተዥጎደጎደለት። ለምን እስረኞቹን ይዞ እንዳልመጣ፣ ለምን ደብዳቤ ወደ ባሕር ወደቡ እንደላከ... ሊላም ሊላም። ጥያቄዎቹ «ግልፅ ያልሆኑ እና የተዘባረቁ» እንደነበሩ ፕሪዶ መዝግቦታል። ለብላንክ ደግሞ «የልጆች» ዓይነት ናቸው። እዚያ የተሰበሰቡት ባለሥልጣናት ሳይቀሩ ራሳም መልሱን ከማረጋገጫ ጋር ሲመልስ በማየታቸው እሱን በመደገፍ ሊሮኹ ምንም አልቀራቸውም ነበር።

ያ ሁሉ ሲሆን ዙፋኑ ባዶ ነው። ቴዎድሮስ ከበሩ በስተጀርባ ተቀምጧል። ለሶስት ቀናት ሲጠጣ ነበር ነው የተባለው። በራሳም ላይ በሚሰነዝረው ጥቃት ምክንያት ናላውን ያዞረው ንዴት የፈጠረውን የሚያምታታ መልእክት እየተንተባተበ ይናገር ነበር። ራሳም ከብሪታንያ ጋር ግንኙነት እንዲጀመር እንዲያደርግ በመጠየቅ



...ም፤ ሆኖም አሁን መዘግየቱን አስተዋለ። ዋናው ነገር አውሮጳውያን እያነሰ ...ደረው ግዛቱ ሲወጡ ማየቱ ሊቋቋመው የማይችለው ነገር ሆኖበታል።

...ለው ዓለም ጋር እመሠርተዋለሁ በሚለው ግንኙነት አንድ ያለውን ተስፋ ...ገሩና ለመጨረሻ ጊዜ ይዘውት እንደሚሄዱ በማወቁ፣ በከዳተኞች ለተከበበው ...ዎድሮስ ምሬት እና የሐሳብ መና መቅረትን የሚያብሰው ደግሞ ከእሱ የሚለዩት ...ምት የሚከዱት መሆናቸው ነው።

# ምዕራፍ አርባ አንድ

ከሦስት ቀን በኋላ ቴዎድሮስ ዳግም ችሎቱን ሰበሰበ። ችሎቱ የተሰየመው ከ በአጥር ከተከለለው ከንጉሣዊው መኖሪያ ግቢ ሜዳ ላይ ነው። ዘውዳን ከበ እድርጎ እሱም አብሮ ተቀመጠ። በማለዳው ፀሐይ በርካታ አድናቂዎቹ ከበሰ ተሰብስበዋል። አንድ ሺህ ወይም ከዚያ በላይ ይሆናሉ። አንዳንዶቹ በጃንጥላ ተከልለዋል፣ ገሚሱ ምንጣፍ ላይ ተቀምጠዋል። ገሚሶቹ ካህናት እና ደብተራዎች ከእናታቸው ላይ ያደረጉት ጥምጥም ፊታቸውን ከልለው፣ ወይባ የለበሱ መነኮሳት፣ የወቅቱ ሚኒስትሮች እንዲሁም የተመረጡ የችሎት ሰዎች በየደረጃቸው ተቀምጠዋል። በቀለም ባሸበረቀው የተዋጊ ሸሚዛቸው ብርማ ጌጥ ባለው ቆባቸው በዚያ ላይ ለፊታቸው ግርማ ያለው እንዲሁም አድርገው ጀነራሎች፣ ልዑላኑ እና የአከባቢው የጎበዝ አለቆች በሰፊው የአንበሳ ገፊ የአውሮጳውያን እስረኞችን ጉዳይ ለመመልከት ተሰይመው ነበር።

ሰሞኑን ከታየው ትርምስ በኋላ ቴዎድሮስ ሊፈታቸው ይሁን ሊያሥራቸው የሚያውቅ ማንም የለም። አውሮጳውያኑ በቅርቡ ካሳቸው አውቅና አኳያ ጥንድ ጥንድ ሆነው ይመጡ ጀመር። በቅድሚያ ሻልድማየር እና የጋፋት የእጅ ጥበብ ባለሙያዎች፣ በመቀጠል የደንብ ልብሳቸውን ያደረጉት ራሳም፣ ብላንክ እና ገበ ደረሱ። በመጨረሻም ከአንድ ሰዓት በኋላ ሰንሰሊታቸው እየተንቃጨለ አሁንም ድረስ የተጠሉት ካሜሮን፣ ሸተርን እና ሮዘንታል እንዲሁም ሌሎቹ እስረኞ መጡ።

አሁንም እንደታመመ የሚገኘው ካሜሮን ለመራመድ ባለመቻሉ ቴዎድሮስ በቅሎ ልኮለታል። ከጠዋቱ 3 ሰዓት እሱ እና ሌሎች እጥፉን ዘልቀው እግራቸውን እየጎተቱ ከተሰበሰበው ችሎት ደረሱ። ቴዎድሮስ እጅግ ያስቀጣት እነዚህን ሰዎች ከዓመት በላይ አላያቸውም ። ባለፉት ወራት ወደ ጣና ሐይቅ አካባቢ ከመጡ ጀምሮ፣ ቴዎድሮስ አይቶአቸው ቀጣው እንዳያገረሽ በሚል ራሳም እነሱን እርቆ ለማቆየት የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። አሁን ግን ምንም ማድረግ አይችልም። በሠንሰለት እንደታሰሩ እያነከሱ ከንጉሡ ፊት ቀረቡ።

«እንዴት ናችሁ?» ጠየቃቸው ፣ «ጤናችሁስ?»

«ደህና ነን» በጉልበታቸው እየሠገዱ መለሱ። «እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነን»። በማንባራቸው አፈሩን ነኩ። ቴዎድሮስ ወደፊት እንዲመጣ ካሜሮንን ጠየቀ። የተሰበሰበው ሁሉ እያየው ቆንስሉ ወደ እሱ ለመጠጋት ተውተረተረ። ቴዎድሮስ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተው፤ ፈገግታ ከንፈሩ ላይ እየታየ ወታደሮቹ ሰንሰለቱን እንዲያወጡለት አዘዘ።



«እንዳትነኩት ተጠንቀቁ እንዳትነኩት ቂጥኝ አለበት» አስጠነቀቀ። ካሜሮን ከራሳም ጋር እንዲቀመጥ ታዘዘ። እየተውተረተረ እና በዝግታ በተሰበሰቡት መካከል አልፎ ከልዑካኑ ጎን ራሱን ዝቅ አድርጎ ምንጣፍ ላይ ተቀመጠ። ሄንሪ ሸተርን ይህን ችሎት ከሁለት ዓመት ከመንፈቅ በፊት ከነበረው ጋር አነፃፅሮታል። «ያኔ በነበረው ግርማ ሞገስ እና ዝና ምክንያት እሱ ራሱ የቴዎድሮስ ንብረት እንደሆነ ይሰማው ነበር»። አሁን ንፅፅሩ እጅግ የሰፋ እና ፀፀት የሞላበት ነው። ግዛቱ አሁን ተኮማትሮ በጥቂት ከፍለ ሃገራት ላይ ተወስኗል። ሠራዊቱም ቢሆን ከ150 ሺህ ወደ 50 ሺህ የጦር መሣሪያ አንጋቾች ወርዷል።

ሸተርን ጉዳዩን አብራርቶታል። እዚህ ዘጌ ላይ የቴዎድሮስ መኳንንት በእሱ ላይ ያላቸው እምነት ፅኑ ነው። እንዲያም ሆኖ ግን ጥላው ተሰባስቦ ግርማዊነቱን ተስፋ መቁረጥ ከቦታል።

ታዛቢዎች እንዲሚሉት የዘር ሐረጉን የገለጸበት መንገድ ከዚህ በፊት ከነበረው የሚለይ ሲሆን የአውሮጳውያኑን ወንጀል ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አጉልቶ ያቀረበ ነበር። «ቴዎድሮስ መቼም ቢሆን እንዲህ እንደ አሁኑ እስረኞቹ ላይ ያለውን ጥላቻ ገልፆ አያውቅም» በማለት ሸተርን ገልፆታል። ያን ቀን ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳም እሱም ሳይቀር በቀጥታ ክስ ሲቀርብበት ያደመጠው። ቴዎድሮስ ጠራው። ከብላንክ እና ከፕሪዶ መካከል ሆኖ ከተቀመጠበት ተነስቶ በንጉሡ ፊት ቆመ። ከንጉሡ አጋማሽ ላይ የወጣችው ፀሐይ ሙቀቷ በርትቷል፤ የችሎቱ መሠረታዊ ጥያቄዎችም ይሰሙ ጀመር። «እስረኞቹ ወደ ቴዎድሮስ ሳይመጡ ለምን እንዲሄዱ ተደረገ?» ቴዎድሮስ ለዚህ ተጠያቂ ያደረገው ራሳምን ነው። "አቶ ራሳም ስህተት ሰርተሃል፤ ከእነሱ ጋር እንድታስታርቀኝ ነግሬህ ነበር። ይህን ያላደረግከው ለምንድ ነው?"

ራሳም አርቆ ባለፈው መጋቢት ችሎት እንዲያካሂድ በታዘዘው መሠረት ሲያከናውን ተደርጓል ብሎ እንደተረዳ ለመግለፅ ሞከረ። «ነገር ግን ለጉዞ መዘጋጀት እንደምትችሉ መልእክት በላኩብህ ጊዜ የተፈቱትን እስረኞች ይዘህ እንድትመጣ አልነገሩህም ነበር? ምክንያቱም በቅሎ ለሌላቸው በቅሎ፤ ገንዘብ ለሌላቸውም ለመንገዳቸው የሚሆን ገንዘብ ለመስጠት ፈልጌ ነበር። አንተም በቅሎዎች እንዳመጣህላቸው ሀገራቸው የሚያደርሳቸው ገንዘብም እንዳለህ ተናግርከ»።"

«እዎ» አለ ራሳም። «ሆኖም ግን ይህን ያደረግኩት ግርማዊነትዎ ከእነሱ ጋር ዳግም ችግር ውስጥ እንዳይገቡ ለማዳን ነበር»። ራሳም በዚህ ጊዜም ቴዎድሮስን በማበሳጨቱ ብቻ ሳይሆን ደግሞ እንዲታሰሩም ምክንያት ነኝ የሚል እንዳች የሚረብሽ ስሜት ወረረው።

ቴዎድሮስ በሰንሰለት ወደታሰሩት እያመለከተ፣ «አሁን እንደምታየው ባንተ ምክንያት እንደገና በሠንሠለት ተይዘዋል። ገና በሌላ መንገድ አልካቸዋለሁ ባንተ ጥርጣሬ አድርብኝ ነበር። እንደማስበው ሀገርህ ስትደርስ አንተ በስልጣንህ እንዳስፈታሃቸው ወይም በኃይልህ እንዳስለቀቅካቸው መግለፅ የፈለግክ ይመስለኛል። ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? ንጉሥ ነህ?»

«በፍጹም ግርማዊነትዎ፣ እኔ የእርስዎ ወዳጅ ነኝ»።

ቴዎድሮስ በድጋሚ ለራሳም እስረኞቹን ወደ እርሱ አምጥቷቸው ቢሆን ኖሮ መሣፈሪያ ሰጥቶ ወደሀገራቸው ይልካቸው እንደነበር አስረግጦ ነገረው። የንጉሡ ቁጣ ጠፋ። እያንዳንዱ ሰው ምልክቱን ያውቀዋል። ራሳም ከፊቱ በመቆሙ ራሱን እንዲቆጣጠር አድርጎት ይሁን ወይም ቴዎድሮስ በልቡ የሚያስበው ሌላ ነገር አግዶት አይታወቅም። ነገር ግን ወዲያው በረደ። ራሳምን ከዙፋኑ ፊት እንዲቀመጥ አዘዘው እና አማፅያኑን እንዲሁም ቱርኮችን ይሳደብ ጀመር።

«ኡፍ» በሰፊው ተነፈሰ። ኢንግላንድ ረድታኝ ቢሆን ስናር ላይ አጥር በገነባን ነበር»። ችሎቱ ያለ ፍርድ ተበተነ። የቴዎድሮስ ቁጣ ግን አልበረደም። ከመነሳቱ አስቀድሞ ራሳምን «ይህ ነው ወዳጅነትህ አቶ ራሳም? የሰደቡኝን ይዘህ እኔን ትተህ ለመሄድ ፈለግክ?»

አሁን ራሳም ከውጭ ዜናቹ እንዳቸውም የሚያስጋ ነገር የለባቸውም ማለት እንደማይቻል ገባው። በቀጣዩ ቀን ንጉሡ ሉብቻ ችሎት አዳራሽ ውስጥ ሰበሰባቸው። አውሮጳውያኑ ፈርተዋል። ወደ ውስጥ ሲገቡ እያንዳንዳቸው በደመ ነፍስ የቴዎድሮስን ስሜት ለማየት ሞከሩ።

ያን ቀን ከቀትር በኋላ የተረጋጋ እና የተሰላች ይመስል ነበር። እንዲያውም እንግዳ ዝቅ አድርጎ። «ስለኢየሱስ ክርስቶስ ብላችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ»። አላቸው። ብዙም ሳይገረሙ እነሱም በአፀፋው አንገታቸውን ዘንበል እያደረጉ በሚያጉተመትም ድምፅ ይቅርታቸውን እሰሙ። እነሱም እንደሁ ይቅርታውን ለመኑ፤ ቴዎድሮስም ይቅር አላቸው ዝምታ ሰፈነ።

ሁሉም መሬት መሬት እያዩ ቆሙ። ቴዎድሮስ ራሱን አጎንብሶ ቆየ። ጋፋት ከነበሩት ሚስዮናውያን አንዱ ለራሳም ስለ ችሎት ይቅርታ ሂደት ሹክ አለው። «ግርማዊነታቸው እንዲቀመጡ መንገር አለብህ»።



# ምዕራፍ አርባ ሁለት

የቴዎድሮስ የቁጣ ሁኔታ ያኔ በ1848 የቅብጡን ፓትሪያርክ እንዳሠራቸው ጊዜ ደግም ታየ። መጀመሪያ ጥርጣሬ፣ ከዚያም ጥፋቱ ተፈጸመ እና አስደንጋጩ አስራት ተከሰተ። ከዚያ ሁሉ ቁጣው ተመልሶ ሠንሰለቱን በመፍታት ይቅርታ ይጠይቃል። አሁን ራሳም «ከዚህ ይፋዊ የእርቅ ሥርዓት ከንዋኔ በኋላ ጉዟችንን የሚያስናክል ነገር አይኖርም የሚል ተስፋ ነበረው»።

በዚያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ቴዎድሮስ የመቅደላ እስረኞቹን ተሰናበተና ራሳምን ከእሱ ጋር አቆየው። ራሳም ለንግስት ቪክቶሪያ የሚወስደውን ደብዳቤ እንዲጽፍ አሌቃ እንግዳን አስጠራ። ጸሐፊው የተባለውን በቀይ ብዕር ሲጽፍ አቶ ሳሙኤል የቴዎድሮስን ቃላት ለራሳም በአረብኛ ይተረጉሙ ጀመር። የግርማዊነትዎ ደብዳቤ እንደተለመደው በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ጀመረ፤ «የእግዚአብሔር ፍጡር እና ባሪያ፣ የዳዊት እና የሰሎሞን ልጅ፣ ንጉሥ ነገሥት ቴዎድሮስ። ይህች አስተኛ ደብዳቤ እግዚአብሔር ከወንዶች በላይ አድርጎ ዘውድ ወዳቀዳጃቸው ሃይማኖትን እና ወዳጅነትን ከሚወዱ፣ የተጨነቀ ደሃን ከሚከላከሉት የኢንግላንድ ንግሥት ቪክቶሪያ ዘንድ ይድረስ»።

ቴዎድሮስ ደጋግሞ እስረኞቹን እንዴት ሊለቅ እንደቻለ አስረዳ። «በጣም ጥሩ፣ በእግዚአብሔር ኃይል አቶ ካሜሮንን ፊትቼ ለአቶ ራሳም ይመልከቱ፤ እርስዎ እንድለቅ የጠየቁኝን ሁሉንም አውሮጳውያን እስረኞች አስረከቢያለሁ። በእግዚአብሔር ኃይል ለቅቄ ወደሃገራቸው መመለስ ስፈለጉ አውሮጳውያን አስረክቢያለሁ። በጣም ጥሩ፣ በእግዚአብሔር ኃይል ሁሉንም ሰጥቻለሁ»።

ራሳም በድጋሚ ስሙን በአማርኛ ሰማ። አለቃ እንግዳ የንጉሡን ቃል ተቀብለው ይጽፋሉ፣ አቶ ሳሙኤል ትርጉሙን ቀጠሉ።

«የእርስዎን አገልጋይ አቶ ሆርሙዝድ ራሳምን ያቆየሁበትም ምክንያት እርስዎ ያሉትን በተመለከተ ከእርሱ ጋር ለመመካከር እና ከእርስዎም ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ነው። እርስዎ ከእኛ የሚፈልጓቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ከእርሱ ጋር እንመካከራለን። እኛ ኢትዮጵያውያን አላዋቂ እንደመሆናችን፣ ዓይናችንን ከፈቱልን፤ እግዚአብሔር በሰማይ ብርሃኑን ያብራልዎ»።

ይኸው ነው። መሄድ አይችልም። ራሳም ምርኮኛ ነው። ጥር ላይ ራሳም ያመጣው የንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ላይ ስህተት ተገኝቷል። ከቀረበለት የአማርኛ ትርጉም በመነሳት ቴዎድሮስ ራሳም «የፍቅር ካሣ» እንደሚሰጠው ተረድቷል። ይህም ማለት በእስረኞቹ ምትክ አንድ ውሊታ ወይም ስጦታ እንደሚሰጠው ጠብቋል።

ቴዎድሮስ አሁንም የሚፈልገው እና የሚያስበው ቴክኖሎጂ ነው። በዚያን ማሳካት ያልቻለውን በኃይል ለማግኘት። እንደሁልጊዜው አሁንም የሚፈልገው ጠመንጃ ፋብሪካ ነው። ጠብመንጃ ብቻ፣ ትልልቅ ጠብመንጃዎች፣ እናም እነዚህን መጠቀም የመቻል ብቃት ሥልጣኑን የማስጠበቅ ዕድል ይሰጠዋል። ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች እና ሠራተኞች ለዚሁ ሥራ እንዲረዱት ጠየቀ። ሁለት የጠብመንጃ ብረት አንጣሪዎች፣ አንድ የጦር መሣሪያ አዋቂ መኮንን፣የብረት ማቅላጫ መሠረትን መገንባት የሚችል፣ እና አስፈላጊ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ይዞ የሚመጣ፣ አንድ ወይም ሁለት ጀልባ ሠሪዎች፣ ጋሪ እና ለዚያ የሚሆን ነገር። እነዚህ ሲመጡ በመደሰትም ቴዎድሮስ በታላቅ አክብሮት እንደሚቀበላቸው እና ጥሩ ክፍያ እንደሚሰጣቸው ቃል ገባ። እንዲህ ያለው ቡድን ቢመጣ ሲያገ የሚችለውን ሥጋት በማመንም፣ «ወደ ሀገራቸው መመለስ በፈለጉ ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል አስፈላጊውን ክፍያ በመስጠት እና በታላቅ ክብር ወደሀገራቸው መልሼ እልካቸዋለሁ» ሲል ጻፈ።

ሠራተኞችን እና መግዛት የሚፈልጋቸውን ነገሮች የያዘው ዝርዝር ሲታይ፣ ለፋብሪካው አነስተኛ የእንፋሎት ሞተር፣ እንጨት ወይም ብረት ማስተካከያ ማሽን፣ ማጣሪያ ማሽን፣ የጠብ መንጃ አፈሙዝ መሥሪያ ማሽን ከነአስፈላጊው ተያያዥ ዕቃዎች ጋር፣ ደህና ቴሌስኮፖች (አቅርቦ መመልከቻ መነፅር) ባሩድ መፍጫ፣ ውብ ምንጣፎች፣ ሀሮች፣ ጠብመንጃዎች እና ሽጉጦች እንዲሁም ሁለት ጦሮች።

ራሳም በበኩሉ ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ዋና ኃላፊ ደብዳቤ ጻፏል። ቴዎድሮስ እንደሚያስነብበው ስለሚያውቅ ሆን ብሎ ቀና መልእክት አሥፍሮበታል። ራሳም የተደረገለትን ድንቅ አቀባበል አጉልቶ እንዲያሳይ በመገደዱ፣ ቴዎድሮስ የተለየ ክብር እንደሰጠው፣ እስር ቤት ድረስ ቴዎድሮስ ራሱ ሄዶ እንደጎበኘው በዚያም ላይ በሁሉም ረገድ ቴዎድሮስ ፍፁም ደግ እና እንግዳ ተቀባይ መሆኑን ገልጿል። በተዘዋዋሪ ግን« ከቡርንትዎ እንደሚረዱት በዚህች ሀገር በአሁኑ ሰዓት ሁላችንም ታሥረናል፣ ለወዳጅነት ሲባል» በማለት የሚገኙበትን ሁኔታ አመልክቷል። አሁን ንጉሡን የፈተነ ጉዳይ የደብዳቤው አድራሽ ነገር ነው። ከአውሮጳውያኑ አንዱን ለመላክ ፈልጓል፣ ግን ደግሞ መልዕክተኛው መመለሱን እርግጠኛ መሆን አለበት። ከሚስዮናውያኑ አንዱ የሆነውን ማርቲን ፍላድን ለዚህ ተልዕኮ መረጠ።

ፍላድም ቢሆን ከእንግዲህ ታማኝ አይደለም፣ ሆኖም ግን ሚስት እና ልጆቹ እዚሁ ይገኛሉ። በ1858 ሚያዚያ ማለቂያ ገደማ ከቀትር በኋላ ወደ ለንደን ለመሄድ ፍላድ ዘጊ ከሚገኘው የንጉሡ መንደር ተነስቶ ወደ ባሕር ጠረፍ ጉዞውን ጀመረ።



«ልቤ እየተናወጠ ውድ ሚስቴን እና ልጆቼን፣ እንዲሁም ሁሉንም ወዳጆቼን በጨካኙ፣ አረመኔው እና ብልጡ ቴዎድሮስ እጅ ጥያቸው ለመሄድ ተገደድኩ» በማለት የተሰማውን በወቅቱ ፅፎታል። ከነአገልጋዮቻቸው ከሠላሳ የሚበልጡት ታጋቾች ረጅም ጊዜ ለሚወስደው ጥበቃ ተደላድለው ተቀመጡ። ሽተርን ደግሞ በመታሠሩ ተበሳጭቷል።

«ከረዥም ጊዜ በኋላ በተገኘው ነጻነት ማግሥት የተሰበሰብንበት ተስማሚ መኖሪያ ያልሆነው ጊዜያዊ መንደር የሚያስጠላ ቤት ሆነ»። «ውጥመዳችን ወርቃማ ነበር፣ ግን ዞሮ ዞሮ ወጥመድ ነው ፣ በዚያም ላይ ከንጉሡ ጋር የነበረን ዝምድና በቋሚነት ከአሁኑ አሁን ምን ይደርስብን ይሆን የሚል ፍርሃት አሳድሮብናል» ብሏል ዶ/ር ብለንክ። ሌተናል ፕሪዶ በበኩሉ «ሀገራቱን በቶሎ እንለቃለን የሚለው ተስፋችን ቢሟጠጥም፣ ከብረነከ እጋጣሚ እንደማይኖር ጠብቀናል»።

ፕቡብ የተላበሰ ዲፕሎማሲ መጀመሪያ አካባቢ ለራሳም ስኬትን አረጋግጦለት ነበር። አሁን ደግሞ ውድቀት እና ፍርሃት ይታገለዋል። ብሪታንያ የቴዎድሮስን ፍላጎት ማሳካቷን ይጠራጠራል። ምንም እንኳን እሱ መንፈሱ እንደተረበሸ ባያምንም ሌሎች ግን ይህን አስተውለዋል።

«ለኩርፊህ የምታመጣው ምንም ጥሩ ነገር አይኖርም» አሉት የቴዎድሮስ የማደጎ እባት ከንቲባ ኃይሉ፣ የቴዎድሮስን ድንኳን የምትጋራው የተመኙ ጥምር«ነገሮችን በደስታ የምትቀበል ከሆነ የሚያስፈራህ አይኖርም። ንጉሡ ከምር ስለሚወድህ በመጨረሻ ነገሮች ይስተካከላሉ» አለችው።

## ምዕራፍ አርባ ሦስት

አሁን ጥያቄው ተፈትቷል፤ ራሳምን ከሚፈልግበት ስፍራ አስቀምጦታል። ቴዎድሮስ ተረጋግቷል። በየዕለቱ ለራሳም ሰላምታ ይልክለታል።

«እንዴት ነህ? ሌሊቱን እንዴት አደርክ? አብረውህ ያሉትስ እንዴት ናቸው?» የራሳም ድንኳን ምንጣፍ እንደሌለው በሰማ ጊዜ ራሱ ወስዶ አነጠፈለት። ወታደሮቹ እና ጠባቂዎቹ፤ እነሱ የሚያከብሩት የበላያቸው «ከተዋረደው» ራሱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ በግቢው ሲዘዋወር ሲመለከቱ ተገርመዋል። ቴዎድሮስ ከራሳም ማደሪያ ደጃፍ የነበረውን ጠባቂ «ከእሱ የምፈራው ነገር የለም» በማለት ዞር አደረገው። ጣቱን አንስቶ አፉ ውስጥ በመክተት «ሌላው ቀርቶ እፈልግ እንኳ አፌ ውስጥ ቢከት!» አለና ለጠባቂው አሳየው።

በመጨረሻም ኒሻኑን ለራሳም አበረከተለት። (አብሮ የታዘዘው መስቀል እና የሰለሞን ማሕተም እስካሁን አልደረሰም) የተጌጡ ጋሻዎች፣ ጦር እና ጎራዴዎች ለእሱ እና ለሌሎች ለሁለት ሰዎች ተሸለሙ። ለእያንዳንዳቸው ደህና ደህና በቅሎዎች እና ጠንካራ የኦሮሞ ፈረሶችም ተሰጣቸው። ቴዎድሮስ፤ ለመኝታ እንዲጠቀሙበት 20 ጥሩ ሸማዎችንም ለብሪታንያ ልዑካን ላከ። ራሳም መልበስ አልፈለገም ነበር፤ ነገር ግን ቴዎድሮስ «ለእኔ ሳይሆን ከርሷ ለወሰድኩት ለንግሥቲቱ ስትል ልበስ አለው»።

ግንቦት 24 (በአውሮጳውያን) የንግሥት ቪክቶሪያ ልደት መሆኑን ሲያውቅም መንግሥታዊ ሥራዎችን ወደ ጎን ብሎ ለግርማዊነቷ ደስታ ሲል አውሮጳውያኑን ሰብስቦ ድግስ አደረገ፤ 21 ጊዜም መድፍ ተተኮሰ። ራሳም፣ ብላንክ እና ፕሪዶ፤ ቫልድማየር እና ጋፋት የነበሩት ሚሲዮናውያን አዲስ የሠሩት ባለ ሦስት እፈሚ ጠብመንጃ ሲሞክር እንዲመለከቱ ጋበዛቸው። ጥይቱ ሲጮህ ቴዎድሮስ በደስታ ተንደርድሮ ሞሪትዝ ሃልን ግንባሩ ላይ ሳመ [illegible]። «የኔ ለማዳ ልጅ! የኔ ለማዳ ልጅ!» በማለት በደስታ ጮኸ። ከዚያም ቀጥሎ አለና በልጅነቱ በጠብመንጃ ያደረጋቸውን አስደናቂ ገድሎች በመተረክ ሁሉንም አፈዘዛቸው። እንዴት ወደ ንግሥናው እንደመጣ፤ ሙስሊሞችን ለማባረር ስለሠራው ፈንጂ… በሌላ ቀን ቴዎድሮስ ልዑካኑን ሁለት አዳዲስ ጀልባዎች ሲመረቁ ጋበዛቸው። ጣና ሐይቅ ላይ የሚጓጓዙት 3 ሰዎችን የሚጭኑት የደንገል ታንኳዎች ናቸው፤ ቴዎድሮስ ግን በእንፋሎት የሚሰራውን ጀልባ አስመስለው እንዲሠሩ በማድረግ ለማሻሻል ሞከረ። ጀልባዎቹ ከዳርቻው ላይ ለመንሳፈፍ ተዘጋጅተዋል።

ርዝመት እና ሥፋታቸው 60 በ20 ጫማ ይሆናል። ወለላቸው እንጨት ሲሆን ጎናቸው በሰንበሌጥ የተሠራ ነው። እንዲዘውራቸው ጥንድ መሪ ተገጥሞላቸዋል።



በውኃ እንዳይርሱ በመስጋት ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ልዑካኑን ከሐይቁ ዳርቻ እንዲቆሙ አስጠነቀቀ። እሱ እና ሌሎች 100 የሚሆኑ ሰዎች በመጀመሪያዋ ላይ ተሳፈሩ። በውኃ ላይ የተደላደለችው ጀልባ ለጊዜው መንቀሳቀስ ያልቻለች ብትመስልም ወደ ውኃው ዝቅ ብላ ዳግም ከፍ አለችና መቅዘፍ ጀመረች። ቴዎድሮስ ልክ እንደ ልጅ ፈነደቀ። ፈጠን እያለችም ወደ ሐይቁ መሐል ተጓዘች።

ወደ ሌላኛው መርከብ ገባ። ከሐይቁ ዳርቻ ስትወጣ የጀልባዋን የሰንበሌጥ ግድግዳ የሚገፋ ነፋስ ተሰማቸው። ነፋሱ ጠነከረ። እንጨቱ እና ሰንበሌጡ መለያየት ጀመሩ። ቀስ በቀስም ጀልባዋ መንኮታኮት ጀመረች። የተሳፋሪዎቹ እጆችም ወደ ዳርቻው ለመቅዘፍ ተፋጠኑ። ለወራትም ሁለቱም ጀልባዎች በውኃው ዳርቻ ተገትረው ተረሱ። ቴዎድሮስ በጣና ዳርቻ ለአደን ሲወጣ ራሳምን ያስከትለው ነበር። ዳክዬ እና ጅግራ እንዲሁም ጉማሬ ላይ ይተኩሳሉ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ራሳም ከረገጠው የውኃ ዳርቻ ተንሸራቶ ሊወድቅ ሲል ቴዎድሮስ ፈጠን ብሎ፤ «ተነስ የኔ ልጅ፤ ባንተ ፈንታ ጠላትህ ይሙት»ብሎ ደግፎ አነሳው። ራሳም ሁሌም በቴዎድሮስ የዕድሜ ሁኔታ እና በባዶ እግሩ በድንጋያማው ግዛቱ በፍጥነት ሲራመድ ያስገርመዋል። በዚያን ወራት ከሌሎች ተዋጊዎች ጋር ጉግሥ ሲጫወት ቢመለከተው ራሳም በእርሱ ተማረከ። እንደሌሎቹ አንድ ዓይነት ልብስ ለብሶም ከሁሉም ጎልቶ የሚታየው የእርሱ ተክለ ሰውነት ነው።

«በዚህ አጋጣሚ ቴዎድሮስ የሕዝቡ በተለይም የሠራዊቱ ተምሳሌት (ድንቅ) የሚያደርጉት በርካታ ተሰጥኦዎች እንዳሉት ማመን ተገድጃለሁ፤ እነዚያ ምርጥ ተሰጥኦዎቹ ሌሎቹ ላይ በጥሩ መልኩ ተፅዕኖ ማድረግ ቢችሉ የገዛ ሕዝቡ ከፋ አይሆንበትም ነበር»። ቴዎድሮስ ቁራዎችን በጥይት ሲመታ ተከታዮቹ የመጥፎ ነገር ገድ ምልክት አድርገው ነው የሚወስዱት። የፈረሶቹ አለቃ ራሳምን እንዲጋልብ ጋበዘው። ቴዎድሮስ የተከበረው እንግዳው በአካባቢው እንዲሆን አልፈለገም። በርካታ ባለስልጣናቱ በዚያን ወራት በጅራፍ ተገረፉ። እንዲት ሴት ባሏ ወደ አማፅያን ከድቶ በመሄዱ በግርፋት እስከትሞት ድረስ ተቀጣች። ቴዎድሮስ ራሱ እንዱን ገበሬ አንዴ አናቱን ቢለው ሞተ።

እስረኞቹ የራሳቸው ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል አውቀዋል። የሚሰጧት እንዴት አስተያየት እንደምታስወግዛቸው፤ በጻፉት ወይም በመጣላቸው ጽሑፍ ውስጥ የተገኘ ስድብ ምን እንደምታስከትል ያውቃሉ። አብዛኛውን ወረቀታቸውን አጥፍተዋል። በውኃ ከእንዲሰምጡ አድርገዋል ኀሚሱን በልተውታል፤ የቀሩትንም ለምግብ አብሳዮቻቸው እየሰጡ በእሳት አቃጥለዋል። ሲነጋገሩም የራሳቸውን መግባቢያ ቃላት ይጠቀማሉ። ቴዎድሮስን «ቦብ» ይሉት ነበር። ወደ ኢንግላድ በተላከው በፍላድ ላይ እጅግም ተስፋ ያደረገ ከመካከላቸው የለም። የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው በአብዛኛው በሞቀው የቴዎድሮስ መንደር እና በዙሪያው ባለው ማባሪያ ያጣ የአመፅ ጥቃት ላይ የተመረኮዘ ነው።

# ምዕራፍ አርባ አራት

በ1848 ግንቦት ወር አንድ ኅብኚ በድብቅ ዘጌ ወደሚገኘው የቴዎድሮስ መንደር ዳርቻ ሳይታይ መጣ። ሸተርን «ነጭ ፈረስ ጋላቢው» እያለ ነው የሚጠራው።

ከዚህ ቀደም ከአሥር ዓመት በፊት በትክክል እዚህ ነበር። እንደ አሁኑ ያኔም ቴዎድሮስ የከብቶች ዝርፊያ አድርጎ ነበር። በዚያም ላይ ያን ጊዜም ንጉሡ በጣና ሐይቅ ዳርቻ ላይ ሰፍሮ ነበር። በ1848 ግንቦት 23 በቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት «እግዚአብሔር ቁጣውን አውርዶ ወታደሮቹ ሁሉ ሞቱ»። ወዲያው ቴዎድሮስ ከብቶቹን ሁሉ ለየባለቤቶቹ መለሰ።

ዘንድሮ ግን በጣም ዘግይቷል፤ ከብቶቹ ሁሉ ተበልተዋል። ቴዎድሮስ ራሱን በራሱ በመከሰስ ፊቱን ወደ መዝሙረ ዳዊት አዞረ። ኢትዮጵያ ውስጥ «ዳለቻ ፈረስ ጋላቢው» ነፍጠኛ ፈንግል በመባል ይታወቃል። ምክንያቱም ሰለባዎቹን የነፍጠኛ ጠብመንጃ በሚያጠቃው ፍጥነት ነው የሚረፈርፈው። ይህም ኮሌራ ነበር።

ዶክተር ብላንክ ችግር እንደሚመጣ አስቀድሞ ተንብዮ ነበር። «ምንም አይነት የመፀዳጃ ሥርዓት በሌለበት ጥቅጥቅ ባለ መንደር ውስጥ ተፋፍጎ በመኖር ጤናችን ለአደጋ ይጋለጣል የሚል ፍርሃት ነበረኝ»።

አሁን የዝናብ ወቅት በመቃረቡ ሁኔታው የከፋ ሊሆን ይችላል። የንጉሡ ቤተሰብ ወደ ደጋማው አካባቢ መዛወሩን አሳውቆ ወደ ደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ። ቴዎድሮስ የተመኘን ብቻ አስቀርቶ፤ ሴቶቹን ከሐይቁ ማዶ አሻገረ። ያ ትልቅ መንደር ብቻውን ቀረ። በሺህ እና አስር ሺህ የሚገመተው ሠራዊት ምግብ እና መሣሪያውን ሸክፎ ለጉዞ ተጣደፈ። ከጀርባ የመጀመሪያዎቹን የበሽታ ሰለባዎች መቃብር እና የተወረረውን አካባቢ ትቶ ተጓዘ።

ጉዞው ብዙም ሳይቆይ የሲኦል መንደር መሰለ። ያልታሠረው እና ከሌሎቹ የጋፋት የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር የነበረው ቫልደማየር የታመሙትን እና የሞቱትን ያስታውሳል። ገሚሱ እየተወተረረ መሬት ላይ ይወድቃል።

«ብዙዎች እያለፏቸው ይጓዛሉ፣ ሽታው ያስፈራ ነበር፣ በዚያም ላይ ለሞቱት የሚወርደው ሙሾ ልብን ይሰብራል»።

ከሐይቅ ዳርቻ ሲደርሱ እና አባይን በተሻገሩበት ወቅት በየዕለቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ይሞቱ ነበር። በሰኔ ወር መባቻ በአንድ ምሽት ብቻ 300 የቴዎድሮስ ወታደሮች ሞቱ። ሌሎቹ 700 የሚሆኑት ደግሞ በበሽታው ተያዙ። ንጉሡ ከንቲባ ኃይሉን እና አንድ ዓይናው አጋፋሪ ጎለም (ገልሞ)ራሳምን እንዲረዱ



ላኳቸው። ሸተርን አጋፋሪ «አጠገቢ ለመፀዳዳት በተቀመጡበት በማይታየው ሽፍታ ተጠቅተው ድፍት ሲሉ ተመልክቻለሁ» ሲል ያስታውሳል። ብዙም ሳይቆዩ ሞቱ። ቴዎድሮስ ራሳም ከሞት በሚል ቀብሩን በተመለከተ ለአቶ ሰሎሞን ትዕዛዝ አስተላለፈ። ቆራጣ ውስጥ የቤተ ክርስቲያኑ መሬት በአዲስ መቃብር ተሞላ። የመንገዱ ዳርም አስከሬን በአስከሬን ሆነ። ከኮሌራ በተጨማሪ ፈንጣጣ እና ታይፈስ ሕዝቡን ያጠቃ ነበር። ሰኔ ኢጋማሽ ላይ አውሮጳውያኑ ከትንሿ ጋፋት ኮረብታ ሲደርሱ አብዛኞቹ አገልጋዮቻቸው ሞተዋል። እንዲያም ሆኖ ለቫልድማየር እና ለእደ ጥበብ ባለሙያዎቹ ወደ ቤታቸው የመመለስ ያህል ነበር። ራሳም፣ ብላንክ እና ፕሪዶ ደግሞ ወደ ቴዎድሮስ የኢንደስትሪ ማዕከል ሲመጡ የመጀመሪያቸው ነው። በዚያ በሚያማታው ነፋስ መካከል ቴዎድሮስ ቴብሪካዎቹን፣ መጋዘኑን፣ የሥራ ቦታውን እና ወፍጮዎቹን ያስጎበኛቸው ጀመር። እንዴያ ሞት ሞት በሸተታቸው ሰዓት ቴዎድሮስ ግን ከዚህ በፊት ስለተሠሩት የጦር መሣሪያዎች እና እንዲሠሩ ስላቀዳቸው ይዘረዝርላቸው ነበር። እሳት በሚነድበት በአንደኛው ስፍራ የራሳምን ብራንዲ እየጠጣ ግብር ስለማይከፍሉት ዘሮቹ እያወራላቸው አምስት ሰዓት ተቀመጠ።

ራሳም እንግሊዝ ፈረሶች እና የወንዶች ንብረት ለሆኑት ሁሉ ጠቃም ያለ ቀረጥ እንደምታስከፍል ነገረው። ቴዎድሮስ ፈገግ ብሎ፤ «አቶ ራሳም አቢሲኒያውያንን አታውቃቸውም። በቅሎ፣ ፈረስ እና የቤት ውስጥ መገልገያዎቻቸውን አስመልክቶ ቀረጥ ብጥልባቸው ማናቸውም ቢሆኑ እነሱን መጠቀም ይተው እና ራሳቸው የራሳቸው ባሪያዎች ይሆኑ ነበር»።

በቀጣይ ለጥቂት ወራት በዚህ ሥፍራ እንደሚቆዩ ቴዎድሮስ አስነገረ። ለራሳም ማረፊያ ቤት ሰጠው፤ እንዲያም ሆኖ ላይመቸው ይችላል በሚል ሌሊቱን ሲሰጋ አደረ። በማግስቱ ጠዋት ወደ ራሳም ማረፊያ ራሱ ምንጣፎችን ይዞ መጣ። እንግዳ ቤቱን በራሱ መቀመጫ አስዋበው፣ መሬቱን ጠርጎ አቧራውን በመስኮት ወደውጭ ደፋ።

ላለፉት ወራት የንጉሡን መንደር በሽታ እንደ ጅብ መንጋ ሲከተለው ሰንብቷል። ዶ/ር ብላንክም ረጅም ሰዓት አገልግሎቱን ቀጥሏል። «ከማለዳ እስከ ወድቅት ሌሊት ሕሙማንን መከታተል ነበረብኝ»። በተለይም አንድ ታማሚው አብዛኛውን ጊዜ ወስዶበታል፤ የቫልደማየር ባለቤት። በግማሽ ወገኗ ኢትዮጵያዊት የሆነችው የጆን ቤል ልጅ። ከታይፎይድ ትኩሳት ስትገላገል አሁን ደግሞ ድንገት በኮሌራ ተያዘች። የራሷ ስቃይ ሳያንስ ሴት ልጇን ሳታቋርጥ ትጣራለች። ሮዛ !ሮዛ !ሮዛ ! ብላንክ ስስ ልብ ያለው ቫልደማየር የሶስት ዓመቷን ሕፃን ወደ እናቷ እንድትቀርብ መፍቀድ እንደሌለበት፣ ካልሆነ ግን ለከፋው ችግር ከወዲሁ መዘጋጀት እንደሚኖርበት አስጠነቀቀ።

«ልቤ ተሰበረ፤ ዛፎቹ እና ቁጥቋጦዎቹ ሁሉ የሚጮኹ መሰለኝ» በውስጡ የተሰማውን ቫልድማየር በማስታወሻው አሥፍሯል። በማለት ጥቂት ቀናት ውስጥ በቫልድማየር ቤት ላይ የሞት ጥላ አንዣበበበት ወደዚህ በመ... ደብረታቦር ሁኔታው ተመሳሳይ ነበር፡ የዶ/ር ብላንከን ምክር ተከትሎ ቴዎድሮ... በመላው ሁሉንም ከዚያ ወደተለያየ አካባቢ በታተናቸው፡ ወታደራዊ መንደሩንም በዚህም የከፋው ወረርሽኝ አለፈ። ሱዛን ቫልድማየርም አገገመች። በተ... ሌሎቹ ጋፋት እንደደረሱም ቴዎድሮስ ጎበኛቸው። ራሳም ብዙ ቦታ ስለያዘ ... ከእርሱ ትንሽ ከፍል እንዲወጣ እና በቦታው ለእንግዶቹ በወንበር ላይ ቀይ ምንጣፍ እንዲዘጋጅ ሐሳብ አቀረበ። ራሳም እና ዙፋ...

ያን ጠዋት ቴዎድሮስ ግሩም የቀልድ ስሜት ተላብሶ ስለነበር ሁለቱ ረዘም ላለ ጊ... ተጨዋወቱ። ንጉሡ ስለ ድዮጋን ጠየቀ። «ለመሆኑ እብድ ነው ወይስ ከተለመደው ወጣ ያለ ሰው?» ታላቁ እስክንድር ድዬጋንን እንደጎበኘው እና ጥያቄ እንደጠየቀው ይነገርለታል።

«ምን ላደርግልህ ትወዳለህ?» ጠየቀ ታላቁ እስክንድር፤ «ከፀሐይ ውስጥ ውጣ፤ እኔም ላይ ጥላህን ማሳረፍህን ተው» ሲል ዲዬጋን መለሰለት።

«እኔ የእስክንድር ዘር ነኝ» አለ ቴዎድሮስ፤ የመቄዶኒያው ሰው አንድ ጊዜ የኢትዮጵያን ታላቅ ንግሥት ሕንደኬን ችሎት እንደጎበኘ ገለጸለት። ከንቲባ ኃይሉም መጽሐፉን እንዲያወጡ አዘዘ። ከንቲባ ኃይሉ ከንጉሡ የችሎት ሰዎች አንዱ ነበሩ። ከመጀመሪያ አንስተውም ቴዎድሮስን ይደግፉ ነበር። አሁንም ቢሆን «በሕይወት ያለ ምርጥ ሰው» አድርገው ይቆጥሩታል። ታማኝነታቸው ይበልጡን ከኀዘኔታ የመነጨ ነው። በጥንቃቄ መጽሐፉን ገለጡት።

የእስክንድር ጉብኝት ለኢትዮጵያውያን ጥቅሙ ከፍተኛ ነው። ቴዎድሮስ ለራሳም እንደነገረው በከፍተኛ አክብሮት የተያዘ ነው። በግዕዙ የተጻፈው ይህን አፈታሪክ የሚያትተው «ዜና እስክንድር» በብዛት ተሰራጭቷል። እስክንድር ንግሥት ሕንደኬን በጎበኛት ጊዜ በውበቷ በቁመቷ እና ልዑላዊ ገጽታዋ በጣም ተደነቀ እና አለቀሰ። ወደ ክፍሏ በቀይ ወርቅ ምንጣፍ ላይ እየመራች ወሰደችው፤ ግድግዳው በውድ ድንጋዮች የተጌጠ ነበር። ሰፊው አዳራሽ ግሩም ብርሃን ተላብሷል። ንግሥቷ ስትጓዝ መላው መኖሪያዋ በዝሆኖች ተጭኖ ይሄድና እሷ በፈለገችው ሥፍራ ላይ ይቆማል። ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት የወርቅ እና የከበሩ እንቁዎች ልብስ ነበር የምትለብሰው። በውብ ሽቱዎችና መዓዛም የተሞላ ነበር። እስክንድርን በእጇ እየመራች ወደ ክፍሏ ወስዳ አቀፈችው፤ የንግሥና ዘውድም ራሱ ላይ ደፋች። ያን ዕለትም እስከ ንጋት ድረስ ከእርሷ ጋር ተኛ። ቴዎድሮስ የሚለው ታሪክ መነሻው ይህ ነው።



ለስለስ ያለው የከንቲባ ኃይሉ ድምፅ የእስክንድርን ጀብድ፣ ያደረጋቸውን ጉዞዎች እንዲሁም ገነትን የቃኙ ሰፋፊ ዓይኖቹን ጉዞ ተረከ። እንደ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ከንቲባውም እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃሎች ይህን አፈ ታሪክ ያምናሉ። «ስለ ታሪኩ ምን ታስባለህ?» ቴዎድሮስ ራሳምን ጠየቀ።

በልቡ ራሳም «ግራ ኢጋቢ እና የማይታመን» ሲል አሰበ።

«እውነቱን ለመናገር ግርማዊነትዎ፤ እስክንድር ወደ ገነት ለመግባት መመኘቱ በልሀነቱን ያሳያል፤ ነገር ግን ወደ ምድር ደግሞ በመመለሱ ሞኝ ነበር» አለ። ቴዎድሮስ በሳቅ ፈነዳ። እንዳውም ከወንበሩ ሊወድቅ ነበር።

«ለመሆኑ በዚህ በማይረባ ነገር የማምን ይመስልሃል?» ከንቲባ ኃይሉ የሚናገሩትን አጡ።

# ምዕራፍ አርባ አምስት

በ1848 ሐምሌ መባቻ የለንደንን የአይሁድ ሚሲዮናውያን የሚመራው ሬቨረንድ ማርቲን ፍላድ ለንደን ደረሰ። በእጁም የጦር መሣሪያ ሥራ ባለሙያዎች እንዲላኩለት የሚጠይቀውን የቴዎድሮስን መልእክት ይዟል። የዲፕሎማሲው ቀውስ እና የተያዙት አውሮጳውያን ዕጣ ፋንታ በእሱ እና በያዘው ደብዳቤ ላይ የተመሠረተ ነው። በውልደቱ ጀርመናዊ የሆነው ፍላድ ከሌሎቹ አውሮጳውያን በበለጠ ለ12 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያ ውስጥ ቆይቷል። በመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የሄደው በሳሙኤል ጎባት ትዕዛዝ በ1846 ሲሆን ያኔ ቴዎድሮስ ገና ደጃዝማች ነበር። በቆይታው የቴዎድሮስን አሳዛኝ የሥልጣን ዘመን ከቅርብ አስተውሏል። ባለቤቱ ፓውሊን እና ልጆቹ ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆናቸውም የብሪታንያ መንግሥት ምናልባት ቴዎድሮስ ላይ ኃይል ሊጠቀም ይችላል የሚል ስጋት ሰቅዞ ይዞታል።

«ብሪታንያ አቢሲኒያ ላይ የጠብ እርምጃዎችን ለመውሰድ ብትሞክር እንደ ቴዎድሮስ ያለ ጨካኝ እና ርኅራኄ የለሽ ሰው የእኛን ሰዎች በሙሉ እርዶ ይፈጃቸዋል» ሲልም የጀርመን ቅላጼ በተላበሰው እንግሊዝኛው ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ አስረድቷል።

«ወይም ደግሞ ወደተራራዎቹ መካከል በመውሰድ ቁምስቅል ይፈፅምባቸዋል። ወታደሮቹ የእሱን ግዛት እንዲለቁ ይድፍ ዘንድ ቁም ስቅል ከማየት በአንዴ ተገድሎ መገላገል ይሻላል። እናም ከዚህ ሰው ጋር ሁሉንም ነገር በሰላም መጨረሱ ይመረጣል»።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአቢሲኒያ ጋር ያለውን ችግር በመጠነኛ መስዋዕትነት ለመቋጨት ሲልም ፍላድን በዕቅዱ መሠረት የብረታ ብረት ባለሙያዎችን እና አስፈላጊውን መሣሪያ እንዲያዘጋጅ ፈቃደለት። ምስኪኑ ፍላድ ግራ ገባው። ለለንደን እንግዳ ነው። ያለፉት 12 ዓመታትን በኢትዮጵያ ጫካዎች ነው ያሳለፈው። የታዘዘውን እንዴት ማከናወን እንደሚችል ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ምንም ነገር እንዳልተከናወነ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የነበረው ጀምስ መሪ ሲረዳም በጣም ተበሳጨ። ፍላድ አይረባም ሲል ጻፈ። እና በእሱ ፋንታ ለኮሎኔል ሜርዌዘር ኃላፊነቱን ሰጠ። ሜርዌዘር በወቅቱ በኤደን የብሪታንያ የፖለቲካ ወኪል የነበረ ሲሆን በአጋጣሚ በዚያን ጊዜ ለዕረፍት ለንደን መጥቶ ነበር።

እሱም ወዲያው ቴዎድሮስን ሊያስደስቱ ይችላሉ ያላቸውን ማሽኖች ሰበሰበ። ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ዝርዝር ዋጋቸውን እያይዞ አቀረበ።



ዕቃዎቹ ዝርዝር መካከልም በእንግሊዝ የሚሰራ ሞተር ከነማሞቂያው፣ ማርበሪያ፣ የብሉን ማጥበቂያዎች፣ ባሩድ፣ የጅ ባትሪዎች፣ ቴሌስኮፕ እና ሌሎች ለጠመንጃ መሥሪያ የሚያገለግሉ ነገሮች ተካተዋል። በዚያም ላይ ሽጉጥና ጠመንጃዎችም አሉ። ቴዎድሮስ ከ16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለውን ገጽታ ማየት የሚያስችል ቴሌስኮፕ ማግኘት እንደሚፈልግ በደብዳቤው ላይ ጽፏል። ... ይህ እንዲካተትለት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

በዚያም ላይ በባለሙያነት የሚላኩ ሰዎችን ከተለያዩ ዘርፎች መለመለ። ለእጅ ሙያዎቹ የሚከፈል ደሞዝ እና በአቢሲኒያ ተራራዎች ላይ ለሚደረገው ጉዞ የሚያስፈልግ የወጪ መጠን በአጠቃላይ ወደ 3,500 ፓውንድ አቀረበ። ዝርዝሩ ... ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ... የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በርከት ያሉ ወንዶች ... የተልዕኮውን አስፈላጊነት አስተዋለ። ... መሪነታቸውን ሲመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ ... ችግር እምብዛም የማያሳስብ ... እስከዚያን ጊዜ ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ችግር ... በሀገሬው ገዥዎች መካከል የተፈጠረ ... እና በቆንስሎቻቸው እና ... ያለመግባባት እድርጎ ነበር ሲመለከተው የቆየው። አሁን ግን ጥርጣሬ ... እነዚህን ሰዎች ከማሰርና ተጨማሪ ጥያቄ ከማቅረብ ምን የሚያግደው ነገር አለ? ቴዎድሮስ የብሪታንያን ልዑካን እንዲለቅ ምን አይነት ማበረታቻ አለ? ... በሚገኙ ተራራዎች መካከል የብሪታንያ ህብቶች ሁሉ ያለ ዋጋ ... ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ግብዖች ወደ ኢትዮጵያ እየተንቀሳቀሱ ነው የሚለው ... ለንደን ደረሰ። አንድ የብሪታንያ ባለሥልጣን »ለተራራ ላይ ውጊያ ... የሆኑ» የጦር መሣሪያዎች ግብፅ ውስጥ ባቡር ላይ ሲጫኑ፣ ወታደሮችም ... በኢትዮጵያ የድንበር አካባቢ ግዛት ቦጎስ ላይ ሲንቀሳቀሱ ተመልክቷል። ... ሜርዌዘር የተገፋው ፍላድ እነዚህን እንቅስቃሴዎች እየተከታተለ መቁነጥነጡ ... ቴዎድሮስን እና ሀገራቱን እንደሚያውቅ ሰው የብሪታንያ ቸልተኛነት ... ለታሰሩት አውሮጳውያን እስከፊ እና የግብፅ ጠብ አጫሪነት ለቤተሰቦቹም ሆነ ... እንደሚሆን ስጋት አድሮበታል።

## ምዕራፍ አርባ አምስት

ለአንድ ዓመት ከዚያም በላይ ግብፃውያን ወደ ደቡብ ሲገፉ ቆይተዋል።በተዋበው የባሕር ድንበር አካባቢም የእቶ ማገን ፍላጎት ለማስፋፋት ቃል ገቡ፤ የቴዎድሮስ ኃይል መመናመንም ለሌሎች በርካታ ዕድሎችን አመቻችቷል። የዋግ ሹም ጎበዜ ተፅዕኖ በትግራይ እና በሰሜን አካባቢ ከፍ እያለ በመሄዱም፣ ለግብፃውያን በሚጠቅም መልኩ የቴዎድሮስ ይዞታ በዚህ አካባቢ እንዲቀንስ ረድቷል። [illegible] ስጋት ትክክል ነበር።

በ1858 የክረምት ዝናብ እስኪጀምር ድረስ ቴዎድሮስ አውሮጳውያኑን በንቃት እየተከታተለ በጣም ደግ ሆነላቸው። በሰኔ ወር ማለቂያ ገደማ አንድ ቀን «የፈጣሪ ያለህ! እንዴት እኛ አቢሲኒያውያን ብዙ ሺህ መጽሐፍ ቅዱሶች የሰጡንን ብሪታንያውያንን እንዴት እንረሳለን?» አለው ቴዎድሮስ ለራሳም። ሆኖም ብዙም ሳይቆይ ከኢየሩሳሌም የመጣ ካህን «የባቡር ሃዲድ ከቀይ ባሕር ዳርቻ [illegible] አቋርጦ ከሰላ ከተማ ድረስ መሠራቱን» የሚገልፅ አሳሳቢ ዜናዎችን ነገሩት። የቴዎድሮስ ጥርጣሬ አሁን ግልፅ ወጣ፤ ግብፆች ከብሪታንያ ጋር በመተባበር ክርስቲያኗን ኢትዮጵያን እስከ መጨረሻው ለመንጣል ወታደሮችን ወደ ደቡብ የሚያጓጉዝ የባቡር ሃዲድ ሠርተዋል። አሁን የራሳምን ተልዕኮ እውነተኛ ፍላጎት ተረዳ። የባቡር ሃዲዱ የእሱን ግዛት ለማንኮታኮት የሶስትዮሽ ትብብር መገለጫ ነው፤ የውጭ ወረራ፣ የባለሥልጣናቱ መክዳት እና የአውሮጳውያን መንታ ገጽታ። ቴዎድሮስ የራሳምን ቡድን ሰበሰበ። የተመኙ በምትገለገልበት ከጥቁር የፍየል ቆዳ በተሠራው ድንኳን ውስጥ ተሰበሰቡ። ቴዎድሮስ ራሱ ሳይሆን በአፈ ንጉሡ አማካኝነት ክሳቸውን አስደመጣቸው። ከቀትር በኋላ በነበረው ጊዜ መልእክተኞች ከቴዎድሮስ ማረፊያ ወደዚህኛው ድንኳን ሲመላለሱ ዋሉ።

የባቡር ሃዲዱ የግብፅ ወታደሮችን ወደ እርሱ ድንበር የሚያጓጉዝ አይደለምን? ይህስ እንግሊዝና ፈረንሳይ በእሱ ላይ የጀመሩት ዘመቻ ማሳያ አይደለምን? አንተ ወዳጄ ራሳም የዛሬ ስድስት ወር በከሰላ በኩል አልፈሃል እና ለምን ይህን ሳትገልጽ ቆየህ? ይህ አንተ ለእኔ የገባኸውን የጓደኝነት ቃል ኪዳን የሚጥስ አይደለምን? እንግሊዞች እውነተኛ እንዳልሆኑ እና እኔን ማታለላቸውንስ አያረጋግጥም?

ራሳም ክሶቹን ሁሉ ውድቅ አደረገ። ለቴዎድሮስ ምንጊዜም ቢሆን ታማኝ እንደነበር ገለፀ። ስለባቡር ሃዲድ ምንም እንደማያውቅም ተናገረ። እነዚህ መረጃዎች ተንኮል ያሰቡ ደካሞች የፈጠሯቸው ናቸው። በአንድ ወቅት ቴዎድሮስ ራሳም እስረኞቹን አስፈትቶ ከሀገሩ ከወጣ በኋላ የብሪታንያ ጦር ወርሮ እርሱን እንደሚያጠቃ ሰምቶ ነበር። «ይህ እውነት ነውን?» ጠየቀ።



ራሳም በበኩሉ፣ «መረጃውን ሐሰት እና መጥፎ ነው» ብሏል። ያን ዕለት እሬ. ንጉሡ በሁለቱ ድንኳኖች መካከል በመመላለስ ሥራ በዝቶባቸው ነው የዋሉት። በአንድ ወቅት በሸተርን እና ሮዘንታል ላይ የደረሰውን ስለሚያውቁም በአንድ ነጥብ ላይ ፍትሐ ነገሥት ሲጠቀስ ሁሉም ከባድ ፍርሃት አደረባቸው። በመጨረሻም በእጅ አዙር የተካሄደው ችሎት የከፋ ነገር አላስከተለም። የቴዎድሮስ ንዴት በመብረዱ ም የራሳም መከላከያ በንጉሡ ነገሥቱ ወገን በቀና ተወሰደ።

«አንደበትህ ጣፋጭ ነው አንተም ጥሩ ሰው ነህ። ነገር ግን ካንተ በላይ ያሉት መኮንኖች ናቸው» አለው ንጉሡ ነገሥቱ። ጥበቃው ጠነከረ። አውሮጳውያኑም በደብረ ታቦር ላይ ተወሰኑ፤ ራሳቸውን እንዳያጠፉም መሳሪያቸው ተወሰደ። ቴዎድሮስ ለራሳም የሚያደርገው እንክብካቤ ወደ ውዴታ ተመለሰ። አልታሰረም፤ እንደውም ቴዎድሮስ ወደ ከተማ እንዲወጣ ያበረታታው ነበር።

«እዚህ ቆይተህ ብታዝን በሽታ ላይ ልትወድቅ ትችላለህ፤ ከዚያ በኋላ እኔ ወዳጅህ ምን ይውጠኛል? እኔም መታመሜም አይደል?» ይለዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ታዲያ የቴዎድሮስ ቁጣ እየናረ ሄዷል። በዋግ ሹም ጎበዜ ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ለማካሄድ አቀደ። በዚህ ወቅትም የዋግ ሹም ሠራዊት ከቴዎድሮስ እኩል ሆኗል ግዛቱም እንዲሁ። የዋግ እና ላስታ ገዢዎች ዘር በመሆኑም ከቋራ ከመጣው ይልቅ ዙፋኑ ለሱ ይገባል የሚሉ ብዙዎች ነበሩ።

በየዕለቱ ቴዎድሮስ ዋግ ሹም ላይ ለመዝመት ክተት ያውጅ እና በሙተው ድንኳኑ መልሶ ይተከላል። አሁን ቴዎድሮስ መወሰን እያዳገተው ነው። በአንድ ወቅት ትዕዛዝ ከእሱ ሲወጣ ሀገሩን ከዳር እስከ ዳር ያዳርስ የነበረው ቴዎድሮስ አሁን የድርቅ ዘመን ላይ የደረሰ መስሏል። የከበቡትን የአማፅያን፣ የግብፆች እና ራቅ ሲልም የአውሮጳውያንን ኃይሎች በቀላሉ መዘንጋት የማይታሰብ ነው። በዚያም ላይ የተለያዩ የራሱን ስሜቶች የመቆጣጠሩ ሁኔታም ሌላ ጉዳይ ነው።

በሰኔ ማለቂያ አንድ ጠዋት ለራሳም እንዲህ ሲል ጻፈ፣ «ጓደኛዬ ነህ እወድሃለሁ፣ ባንተ ፈቃድ የልጆቼን ሥራ ለመመልከት ወደ ጋፋት እሄዳለሁ»።

# ምዕራፍ አርባ ሰባት

ያን ዕለት ጠዋት ቴዎድሮስ እና ተከታዮቹ ከደብረታቦር ተነስተው የልጆችን ሥራ ለመመልከት ወደ ጋፋት ሄዱ። ጉዞው ከጥቂት ሰዓታት በላይ የሚወስድ ባይሆንም ቴዎድሮስ በፊት እጅግም የማይወደው ጉዞ ነበር። እሱ ከሚወዳቸው ችሎት እና ጉዳይ አስፈጻሚዎች ከሚገኙበት አካባቢ በተቃራኒ ጋፋት ከሚኖርበት እና ጥላቻ ነጻ ሥፍራ ይመስላል። ከቫልድማየር ጋር ከባለ ሁለት ደርብ ቤቱ ፊት ለፊት በመቀመጥ ስለመጽሐፍ ቅዱስ እና ቴክኖሎጂ መከራከር፤ ወይም የሀገሩን እድገት የሚመለከቱ ሐሳቦችን በማንሳት፣ ወይም ሁለቱም ስለሚያውቁት የሳይንስ ግኝት በመነጋገር ጊዜውን ያሳልፋል።

በንጉሡ ጋባዥነት ጋፋት በሚሲዮናውያን የሚንቀሳቀሰውን የመድፍ ፋብሪካ የጎበኘው ሄንሪ ዳፍተን ገና ወደ ሀገሪቱ መግባቱ ነው። ቴዎድሮስም ከደብረ ታቦር ከነአጃቢዎቹ ተነስቶ በባዶ እግሩ ቁልቁል በድንጋያማው መንገድ በፍጥነት ጉዞውን ጀምሯል። ከኮረብታው በታች ሲደርስ ዳፍተን እየተመለከተው ፈረሱ ላይ ወጣ። ፈጥሮኖ በቀላሉ ርካቡን እንኳን ሳይረግጥ ኮርቻው ላይ ተቀመጠ። ከዚያም ንጉሡ ፈረሱን ሽምጥ ያስጋልበው ጀመር። ግልቢያው ከችሎታ ታዳሚዎቹ አንዱ ከሆነው ሰው ጋር የፉክክር እና የመባረር ዓይነት ነበር።

ያንኑ ቀን ከቀትር በኋላ ከሚሽነሪዎቹ የአንዱን ልጅ አንገት አቅፎ ሲያወራ የተመለከተው ዳፍተን እንዲህ ሲል ጻፈ። «በፍጹም፣ ቴዎድሮስ ሙሉ በሙሉ ሰይጣን አይደለም! እርሱን ደህና አድርገው እና ለረዥም ጊዜ የሚያውቁት በሰለሉ እምንታዊ አማኝነታቸውን የሰጡትም ለዚህ ይሆን?»

ቴዎድሮስ ወደጋፋት በዝምታ ተጓዘ። ደብረታቦር ከጀርባው ቆሟል። ከፊት ለፊት ደግሞ የንጋት ፀሐይ ደምቃለች። ከዘጌ ከተመለሰ ጀምሮ ንጉሡ በዋግሹም ላይ ሊከፍት ስለፈለገው ዘመቻ ከነቫልድማየር ጋር ሲወያይ ቆይቷል። መድፍ የሚሸከሙ ጋሪዎች ያስፈልጉታል፤ ጉልበት በሚሰብሩት የላስታ ጎዳናዎች ላይ ደግሞ ጋሪዎቹን የሚሸከሙ በቅሎዎች ያስፈልጋሉ። ደብረታቦር ላይ ስለዘመቻው የሚ ለው ጋፋት ላይ ካልተለወጠ ጉዳዩ እውነት ነው ማለት ነው።

ሆኖም ግን ያን ዕለት ጠዋት ጋፋት ንዴቱን ሊታስግስ አልቻለችም። ቴዎድሮስ የመሣሪያ ፋብሪካውን ተመልክቶ ሲወጣ አንድ የእኔ ቢጤ ወደ እርሱ ቀረበ። «አውሮጳውያን ጌቶቼ ለእኔ ደጎች ነበሩ፤ የኔ ንጉሥ እርስዎም ችግሬን ሊያስወግዱልኝ ይችላሉ »በማለት ለመነ። ንጉሡ ወደ ለማኙ ዞረ እና «እንዴት ብትደፍር ነው ከእኔ በቀር ሌላውን ጌታዬ የምትለው?!» ሲል ተቆጣው። ተከታዮቹም እንዲገርፉት አዘዘ። «ይማሩኝ! ይማሩኝ!»ጮኸ። ያረፈበት ዱላ ወዲያው ከዚህ ዓለም ጉስቁልና አሳረፈው።



ቴዎድሮስ ወደ ሮዘንታል ዞረ። በእጁ የያዘው ጠብመንጃ ተንቀጠቀጠ። «እህያ! ለምን የድሀ ሴት ልጅ አልከኝ?» አፈጠጠበት ብላንክ ጠብመንጃው ላይ ነው ተሰከረ። «በሆነው ቅፅበት የሚወረውረው መሰለኝ»። ብላንክም ዓይኑ አጃቢዎች በፊጥኝ ተይዟል። የቴዎድሮስ ቁጣ ከቁጥጥር ውጪ መሰለ። በንጉሡ አውሮጳውያኑ ላይ ተፋባቸው። «እንዴት ብትደፍሩ ነው ራሳችሁን ባርቾ!» ... «ዶክተሮች የምትሉት?»

ቴዎድሮስ! ብላንክ እና ሮዘንታልን ወደ ደብረ ታቦር ይዞ ተመለሰ። እቶ ብሎ አልጋም ራሳም፣ ፕሪዶ፣ ካሜሮን እና ሽተርንን እንዲያመጡ አዘዘ። ከታቸው እየተጎተተ አውሮጳውያኑ ተጣድፈው መጡ። ንጉሡ ከፍ ብሎ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ባለሥልጣናቱም ከበታቹ ከበውት አገኙት። ራሳም፣ ሮዘንታል እና ብላንክ ተይዘው ሲመለከት አንድ ነገር እንዳለ አወቀ። ሁኔታውን ሲያስተውል «ቴዎድሮስ ያበደ ይመስል ነበር» ይላል። ቁጣው የምር ይሁን የማስመሰል መለየት አልቻለም። ዶ/ር ብላንክ የቴዎድሮስን ቁጣ እንዲህ ይገልጸዋል፤«ጥቁር ነገር እመድማ ይመስላል፣ ዓይኑ ደም ይረጫል፣ እሳት የለበሰ ይመስላል፣ ስስ ከንፈሩ ይጠብቃል፣ አፉ አረፋ ይደፍቃል፣ ፀጉሮቹ የቆሙ ይመስላል»። ቴዎድሮስ ብቻውን ድንጋዩ ላይ ተቀምጦ በጦሩ ጫፍ ድንጋዩን ይጠርባል። ከበታቹ ያሉትን የሚያውቃቸውን አውሮጳውያን ገረመማቸው። ሽተርንን እየተመለከተ፤ «እኔን ያዋርድከኝ በከርስቲያናዊ፣ አረማዊ ወይስ አይሁዳዊ ልማድ ነው? መጽሐፍን ስትጽፍ በማን ኃላፊነት ይህን አደረግህ?»

በዚያን ዕለት ከእሱ አምንታዊ ደብዳቤ ወደ ደረሰው ወደ ራሳም ዞር አለና «አንተም አዋርደኸኛል» አለው። «እኔ?!»

«አዎ አንተ! በአራት ጉዳዮች»

በመጀመሪያ ቴዎድሮስን የሚሰድበውን የሽተርንን መጽሐፍ አንብቧል፤ ያም በራሱ ስድብ ነው። በመቀጠል ደግሞ እስረኞቹ ከመሄዳቸው በፊት ከእርሱ ጋር እርቅ እንዲያደርጉ አላመጣቸውም። ሶስተኛ፤ የራሳም መንግሥት ኢየሩሳሌም በቱርክ መወረሯን ተቀብሏል። እዚያ ደግሞ የእርሱ ውርስ ይገኛል።

አራተኛውን ዘነጋሁት። ድንገት ድምፁን ከፍ አድርጎ፤ «አውሮጳ በቅድስት ሀገር ይዞታዬን እንድታስከብር እፈልጋለሁ» አለው። ራሳም ሁሉንም አዳመጠ። እስረኞቹ በንጉሡ ፈቃድ ሚያዝያ ወር አጋማሽ ላይ ቆራጣን ለቀው መውጣታቸውን፤ኢየሩሳሌምን በሚመለከት ደግሞ አውሮጳውያን ኃይላት ጣልቃ የመግባት መብት እንዳልተሰጣቸው ለማብራራት ሞከረ።

«አቶ ኮከብ፤ታሪክ ታውቃለህ፤ ኢየሩሳሌም ውስጥ ውርስ እንዳለኝ እና እንደ ሌለኝ ልትነግረኝ ትችላለህ?»

«ኢየሩሳሌም ገዳም ውስጥ የሚኖሩ አቢሲኒያውያን እንዳሉ አውቃለሁ» መለሰ ሽተርን።

"ለመሆኑ ሕንድና ከፊል ዓለም የእኔ ግዛት መሆኑን አታውቁምን?" ቴዎድሮስ በዙሪያው በተሰበሰቡት ላይ ጮኸባቸው። ድምፁ በድንጋዮቹ፣ በኮረብታዎቹ ጫፍ ፣ እንዲሁም በዙሪያው ተሰብስበው በሚያፈጡበት ወታደሮች፣ የችሎት ሰዎች፣ ሚኒስትሮች እና አውሮጳውን መካከል እንደ ገደል ማሚቶ አስተጋባ። ትንፍሽ አላሉም። አንዱም እንኳ ሊናገር አልደፈረም።

ቴዎድሮስ አውሮጳውያኑ እንዲያዙ ትዕዛዝ ሰጠ። 15 ጠባቂዎች ወንዶቹን በልብሳቸው ጫፍ እንጠለጠሏቸው፣ እየመሩም ወደ ጠባብ እና የሚ ሽት ክፍል አስገቧቸው። መስኮት የለውም። አንድ ወይም ሁለት ሻማዎች ቀን እና ማታ ቢጫማ ብርሃናቸውን በጥቅጥቁ ጨለማ ውስጥ ጭልጭል ያደርጋሉ። ፕሪዶ እንደጻፈው በዚህ ሥፍራ ነው የእውነተኛ እሥራትን መራርነት ለመጀመሪያ ጊ የቀመሱት። ራሳም ግምጃ ቤት ነበር ይለዋል። ለፕሪዶ ከስ ደግሞ መጋዘን ወይም ዕቃ ቤት ነበር። ብላንክ «ወደ ታች የወረዳ ጥቁር ቤት» ብሎታል።

ለሦስቱ የብሪታንያ ልዑካን አንድ የሽግግር ሂደት ነበር። በስድስት ወራት ውስጥ ከአከብሮት ወደ ውርደት፤ በጥር መጨረሻ ገደማ በ10,000 ፈረሶች በሐይቁ ዳርቻ በደስታ እና በስጦታዎች አቀባበል የተደረገላቸው እነዚህ ልዑካን ለመጀመሪያ ጊዜ ሚያዝያ ላይ ታሠሩ። አሁን ደግሞ ወደ ሙሉ እሥረኛነት ተሸጋገሩ። በዚያን ዕለት ምሽት ራሳም ለንጉሡ መልእክት ላከ። «ገና ከምፅዋ ስንነሳ የተነገረንን አለማመናችን የእኛው ጥፋት ነው ፤ ቢሆንም ግን የግርማዊነትዎ ጠላቶች ስለ እርስዎ ለሚሉት ዋጋ ልንሰጠው አልቻልንም»።

«ጠላቶቼ በጭንቅላቴ እንኳ ብሸከማችሁ ስለእኔ መጥፎ ወሬዎችን ማሠራጨታቸውን አይተውም።" የሚል መልስ መጣለት። እንደተለመደው ቴዎድሮስ ንዴቱ፣ ፀፀት እና ስሱነትን ትቶለት በረደ። ራሳምን ማየት ፈለገ። በግል ድንኳኑ የተመኙ ንጉሡ አብሯቸው እንዲቆይ ለመኑ። እሱ ግን ያንኑ ዕለት ማታ ወደራሳም መልዕክተኛውን መልሶ ላከ።

«አንተ ወዳጄ መከፋትህን እያወኩ እንዴት እኔ እተኛለሁ?»

በዚያን ዕለት ምሽቱ ገፋ ሲል ጠባቂዎች በሩን ከፈቱ እና ንጉሡ ወደዚያች ጠባብ መስኮት አልባ ክፍል ገባ። በቀኝ እጁ ሻማ ይዟል። በትከሻው የአረቄ ኮዳ



ተሸክሟል። ከጀርባው አስተናጋጅ ጠጅ ይዞ ተከትሏል። ጠባቂዎቹን አሰናበተ እና ተቀመጠ። በሩን ዘግተው ሲወጡ ነፋሱ የሚያውለበልባቸው ሻማዎች ቀጥ አሉ። ፈገግ እያለ አረቄ ቀድቶ ለራሳም ሰጠው።

«እንደማትጠጣ አውቃለሁ፤ ሆኖም እንዲህ ባለው አጋጣሚ እኔን ደስ እንዲለኝ እምቢ እንደማትለኝ እርግጠኛ ነኝ»። መለኪያዎቻቸውን አጋጩ፤ ቴዎድሮስ ደጋግሞ ጠጣ እና ለብላንክ እና ፕሪዶም ሰጣቸው። ከፍተኛ ክስ የቀረባበቸው ሽተርን እና ሮዘንታል ቆመዋል።

«አቶ ኮከብ እንደምን አለህ?» ንጉሡ በትከሻው አሻግሮ ጠራው። «ምነው ጠፋህ ትመስላለህ?» ቴዎድሮስ እየሳቀ «አታልቅስ በለው» አለው ለራሳም።

ከዚያም ኮስተር አለና ራሳምን ይቅርታ ጠየቀው። «ፊቴን ሳይሆን ልቤን ተመልከት፤ ምክንያቱም ከምር እወድሃለሁ»። በዚያች ክፍል ብቻውን ያለጠባቂዎቹ በተራ አለባበስ የተገኘው ቴዎድሮስን ሲመለከቱት በቀላሉ ለጥቃት የተጋለጠ ይመስላል።

«አባቴ እብድ ነበር» አለ በለሆሳስ። «ሰዎች እኔንም ብዙ ጊዜ እብድ ይሉኛል። አላመንኩም ነበር፤ አሁን ግን እውነት መሆኑን አወቅኩ»።

«እንዲህ ያለ ነገር አይናገሩ» ራሳም ተማፀነ ። ቴዎድሮስ ተነስቶ ቆመ። በለሆሳስ « እብድ ነኝብሎ ወደበሩ ዞረ፤ እነሱን መለስ ብሎ እያየ ደህና ሁኑ» ብሏቸው ወደ ጨለማው ወጣ። ከ21 ወራት በኋላ ነው ድጋሚ ያያቸው።

# ምዕራፍ አርባ ስምንት

ለንደን፤ ከኢትዮጵያ የተምታታ ዜናዎችን የምትሰማበት ወቅት ነበር። በሚያዝያ፣ የራሳም ተልዕኮ መሳካቱ እና እስረኞቹም መለቀቃቸው እሱም እነሱን ይዞ ወደ ሀገር ለመመለስ እየጠበቀ መሆኑ ተሰማ። በመቀጠል ደግሞ መታሠራቸው ተነገረ። በመጨረሻም መስከረም ላይ ሁሉም የመታሰራቸው ወሬ መጣ።

ማርቲን ፍላድ ከጋፋት በሰኔ ወር መጨረሻ ከባለቤቱ የተጻፈ ደብዳቤ ደረሰው፡ «ውድ ማርቲን፤ በጥቂት ቃላት አሳዛኙን ገጠመኞችን ልግለጽልህ። የአሁኑን ይዞታችንን እና የወደፊት ቀፋፊ ዕጣ ፈንታችንንም ልንገርህ» በማለት ከጣና ሐይቅ አካባቢ ከለቀቁበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን በዝርዝር ተረከችለት። በኮሌራ ምክንያት አብዛኞቹ ሰራተኞቻቸው እና ሃይማኖታቸውን የለወጡት ማሊቃቸውን አወጋችው። ከሁሉም ግን አሳሳቢው የራሳም መታሰር ነው። ብሉምስበሪ ላይ ተቀምጦ ደብዳቤዎን ያነበበው ፍላድ ድንገት ቴዎድሮስ ምን ያህል እየወደቀ እንደሆነ ታየው። ደብዳቤዋን ስታጠቃልልም፤ «ዳግም እንገናኝ ይሆን? ወይንስ በዚያ የሐይቅ ዳርቻ የተለያየነው ለዘለዓለም ይሆን?»አለች።

ለንደን ላይ ሆነው የቀውሱን ሁኔታ ለሚከታተሉት የቴዎድሮስ አውሮጳውያን በኃይል ማሠር ድንጋጤ ፈጥሯል። ወታደራዊ ርምጃ መውሰድ የሚለው ሐሳብ ከፍ አለ። ሌላው ቀርቶ ፍላድም ጭምር የብረታ ብረት ሥራ ባለሙያዎቹን መላኩ ምንም መፍትሔ እንደማያመጣ ተረዳ። የቴዎድሮስን ድጋፍ ለማግኘት ከኢየሩሳሌም ከተባረሩት መነኮሳት ጎን ሆኖ መርዳቱ የተሻለ እንደሚሆን ሐሳብም አቀረበ። ሆኖም ግን፤ «ይህ ሁሉ ተደርጎ ንጉሡ በጀመረው የሚገፋበት ከሆነ የሚያስከትለው መዘዝ ምንም ይሁን ምን በመሣሪያችሁ አጥቁት» የባለቤቱ ደብዳቤ ተተርጉሞ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ታትም በሎርድ ደርቢ ካቢኔ ፊት ቀረበ። ካቢኔው ኃይል መጠቀም በሚለው ላይ አልተስማማም። ድርድር ለማድረግ በሚለው ተስማማ። ፍላድ የብረታ ብረት ሠራተኞች እና ማሽኖቹን እንዲሁም የንግሥት ቪክቶሪያን ደብዳቤ ይዞ ወደ ምፅዋ ይሄዳል። ወደ ደጋማው አካባቢ ወደ ቴዎድሮስ ብቻውን ይሄድና፤ የመጣለት ዕቃና ባለሙያዎች ወደ እሱ የሚመጡት የታሰሩት ተለቀው ሲሄዱ ብቻ እንደሆነ ያስረዳል።

በመካከሉም ፍላድ ያቀረበው ሐሳብ መጣ፤ የመነኮሳቱ ጉዳይ በወቅቱ የነበረው የሃይማኖት ክርክር እና ከፍፍል እንዳለ ሆኖ በቁስጥንጥንያ የአርሜኒያ ፓትሪያርክ በኦቶማን ሥር ወደሚገኘው የብሪታንያ አምባሳደር ሎርድ ሊዮን ቀረቡ፡ በቴዎድሮስ እና በእነሱ መካከልም በሽምግልና መግባት እንደሚችሉ አስታወቁ። ሎርድ ላየንስ ጉዳዩን ኢየሩሳሌም ወደሚገኘው የብሪታንያ ቆንስላ አስተላለፈ። በዚያን ጊዜ አርመናውያን ኦርቶዶክሶች የኢትዮጵያን መነኮሳት በኢየሩሳሌም



ይሰጡ ነበር። በግብፅ ቅብጥ ኦርቶዶክሶች ለተባረሩት፣ ቤት እና ምግብ ላጡት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ካላቸው ያካፍሉ ነበር። ከኢየሩሳሌም የአርመን ፓትሪያርክ፤ አንድ ሊቀጳጳስ፣ አንድ መነኩሴ እና አንድ ረዳት በማድረግ ወደ ኢትዮጵያ ከላኩ በኋላ ይህን መልዕክት ለብሪታንያ ጻፉ። «ይህን አስቸጋሪ ተልዕኮ ለመቀበል ለብሪታንያ መንግሥት ካለን ክብር እና ከሰብዓዊነት በመነሳት አላቅማማንም»። ልዑካኑ ኢትዮጵያ ለመድረስ አራት ወር ፈጀባቸው።

ረዳቱ በሕመም ምክንያቱ ሞተ። ሁለቱ መነኮሳት በደጋማው አካባቢ ጥቁር ፎቶቶ ቀሚሳቸውን እና የሐር መጎናፀፊያቸውን እንዳደረጉ የስጦታ ሳጥኖች እና ለንጉሡ የሚሰጥ ደብዳቤ ይዘው ጉዟቸውን ቀጠሉ። መምጣታቸውን የሰማው ቴዎድሮስ ሊያያቸው እንደሚፈልግ ገለፀ። ወታደሮችን ልኮ እሱ የጦር ሠፈር ድረስ እንዲያመጧቸው ለማድረግ ፈልጎ ነበር። ግን ዝናብ፣ አማፅያን እና የተቀሰቀው ትርምስ እንቅፋት በመሆናቸው አልተሳካም። ዕድሉ አመለጠ። ወደ ኢየሩሳሌም ከመመለሳቸው በፊት ለአንድ ዓመት ተመንፈቅ ያህል አርመናውያኑ ማስተማሪያ ተቋማቸውን ቀጠሉ።

# ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ

ባሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ የውጭ ዜጋ የሆኑት እሥረኞች ከደብረ ታቦር ለቀቁ። በጉና ተራራ ቁልቁለት አድርገው ወደምሥራቅ በኩል ተጓዙ። ወዴት እንደሚሄዱ ባይነገራቸውም አውቀውታል። በመንገዱ ግራ እና ቀኝ ሲሄዱ መንገድ እየሰጡ የሚ ያሳልፉቸው የአገሬው ነዋሪ በእጅብ ሸኛቸው። «እግዚአብሔር ይፍታችሁ» ሲልም መልካም ምኞቱን አሰማቸው። ወደ መቅደላ ነበር የሚጓዙት። አንድ ሳምንት ገዳማ ተጉዘው በጭለማ እሥረኞቹ ለሳምንት ደረሱ። በጨረቃ ብርሃን ወደ ላይ ሲመለከቱ ገደላማው መተላለፊያ ይታያል። ሁለተኛው መግቢያ ላይ ሲደርሱ ወረቀታቸው እስኪታይ ጥቂት ቆዩ። «በመጨረሻም አንድ በአንድ እንደ በግ እየተቆጠርን በሩን አልፈን ገባን»በማለት ብላንክ ጽፎታል። በተራራው አናት ላይ ከንጉሡ ቤት ፊት ለፊት ወደሚገኘው ባዶ መሬት ተወሰዱ። እነሱን ለመቀበልም የተራራው ላይ አዛገኙ ራስ ኪዳነ ማርያም እና ስድስት የምክር ቤት አባሎቻቸው ተሰልፈው ጠበቋቸው።

ለጥቂት ቀናት ሁሉም በአንድ ጎጆ ውስጥ አደሩ። 10,000 ጫማ ከፍታ ባለው ተራራ ላይ ምሽቱ ቀዝቃዛ ነበር። በሦስተኛው ቀን ራስ ኪዳነ ማርያም እና ሰዎቻቸው ሌሎች ሰዎችን አስከትለው ወደ ታሣሪዎቹ መጡ። ሁሉም በጎጆ ውስጥ ታጨቁ። ሰላምታው ጥቂት ጊዜ ከወሰደ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ስለሃይማኖት ይጨዋወቱ ጀመር። አውሮጳውያኑ ሰዎቹ ለምን ወደ እነሱ እንደመጡ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። መኮንኖቹ ጥብቅ ሃይማኖተኞች መሰሉ። በመጨረሻም ደግ እና ቁጥብ የሆኑት ራስ ኪዳነ ማርያም ወደ ሥራቸው ተመለሱ።

ከውጭ በርካታ ሠንሰለቶች ተቀምጠዋል። እሥረኞቹ ተራ በተራ እግራቸው ውስጡ እየገባ ታሠሩ። ቀጥቃጩ በርከክ ብሎ ከየቁርጭምጭሚታቸው በላይ እያስገባ እግራቸውን ድንጋይ ላይ በማድረግ በመዶሻ እየመታ ቆለፈው። በሰንሰለቱ እና አካላቸው መካከል ያለው ክፍተት ከአንድ ጣት በላይ አያስገባም። ዶ/ር ብላንክ ህመሙን ለመቋቋም ከንፈሩን ነከሰ። ሲያልቅ ለመቆም ተውተረተረ፤ ኮፍያውን አውልቆ በዙሪያው ለተሰበሰቡት እና ለመኮንኑ ፈገግ ካለ በኋላ «እግዚአብሔር ንግሥቷን ይጠብቅ!» ሲል ጮኸ። ራስ ኪዳነ ማርያም ይቅርታ በሚጠይቅ ፈገግታ፤ «እግዚአብሔር ያስፈታችሁ!» አሉ።

እሥረኖቹ ወደ ጎጇቸው ተመለሱ። ከብ ሠርተው ተቀመጡና እንዳቸው የሌላቸውን ስንሰለት ተመለከቱ። «የሚታየው የማይታመን ነበር፤ ግራ የሚያጋባ በዚያ ሁሉ ጎዞናችን ላይ መሳቃችን አልቀረም» ሲል ብላንክ ሁኔታቸውን ገልጿል።



ቀላንዘ በፍሊድ ተልዕኮ ላይ ጥቂት ተስፋ አሳድሯል። ስለሚገኙበት አናዳጅ ይዞታ ብሪታንያ ሲሰማ ወታደሮች ተልከው በአንዴ ነጻ እንደሚያወጧቸው እርግጠኛ ነበር። እንዲያም ሆኖ ስድስት ወራት መጠበቅ ነበረባቸው።

ራሳም ግን እርግጠኛ አልነበረም። ምዕዋ ላይ ለአንድ ዓመት የጠበቀው፣ ጉዞው፣ ሚያዝያ ላይ ያጋጠመው ሁኔታ፤ በዕናት ያለፈባቸውን ነገሮች ሁሉ ሲያስብ ለሃዘው ተልዕኮ ቁርጠኛ ነበር።

እሱን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታዩ እና ዲፕሎማሲያዊው ጥረቱ እንዲወድቅ ችላ አለው። ወደ ቴዎድሮስ መልእክት እንዲልክ ሲጠይቁት፤ በምፀት «እኔ እና አብረውኝ የታሠሩት በሰላም ከዚህኛው እስር ቤት መድረሳችንን ለንጉሡ ነገሯቸው። እናም ይህ ድርጊታቸውን በተለይም ደግሞ አንድ ታላቅ ሉዓላዊ ንጉሥ ጻደኛው በመሆኑ አንድን ሰው በፍቅር እሥሮታል የሚለውን ሌሎች ሲሰሙ ዝናቸውን በእጥፍ ከፍ ያደርገዋል» አለ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ አቶ ሳሙኤል መልዕክቱን ለቴዎድሮስ ተረጎሙለት። መቅደላ በቆየባቸው የመጀመሪያ ቀናት ራሳም እሱን ብቻ የሚመለከቱ ነገሮችን ያሳደገባቸው ጊዜያት ነበሩ። «የሁላችንም ነፍስ በክር ተንጠልጥላለች» በማለት ተስፋ በመቁረጥና በኀዘን ይናገር ነበር። ብሪታንያ የጦር ኃይል የመጠቀሚ ነገር ብዙም ስላላሳመነው ስለማያምለጥ ያስብ ነበር።

ከታሠሩበት ጎጆ አጠገብ አውሮጳውያኑ መምጣታቸውን የተረዱት አቡነ ሰላማም ተመሳሳይ ሐሳብ ነበራቸው። ፊታቸውን አጥቁረው ራሳቸውን በመለወጥ በመግቢያዎቹ አልፈው ከእግፅያኑ ጋር እንዴት ለመቀላቀል እንዳሰቡ ዕቅዳቸውን ለራሳም ላኩለት። የእሳቸው ተቀባይነትም ከቴዎድሮስ አምፀው ለተለዩት የመጠናከሪያ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ዕቅዱ የሚመስል ቢሆንም ግን አልተሞከረም።

በቀጣይ ሳምንታት ራሳም መቅደላ ያለውን ሕይወት ተላመደው። አስገራሚ እሥራት ነበር። የታሠሩበት ስንሰለት በጣም አሲቃያቸው። እንደዚያ ሆነው በግቢያቸው ውስጥ መንቀሳቀስን ለመዱ። ራሳም እና ብላንክ ከፕሪዲዶ፣ ካሜሮን እና ሽተርን ጋር ይቀልዳሉ፤ ማታ ማታ ደግሞ ጎጇቸውን በሚያሞቀው የእሳት ብርሃን እየታገዙ ሕንዳውያን አገልጋዮቻቸው የሚያመጡላቸውን ራት ይመገባሉ።

የሚቀርብላቸውን ምግብ አስመልክቶ፤ «ሚሊዮነር እንኳን እንደእኛ ሊኖር አይችልም» ይላል ራሳም። ገንዘብ መቅደላ ላይ የነበራቸውን ቆይታ ምን ያህል እንዳመቻቸ ያስታውሳል። የራሱን ገንዘብም ሆነ የሚመጣለትን ስጦታ ያከፋፍላል። ገንዘባቸው እያለቀ ሲመጣ ቫሊድማየር ከጋፋት ላከላቸው።

አማፅያኑ የተቆጣጠሩት አካባቢ እየሰፋ ሲመጣ ቴዎድሮስ መቅደላ በሚገኘው ንብረት ላይ ራሳም እንዲያዝ ትዕዛዝ ሰጠ። ራሳም ታዲያ ራስ ኪዳነ ማርያም ሆኑ አማካሪዎቻቸው ጥሩውን ጠጅ እና አረቄ እንዲያገኙ ያደርጋል። በዚህ ሥፍራም ቢሆን ቴዎድሮስ ለእርሱ የሚያሳየው ውዴታ ጠቅሞታል። በማዕረጋቸው ከፍ ያሉ ሴቶች ለማወቅ ካላች ጉጉት የተነሳ ወደእሱ ጎጆ ደጃፍ ይሰበሰባሉ።

በኀዘኔታ «እግዚአብሔር ይፍታህ» ይሉታል። የእነሱ ለስላሳ አነጋገር እጅግ ያጽናናዋል፤ እንዲያም ሆኖ «እንደዚያ ሆኖ ከእነሱ ፊት መቀመጥ ምቾት አይሰጥም» በማለት ገልፆታል።

ሴቶቹ ብሪታንያ ውስጥ ስላለው ኑሮ የጥያቄ ጋጋታ ያቀርቡለታል። የፎቶ አልበሙ ን ተሰብስበው ያያሉ። አንዳንዴም ለሳምንት ወይም ለሁለት ሳምንት በሴት ጎብኚዎቹ እጅ ላይ ይቆያል።

ከወደቡ ከመጣለት መልእክት ጋር ከኢንግላንድ አንዲት ሴት የላከችለት ካርድ ደረሰው። ኢትዮጵያውያን ወይዛዝርቱ ሲመለከቱ "ሚስተር ራሳም በሰንሰለት መታሠራቸውን ስትሰሚ አላለቅስሽም?" ሲሉ ካርዱ ላይ ያለችውን ሴት ጠየቁ። ከእሱ ተቀብለው ሳሙት ከዚያም፤«እግዚአብሔር ፅናቱን ይስጥሽ!» አሏት።





ፍርሃት እንዳደረባቸው ብጤ «በሰማይ ያሉ ... እና መዋዕል «በጎዳር ስድስት» ... ከዋክብት መብረር ጀመሩ» ሲል ጽፏል።

ቴዎድሮስ የወንዶቹን አስከሬን ወደ ጎንደር ወሰደ። ደብረ ታቦርን እና ... በስተምዕራብ የሚወስደውን ጎዳና ትቶ ያለምንም ዕረፍት በጨለማ ለ16 ሰዓታት ተጓዘ። ምሽቱ የፈራረሰውን የቤተ መንግሥት ግድግዳ፣ የከበበውን ግንብ እና ሰቀላዎች ኢጋልጦ አሳየ። ነጭ ሸማ የለበሱ ሴቶች የንጉሡን ሠራዊት ፈረሶች በመከበብ በእልልታ እና በጭብጨባ ደስታቸውን ገለፁ። ከከተማው በአንደኛው ወገን የመጨረሻዎቹ አማፅያን ወደ ኮረብታዎቹ ወጡ።

ንጉሡ የቀረ እንዳለ እንዲያስሱ ትዕዛዝ ሰጠ። አንድም አልተገኘም። አብያተ ክርስቲያናቱን አቃጠለ። አዘዘ፤ ልደታ እና ቁስቋም፤ መጥምቁ ዮሐንስ እና ቀሃ ኢየሱስ ግን የሚወዷቸው ስለነበሩ ተረፉ። የአቦራ እና በዓታ እንዲሁም አደባባይ ተክለይማኖት አብያተ ክርስቲያናት በተዓምር በእሳቱ ነበልባል ከመቃጠል ዳኑ። ንጉሡ 5,500 ቅዱሳት መጻሕፍትን እና አልባሳትን፣ የብርና የወርቅ መስቀሎችን፤ ከበሮ እና ነጋሪቶችን፤ ፅናዎች፣ ጽዋዎችን፣ እንዲሁም ፃህል እና ኩስኩስቶችን ወሰደ። ቅሬታ ያሰሙ ካህናት ወደ እሳት ተጣሉ። የነጋዴ ሚስቶች ወርቅ እንዲያመጡ እየታዘዘ እጅና ፀጉራቸው በእሳት ተለኮሰ። በመቀጠል ነጭ ልብስ ለብሰው የተቀበሉት ሴቶችም ወደእሳት እንዲጣሉ አዘዘ። ጎንደር ወደመች። በፍርስራሹ መካከል ዐራዊት ብቻ ቀሩ። ቴዎድሮስ በሺህ የሚቆጠሩ ተከታዮቹን ድንኳን አስወሰደ እና መናገሻ ከተማው ደብረ ታቦር መሆኗን አሳወጀ።

እንደ ወራሪ ነበር የተቀበሉት። ማንም እሱ ካለው ውጭ ማድረግ አልቻለም። ከንቲባ ኃይሉ ጎንደር በመውደሟ ተደብቀው አለቀሱ። በጎንደር ተወልደው ያደጉ እና ኋላም የከተማዋ ከንቲባ ሆነው ቆይተዋል። በልባቸው በታላቁ ንጉሥ መቃብር፣ በተፈጸሙት ግድያዎች እና በአስከፊ መንገድ ስለወደሙት አብያተ ክርስቲያናት አምርረው ለብቻቸው እንባቸውን አፈሰሱ። የጥንቁቁ ጥበብ ያውቃሉ የሚባሉት ከንቲባ ኃይሉ ለቴዎድሮስ የማያወላውል ፍቅር ነበራቸው። ደግ እና ታማኝ ሰው ነበሩ፤ ሆኖም በንጉሡ መወደዳቸው በዙሪያው ባሉት መኳንንት ዘንድ ጠላቶች አፍርቶላቸዋል።

ከእነዚህ ጠላቶቻቸው አንዱ ታዲያ ተደብቀው ማልቀሳቸውን ለቴዎድሮስ ሹክ አለባቸው። ከዚያም ቴዎድሮስ ከንቲባውን በጣም ከሚወዱት የልጅ ልጃቸው ጋር አሠራቸው። አንድ ላይ በገመድ ጥፍር ተደርጎ በመታሠራቸው «ከጣታቸው ደም ተንጠባጠበ»።

«ሥልጣንዎ በቅርቡ ይጥፋ! ዘመነ ንግሥናዎም ከ14 ዓመት አይበልጥም!!» ሲሉ ከንቲባ ኃይሉ ተራገሙ።

ቴዎድሮስም፣ «መልካም የተናገርከው ሐሰት ከሆነ በሕይወትህ ዋጋ ትከፍላለህ» አለና ወደ መቅደላ ላካቸው። በዚህ ወቅት በ13ኛው ዘመነ ንግሥናው ላይ ነበር።

ጋፋት የሚኖረው ማሕበረ ሰብ ለቴዎድሮስ ሰላምታ ሊያቀርብ መጣ። በእጃቸው የያዙትን ችቦ እያጋጩ ዘፈኑ። «ግርማዊነትዎ በእግዚአብሔር ፊት መልካም እንዳደረገው ልክ እንደ ሕዝቅኤል ነዎት»።ሕዝቅኤል «ኮረብታዎችን ያስወገደ፣ ምስሎችን የሰባበረ፤ ጫካውን የመነጠረ እና ሙሴ ያቆመውን የብርት ምስል የሰባበረ ነው»።

እንዲያም ሆኖ ግን ቫልደማየር ሳይቀር በቴዎድሮስ ላይ የነበረው እምነት ጠፍቷል። «በአውሮጳውያንም ሆነ በተወላጆቹ ላይ ንጉሡ የነበረው ንዴት እና ጥላቻ ከቀን ወደቀን እየጨመረ ነው»።

ጋፋት በሚገኙት ሚሲዮናውያን ላይ ቴዎድሮስ የሚያደርገው ጫና እየጠነከረ መጥቷል፤ መስከረም ላይ ትልቅ ከሚባሉት መድፎች አንዱን ሰርተው ጨረሱ። በዚህ ወቅት ነበር ቴዎድሮስ ከእንግሊዟ ንግሥት የተላከ ደብዳቤ የደረሰው። ፍላድ ባለሙያዎችና ማሽኖቹን ይዞ ምፅዋ ገባ። የፍላድ የብሪታንያ ጉዞ ምንም ነገር ያመጣል ብሎ አልገመተም ነበር። ቅድመ ሁኔታዎች ተያይዘው ቀርበውለታል፤ ቴዎድሮስ ግን ቁብ አልሰጠውም።

«ከነጓዛቸው እዚህ ካላመጣኋቸው ሴት ብለህ ጥራኝ»። አለው ቫልድማየርን። ቴዎድሮስ አሁንም ሥልጣኔን ማደላደል እችላለሁ ብሎ ያምናል። ብሪታኒያ ጦሯን ወደ ተራራማው አካባቢ አትልክም የሚል ግምት አለው። ትክክልም ነው። በንግሥት ቪክቶሪያ፣ በመጡት አዳዲስ ባለሙያዎች እና ማሽኖች ርዳታ ጋፋት ላይ የሚሠሩት የጦር መሣሪያዎች አማፅያኑን ወደ ሲኦል እንዲሸኛቸው እንደሚያግዙት ተስፋ አድርጓል። ለራሳም ትዕዛዝ ሰጥቶ ባለሙያዎቹ እንዲመጡ እንዲያደርግለት ደብዳቤ ወደ መቅደላ ላከ። «ይህ ከሆነ በኋላ በእግዚአብሔር ኃይል አስደስቼ ወደሀገርህ እንድትሄድ ከሸኚዎች ጋር እልከሃለሁ»።

እውነት ነው ችግር ገጥሞታል። ከእሱ አስቀድመው የነበሩት ነገሥታትስ ተመሳሳይ አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሟቸው የለ? «ሰለሞን ሳይቀር፣ ታላቁ ንጉሥ የዳዊት ልጅ፣ የእግዚአብሔር ፍጡር እና ባሪያ ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ከባድ ችግር ገጥሞታል»ኪራም የጢሮስ ንጉሥ።



«ሰለሞን ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ሲል በጢሮስ ንጉሥ ኪራም ጫ ማ ሥር ጠርቶ በመማፀን የግንባታ ባለሙያዎችን ቁሳቁስ አግኝቶ ያሰበውን ለመገንባት ችሏል። አሁንም ሰለሞን በኪራም እግር ላይ እንደወደቀ እኔም በንግሥቷ ባለስልጣናት እና ወዳጆቿ ጫማ ሥር ወድቄያለሁ»።

መቅደላ ላይ የታሠረው ራሳም የመጣው ይምጣ በሚል ደብዳቤ ሲጽፍ እጁን አነሳ። ለቴዎድሮስ በላከው ግልፅ ደብዳቤ የብሪታንያ መንግሥት ምፅዋ የሚገኙት ባለሙያዎች እና ፍላድን ወደዚህ እንዲመጡ እንዲያደርግ የሚጠይቅ መልእክት ላከ። በሌላ በኩል በምሥጢር ሰዎቹ ካሉበት እንዳይንቀሳቀሱ የሚያሳስብ ደብዳቤ በቀጥታ ጻፈላቸው። ይህ ደብዳቤ ከወደቡ ባይደርስ ወይም ከቴዎድሮስ እጅ ቢገባ ምን ሊከተል እንደሚችል ማመዛዘን አልቻለም ወይም አልፈለገም።

ጋፋት የምትገኘው ፓውሊን ፍላድ ባሏ ምፅዋ መድረሱን ስትሰማ «በቀላሉ ለቅሶ ቀንና ማታ ምግቤ ሆኗል።" በማለት ማባሪያ ያጣ ስጋቷን ጻፈችለት። በሂደትም ቴዎድሮስ ምርኮኞቹን የመልቀቅ ፍላጎት እንደሌለው ይልቁንም ሊጫወትባቸው እንደሚፈልግ ተረዳች። እናም ድጋሚ ሌላ ደብዳቤ ለባሏ ላከች።

«የምነግርህ እንደውም የምለምንህ አትመን፣ አትመን፣ አትመን፣ እነዚህ ሠራተኞች ከመጡ እንዴት ነፍስ እንኳን ከዚህች ሀገር መውጣት አትችልም»።

ቫልድማየርም በበኩሉ የተዋበውን የዓለም ገፅታ ለመጠበቅ ሲባል የከፋ ጥቃት መመልከት ችሏል። እናም « ብሪታንያ ያላትን ሁሉ ምፅዋ አምጥታ ባሕሩ ውስጥ ብትጥል እንኳን ቴዎድሮስ አውሮጳውያኑን አሳልፎ ከሚሰጣት ይልቅ ቢቆራርጣቸው ይመርጣል» በማለት ጽፏል።

## ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

በመጨረሻም ፍላድ መጣ፤ ግን ብቻውን ነው። ከእንግሊዝ ለታሣሪዎቹ ቤተሰቦች ጥቂት ስጦታዎችን ተሸክሟል። ለቴዎድሮስ ደግሞ ጠብመንጃዎችን እና ትንሽ የዱቄት ወፍጮ አምጥቷል። ቴዎድሮስ በራሳም በኩል የጠየቀውን ቴሌስኮፕም ይዟል። ከብሪታንያ መንግሥት ግን ከደብዳቤ ሌላ ያመጣው ነገር የለም። ሚያዝያ አጋማሽ ላይ ቴዎድሮስ ፍላድ ብቻውን መተማ መግባቱን ሰማ። ባለሙያዎቹ እና ማሽኖቹ ግን ምፅዋ ናቸው። ራሳም ያቀረበው ጥያቄ እምንታዊ ምላሽ አለማግኘቱ የተለመደ ነገር አልነበረም እና ገረመው። ቴዎድሮስ ጥርጣሬ ቢገባውም የተፈጠረውን ሸር መለየት ግን አልቻለም።

አሁን ምንም መውጫ እንደሌለ ተረዳ። ብሪታንያውያንም የሚፈልገውን አይሰጡትም። በሚቀጥለው ቀን ወደ ጋፋት ወታደሮቹን ይዞ ሄደ እና አውሮጳውያኑን በሙሉ አሠራቸው።

«እኔ የምገደል ከሆነ፤ እናንተ በመጀመሪያ ትሞታላችሁ» አላቸው። ከአንድ ዓመት በፊት ከፖላንድ ተነስቶ በነጻነት እየተጓዘ የመጣው ጥሬትዝ ሀል፤ « እንዲህ ከምታዋርደን በአንድ ጊዜ ግደለን» ብሎ ጮኸ። ንጉሡ ፀጥ እንዲል አዘዘው።

በቀጣይ ጥቂት ቀናት ጋፋት ወደመ። ዋልተር ፕላወደን በአንድ ወቅት የኖረባት ትንሿ ኮረብታ፣ ቴዎፍሎስ ቫልድማየር ለስድስት ዓመታት የተቀመጠባት እና የጦር መሣሪያ ፋብሪካ የነበረችው፤ በዚያም ላይ አራት ልጆቹን የቀበረባት ይህች ሥፍራ ወና ቀረች። መድፎቹ ወደ ደብረታቦር ተወሰዱ። ቤቶቹ ፈራረሱ፣ ፋብሪካዎቹ ወደሙ፤ የሚሲዮናውያኑ ት/ቤት ባዶ ሆነ። ከላይኛው ክፍል ሰዛን ቫልድማየር በግድግዳው ላይ የሠርጋቸው ጊዜ ቴዎድሮስ ለቴዎፍሎስ የሰጠውን ወርቃማ ኮርቻ ተሰቅሎ ተመለከተች። በከፍተኛ ንዴት አውርዳ በመስኮት ወረወረችው። በተሰበሰቡ ወታደሮች ላይ ወደቀ። ሐጎስ የተባለው አንበሳ ተገደለ። ከቴዎድሮስ ጀኔራሎች አንዱ ጎፈሩን ወስዶ ለምድ ሰራው - ደብተራ ሳሕሉ የጋፋትን ት/ቤት እንዲመራ በቫልድማየር ተሹሞ ነበር። የቴዎድሮስ ሰዎች መጡና ከቤቱ አውጥተው እጅና እግሮቹን ቆረጡት። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሞተ። የአውሮጳውያኑ ማሕበረሰብ ወደ ደብረ ታቦር ተወሰደ። ቴዎድሮስ ደምቢያ የሚገኙትን አማፅያን ሊጠራርግ ሄደ። እዚያ ነው ፍላድን ያገኘው። በረሃብ በተጎሳቆሉት አካባቢዎች እያለፈ ነበር የመጣው። በጦር ሠፈሩ ዳርቻ ዓዞን አሳርፎ በእግሩ መጣ። ባልተለመደ መልኩ እርጭ ብሏል። የበሰበሰው የፈረሶች ሥጋ ሽታ አፈነው። መጫኛዎቹ በየቦታው ተበታትነዋል። እጅግ ብዙ ረሃብተኞች፣ ወታደሮች እና አጃቢዎች ሲያልፍ በዓይናቸው ሸኙት።



የዕቃውን ለቴዎድሮስ ሰጠ እና ቴሌስኮፑን ይዞ መምጣቱን ነገረው። «እስኪ ይምጣ።»

ፍላድ የታሸገውን እንስቶ መክፈት ጀመረ። እወጣ እና መገጣጠም ያዘ። ቴዎድሮስ በአንክሮ ይመለከተዋል። ተራ በተራ የሚገቡትን እያበጃጀ ገጣጠመ። ለመጨረሻም ለመመልከት በሚያመች አያያዝ በእጁ ላይ አስቀመጠው። በጣም የጓጓ ነበር። ቴዎድሮስ ተቀበለና ወደዓይኑ አስጠጋው፤ ግን ምንም ማየት አልቻለም። ፍላድ ሌንሶቹን ማስተካከል ያዘ ፤ ግን አሁንም አያሳይም። ቀጠለ ወደሌንሶቹን አመሳቀለ ዕይታውን ለማስተካከል። ቴዎድሮስ ትዕግስቱ አለቀ መልሶ ወደ እሱ ገፋለት። «ይህን የላከልኝ ሰው ሊያበሳጨኝ ብቻ የፈለገ ነው»። ከአስተረጓሚ በቀር በአጠገቡ የነበሩትን ሁሉ ዞር እንዲሉ አዘዘ።

«ሰማሁ ንግሥቷን አይተሃቸው ነበር?» ጠየቀው ፍላድን። «እዎ አይቻቸዋለሁ፤ እናም በቃል መልእክት ልከውኛል» አለ ፍላድ።

«ምንድነው?» ጠየቀ ቴዎድሮስ።

«ያስፍላጊታቸው ያሠሯቸውን ሰዎች ከሀገርዎ እንዲወጡ እስካላደረጉ ድረስ፤ ከእንግዲህ ወዳጅነት የመጠየቅ መብት የለዎትም። ፍላድ ግዳጁን ፈጸመ።

ቴዎድሮስ ፀጥ ብሎ መልዕክቱን አደመጠ። ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ እንዲደገምለት ጠየቀ። «ከእንግዲህ ቀጣይ ወዳጅነት የመጠየቅ መብት የለዎትም»። ቴዎድሮስ ድንዝዝ ብሎ ቆየ። አሁን ተረጋገጠ። «የወዳጅነት ማሳያ ምልክት የዋኳቸው፤ ነገር ግን ከለከሉኝ»።

ፍላድ ወደ ደብረ ታቦር ተጓዘ። እንግሊዝ ውስጥ ነጻነት ነበረው። ወደመኖሪያቸው አብሮን ሐውስ ተጉዞ ከንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ራት በልቷል። አሁን ደግሞ እጅግ ጠባብ እና ጭቃማ በሆነ ሥፍራ በረሃብ እና ፍርሃት ውስጥ የሚገኙ እሥረኞች ጋር በፈቃደኝነት ለመግባት መጣ። ከታሣሪዎቹ መካከል ባለቤቱ ፓውሊን እና የስት ልጆቻቸው ይገኙሉ። «እንዴት ያለ ዳግም መሰባሰብ ነው ፤ እንዴት ያለ ደስታ! እንዴት ያለስ ስቃይ ነው» ሲል በጽሑፍ አሥፍሮታል።

## ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

በአንድ እና ሁለት ወር ከመቅደላ አንድ ሰው ቀስ ብሎ በጠባቂዎች ሳይታይ ገደሉን ወርዶ በአማፅያኑ ወደተያዙት የላስታ ተራራዎች ይገባል። በሱሪው ወይም በቀበቶው አንዳንዴም ክርስቲያኖች አንገታቸው ላይ በሚያስሩት ክታብ ውስጥ አዚያ ከታሰሩት ከራሳም ወይም ከብላንክ ወይም ደግሞ ከሸተርን የተጻፈ ደብዳቤውን ሸሽጎ። ከመቅደላ የሚላከው መልእክት ሁልጊዜ ፍጥነትን የሚጠይቅ ተማፅኖ ነው። «እያንዳንዷ የምትቀጥል ሰዓት የእኛን መገላላት እና ስቃይ የምትጨምር ናት» ትላለች ብላንክ የጻፈት አጭር መልእክት። እነሱን ከዚያ የሚያወጣው መድኀን እጅግም የዘገየ አይሆንም በሚል ተማፅኗል።

እንዲህ መልእክት መላኩ በራሱ በየደረጃው ከፍተኛ አደጋ ያለበት ነው። ሌላው ቀርቶ ቁንጥንጥ ከሆኑት ጠባቂዎች ዕይታ ተሠውሮ ማለፍ በራሱ እጅግ ከባድ ነበር። በዚያም ላይ ታማኝ እና ፈቃደኛ የሆ መልእክት አድራሽ ማግኘቱም ቀላል አልነበረም። ምክንያቱም ይህ ሰው በመጀመሪያ ይዘው ሲደበድቡት ወይም ሊገድሉት ከሚችሉት የቴዎድሮስ ሰዎች እሥራት ማምለጥ አለበት።

ከቴዎድሮስ ግዛት ወጥቶ ወደ ዋግሹም ጎበዜ ክልል ሲገባም ከመቅደላ መምጣቱን አውቀው ከሚያደርሱበት ድብደባም ሆነ ግድያ መሠወር መቻል አለበት። በዚያም ላይ ገንዘብ ያገኛል እና በየትኛውም አጋጣሚ ከዘራፊዎች መጠንቀቅ ይኖርበታል።

ባለፈው ወር እስከታየው ትርምስ ድረስ አንድ ጊዜ ብቻ ነው መልዕክተኞቹውን ያጡት። ያኔ ደግሞ የተላኩት ሁለት ሰዎች ነበሩ። የሁለቱ መጣላት የጠባቂዎችን ትኩረት ሳበ። በገመድ ተጠፍንገው ታሠሩ፤ ደብዳቤውም ጠፋ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እሥረኞቹ አንድ ብቸኛ መልዕክተኛ መላክ እንዳለባቸው ተረዱ። ወደባሕር ወደቡ ለመድረስ ሁለት ወራት ይፈጃል ተብሎ ነበር የተገመተው። ሆኖም ግን ልዑካኑ መልዕክተኛው ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊያደርገው እንደማይችል በመጀመሪያው መልእክት ተረድተው ነበር። 20 የጀመርን የብር ማንቲም ከፍለውት ነበር ሆኖም ቀጣዩን ጉዞውን አዘገየው።

ባለው ገንዘብ የትግሬ ሴቶች የሚያዘጋጁትን ጠጅ በመጎንጨት እና ከእነሱም ጋር በመዳራት ይሰነብታል። እንዲህ ባለው ሁኔታ ዳግም ቀኖቹ ይነጉዳሉ፤ ተልዕኮውም ይዘገያል። መቅደላ ላይ ደግሞ አውሮጳውያኑ አዳዲስ መልዕክተኞችን በስውር ይመለምላሉ። ሁለተኛው የዝናብ ወራት ሲቃረብ እነሱን ከዚያ የሚያወጣው ኃይልም ሲዘገይ፤ ብላንክ መጀመሪያ የነበረው የመተማመን ስሜት ከዳው። «ግሩም ነገርን ጠብቀን ነበር ሆኖም ተግባራዊ የሆነ ነገር የለም»።



በ1859 መጋቢት ወር ወደውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አሹልኮ በላከት ደብዳቤ ርምጃ እንዲወሰዱ ጠይቋል። የቴዎድሮስን እኑዛስ ፤ ከዚያም ለውድቀት ያተረበውን ኑሮ እና ጥቃት በጊዜ ቅደም ተከተል ዘርዝሮ ዲፕሎማሲ የሚያመጣው ጠቡት እንደሌለ ሲገልፅም፤ «የቀረው አንድ ነገር ብቻ ነው። ኃይል» በማለት ደምድሟል።

ለንደን ላይ የጦርነት አማራጭ ተቀባይነት ያገኘ አይመስልም። የተወሰኑ ወገኖች ተቃውሞ ቀውስ ተባብሷል፤ በታይምስ ጋዜጣ ላይ የደብዳቤዎች ዓምድ አዘጋጆችን ጠቢብ አድርገው በሾሙ ሰዎች፣ በአዋቂ ሰዎችና በመንግሥት ተሞልቷል። «ገዳይ ትኩሳት፣ የማይድኑ በሽታዎች እና በጫካዎች ምክር ተሞልቷል። «ገዳይ ትኩሳት፣ የማይድኑ ሥጋ በል ትላትሎች እና ስግብግብ ሰዎች ያሉበት ነው» የሚሉ ቀለሞች ተነጉድጉደዋል። የየጋዜጣዎቹ ቁራጮች በምስጢር ወደ እነሱ ይላካሉ፤ ብላንክ እና ራሳም ተስፋ በመቁረጥ እና በንዴት ያነቧቸዋል።

ጉዳዩ ከማይንቀሳቀስበት ሥፍራ ደረሰ። ዲፕሎማሲው አልተሳካም፣ ኃይል መጠቀሙም አደጋ ያለው ሆነ። እሥረኞቹም እንደማንኛውም በቴዎድሮስ ግዛት ውስጥ እንደሚኖር ሰው የእሱ አስተዳደር ያለደም መፍሰስ እንዲያከትም ተመኙ። በሁሉ ስኬት ካገኙት አማፅያን አንዱም እንኳ ቴዎድሮስን ለማጥቃት አልሞከረም። ቢሞክሩ እንኳ ንጉሡ ወደ መቅደላ ከማፈግፈግ የተሻለ አማራጭ አልነበረውም።

እያንዳንዱ የውጭ ዜጋ እሥረኛ በየራሱ መንገድ እሥራቱን በፅናት እየገፋ ነው። «ሥጋት የሞላባቸው ቀናት እና እረፍት የሌላቸው ምሽቶች፤ የማያባራ ጭንቀት እና ማለቂያ የሌለው የልብ መንጠልጠል፤ መደበኛው መንፈሳዊ ፀጋ ከሚፈልገው በላይ የተላበስነው እምነትና ትዕግስት የነበረንበትን አስከፊ ሁኔታ እንድንቋቋም ረድቶናል» በማለት ሽተርን ጽፏል።

ራሳም በበኩሉ ጥሩ ቪክቶሪያዊ ሥነ ምግባር ተላብሶ ኑሮውን ቀጥሏል። " ጥሩ ይለብሳል ጢሙን በየጊዜው ይከረክማል እንዲሁም ይታጠባል። የሚጎበኙት ሴቶች በማይመጡ ጊዜ፤ ወይም ደግሞ የሌሎች ታሳሪ ጓደኞቹን ደህንነት ለማስጠበቅ ጠጅ የሚጋብዛቸው የተራራው ላይ ባለሥልጣናት ካልመጡበት ወይጋር አትክልቱ ዘር ብሎ ይሰራል። አንድ ግብፃዊ ነው የቲማቲም ዘር የሰጠው። በሆ በደጋማው አካባቢ ቲማቲም የተለመደ አልነበረም። በአጭር ጊዜ ግን ተለምዶ ተስፋፉ። እነዚያ የቲማቲም ተክሎችም አድገው ጥላቸው በአካባቢው ከመስራት ሌላ ፍሬም አፈሩ። ከወደቡ አካባቢ ተጨማሪ እንዲላክላቸውም ውሎ አድሮ ጠየቀ። አሁን የታሣሪዎቹ ምግብ ላይ የቲማቲም ሾርባ ተጨመረ። ባቄላ፣ የፈረንሳይ አተር፣ ድንች፣ ቀይ ስር እና የመሳሰሉት እዚያው ይበቅሉ ጀመር።

የራሳም አትክልቶች ተጨማሪ ጥቅም አመጡ። በአከትልቱ ላይ የሚያርፉትን ወፎችም ይወድ ጀመር። ከጎጆው ፊት ለፊት ባለው ሜዳ ላይ ጥሬ እየተበተነ ሌሎቹን አእዋፍም ይስባቸው ገባ። ወፎቹ አካባቢውን ተላምደው አዘውትረው ለመጠጥ ባስቀመጠላቸው ውኃ ውስጥ ገብተው ሲታጠቡ መመልከቱም ያስደስተው ነበር። አእዋፍም ግር ብለው ከመምጣት ተራ በተራ መታየትን አዘወተሩ። ድምፃቸውና ላባቸው ይስበዋል። በአስረኞቹ ጎጆ ላይ እንገርበው ወዳሻቸው ብር ይላሉ። «በነፃነታቸው ቀናሁ» ሲል የራሱን እሥራት አስታወሰ። አንዳች እንቅስቃሴ ከጆሮው የማያመልጠው ቴዎድሮስም ወደዚያ የሄዱ ሰዎቹን «የራሳም ልጆች እንዴት ናቸው?» ሲል ይጠይቃል።

እሥረኞቹ ሌላም ሐሳባቸውን የሚከፍሉበት ነገር አላጡም። ጥቂት የመጻሕፍት ስብስብ ነበራቸው። ሽተርን በቆይታው ወቅት ከንባብ ሳይሆን በተግባር ያገኘውን እውቀት ተመርኩዞ ስለፍላጎትና አቅርቦት ጉዳይ ከማንም በላይ ማብራራት የሚችልበት ግንዛቤ እንዳገኘ ጽፏል። ሮዘንታል ደግሞ በጣሊያንኛ መጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ራሱን ጣሊያንኛ ቋንቋ አስተምሯል። መጠነኛ ፈረንሳይኛም እንዲሁ።

ብላንክ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜውን ከካሜሮን ጋር ፒፓ በማጨስ፣ ጋደም ብሎ የማከካሎትን መዝገብ ቃላት በማንበብ ያሳልፋል። በሚኖሩበት ተራራ ላይ ፈንጣጣ፣ ኮሌራ እና ታይፈስ ተስፋፍተው መኖራቸው ታውቋል። የዶ/ር ብላንክ አንደኛው አገልጋዩ እግሩን መላወስ እስኪያዳግተው ገዝሆኔ በሽታ ይዞታል። ከባሕር ወደቡ ኮሎኔል ሜርዌዘር ጥቂት ክትባቶች ላከለት። ወላጆችን አግባብቶ ልጆቻቸውን እንዲከተቡ አደረገ። ክትባቱ ሲያልቅበት ከተከተሉት ሰዎች ላይ ወስዶ ተጨማሪ ክትባት አዘጋጀ። ምን ጊዜም የሙቀት መለኪያውን ሳይገዘ አይሄድም። በህመማቸው ከመርዳት ውጪ ብላንክ ለኢትዮጵያውያን እጅግም ጊዜ አልነበረውም። «እኔ እስከገባኝ ድረስ አቢሲኒያውያን ምንም ጥሩ ነገር እንደሌላቸው መግለፅ እፈልጋለሁ» ብሏል። አብሯቸው ሲጫወትና ሲስቅ የሚውለው የራሳም የማይናወጥ ትዕግስትና ዲፕሎማሲ ፍፁም ሊገባው አልቻለም። በተቃራኒው በንፁህ አእምሮ ላስተማራቸው ራሳም ሰዎቹ «ነገሮችን በአከብሮት የሚከተታሉ እና ብልጣብልጦች፣ ለመማር የሚታተሩ እና የእውቀት እጥረት የሌለባቸው ናቸው»።በህክምናው ዘርፍ ላይ ያተኮረው ብላንክ ራሱ ለኮሎኔል ሜርዌዘር በጻፈው ደብዳቤ፣ «የእኔ ችሎታ በመድኃኒቶች ላይ የተወሰነ ነው፤ ራሳም በተደጋጋሚ ለፖለቲካ ጉዳዮች የማልረባ መሆኔን አረጋግጦልኛል። አሜን!» በማለት ገልፆታል።

የድርቁ ወራት ለመጠናቀቅ ሲቃረብ በተራራው ላይ ያሉት የውኃ ማጠራቀሚያዎች ሳይቀሩ በጣም ጎድለዋል። ውኃው ሲቀዳ የሚሰማው ድምፅ በጣም ራቀ። አውሮጳውያኑ እሥረኞች በበኩላቸው ገንዘባቸው እያለቀ ነው። እጅግ አስከፊ ከሆኑት የተራራው ላይ እሥር ቤቶች ደህንነታቸውን ያረጋገጠላቸው



...ብቻ ነበር። በዚህ ወቅትም ተላላፊ በሽታ በእሥር ቤቱ ውስጥ ስምንት ...ኞች ገድሎ ወደ ጠባቂዎቹ ተዛምቷል። ቴዎድሮስ የእሥረኞቹን ቁጥር ...ቂዎቹ ጋር በማነፃፀር ስጋት ገብቶታል። የጠባቂዎቹን ቁጥር እንደመጨመር ...ት ሙቶ እሥረኞች እንዲገድሉ ትዕዛዝ አስተላለፎ። ተጨማሪ ትዕዛዝ ደብረ ...ር ከሚገኘው የቴዎድሮስ ሠፈር መጣ። ስድስት ሙቶ ወታደሮች ተገደሉ። ...ንዳንዱ ራሱን ለማዳን ሲል ትዕዛዙን ፈጸመ። መቅደላ የሚገኙት እሥረኛ ...ሞ ዜናቸ በቅርቡ ወይም ቆየት ብሎ የቴዎድሮስ ትኩረት ወደ እነሱ ...ዞሜዙር ያውቁ ነበር።

...ክን ለሚስቱ ደብዳቤ ላከ። ይህ የመጨረሻቸው ሊሆን እንደሚችልም ...ነበሩት፡ «የምንለያየው ለአጭር ጊዜ ቢሆንም በሰማይ ለዘለዓለም አንድ ላይ ...እንሆናለን። እግዚአብሔር ይባርክሽ የኔ ፍቅር! ውድ ልጆቼንም እንዲሁ»።

## ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

በ7359ኛው ዓመት በዘመነ ሉቃስ፣ ጨረቃ በወጣች በአምስተኛ ቀን፣ በወሩ 25ኛ ቀን ሸብር በመላው ዓለም ታየ። አርማግ ሸብሩ ኃይሉን አጠናክሮ ከጀመረ ስንባብቷል፤ አሁን ግን ወደዚህች ሀገር እየቀረበ ነው። በየአቅጣጫው የሚታየው ጭስ እና አዚህም አዚያም የተለከሱ ጎጆዎች፣ በከፍለሃገሩ በንጉሡ ላይ የተተማጠለው አመፅ፣ ድብረ ታቦር ላይ የየዕለት ውሎ ከሆን ሰንባበተ። ከበሰበሰ የሚሻገሩት ለመቆም የሚያስበ አይመስሉም፣ ከሚቃጠለው ጎጆ ውስጥ የሚሰማው የሰዎች ጩኸትም ፍንከት አላደረጋቸውም፤ እጅ እና እግራቸውን አጥተው አቧራ ላይ ለወደቁትም ቢሆን ውኃም ሆነ ምግብ አይሰጥም።

«የአምላክ እናት»ይላሉ በለሆሳስ «ለነፍሳችን ራራልን» እስካሁን በነጻነት የሚንቀሳቀሱት ያልተከሰሱት ወገኖች ከሰፍራው የሚያመልጡበትን መንገድ ያሰላስላሉ። ከዚያ ርቀው አማፅያኑ ከሚገኙበት ስርጥ ለመሸሽም ይመኛሉ። ሆኖም በከተማው ዙሪያ አጥር ተሠርቷል። ሸልከው ለማለፍ ሲሞክሩ የተያዙት በርካቶች ተገድለዋል። ማምለጡ የተሳካላቸውም ቢሆኑ ጫካ ውስጥ በሚገኙት ሽፍቶች ታርደዋል። ሆኖም ብዙዎቹ የአጥሩ ዋና ተግባር ሽፍቶቹን ከውጭ እንዳይገቡ የመከላከሉን ያህል እነሱን እዚያው ባሉበት ወስኖ ለማቆየት እንዳልሆ ያውቃሉ። አንድ ጊዜ ኃይሉን ተጠቅሞ ማምለጥ የቻለ ስኪታማ ነው። የአማራ ሳይንት የጎበዝ አለቆች አመለጡ። በዚያም ምክንያት አምስት መቶ የሚሆኑ ወንዶቻቸው ተገደሉ። ሌሎች ሊያመልጡ እንዳሰቡ የተደረሰባቸው 500ዎቹ በጦር ሞቱ። ሦስት መቶ ደግሞ በአሾህ መካከል ታስረው ተጣሉ ሚስቶቻቸው ኀዘኑን መቋቋም ስላቃታቸው ተከተሏቸው። ከሁለት ሳምንታት በኋላ በህይወት የተገኙትም ተገደሉ። ምንም ቢያደርጉ ሞት እንደማይቀርላቸው የሰጉ በከተማዋ የሚገኙ ሰዎች ማሰብ ተስኗቸው ፈዘዙ። ያላቸውንም ቀሪ ሃብት ንብረት ረሃብ ጠራረገው፤ ጉንጫቸው ሟሸሸ። የሕፃናቱን ዐይን አሰረጎደው።

በዚህ ሁሉ መካከል ቴዎድሮስ ብቻ በንቃት ይንቀሳቀሳል። ከፊቱ ሁሉንም ይገፋል፤ ዕረፍት አይሰጠውም፣ አያንዳንዱን ቅዕበት ትዕዛዝ እንዲያስተላልፍ፣ እንዲበቀል፤ የሚከዱትን እንዲቀጣ፤ በጨለማው እንዲያነፈንፍ እና በሕዝቡ አዕምሮ የሚመላለሰውን ሐሳብ ሁሉ እንዲከተታል ያደርገዋል። እሱ ማለት የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። በድንኳኑ ውስጥ ሻማዎቹ መላ ሌሊቱን ብርሃን ይሰጣሉ። በዙሪያው ያሉት ሊሰግድ፣ ጸሎት እና ርግማን ሲያነበንብ ያዩታል። አንዳንዴም በምሽት አራቱ የአንበሳ ደቦሎቹ ከሚገኙበት ወጥመድ አጠገብ ሄዶ ይቆማል። እጅግም እንቅልፍ የለውም። በየደረሰበት ጎጆዎችን ከነኗሪዎቻቸው እያጋየ ቢመጣም አንድ የአምስት ዓመት ልጅ በፍርሃት ከታሠረች እናቱ ጋር ሲመለከት መንፈሱ ተናወጠ።



«አምላኬ ፈጣሪዬ! እንዴት ያለ ሰው አድርገህ ነው የሠራኸኝ? ፍጡሮችህ ፊትህ እንዲያገኙ እኔን በቶሎ አጥፋኝ!» ሲልም ዐዐቱን ገለዐ። አንድ ማጥም በሕዝቡ መካከል ወጥቶ እየተዘመተ ከንጉሡ ዘንድ ደረሰ።

እግዚአብሔር እና ንጉሡ አንድ ቀን ተጣልተው

ቅዱስ ሚካኤልን አደረጉት ዳኛቸው

እግዚአብሔር በግራ ንጉሡ በቀኝ

እግዚአብሔር ለንጉሡ አለው ቀኝህን ስጠኝ።

ዓለምን እንዳጠፋት አለው ቀኝህን ስጠኝ። የገዢው ጉዳይ ነበር። ቀለብ በዚህ ዓመት ንጉሡን ከአማፅያኑ ይልቅ ያሳሰበው የገናቡ ጉዳይ ነበር። ቀለብ በሽፍትነት ቋራ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ አሁን ባለው ሥልጣን ደረሰ በሰሩ ያሉትን ለመቀለብ ተቸግሮ አያውቅም። ላይ እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ በሰሩ ያሉትን ለመቀለብ መሰዋዕትነት ከፍሎ እና ሀብታቸው ያለው ነገር ሲያልቅ ሲቃረብ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ከፍሎ እና በደብረታቸው ጭምር ሰዎቹን ይመግብ ነበር። አሁን ግን ግዛቱ እጅግ ውስን ሆኗል። ዘርፎም ደብረ ታቦር አከባቢ ያለው ሁሉ ባዶ ሆኗል። የተረፈው በስተምስራቅ የሚገኘው በለሳ ብቻ ነው። እህሉንም ሆነ ከብቱን በወጉ ጠብቋል በለሳ። ቴዎድሮስ ወደምዕራብ እንደሚዘምት አስነገረ። በስውር ግን በፍጥነት በረሃብ የተጎዱ ሠራዊቱን ወደምስራቅ ላከ። ወደ በለሳ። ሆኖም ምሥጢሩ የመደበቁ ነገር አከትሟል። ወደበለሳ ሲቃረቡ ከተማዋ መቃጠሏን የሚያመለከት ጭስ ከርቀት ተመለከቱ። ገበሬዎቹ እህላቸውን ጭነው ሸሽተዋል። ከዚያም ንጉሡ ሠራዊቱን ይዞ ወደ ጋና ዘመተ። በጣና ምጥረሃ ደሴት ገዳም የተከማቸውን እህል እና ንብረት ወሰዱ።

ለኔ መጀመሪያ ገደማ ከብሪታንያ መንግሥት ደብዳቤ ደረሰው ቴዎድሮስ። በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እሥረኞቹን ወደ ምፅዋ እንዲልክ፣ ከዚያም ውጪ ምንም ድርድር እንደሌለ፤ ምንም ዓይነት ንግግርም እንደማይኖር ያስሰባል ደብዳቤው። ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ተቀብሎ በአክብሮት ጭንቅላቱ ላይ አስቀመጠው። ሆኖም ግን ፖስተኛውን ያለምንም ምላሽ ሸኘው። የብሪታንያ ልዑካንን ማሠሩ ውሎ አድሮ አንዳች ነገር ሊያመጣ እንደሚችል ያውቅ ነበር። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ብሪታንያ ከንጉሡ ጋር በመታገል «በሰሩ በስቃይ የሚኖሩትን «ነጻ» እንደምታወጣ» ተረድቷል። ቀኑ እየከበደበት ሲመጣ የሽንፈት ስሜት ይከበዋል። በሌላ ጊዜ ደግሞ የወረራ ማስፈራሪያው በዙሪያው ያሉትን ጠላቶቹን ሳይቀር አስተባብሮ መነሳት እንደሚችል ይሰማውና ከብሪታንያ ጋር ሊያደራድረው የሚችል ሌላ ዕድል ያመጣለት ይመስለዋል። አቅዱም በአይደፈሬው የመቅደላ ተራራ ላይ ኃይሉን አጠናክሮ በፅናት መመከት የሚል ነው። ለዚህ ደግሞ የጦር ኃይል አቋሙ ን መሣሪያ ማጠናከር ዋናው መሠረት ነው።



## ምዕራፍ ሃምሳ አራት

የደብረ ታቦር ሥቃይ ቀጥሏል። ፈሪዎች በረሃብና ፍርሃት ተውጠዋል። ጅቦች ከተቃጠሉት ቤቶች የሚቀኙትን አግር ይጎትታሉ። ቴዎድሮስ የቀድሞ ወዳጁን ቫልደማየርን አስጠራው።

«እናንተ አውሮጳውያን በጣም ብልህ ናችሁ 1000 ፓውንድ ክብደት ያለው ቀለሀ የሚተኩስ የጦር መሣሪያ እንድትሰሩልኝ እፈልጋለሁ»። ባለፉት ዓመታት ጋፋት ላይ ቫልድማየር እና እዚያ የሚገኙ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች አራት ትላልቅ ስምንት አነስተኛ መድፎች እንዲሁም ሌሎች በርካታ የጦር መሣሪያዎችን ሠርተዋል። አሁን ግን የጋፋቱ ኢንደስትሪ ወድሟል ሠራተኞቹም ተበታትነዋል። አሁን በቦታው ረሃብ ነግሷል። ቫልደማየር የቴዎድሮስን ጥያቄ ከሰማ በኋላ የተፈለገውን ለመሥራት እንኳን አሁን ያኔም እንደማይችል አሰበ።

«ይህ እንዴት እንደሚሠራ አናውቅም ካልከኝ እንደ ውሸታም ነው የማይህ፤ መቼም ሲያታልሉኝ የሞከትን ያደረኳቸውን ታውቃለህ» አለው ቴዎድሮስ። «የምንችለውን ሁሉ እንሞክራለን» መለሰ ቫልደማየር። ሥራው ተጀምረ። ቫልድማየር ም ንድፉን አዘጋጀ። ቴዎድሮስ ይበል ሲል ድጋፉን ገለፀ። መሣሪያው የቀደሙትን መድፎች ቅርፅ እንዲይዝ ነው የታሰበው። መጠኑ ግን ከበፊቶቹ ይበልጣል። 2000 ሰዎች አወሮፓውያኑን በሥራው እንዲረዱ ተመደቡ። ለሁሉም ምግብ ይሰጣል። ሳምንታት ሲያልፉም በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ሁለት የብረት ማቅለጫዎች ተገንብተው ጎልተው መታየት ጀመሩ። በሥራቸው ላይ ሳሉ ከወደ ንጉሡ ችሎት በቫልደማየር ጆሮ ወሬ ሽው አለ። «ለመሣሪያው ማንባታ ሥራ የተሰማሩትን አውሮጳውያን እንደ ባሪያ ተጠቅሞ ሥራቸውን ሲጨርሱ ከአካባቢው አውጥታችሁ ግደሏቸው ተብሏል»። ቫልድማየር በጭምጭምታው ቢረበሽም የጀመረውን ሥራ ቀጠለ። በየቦታው የተገኘ የብረት ቁርጥራጭ ሁሉ ወደ ማቅለጫው ምድጃ ይገባል። ከመቅደላም እስ የተባለ ብረት ነክ ነገር ሁሉ ተሰብስቦ ተላከ። ሌላ ቀርቶ ቴዎድሮስ ከጎንደር ዕቃ ቤት የወሰደው 490 የብር ሣንቲም ሁሉ ለመድፉ መሥሪያ ቀለጠ። ቴዎድሮስ በየዕለቱ ወደዚህ ስፍራ ይመጣና ይጎበኛል ጉብኝቱም ዘለግ ያለ ጊዜ ይወስድ ነበር። ቫልደማየር አጠገብ ሄዶ ይቆማል። ያኔ ቫልደማየር ሳይታወቀው ይንቀጠቀጣል። በብዙ ድካም የታሰበው መድፍ መተኮሻ ተዘጋጀ ተባለ። ወሬው የደረሰው ቴዎድሮስ በጉጉት ከነሰዎቹ ተሰበሰበ። ቫልደማየር እና ሠራተኞች የብረት ምድጃውን ኢጋሉት። መቶቱ እየጨመረ ሄደ በዙሪያው ያሉት መቶቱ ተስማቸው የሆነ ነገር የለም።ግን ቫልደማየር እየጸለየ በጭንቅ ይጠባበቅ ጀመር። በመጨረሻ «አሁን ዝግጁ ነው» አለ። ቫልደማየር ሥጋቱን ለመሸፈን እየታገለ፤ ቴዎድሮስ ትዕዛዝ አስተላለፈ፤ መተላለፊያው ተከፈተና የጋለው ብረት መፍሰስ



ጀመረ። ማቃጠያው እሳቱ እብዝቶ እየነደደበት ፍሰቱ ቀጠለ። ቫልደማየር ከአሁን አሁን ይቋረጣል በሚል በፍርሃት ተውጧል። ግን የፈራው ቀርቶ መተላለፊያው ሞልቶ ተዘጋ።

ከሦስት ቀናት በኋላ ያ ማቃጠያ ጥቃት ደረሰበት ቋ........ቋ የሚለው ድምፅ በመላ ከተማ ተሰማ ሲፈራርስ ከውስጡ መድፉ ምንም ሳይሆን ቁጭ ብሏል። ያ ዕለት የቴዎድሮስ የደስታ ቀን ነበረች።

እንግሊዝ ወታደሮች ወደሀገሩ ገብተው ወዳለበት ሥፍራ ሲተምሙ በምናቡ ታየው። እሱም ከታማኝ ሠራዊቱ ጋር ሆኖ መቅደላ ላይ መሽጎ መድፉን አቀባብሎ ፈረንጆች ከሬሚያ ላይ እንዳደረጉት ለመመከት ሲጠብቅ ታሰበው። መድፉንም ቴዎድሮስ ሴቫስቶፖል ሲል ሠየመው።

አሁን በንጉሡ ዙሪያ የሚገኙት አማካሪዎች አውሮጳውያኑን እንዲገድል ይጐተጉቱት ጀመር። «የለም» አለ ቴዎድሮስ «አሁን ደግሞ መድፉን የሚጎትት ተሽከርካሪ ይሥሩ»።

ጋሪውን ሠርተው እንደጨረሱ ከአዛገሮቹ አንዱ ወደ ንጉሡ ቀርቦ «ጃንሆይ ምርማሪነትዎ የምንፈልገው ሁሉ አሁን አለን ለራስዎም ዘላለማዊ ስም ተክለዋል። እነዚህ ነጮች ከእንግዲህ አንፈልጋቸውም» አለ። ቴዎድሮስ ግን ፈቃደኛ አልነበረም። መድፉን ወደ መቅደላ ተራራ የሚያደርስበትን መንገድ እንዲሠሩለት ፈለገ።

# ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

በጎርጎሪዮሳዊው 1867 ነሐሴ ወር በአንድ ሞቃታማ ዕለት ማለዳ የሎርድ ደርቢ ካቢኔት በኢትዮጵያ ቀውስ ላይ ለመወያየት ተሰበሰበ። ከብዙ ማመንታት፣ መጓተትና እና ጭፍን ተስፋ በኋላ ኃይል ለመጠቀም ወሰነ። ከብዙ ማመንታት፣ አማራጭ አለመኖሩን፣ ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ነው የተወሰደው። ከምንም በላይ የተከበሩትን ግርማዊት መልዕክተኞች ማንም እንዲያ ሊያንሳቁል አይችልም ተባለ። የብሪታንያ መንግሥት እንዲህ ባለው ሁኔታ ኃይል አይጠቅምም ማለት አይቻልም። በአመፅ የተነሳው የሕንድ እና የአረብ ሃገራት ሕዝብ፣ በመሥፋፋት ላይ የነበረው የሩሲያው ዛሩ መንግሥት ይህን እንደድክመት ቆጥረውታል። ቀደም ብሎ እዚህ ትርጉም ያለው ርምጃ ተወስዶ ቢሆን ኖሮ እዚያ ያለውን ሁኔታ በለወጠው ነበር። አሁን በጣም ዘግይቷል። የግርማዊነቷ መንግሥት ወደ ጦርነት መመለስ ግድ ሆኖባታል።

እንደ እዕድል ሆኖ ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ መውሰድ አይኖርበትም። ወደ ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሰው ኃይል ከሕንድ ቢሆን እንዲሚሻል ተወስኗል። በዚያው በነሐሴ ወር አንድ ቴሌግራም በምቤይ ላይ ወደ ተሾመው ሌተናል ጄኔራል ሮበርት ኔፒር ተላከ። ኔፒር የሕንድ የጦር ኃይል አዛዥ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሰውን ጦር እንዲመራ ታዘዘ። ይህም የፓለቲካው ጨዋታ ማክተሙን አመላካች ነበር። በሰዓታት ውስጥ ለዓመታት የተጓተተው ጥረት ሁሉ በወታደራዊ ዘመቻ እንቅስቃሴ ተለወጠ። ታዛቢዎች በወቅቱ በምቤይ ለጦርነት ዘመቻ በሚደረገው መሰናዶ መዋጧን አስተውለዋል።

ከጦር መኮንኖች እስከ ሂማሊያ ተራራ ላይ የተመደቡ ቀያሾች ተሰባሰቡ። ወደ አቢሲኒያ ለሚደረገው ዘመቻ በከተቱ የተሰባሰቡት ሲታዩ ሕንድ ዜጎቿን ሁሉ ጠራርጋ የምትሰድ ይመስል ነበር። የብሪታንያ ፖለቲከኞች ኔፒር ወጪ ላይ ጥንቃቄ እንዳያደርግ ያሳስቡ ጀመር፤ አላስፈላጊ ወጪ እንዳይኖር። ኔፒር ግን ወጪው ሁሉ አስፈላጊ ነው ባይ ነው። ከሬሚያ ላይ የተፈጠረው ዓይነት አሳፋሪ በዚህ ዘመቻም እንዳይ ከሰት የሰጋው ኔፒር በወጪ ቁጠባ ሰበብ የጓጓለት ስኬት እንዳይከሸፍ ተጠንቅቆ ዝግጅቱን ቀጠለ። ኢትዮጵያን የመውረሩ ዝግጅት በርካታ ችግሮችን ጋርጧል። ይህን በሚመለከት በቦምቤይ የተባባሪ ማሕበረሰብ ቤተ መጻሕፍት ኔፒር እያንዳንዷን የጉዞ ሰነድ እና ታሪካዊ ሂደቱን የሚዘረዝሩ መረጃዎችን አስቀምጧል። ሁሉም ጉዳይ ከተብላላ በኋላ «ስለእነሱ ጥቂት ነገር ብቻ የምናውቅ ሃገራት እጅግ ጥቂት ብቻ ናቸው» ያሉት የሚል ውሳኔቀረበለት፣ ኔፒር እና ተባባሪዎቹ በቀይ ባሕር ላይ ይዘውት የሚሄዱትን ኃይል እና ጓዝ የትጋ እንደሚያሳርፉ አያውቁም። የቱጋ ንፁህ ውኃ ማግኘት እንደሚችል፣ ወደ ደጋማው አካባቢ በየት በኩል ቢጓዙ እንደሚቀል፤ ሠራዊቱንም ሊያጠቁ ስለሚችሉ የበሽታ ዓይነቶች እና አውሬዎች የሚያውቁት ነገር የለም። ቴዎድሮስ



ቶ እንዳለም አያውቁም። ከእንግሊዝና ሕንድ ጦር ጋር በመተባበርም ቴዎድሮስን ሊገድሉ የሚችሉ የአካባቢው ገዥዎችም በየት በኩል እንዳሉ ሚጃው የላቸውም። ከምንም በላይ አሳሳቢው በምን መልኩ ዘመቻውን ማሸነፍ እንዳለባቸው አለማወቃቸው ነው። ተቺዎችም ከዚህ ቀደም ጠቅላቸውን ዘመቻዎች መለስ ብለው በመቃኘት ከወዲሁ አስጊውን ውጤት መተንበይ ጀመሩ። አፍጋኒስታን ላይ በተደረገው ዘመቻ 15,000 ኃይል ደምሷል፤ በክሬሚያው ጦርነት 50,000 ጦር እንዳልነበረ ሆኗል። ወደ ሜክሲኮ በዘመተው ሠራዊት ግማሽ ያህል የፈረንሣይ ኃይል እንደወጣ ቀርቷል፤ እናም ታሪክ ዘር ብሎ ሲታይ ሽንፈትን እንጂ ስኬትን አላሳየም።

ኢትዮጵያ ታዲያ ከተጠቀሱት ቦታዎች ሁሉ አስቸጋሪዋ ሆና ቀረበች። ዴቪድ ዐርኬርት በዲፕሎማቲክ ከለሳው እንደጻፈው «ስንሰለታማ ተራሮች እንዳሏት የሚታወቀው አገር፣ አገሬው ከከፍታ ሥፍራ ላይ ሆኖ የሚያዘንበው የድንጋይ ናዳ ብቻ ሊያደርስ የሚችለው አስከፊ ጉዳት ታሰበ። የሚያገለ ሙቀት፣ ከፍተኛ ዝናብ የሚያስከትል ዝናብ፣ ያልታሰቡ አደጋዎች እና ያልታወቁ ወረርሽኞች ሠራዊቱን ሊያጋጥሙ ይችላሉ» ሲል አሥፍሯል። ኔፒር ግን በዚህ ሁሉ አልተፈታም። በተቃራኒው ለዘመቻው የሚያስፈልገውን ሁሉ ማቀድ ማደራጀቱን ቀጠለ። 5,000 ግንባር ቀደም ተዋጊ፣ ተጨማሪ 7,000 ለዚህ ኃይል በደጀንነት የሚዘምት ሠራዊት፤ እንዲሁም ለዘማቹ የሚያስፈልገው ማንኛውም አቅርቦት የሚደርስባቸውን ሁለት መሥመሮችን ዘረጋ። አንድ ከቀይ ባሕር እስከ ስዌዝ ካናል ሌላኛው ሕንድ ውቅያኖስን አቋርጦ በምቤይ ወደብ።

በ1860ዎቹ የብሪታንያ የግዛት ኃይል እና ቴክኖሎጂው ከሚገመተው በላይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። ኔፒርም የሚያሻውን ሁሉ ለማግኘት አይገደውም። ከሊቨርፑል እስከ ውልዊች፣ ከቻተም እስከ በምቤይ፣ ከኤደን እስከ ማድራስ የአካባቢ ኃላፊዎችን እና የግምጃ ቤት ኃላፊዎች ፣ቴክኒሽያኖች እና ቀማሚዎች፤ ኩሊዎች እና አብሳዮች፣ ዕቅድ ነዳፊዎች እና የመዝገብ ተቆጣጣሪዎች፤ የመርከብ ኢታ ማዦር እና አውራጆች ከወዲሁ ከሽፈቱት ንጉሥ ይዞታነት ቦታዎችን ለማስለቀቅ የሚደረገው እንቅስቃሴ መሳተፍ ጀምረዋል።

ቴዎድሮስ በበኩሉ ዓለም ኢትዮጵያን ወርሮ ትንቢቱን እንዳያጨልምበት አቅሙ ን በማጠናከሩ ላይ አተኩሯል። ምንም እንኳን አቅሙ በንፅፅር እዚህ ግባ ባይባልም በወቅቱ ቴዎድሮስ ኔፒር ያለ የሌለ ኃይልና አቅሙ ን ለዚህ ዘመቻ አውሎ ለጦርነት እንዲዘጋጅ አድርጎታል። ለዘማቹ ኃይል የታሰበው ክፍያም አስገራሚ ነው። አልባሳት ምግብ እና የጦር መሣሪያ ለዚህ የሚሆነው በጅት ሆነ እዝ ተመቻችቶ በምቤይ እና ስዌዝ በሚገኙ መጋዘኖች ተደራጀ። በመርከቡ ጉዞ ላይም ለወታደሮቹ ራሽን ይሰጣል። ሰኛ እና ሐሙስ 340 ግራም የሚሆን በጨው የተዘጋጀ የበሬ ሥጋ ፣ ረቡዕ ደግሞ ተመሳሳይ መጠን ያለው የአሳማ ሥጋ

ይሰጣቸዋል። በዚያም ላይ 56 ግራም ስኳር ያገኛሉ፤ ዳቦም ካላፍ አገደም ይታደላቸዋል። እንዲህ እንዲህ እያለ የሠራዊቱ ቀለብ ይሠፈራል። ለእንግሊዛውያን ወታደሮች፣ ለሂንዱዎችና ሙስሊሞች የሚደረገው አቅርቦት ለየት እንደሚልም ተመዝግቧል። ከዚህ ቀደም በዚህ መልኩ የምግብ የተደረገለት ሠራዊት የለም። ሦስት ሆስፒታሎች ያሉባቸው መርከቦች ከብካቢ በቀይ ባሕር ወደብ ቆመዋል። እያንዳንዳቸው መጽሐፍ ቅዱሶች፣ የጸሎት መጽሐፍት ሌሎችም ሰማንያ የተለያየ ታሪክ ያላቸው መጽሐፍት እሷቸው። በዚያ ላይ ወይን፣ ሻምፓኝ እንዲሁም የጥንቱ ቆም ጂንም ተጭኗል። 200 የኢትዮጵያ ቃላትም ከጓዞቹ ተካተዋል። ቀለሞች እና 350 ማይል (563.27 ኪሎ ሜትር) የሚሆን የመዳብ ቴሌግራፍ አብሮ አለ።

ሌሎችም ለቀለብ እና ስንቅ የሚሆኑ ከየዓይነቱ በርከት ብለው ተጭነዋል። ዘመቻው ዘመናዊ ቴክኒዎሎጂንም አካቷል። ሰባት ፎቶግራፍ አንሺዎች፣ ለአጥበት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ካሏቸው ድንኳኖች ጋር ተዘጋጅተዋል። በጨለማ ሲደርስ በሚችል ደንገተኛ ጥቃት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ባውዛ መብራቶችም አሉ። ከተት በታወጀባት ሀገር መንገድ ባለመኖሩ ተሽከርካሪዎችን ማስከተሉ ዋጋ እንደሌለው ታመነበት። ኔፒር በቅሎዎች ያስፈልጉታል። 2000 በቅሎ ፕንጃብ ላይ ተገኘ። ተጨማሪ አንድ ሽህ ደግሞ ባግዳድ ላይ ተገዛ። ይህ ሁሉ ግን እሱ እንዲጥረው ካተደው ብዛት ጥቂቱ ነው። ማላጋ፣ አልካንቴ፣ ካዲዝዝ፣ ባርሴሎና፣ ጀኖዋ፣ ትሪፓሊ፣ ቤይሩት፣ ቁስጥንጥንያ እና ስምሪያን የሚገኙ የብሪታንያ ቆንስላዎች በአንድ ጊዜ በቅሎዎችን እንዲፈልጉ ተጠየቁ። በዚያ የመሀው ወራት ሲያቋርጡት ከረሙ። በአስር ሺህዎች የሚገመቱ በቅሎዎች እስከንድሪያ ወደብ ላይ ተከማቹ በአንገቱ ለንደን ላይ የዘመቻው ወጪ እና የገዛጅቱ ስሌት ላይ ትችቱ ከፍ እያለ ሄደ፤ በተለይ ደግሞ የበቅሎዎቹ ነገር።

«ዘመቻው የበቅሎ እጥረት ከገጠመው በነጻ ሊቀርቡ የሚችሉ በርካታ አህዮች እዚህ ይገኛሉ»የሚል አስተያየትም ተሰጠ። የኔፒር ጥያቄ ግን ገና አላበቃም። አዳዲስ ቀለብ እና ማባያ ለመግዛት እንዲሁም ኢትዮጵያ የምትገበያየው በማርያ ቴሬዛ የብር ሣንቲም መሆኑ ተደረሰበት። ያኔ ደግሞ በፈረንጆቹ 1704 ሥራ ላይ የነበረው ማሪያ ቴሬዛ አመርጋ ውስጥ ቀርቷል። እናም የጀርመን ወኪሎች ያን እንዳለ ገዝተው እንዲሰበስቡ ተጠየቀ። ቪየና ደግሞ ብሪታንያ ብሩን እስከቀረቡት ድረስ በአንድ ሳምንት ውስጥ 200,000 ማሪያ ቴሬዛ ሳንቲም ለማዘጋጀት ፈቃደኛ ሆነች። ዘመቻው እየተቃረበ ነው። የኔፒር እቅድም ከተገመተው በጅት እያለፈ ነው። በተጣይ ጥቂት ወራት 300 የሚሆኑ መርከቦች ዓዙን ሁሉ ወደ ቀይ ባሕር ወደብ እንዲያደርሱ ተጥዋሉ። ይህ ሁሉ የዘመቻ ግርግር በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን ነጻ ለማውጣት ነው።



ከመካከላቸው እርግጥ ጥቂት የብሪታንያ ዜጎች አሉ። ሼተርን ፣ ሚስ ሮዘንታል እና ቢሯን ቢተሰቦች። እርግጥ ነው ዋናው ትኩረት አራቱን የብሪታንያ ባለስልጣናት፣ ማለትም እዚያ የታሰረውን ቆንስል ካሜሮንን ለማስፈታት የተዛዙትን ልዑካን ለማዳን ነው። እናም ይህ ሁሉ ዝግጅት፣ እያንዳንዱ የናፒየር ዘመቻ እቅድ፣ በስፔን መንደሮች እና በየሀገሩ በቅሎ ያሸመተው፣ ያ ሁሉ ስንቅ እና ትጥቅ የተሰባሰበው እጅግ ሩቅ ቦታ በሚገኝ ተራራ ላይ የታሠረውን አንድ እሥረኛ ለማስለቀቅ ነው ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት

መቅደላ ተራራ ላይ በምትገኘው ጎጆው ውስጥ ቀንሰል ቻርለስ ዳንከን ካሜሮን ድንግዝ ባለው ጨለማ ተጋድሟል። የተኛበት አልጋ ትንሽ ሲንቀሳቀስ ትርጫኻለች። ሰንሰለቱ እግሩ ላይ እንደ እባብ ተጠምጥሟል። አንዳንድ ጊዜ ይነፍ ግቢው ውስጥ የመንፏቀቅ ያህል ይራመዳል። ብላንክ እንዲሚለው ካሜሮን ሶሱን ችላ በማለቱ በሁሉም ዘንድ ከብሩን አጥቷል። ገና መጀመሪያ በ1854 መስከረም ወር ማለቂያ ገደማ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ቴዎድሮስ ድንኳን ውስጥ ሲገባ እንዲቀመጥ ሲነገረው ግትር በማለቱ የታመመ ይመስል ነበር። ከብጤዎቹም ቢሆን ብዙም የሚያገዝንለት አልነበረም። ከአሥር ዓመት በኋላ ቴዎድሮስ ከታሠሩት የወጪ ዜጎች ጋር እርቅ ለማውረድ ሲነጋገር ካሜሮን ሲቀር ሁሉም ከንጉሡ ፊት መሬት ላይ ተነጠፉ።

ሽተርን «ካሜሮን በገዛ እጁ ነገሮችን አበላሽቷል»ይለዋል። ወይ ጉልበቱ ወይም አከርካሪው ከጥቅም ወጪ ሳይሆን አይቀርም። እንዲያንኮበስ ወይም እንዲቆም ሲታዘዝ አይንቀሳቀስም። እጋፋሪዎቹ ሥርዓቱን እንዲለማመዱ ለማድረግ የሞከሩትን ሁሉ ከንቱ አስቀርቶታል። እንዲያውም ካሜሮን ሁሉንም ወገኖች ማናደዱ ተሳክቶለታል። ገና ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ለንደን ውስጥ ወዲህ ወዲያ እያለ ጊዜ በማባከኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተበሳጭቶበት ነበር። ቴዎድሮስንም መጀመሪያ ሲያነጋግረውም ቢሆን ትዕዛዙን በመተላለፍ አስቆጥቷል። ከሀገር እንዲወጣ ሲታዘዝ አልወጣም የቴዎድሮስን ጠላቶችም ሄዶ ጎብኝቷል። ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ እንዲያደርስ የላከውን ደብዳቤም እንደዋዛ ለመልዕክተኛ መስጠቱ ተደርሶበታል። እንዲያም ሆኖ ለተፈጠረው ቀውስ ምክንያት ነው ተብሎ አይወሰድም ግን ደግሞ አስተዋፅኦ አድርጓል። አሁን መቅደላ ላይ ታሥሯል። ተስፋ ቆርጧል። ስለ ሞት መፍራቱን ትቶትም ቆሎ ቢሆን ማለት ጀምሯል። የዝናቡ ወራት እያለቀ ነው። ላለፉት በርካታ ወራት በአየር ጠባዩ ምክንያት ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ መሄድ አልቻለም ነበር። አሁን የወንዞቹ ሙላት ሲቀንስ እና መንገዱም ማንቀሳቀስ ሲችል ቴዎድሮስ ደብረታቦርን ለቅቆ ወደ ተራራው ይመጣል በሚል ስጋት ገብቷቸዋል። እንዲያ ከሆነ ደግሞ ማናቸውም ሰላም አያገኙም።

ደመናው ቀስ በቀስ እየቀነሰ ዝናቡም እያነሰ መጣ። በቅርቡ የመስቀል በዓል ይከበራል። በመቶ ሃምሳ ማይል (241 ኪሎሜትር)ርቀት ላይ ከደብረታቦር ተሴራ ጅርባ እስደንጋጩ ሁኔታ ቀጥሏል። አማፅያኑ እየተጠጉ ነው። ጅቦቹም በግልፅ ይታዩ ጀመር። ቴዎድሮስ ደግሞ ሲቫስቶፓል ላይ ቀልቡን አድርጓል።

«እስቲ ተኩሱ ድምፁን መስማት እፈልጋለሁ» አለው ቫልድማየርን። መሥራት አለመሥራቱን ቫልድማየር ርግጠኛ አይደለም። መድፉ ኃይለኛ በመሆኑ ችግር



ሊያስከትል እንደሚችል ለማስረዳት ሞከረ። «አሁን ብንተኩስ ሴቶች እና ሕፃናት ይሞማሉ፤ ሰው ሁሉ ታምሞ ይሞታል»። አንዳንድ ቀን ቴዎድሮስ በጣም አስገራሚ ነገር ሲሰማ የሚስቀው ሳቅ አለ። በተለይ እንዲህ ባለው የማይመስል እንዳ እምነት መሳይ ነገር መሳቅ አማረው። የቴዎድሮስ አነሳስ ለየት ያለ ምልክት እንደነበረው ሁሉ የዘመኑ መጨረሻም ማመላከቻዎች ታዩት። ከንቲባ ኃይሉ እንደሚሉት ከስድስት ወራት በኋላ ንግሥናው 14 ዓመት ይሞላዋል። ሥጋ እንደልብ ማግኘት ስላልተቻለ አንበሶቹን በመርዝ መግደል ግድ ሆነ።

በርከት ያሉ ከብቶች ተዘርፈው ተያዙ። ገበሬዎቹ እንዲመልሱላቸው ተማፀኑ። ሆኖም ግን አንዱ እንዲህ አለው «ግርማዊነትዎ አንድ ትንቢት አለ፤ ንጉሡ በርካታ ከብቶችን ይይዛል፤ ገበሬዎች እንዲመልስላቸው ይለምናሉ፤ ይመልስላቸዋል፤ ግን እሱ ይሞታል»። ስለዚህ እንዲያርዷቸው አዘዘ። ወታደሮቹ አንድ ቀን ሙሉ ከብቶቹን ሲያርዱ ዋሉ። የተከመረው ሥጋ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለጅቦች እና ለአሞራዎችም ተረፈ። የደብረታቦርን ዙሪያ ገባ ቴዎድሮስ ተመለከተ። ልቡ ወደ መቅደላ ተነሳ። ለየተመኙም እንዲህ ሲል ደብዳቤ ጻፈ።

«እትፍሬ ሞቼ ካልተቀበርኩ በቀር በእግዚአብሔር ኃይል ሳላይሽ አልቀርም። ከደጃች ጎሹ ጋር ስዋጋ ተዋበችን ቋራ ትቻት ነበር። ከብሩ አሊጋዝ ጋርም እንዲሁ ነበር። አሁን መቅደላ ቋራ ሆኗል፤ ቤቴ ነው። ከዚያ መራቅ አልችልም። ነፍስና ሥጋዬ ካልተለያዩ በቀር»። ከሦስት ሳምንት በኋላ ደብረታቦር ላይ የተረፈው ሁሉ እንዲቃጠል አዘዘ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት

ድብረታቦር እንደተቃጠለ የመጀመሪያው የብሪታንያ ዘማች ከነጓዙ ቀዪ ባሕር ወደብ ደረሰ። 24 የጦር መኮንኖች፣ አንድ ባታልዮን የቦምቢይ የባሕር ኃይል ሠራዊት ጥቂት መንገድ የሚገነቡ ወታደሮች ፣ ፈንጅ ቀባሪዎች የሕንድ ሚሊሺያዎች፣ ከቦምቢይ ቀላል ጦር 40 ሰዎች እና 149 በቅሎዎች በዚህ ቡድን ተካተዋል።

የተሰጣቸው ኃላፊነት በባሕሩ ዳርቻ ለሚመሠረተው የጦር ሠፈር ቦታ ማዘጋጀት ነበር። ምዕዋ ጥሩ ቦታ አልነበረም። እጅግ ጥቂት ለመጠጥ የሚሆን ውኃ ነው ያለው፤ የባሕሩ ዳርቻም እጅግ ሰፊ ነው። በጥቅምት ወር መባቻ ገደማ በስተምሥራቅ በኩል ወዳለው የዙላ ባሕረ ሰላጤ ለመጠጋት ሞከሩ። መሄቱ ገሬቶቸው ወደሥፍራው ለመጠጋት የሚያደርጉት ሙከራ አስቸጋሪ ነበር። አንደኛው መርከብ ከባሕር ውስጥ ቋጥኝ ተጋጨ። በአትራብያው ከተማ አልነበረም። ምግብ ተፈልጎ የሚገኝበት ሥፍራም የለም። በተከፈለው ባሕረ ሰላጤ መካከል ሆኖ ባሕሩ የት እንደሚያበቃ እንዲሁም ከየት እንደሚጀምር ማየት አይቻልም። ድንጋይም ሆነ እንጨት የሚባል የለም። እንዲያም ሆኖ ሊያርፉበት የመረጡት ይህንኑ አካባቢ ነበር። የባሕሩ ዳርቻ ሜዳማ ቦታ በስተሰሜን በኩል ጠበብ ብሎ ይታያል። የአቅጣጫ ማመልከቻ መብራቶችን በሹማ እና ዶሲ ደሴቶች ላይ መሥመር በመዘርጋት ተከሉ። የቦምቢይ ባሕር ኃይሎችም ድምፅ የሚሰጡ ምልክቶችን አደረጉ። በቅሎዎቹ ወደ የብስ ለመሻገር በውኃው ሲንቦጫረቁ የተመለከታቸው ኢንጂኒየር መሿለኪያ ነገር እንደሚያስፈልጋቸው ታሰበው። 700 ሜትር ርዝመት ያላቸው ጠሦስት መሿለኪያዎችን አዘዘ ከሕደን መጣለት። በአሥር ቀናት ውስጥ የመጀመሪያው 650 ቶን ከሰል፣ አንድ መርከብ ግመል፣ በአምስት የእንጨት ሳጥን የታሸገ 50,000 ማርያ ቴሬዛ የብር ገንዘብ በተዘጋጀው ደረቅ ወደብ ተራገፈ። አንድ ቡድን ወደ ደጋማው የሀገሪቱ ክፍል የሚያደርሰውን መንገድ እንዲቃኝ ተላከ። ከአሥር ቀናት በኋላ ቡድኑ ተመለሰ። መንገዱ ባልተለመደ መልኩ እጅግ አደገኛ ነው ሲል ግኝቱን ገለጸ። እንደገና ወደሌላ አቅጣጫ ተጓዘ።

በስተምዕራብ በኩል ደረቃማ ፈለግ ተከትለው ሲሄዱ ቁልቁለት አጋጠማቸው የቁልቁለቱ መንገድ በየጠርዙ እየጠበበ የሚሄድ ነበር። መሬቱ እዚህ ጋር ለስላሳ ሲሆን በቅርቡ ባከተመው የዝናብ ወራት ተጠርጎ በመጣለት አዲስ አሸዋ ተሞልቷል። ዳገቱን መውጣት ሲጀምሩ ገደሉ ይበልጥ እየጠበበ ሄደ እና ድንገት ከሜዳ ደረሱ። የገደሉ ግራና ቀኝ ጠርዙ አንድ ሺህ ሜትር ከፍ ያለ ነበር። እዚያ ላይ ሆነው ነጠብጣብ ያለበት ላባቸውን ተሸክመው የጥንብ አንሣ እና አሞራ መንጋ በሰማይ ላይ ሲንሸራሸር አዩ::



«ገደሉ እርስ በራሱ በሻካራ ደረቱ ሊተቃቀፍ የናፈቀ ይመስላል» ሲል ለመቃኘት የተላከው ቡድን ገልጾታል።:: ሸለቆው ከ228 ሜትር ገደማ ባይበልጥም በውኃ ከፉኛ ተሸርሽሯል። ሥፍራውንም «የሰይጣን መሻገሪያ ደረጃ» አሉት። ሰንዓፈ ሲደርሱም ይህ መንገድ ወደ ደጋማው አካባቢ ይወስደናል ሲሉ ተስማሙ። ወደ ወደቡ እንደተመለሱም ኮሎኔል ሜርዌዘር አሥር አግረኛ ተዋጊዎች እና ከቦምቢይ የመጡትን መንገድ ጠራጊ ወታደሮች 228 ሜትር ይሆናል በተባለው የሰይጣን መሻገሪያ ደረጃ መንገድ እንዲያወጡ አሠማራ። ቡድኑ ሥራውን ለማጠቃለል ሦስት ወር ፈጅቷል።

ቴዎድሮስ የተቃጠለችውን ከተማ ወደ ኋላው ትቶ ወደ መቅደላ ጉዞ ጀመረ። 50,000 የሚሆን ሕዝብ እያመነታ ተከተለው። ወታደሮች፣ ሲቪሎች፣ ከለላ ፈላጊዎች፣ እሥረኞች ነበሩ። ሁሉም በአንድም በሌላም በኩል ግዞተኞች ናቸው። አንድም በንጉሣቸው እብደት፣ አንድም በታላቁ ሲቫስቶፖል መድፍ ይዞታ ተስበው። በእነዚህ ወራት በመንገድ ላይ ቴዎድሮስ ከሠራዊቱ ጋር እኩል እየሠራ ጨለማው ተገፎለታል። እንደ እነሱ ለብሶ፣ የሚሠሩትን ሁሉ ይሠራል። ማምሻውን ደግሞ ወደ እርሻ ሄዶ ጭብጥ የጉበስ ፍሬ ያመጣና ይፈጫል። ከዚያም በምንጭ ውኃ ሙቅ(አጥሚት) ይሠራል። ከፊቱ በተጋረጠው ከባድ ሥራ ምክንያት ጭካኔው ቀስ በቀስ እየተነነ ጠፍቶ የቀድሞው ካሣ ብቅ ማለት ጀመረ።

ብላንክ እንደጻፈው ፣ ጉዞው አስከዛሬ አሳከፍቶት ከነበረው እጅግ ግሩም የሚባል ነው። በአያንዳንዱ ርቀት ከገደል እናት እና ከየሜካው አማፅያኑ እንቅስቃሴውን ይከታተሉ ነበር። እንዳቸውም ግን ጥቃት ሊሰነዝሩበት አልደፈሩም። ላለፉት ሃያ ዓመታት በየሥፍራው እና ገበያው የሚገናኘው ሰው የሚነጋገረው ቴዎድሮስ የተለየ ኃይል አለው የሚል አስተሳሰብ አዳብሯል። ጥቃት ልትሠነዝርበት አስበህ፣ ምንም የሚያሠጋኝ ነገር የለም ባልክበት ቅፅበት ያኔ ነው ድንገት አደጋ ሊያደርስብህ የሚችለው።

«ዓይኖቹን ከድኖ አያውቅም» ይባላል። «ሕልም አያልምም። ደመናው ሳይገፋ በጨለማው ከአርሱ ተጠንቀቁ » ።

ከአምስት ሳምንታት ጉዞ በኋላ ጨጨሆ ደረሱ። እዚያ እስኪደርሱ መንገዱ ከሞላ ጎደል የተደላደለ ነው። አሁን ወደ ሰሜን የሚያቀናው ጎዳና ወደተከዜ የሚወስድ ሰርጥ ነው። በስተደቡብ ሸለቆው ወደ አባይ ይወስዳል፤ ወደ ጥቁሩ አባይ። ወደ ተፈጥሮው ድልድይ ደረሱ። እንደ ቢላ ጫፍ የሾለ ዐለት በመካከላቸው ያልፋል። በሌላው ወገን ራቅ ብሎ የጥቁር ድንጋይ ግድግዳ ተጠማዞ ወርዶ ይታያል። ሚሲዮናውያኑ ዛንደር፣ ቤንደር፣ እና ኪንስለን በዚህ ሥፍራ መንገድ ሠርተዋል። እንዲያም ሆኖ እነሱ የጠረጉት መንገድ ሲቫስቶፖልን ለሚጎትት ጋሪ የሚበቃ ዓይነት አልነበረም። ለሳምንታት የድንጋይ ጠረባው ቋቋታ እና የሠራተኞች የሥራ ወቅት እንጉርጉሮ በዐለቱ ግድግዳ መካከል ሲያስተጋባ ሰንብቷል። ዐለቱን ሲጠርቡ የሚፈርሰው መሬት ከመድረሱ አስቀድመው እየቀለቡም ከሚሸት ሥፍራ እየከተቱ ገደሉን አመቻችተው መረማመጃ ማድረግ ቻሉ።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ቴዎድሮስ ጨጨሆ ላይ ከቀትር በኋላ ሲሆን ለአውሮጳውያኑ፤ «ባሮቹን ለመሥረቅ እህዮቹ መጥተዋል መባሉን ሰማሁ» አላቸው ። ምን ማለቱ እንደሆነ አላብራራላቸውም። በዚያን ቀን ምሽት ወታደሮች ወደ ጎጆቻቸው አከባቢ የመምጣታቸውን እንቅሥቃሴ ሰሙ። ወደ ንጉሡ



መሰዱ። በአውሮጳውያኑ ላይ ክሱን ሲያቀርብ በርካታ ሰንሰለቶች ከፊቱ ተቀምጠው ነበር። ቴዎድሮስ በካቴናው አላሠራቸውም ነገር ግን በትንሽ ጎጆ ውስጥ ከአርሱ አቅራቢያ እንዲቀመጡ አደረገ። ይህን ለምን እንዳደረገም ፍፁም አልነገራቸውም።

ታሕሳስ ወር አጋማሽ አካባቢ መንገዱ ተጠናቀቀ እና ጨጨሆ ላይ የተደራጀው የጦር ሠፈር ተነሣ። ያ ሁሉ ሠራዊት ገደሉን መውጣት ሲጀምር እና መሣሪያ የተሸከሙት ጋሪዎች በአዲሱ የድንጋይ ጎዳና ሲንቀሳቀሱ ጥቃት ተከፈተባቸው። ጦሮች እና የድንጋይ ናዳ ከገደሉ ይወርድ ጀመር። የሞቱት እና የቆሰሉት በያሉበት ወድቀው የተተፉት ድንጋጤ ወደቀባቸው። በግርግሩ ሚስስ ሮዘንታል አዲስ የወለደችው ሕፃን ልጇ ከእጇ ሊያመልጥ ነበር። አማፂዎች በወቅቱ ያንን ጥቃት ቴዎድሮስ ብቻውን ቆሞ በአንባ እየተመለከተ «እኔ መጥፎ ከሆንኩ ለምን እግዚአብሔር አይገድለኝም? ፍትህ በሰማይ ተኝቷል፤ እሱ እስኪነቃ እኔ በዙፋኑ እለሁ እናም ተገቢውን ቅጣት እሰጣለሁ» ማለቱን መዝግበዋል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ መልዕክተኛ ከበስተ ሰሜን ቴዎድሮስ የተናገረውን የሚያረጋግጥ መልእክት ይዞ መጣ። ባሮቹን የሚሠርቁት እህዮች መጥተዋል።

«አገሬ ገርዎች፣ አለቆች፣ የሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም የአቢሲኒያ ሕዝብ፤ የአቢሲኒያ ንጉሥ የሆነው ቴዎድሮስ የብሪታኒያውን ቆንስል ካሜሮንን፣ የብሪታኒያውን ልዑክ ራሳምን፣ እንዲሁም ሌሎች በርካቶች የሠለጡ ሃገራትን ሕግ በመጣስ ማሠሩ ይታወቃል። እነሱን ለማስለቀቅ የተሞከሩ ሁሉም ወዳጃዊ ጥረቶች አልተሳኩም። ንግሥቱ እነሱን ነጻ ለማውጣት ጦር መርቼ እንድመጣ አዝዘውኛል። የብሪታንያ ጦር በአከባቢያችሁ በሚደርስበት ጊዜ የብሪታንያ ንግሥት ከእናንተም ሆነ ከሀገራችሁ ጋር ፀብ እንደሌላቸው የአብሲኒያ ሕዝብ ሆይ ልብ በሉ» የሚለው ደብዳቤ ታትሞ በሮበርት ኔፒር ስም ተፈርሟል። ቴዎድሮስ በምፀት ፈገግ አለ። አዋጁ ምን እንደሚል ለማንም አልተናገረም። ራሳም በሰጠው የቆርቆሮ ሳጥን ውስጥ ከተተው እና ወደ ሥራው ተመለሰ። ወደ መቅደላ መድፍ ጉተታ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ

መቅደላ ላይ ሁለት መልእክት በአንድ ጊዜ ደረሰ። ቴዎድሮስ እና ሠራዊቱ ከደብረ ታቦር ተነስተዋል፤ ምኒሊክ እና ጦሩ ከሸዋ ጉዞ ጀምረዋል። ሁለቱም ወደ መቅደላ ነው የሚገሠግሡት። ሥልጣን ላይ ያሉት ከሰሜን በኩል ቴዎድሮስ እንዲመጣላቸው ይመኛሉ። ቀሪዎቹ ደግሞ ምኒሊክ ቀድሞ እንዲደርስ ይጸልያሉ። ከጥቂት ወራት በፊት ነጻ ስለማውጣት የሚጠቁም ሌላ ሹክሹክታ ነበር ተራራው ላይ የተሰማው። ዋግሹም ጎበዜ በድብቅ ለአቡነ ሰላማ ማንሳሳት ይችሉ እንደሁ የሚጠይቅ መልእክት ላኩ። እመዕ ቀሳውስት ተመለመሉ። ሽተርን ድንገት በአካባቢያቸው ለጦርነት እና ለግድያ የሚዘጋጅ እንቅስቃሴ መኖሩን ልብ ብሏል። ብዙ ጠበቁ ዋግሹም ጎበዜ ቴዎድሮስን ሊፋለሙት ነው የሚል ወሬ ደረሳቸው። «ይህን አውሬ ካላጠፋሁ ወታደሮቼ ይፈሩብኛል፣ ሚስቴም ትትፋብኛለች» ፎከሩ ዋግሹም፤ ግን አላደረጉትም።

ስለምኒልክ የተወራው ይልቁንም የተሻለ ተጨባጭ ነገር ነበር። ዜና መዋዕሉ እንዲህ ጽፎታል፤ «መቅደላ ላይ ምኒልክን የማይወድ አልነበረም። መቅደላ በቆየበት ጊዜ በስፖርት እና በፈረስ ግልቢያ እንዲሁም በበዓላት ቀን የሚመስለው አልነበረም» ከመቅደላ ካመለጠ ከሁለት ዓመታት በኋላ ወጣቱ ምኒሊክ የሸዋ ንጉሥ ሆነ። የቴዎድሮስን ሕጎች ሲቀስም ኖሯል እናም 30 ሺህ የራሱን ወታደሮች አደራጀ። መቅደላን መቆጣጠር ከቻለ ከጉንት ወዳጁ ከአቡነ ሰላማ ይገናኛል። ሁለቱ በጋራ ሆነው መላ ሀገሪቱን አንድ ያደርጋሉ። ዋግሹምም ሆኑ ምኒሊክ አቡነ ሰላማን ለመቅደላ ብቻ ሳይሆን በመላ ሀገሪቱ እንደ ግንባር ቀደም አርማ ነው የሚመለከቷቸው። እውነታው፤ አሁን እሳቸው የከሰሩ ዓይነት ሰው ናቸው። ሌላው ቀርቶ በእሳቸው እና በቴዎድሮስ መካከል የነበረው መልካም እና ታላቅ ግንኙነት እንኳ የለም። በወርቃማው ዘመን በ1846 በመንግሥት እና በቤተክርስቲያን መካከል የነበረው መከባበር አከትሟል።

በሁለቱ መካከል የተነሳው ፀብ ሁለቱንም ነው የጎዳቸው። በዚህም ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ በአንድ ሥፍራ ተወስነው ነው የኖሩት። እንዲያም ሆኖ አቡነ ሰላማ ከፈረንጆቹ እሥረኞች ጋር ተገናኝተው አያውቁም። ሆኖም ግን ከራሳም እና ዶ/ር ብላንክ ጋር በድብቅ ደብዳቤ ይላላካሉ። የአቡኑ ጤና ታውኳል። ዶ/ር ብላንክ እንደሚለው ተስፋ የቆረጡ ወንዶች እንደሚያደርጉት ብዙ በመጠጣትና በመብላት ሆኖም ግን በቂ እንቅስቃሴ ባለማድረግ የመጣ የጤና ችግር ነው። እየቆየ ሲሄድም ብላንክ ይህን ልማድ እንዲያስሽሉ አግባባቸው። በአግባቡ በመመገብ መጠጣቱንም በልክ አደረጉት። ያኔም የጤናቸው ይዞታ ተሻሻለ። ግን ብዙም ሳይሰነብት ብላንክ ከወዳጁ የከረመው ጥያቄ መጣበት። «ትንሽ አረቄ አለህ?፣ ወይም ደግሞ ትንሽ አፒየም? »



ወር አንድሮና የአቡኑን ተስፋ ያንሰራራ አዲስ ጭምጭምታ መቅደላ ላይ ተሰማ። ምኒሊክ እየገሠገሠ ነው። ምኒሊክ እንደሚወራው ወደ መቅደላ ውጤት ከእሳቸው ጋር የሚገናኝ ከሆነ ታማሚው ጳጳስ አንድ እንዲሳካ ይሻሉ። ወደ ግብፅ መመለስ። በዚህ ወቅት ግን የጤና ዳግም ከፋ። ዶ/ር ብላንክን ያገኙ ዘንድ የእሥር ቤቱ ኃላፊ ጠየቁ። እምቢ አሏቸው። ቴዎድሮስ ጠላቱ እና አውሮጳውያኑ እንዲገናኙ አልፈቀድም። እናም በብላንክ ፋንታ የተራራው ላይ የከብት ሃኪም ተላኩላቸው። ቴዎድሮስ ከደብረ ታቦር በተነሣ በሁለት ሳምንቱ ጥቅምት አምስት አቡነ ሰላማ ዐረፉ። መቅደላ ላይ ታላቅ ኀዘን ሆነ። ቀሳውስት እና ደባትሩ ለ24 ሰዓታት ጸሎት ፍትሐት አደረጉ። አስከሬኑ በወርቅ ዘቦ ተሸፍኖ ተቀመጠ። የጸሎት ሥርዓቱ እጅግ ረዥምም ነበር።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ኅዳር ወር ማለቂያ ገደማ ከወደ ደቡብ በኩል አመሻሽ ላይ አቧራ ይታይ ጀመር። በማግሥቱ ጠዋት ቀድመው የተነሱት ከበታች የጦር ሠፈር ተመለከቱ። ወታደሮች፣ የተጫኑ ከብቶች፣ አግረኛ ሠራዊት እንዲሁም ጥቁር እና ቀዩ የሸዋዎች ድንኳን ተዘርግቷል። «ምኒሊክ ነው!» የመቅደላ ሰዎች ጮኹ። « በግዛቱ ያለውን ፍጥረት ሁሉ ይዞ ነው የመጣው! ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም! »

ከቴዎድሮስ የተቃቃሩት ንግሥት ጥሩነሽ የተራራውን ጥበቃ ለማጠናከር ሞከሩ። ለባለቤታቸው ታማኝ ያልሆኑ ግን ደግሞ ለእሳቸው ለታመኑ ወታደሮች የቁርስ ግብር አበሉ። ጠጅ እና በቂ ምግብ አቀረቡ። ከዚያም ተራራው በተቃውሞ ጩኸት ተናወጠ። በዚያን ዕለት ማለዳ እታች ከሠፈረው ጦር ጥቂቱ ከሠፈሩ ለቅቆ ወደ ገደሉ ሲያመራ ተመለከቱ። የጠመንጃ እና መድፍ ተኩስ እርምጃቸውን ገታው። ከዚያም ወደ ሠፈሩበት ሲመለሱ ታዩ።

በማግሥቱ እሑድ ነበር። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አልታየም። ሽተርን ይህ ኢትዮጵያ ውስጥ በተዳረሰው ስብከተ ወንጌል ምክንያት የመጣ መሆኑን አልተጠራጠረም እናም ክርስትናን እንዲቀበሉ ሲሰብካቸው ወደነበረው ጥቂት ሙስሊም ዘንድ ይህንኑ ሊነግራቸው ሄደ። ፈረሰኞች ከጦር ሠፈሩ ሲወጡ ተመለከተና ሰንበቱን እና ለሙስሊሞቹ ሊያወራ የነበረውን ሁሉ ተወው እና ባለበት ሆኖ እንቅስቃሴያቸውን መከታተል ቀጠለ። ሆኖም የተከሰተ ነገር የለም። ወደ ኋላቸው ተመለሱ። በማግሥቱም ሆነ በተከታዩ ቀን አንዳች የሆነ ነገር አልነበረም። ረቡዕ ዕለት የመቅደላ ተራራ ላይ ነዋሪዎች በአካባቢያቸው ምን እየተከናወነ እንደሆነ ለማጣራት ያነፈንፉ ጀመር። ከበታቻቸው ከሠፈረው ጦር ከፊሉ መንቀሳቀሱን አዩ። እርግጥ ነው፤ የሸዋው ቅዱስ ተክለሃይማኖት ታላቅ በዓል ነው። ምኒሊክ ተራራዋን ነጻ ለማውጣት ይህቺን ቀን ይጠብቅ እንደነበረ ሁሉም ተረዱ።

«አሁን መጡ!" ጮኸ ሽተርን። «አሁን ሰዎችን የሚያድነው አውሬ ድራሹ ይጠፋል። አሁን ሰንሰለታችን ይበጠሳል! አሁን የእሥር ቤት በሮቻችን ይበረገዳሉ!»።

ሆኖም ግን ዓይናቸው እያየ የምኒሊክ ሠራዊት ፊቱን አዞሮ ወደሸዋ መጓዝ ጀመረ። የመቅደላ ጠባቂዎች በድል አድራጊነት ስሜት ፈነጠዙ። እሥረኞቹ ኢትዮጵውያን እና እነሽተርን እጅግ አዘኑ።። ምኒሊክ ለራሳም ሕግን በማክበር ጦሩን ለመመለስ መወሰኑን የሚገልጽ መልእክት ላከ። ሌላ ምክንያት ግን ወዲያው ይናፈስ ጀመር። ማክሰኞ ማምሻው ላይ ከወደሰሜን አከባቢ ምልክት ታይቷል። ብላንክ እንደሚለው ምኒሊክ ሠራዊቱ «ቴዎድሮስ መጣ!» የሚለውን ቢሰማ ከተራራው ላይ እንደ ነፋስ ዕልም እንደሚል ያውቃል።



## ምዕራፍ ስድሳ

እንዲያም ሆኖ ቴዎድሮስ ገና ረዥርም ጉዞ ይቀረዋል። አውሮጳውያኑ እሥረኞች ከባሕር ወደቡ የመጣ መልዕክተኛ ካዩ ሰነበቱ። በአማፅያኑ በኩል እናገኛለን ብለው የተጠበቁት የነጻነት ተስፋ ጠብ የሚል ባለመሆኑ ሥጋታቸውን መቆጣጠር አልቻሉም። የወቅቱን ስሜታቸውን ሽተርን ሲገልጸው፣ «ጥላዎች፣ ጭጋግ እንዲሁም ተስፋ መቁረጥ በእሥር ቤት ግድግዳችን ላይ ይደንሱ ነበር፤ በዓይኖቻችን ላይ ያንፀባርቁ ነበር» ብሏል።

ዓርብ ዕለት ከቀትር በኋላ ታኅሣሥ ወር ኢጋማሽ ላይ መንገድ ያደከመው ሰው የተራራውን መግቢያ አልፎ መጣ። በሚያስፈራው የቴዎድሮስ ግዛት በዋግሹም እና ራስ ካሣ ግዛት፣ በዚያ ላይ በዋግ እና ላስታ እንዲሁም ትግራይ ተራራማ ቦታዎች አልፎ መቅደላ ደረሰ። ደብዳቤ እንዳመጣላቸው ለፈረንጆቹ በሹክሹክታ ጠቆመ። ቆየት ብሎ እንደሚሰጣቸው ነገራቸው በዚያች ዕለት ምሽት ሁሉም ዶ/ር ብላንክ ጎጆ ውስጥ ጠበቁት።

ሽተርን ግን ከዚህ በፊት ስለመጡላቸው ደብዳቤዎች ለማሰብ ሞከረ። «ምን ይዘውልኝ መጡ?» ጠየቀ። «ምንም» እናም ወጥቶ ለብቻው ወደጎጆው ሄደና መጽሐፍ ለማንበብ ከስሜቱ ጋር ይታገል ገባ።

ወዲያው ግን «ሽተርን! ሽተርን!» ዶ/ር ብላንክ ጠራው። እንደገና ወደጠራው ሲመለስ «ወታደሮች እየመጡ ነው ! ኮሎኔል ሜርዌዘር ከባሕር ወደቡ ደርሷል!»።

ወዲያው ሁሉንም ረሳውና፣ «ሠንሠለታችን ቀለለ፣ ልባችን ተደሰተ፣ በተምታታ ጉዞ ላይ ነበርን፣ ላለፉት አራት አመታት በትክክልም ግራ የተጋባን እንግዶች ነበርን» አለ። ብላንክም እጅግ ተደስቷል። መልዕክቱን ደጋግሞ አነበበው። «እንዲህ አድርጎ ከናፈቀው ፍቅረኛው የተላከለትን መልእክት ያነበበ አፍቃሪ የለም» ብሎም ጽፏል። ተጣልኩ የሚል ስሜት እና አገልግሎት ሰጥቶ ምሥጋና ሲጠብቅ ዋጋውን ያጣ ያህል ይሰማው ነበር።

እሱ የተሰማውን ስሜት ሊረዳ የሚችለው «ለወራት በአእምሮ ሥቃይ ላይ ከርሞ በመጨረሻ ደስታ ያገኘ ሰው ብቻ ነው» ሲልም ገልጿል። ያም ሆነ ይህ የብሪታኒያ ክብር ሊመለስ ነው፤ የልጆቹ ደምም አፀፋው ሊከፈል ነው።

አሁንም ግን እሥረኞች ናቸው። ሌሊቱ እየተጋመሰ የደረሳቸውን ዜናም ሲያብላሉት ሠንሠለቱ በእግር በእጃቸው እንዳለ ነው። አሁንም ተራራው አናት ላይ ነው የሚገኙት። ለመሆኑ ኔፒር ምን ያህል ተዘጋጅቶ ይሆን? ለመሆኑ

ስለዚህች አስቸጋሪ ሀገር ያውቅ ይሆን? ለሀገሪቱ የቀረቡ ሌሎች በርካታ ሳይሳካላቸው እሱ እንዴት ቴዎድሮስን ከሥልጣን ማስወገድ ይቻለዋል? ቴዎድሮስ መቅደላ አስቀድሞ ከደረሰ እንዴት ነው ተባባሪው ኃይል ሊደርስ የሚችለው?

በዋግሹም ጎበዜ እና በምኒሊክ አማካኝነት ነፃ የመውጣታቸው ተስፋ ከንቱ ቀርቷል። አሁን ደግሞ ውጥረት የበዛበት ሁኔታ ከፊታቸው ተደቅኗል። «ከነ አውጪዎቹ በቁጥጥሩ ሥራ ያደረጋቸውን ማሸነፍ ይችሉ ይሆን? ወይም ደግሞ መቃረባቸውን ሲሰማ አምባውን ደም በደም እንዲያደርገው ኢጋጣሚውን ያመቻቹ ይሆን? » ሽተርን ስጋት ገብቶታል። «የነጻነት እና የሞት መቃረብ እንዲህ እኩል ተመዝኖ አያውቅም የወዳጅ እና የጠላት ዱካም እንዲህ በጉጉት ተጠብቆ አያውቁም» ።



## ምዕራፍ ሲድሳ አንድ

[illegible] ወደቡ ላይ የሚደረገው የብሪታንያ ጦር ዝግጅት በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ [illegible] አዲስ ዓመት ሲገባ በርካታ ጓዝና አቅርቦት ከወደቡ ደርሷል። [illegible] መንገድ ሥራ እየተካሄደ ነው። የእንጨት ነጋዴዎችም [illegible] ሚሽለኪያው ጦሩን የተከተሉት ሕንዶች በበረሃው ሥፍራ [illegible] ማለት ጀምረዋል። [illegible] ግን በዚህ ወቅት ተከሰተ። የኒው የርከ ሄራልድ [illegible] አንድ ችግር [illegible] ሰራዊቱ የደረሰበትን ደረጃ ለመዘገብ [illegible] ተንታኝ ጄንሪ ሞርተን ስታንሊ የዘመቻው [illegible] ደረሰ።

[illegible] እና ቻታም ላይ ከርሞ የላሸቀው የብሪታንያ ጦር ሠራዊት ለዘመቻ [illegible] አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ዘንግቷል» በማለትም ከመምጣቱ ትችቱን [illegible] 8,000 በቅሎዎች መጥተዋል ሆኖም እንዳቸውም ኮርቻ የላቸውም። [illegible] ይሄ አይገኝም። እነዚህ እንዲቀርቡ ወዲያው ወደ ውልዋች ትዕዛዝ [illegible] የታዘዘው ከሬሚያ ዘመቻ ላይ ለተመሳሳይ ተግባር የዋለው ዓይነት [illegible] እንዲመለስ ተደረገ እና ከስዊዝ [illegible] መጥፎ ነው በሚል በሙቶችት [illegible] ጥሩ አልነበሩም። በመጨረሻ ያን ያህል የተዋጣለት [illegible] እነዚህም ኮርቻ ተመረጠ። ኮርቻው ብቻውን 20 ኪ.ግራም [illegible] ከአታጉ የተገኘው ኮርቻ ተመረጠ። ኮርቻው ብቻውን 20 ኪ.ግራም ይመዝናል፤ በዚያም ላይ ትልቅ ዕቃ ለመጫን የሚመች አልነበረም።

ሁኔታው በእንዲህ እንዳለ፤ ፋርሶቹ (ፐርሺያውያኑ) በቅሎ ጋላቢዎች አስቀድሞ [illegible] እንዲከፈላቸው ጠየቁ እና አድማ አደረጉ። ይፋዊው ዘገባ እንደሚያሳየው [illegible] የባሰ ነበሩ። ከፐርሺያውያኑ ተምረው እነሱም በቅሎ መጋለብ [illegible] የማመላለሱን ሥራ በመጠኑ አቅልለውት ነበር ማለት ይቻላል። [illegible] ባልደረባ ኮሎኔል ዋርደን ሕንዳውያን ባልደረቦችን የቦንቤይ ጎዳና [illegible] ጦር ባልደረባ ኮሎኔል ዋርደን [illegible] የተለያየ ደረጃ እና የኋላ ታሪክ ውልዶች ይላቸዋል። በዘመቻው የተከተሉት [illegible] ከሀኪም ቤት የወጡ አውሮጳውያን እና ያላቸው ሰዎች ናቸው። የከበሩ ነጋዴዎች [illegible] አብዛኞቹም ኢጋጣሚውን ለመጠቀም የፈለጉ [illegible] ነበሩበት። [illegible] በዚህ ቡድን ውስጥ የገባው አግረ ናቸው። ለምሳሌ አንዱ ፋርሳዊ (ፐርሺያዊ) በዚህ ቡድን ውስጥ የገባው [illegible] ከዕለታት በአንዱ ቀን በርከት ያሉ በቅሎ ጋላቢዎች መንገዱን ሃጂ ለማድረግ ነው። ከዕለታት በአንዱ ቀን [illegible] ነበር የተጓዙት። ድንገት ጠፉ። አብዛኞቹም ወደ ምዕዋ ነበር የተጓዙት።

አዛዡ የማይጠየቅበት በቂ ምክንያት አለ። ይኸውም የሚያግባባቸው የጋራ ቋንቋ የለም። አንድ ቀን 150 በቅሎ ጋላቢዎች በቁጣ እየተንጫጩ አንዱን አዛዥ ከበቡት። ወዲያው አምፀዋል ብሎ ከሰሳቸው። ጉዳዩ ሳይታወቅ ገሚሱ 50 ጅራፍ ተገረፉ። በኋላ ግን ሲጣራ ችግሩ ለቀናት ምግብ ስላልተሰጣቸው ምክንያቱን ለመጠየቅ የተሰበሰቡ ሰዎች ሆነው ተገኙ።

አብዛኞቹ በቅሎዎች ብቻቸውን ቀሩ። በጦር ሠፈሩ መካከል (ወዲህና ወዲያ ይዟዟሩ) ጀመር፣ ባልለመዱት አከባቢ ተደናግረዋል። ድምፃቸውን እያሰሙ ይዟዟሩ እና ወዲያው የሚያገኙትን የውኃ ጉድጓድ ተጋፍተው ባዶውን ያስቀሩታል። ጥማት እና በሽታ የተፈራረቀባቸው በቅሎዎች ቀስ በቀስ መሞት ጀመሩ። በየቦታው የሚወድቀው አካላቸው የጦር ሠፈሩን እና የባሕር ዳርቻውን ከበርካታ የግመል በድን ጋር ተደምሮ ሞላው። በሕይወት የቀሩት እንስሳት ሥራቸው በእጥፍ ከፍ አለ። ብዙዎቹ ታድያ ከድካም ብዛት ራሳቸውን እየሳቱ መፈንገል ጀመሩ።

የእንስሶቹ በድን በወደቀበት እየተነፋ በሚያስከትለው ሽታ አከባቢው ታፈነ። ይህ እንዳይበቃ አዲስ እና በአፋጣኝ የሚገድል በሽታ ተቀሰቀሰ። የሞቱትን እንስሶች እንዲቀብሩ ለአከባቢው ነዋሪዎች የዕዳት መኮንኑ በመጀመሪያ ለሂንዱ ሠራተኛ የሚያስተላለፈው ትዕዛዝ ወደ አረብኛ ይተረጐማል፤ በመቀጠል ወደ ሳሆ። ሆኖም ግን ሳሆዎቹ የሚባለውን በትክክል አይረዱትም። በመጀመሪያ እንዴት እንደሚሠራ አያውቁም በዚያ ላይ በቅሎም ሆነ ሌላ እንስሳ ስለመቅበር የሚያውቁት የለም፤ ከዚህ ሌላ እንዲህ በድንገት በአንድ ጊዜ ይህን ዓይነት የእንስሳት ዕልቂት አይተው አያውቁም።

በመጨረሻ የእንስሳት ሃኪሙ የበሽታውን ምንነት ደረሰበት። የታይፎይድ ትኩሳት ነበር። ያለ ምግብ እና ውኃ እንዲህ ባለው የባሕር ወደብ ላይ በውድ ዋጋ የተገዙ በቅሎዎችን ያለ ዕረፍት እና ያለተመልካች አምጥቶ የሚያሠራ እንዴት ያለ ጭንቅላት ያለው ሰው ይሆን?

11 ሺህ ነፍስ በየቀኑ ከዐራት ሊትር በላይ ሥሣ በነፍስ ወከፍ ይፈልጋል። ይህን ለማቅረብ ለሳምንት 28 ሺ ፓውንድ ያስወጣል። የውኃ እጥረት የየዕለቱ ሥጋት ነው። ለአስቸኳይ ጊዜ የሚሆኑ ሁለት ማጣራቀሚያዎች ከብሪታኒያ እንዲመጡ ተደርጎ ስዌዝ ላይ ተሞልተው ወደ ቀይ ባሕር በመርከብ ተላኩ።

ተዋጊውን ኃይል በሙቶዎች የሚቆጠር ርቀት ወደ ኢትዮጵያ እያቀረቡ፣ ውኃ እያጠጡ እና እየተከላከሉ፤ አስፈላጊውን እያቀረቡ መምራት ትልቅ ሥራ ነው። ሂደቱም ቢሆን የሚያበረታታ አልነበረም። ሎርድ ራግላን ወታደሮችን ቫርና ላይ በማብዛቱ ነበር የክሬሚያው ዘመቻ ውድቀት የጀመረው። ከጠላት ኃይል በሚበልጥ ሁኔታ ዘጠኝ መቶ ወንዶች እዚያ አልቀዋል። እጅግ ኃይለኛ ሙቀት ባለበት የቀይ ባሕር ዳርቻ አሁን የሚታየው ትርምስም እንዲሁ አሥጊ ነው። በዚያ ላይ በማይመቸው እና ምሥጢራዊ በሆነው ተራራማ አከባቢ የሚካሄደው ዘመቻ መጠነኛ ወታደራዊ ብቃት ላላቸው የሎንደን እና በምቤይ የጦር ሰዎች ከፍተኛ ጥፋት ይደርሳል የሚል ግምት አሳድሮባቸዋል።



## ምዕራፍ ስድሳ ሁለት

ቴዎድሮስ እየገፋ ነው። ተደናቂው ሲቫስቶፖል ዘቢጥ ኮረብታ ላይ ደርሷል። ከአማፅያን ከተሰነዘረበት ጥቃት ተርፏል። የአከባቢው ነዋሪዎች ቴዎድሮስ እዚያ ይደርሳል ብለው አልገመቱም። ከብቶቻቸው መስኩ ላይ ተሠማርተዋል። ሠራዊቱ በቀላሉ የሚፈልገውን ያህል ወሰደ፤ ከደብረ ታቦር ከተነሱ ወዲህም ለመጀመሪያ ጊዜ ደህና ተመገቡ።

ከአሥር ቀናት በኋላ ሁኔታው ተቀየረ። የቁልቁለቱ ጉዞ ሲጀመር ሲቫስቶፖልን የመንከባከብ ተግባር ጀመረ። መድፉ እንዳይወድቅ በርካቶች ከፊት፣ ከኋላ በጋሪው ሥር ድጋፍ የሚሆን ኮረት እየሞሉ መውረድ ቀጠሉ። በአንድ ወገን ከበታቻቸው ሺ ስልሳ ስድስት ሜትር ዝቅ ብሎ የጅዳ ወንዝ ተንጣሏል። ቴዎድሮስ ቴዎፍሎስ ቫልድማየርን ጠራው።

ከደብረ ታቦር ከተነሡ በኋላ ላለፉት ሁለት ወራት ቫልድማየር ታምሞ ነበር፤ ተቅማጥ ብዙ ስለጎዳውም በሰው ሸክም ነበር የሚንቀሳቀሰው። ከሳምንታት በፊት አንድ ቀን ማታ ቴዎድሮስ ከመኝታው አስነስቶ ከፊቱ አቆመው እና ጣቱን እያወዛወዘ፤«እሞህ ሳይሆን እየተሳለቅከብኝ ነው ፡ ለማምለጥ አቅደሃል። አንተና ሌሎቹ ልታመልጡ ነው» አለው። «ግርማዊነትዎ፤ ብፈልግ እንኳን አልችልም» አለ ቫልድማየር። ሠንሰለት እና የእግር ብረት ወደ ድንኳኑ መጣ፤ ጠባቂዎቹ ግን «ግድ የለም ይህንን ባይታሠርም እኛ መጠበቅ እንችላለን» አሉ።

አውጥተው ሣሩ ላይ ጣሉት። ከጥቂት ሰዓት በኋላ ቴዎድሮስ ወደ ሚስቱ እና ቤተሰቦቹ መልሶ ሰደደው። እንደገና በሚቀጥለው ቀን ማታ እንዲወስዱት አዘዘ። ከጦር ሠፈሩ ዳር አስቀምጠው ተውት። ቀዝቃዛው መሬት ላይ ተንጋለለ። ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ በቅዝቃዜ የሠራ አካላቱ ደንዝዟል።

ቫልድማየር ስምንት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ቆይቷል። በቆይታውም አግብቶ ልጆች ወልዷል፤ ትምህርት ቤት ከፍቷል፤ ወንጌል ሰብኳል በዚያም ላይ የቴዎድሮስን ወዳጅነት አትርፏል። አሁን ግን ሁሉም እንዳልነበረ ሆኗል። እግዚአብሔር ከዚህ ከባድ ሥቃይ እንዲገላግለው ተመኘ። በነበረበት ሥፍራ ለብዙ ሳምንታት ቆየ። ሚስቱ የባህል መድኃኒት አዋቂ እማከራ ሰደደችለት። የተሰጠውን ባህላዊ መድኃኒት ወስዶ መሻሻል አሳየ።

ጂዳ ሸለቆ ሲደርሱ ቴዎድሮስ እንደገና አስጠራው። አሁንም በደንብ ያላገገመው ቫልድማየር ሸለቆውን ሲመለከት የሚጠብቀውን ሥራ ገመተ። በቀጣይም ሳምንታት እሱ እና ቴዎድሮስ ሆነው በቁልቁለት የሚያወርድ መንገድ እንዲሁም ወንዙን ተሻግሮ ማዶ የሚያደርስ ጎዳና በመፈለግ ተጠምደው ሰነበቱ። በሺዎች

የሚገሙቱ ሰዎች መንገድ ለመጥረግ ድንጋዩን ሲገምሱ ሲያስተካክሉ እና ሲያንቋቁ ይታዩ ነበር።

በወዲያኛው ወገን በቴዎድሮስ እና በመቅደላ መካከል ሁለት ኮረብታዎች ተደንቅረዋል። ደላንታ እና ዳውንት። የአዚያ አካባቢ ነዋሪዎች በአስቸጋሪነታቸው ይታወቃሉ። እነሱ ካመፁ ቴዎድሮስ መቅደላ መድረስ አይችልም። ለወራት እንደ መቅደላ ነዋሪዎች ዋግሹም ጎበዜ ቴዎድሮስ ላይ ጥቃት ያደርሳል በሚል የደላንታ ሹሞች ተባብረው ንጉሡን ሲወጉ እና ሲያስወግዱት ሲጠባበቁ ነበር። ዋግሹም ግን የተጠበቀውን አላደረገም።

ቴዎድሮስ እንዳይተናኮሉት ብቻ ሳይሆን ምግብ እና ሠራዊት እንዲሰጡት ይፈልጋል። ለአለቆቻቸው መሃላውን የያዘ ቃሉን ላከ። በክርስቶስ ሞት እንደማይዘርፍ እና እንደማያጠቃቸው ማለላቸው። ወዲያው እህል የጫኑ በቅሎዎች ከደላንታ ተላኩ። በሺህ የሚቆጠሩም በመንገድ ሥራው ሲረዱ መጡ።

ከደብረ ታቦር እዚህ ለመድረስ ሦስት ወር ፈጅቶባቸዋል። ከሁለት ሸለቆዎች ባሻገር 32 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ መቅደላ ይገኛል።

## ምዕራፍ ሲድሳ ሦስት

የዘመቻው ዋና አዛዥ እና መሪ ሮበርት ኔፒር ዙላ የባሕር ሠርጥ ወደብ ሲደርስ የተደረገለት ወታደራዊ አቀባበል ራሱን የቻለ ቲያትር ነበር። ቦንቤይ የቆየው ስንቅ እና ትጥቅ መላኩን ለማጠናቀቅ ነው። ታህሳስ 29 ቀን 1860 ዓ.ም በወታደራዊ የደንብ ልብሱ አጊጦ፤ በመዳሊያና ኒሻን ደረቱን አሸብርቆ ከተሣፈረበት መርከብ ሲወርድ የደንብ ልብስ በለበሱ የባሕር ጠላቂዎች መካከል ሲያልፍ የመድፍ ተኩስ ተቀበለው።

ከተደራጀ ሁለት ወራት ካስቆጠረው ወደብ የአርምስትሮንግ ባውዛ እንፀባረቀ። ገሚሱ ብርሃን ሞቃትና ቅርብ ወደሆነው ባሕር ሲያበራ ቀሪው ከውኃው አልፎ ያለው አከባቢ ላይ አንጣጠረ።ኔፒር በወደቡ ላይ የተሠራውን የኮሚሳሪያት ማደራጃ መጋዘን፤ የወደቡን ኃላፊ ቢሮዎች፣ 10 ሺህ ሰዎች የሰፈሩባቸውን ድንኳኖች እንዲሁም ሌሎች ነገሮች ተመለከተ። የክብር ዘቦች በጠብመንጃ ሰላምታ ሰጡ ወታደራዊ ባንዱም ማርሽ አሰማ። ኔፒር ከመርከብ ወረደ።

የ57 ዓመቱ የጦር መሪ ከነሙሉ ግርማው ንጉሣዊ ባለሥልጣን ነበር። ለስላሳ አነጋገሩ እና ትክ ብሎ ማየቱ የማይነቃነቅ ጥንካሬው ማሳያ ናቸው። ለ42 ዓመታት በሕንድ ጦር ኃይል ውስጥ በኢንጂኔርነት እና ከዚያም በተዋጊነት አገልግሏል። በአመፅ ወቅት የመከላከያ ኃይሉን፤ በ1852 ደግሞ ወደቻይና የዘመተውን የብሪታንያ ጦር መርቷል። ሚስቱ በመሞቷ በቅርቡ ነው የ18 ዓመት እንግሊዛዊት ያገባው። ዘመቻ መሄድ ስላለበት በምቤይ ጥሏት ነው የመጣው።

በቅሎዎቹ ላይ የደረሰው ነገር አደናግጦታል። አጠቃላይ እቅዱ በመጓጓዣ ላይ ጥገኛ ነበር። አስቀድሞ መንቀሳቀስ የሚቻል አልነበረም። የብሱ ላይ በ40 ማይል(64 ኪሎ ሜትር) ርቀት ቀዳሚው ጦር እና 2,000 ተከታዮቹ ፣ 1,300 ሻምላ(ጎራዴ) እናሳንጃ እንዲሁም አራት ጠብመንጃ ብቻ ነው ያላቸው። የደረሳቸው ተጨማሪ አቅርቦት ለምን ያህል ጊዜ በሕይወት እንደሚያቆያቸው አይታወቅም። ወደቡ ላይ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ አለ። አንድ አደጋ ቢደርስ የከፋ ጥፋት ያስከትላል። ኔፒር ስንቅ እና ትጥቅ ያስከተለ አንድ መኮንን በሰንዓፈ በኩል ላከ። ሥራው ስለእያንዳንዱ እንቅሥቃሴ መረጃ ማምጣት ነው።

በወረርሽኝ በሽታ የተዳከመውን የበቅሎዎች ጉዞ ዳግም ያደራጅ ጀመር። እስካሁን ሳይጠፉ የቆዩትን በቅሎ ጋላቢዎች በ5 ሺህ ከፑንጃብ በመጡ አዳዲስ ሰዎች ተካ። ከኮሚሳሪያቱ ጋር ተነጋግሮ መረጃ ካሰባሰበ በኋላም ኔፒር 15 ሺህ ጥንድ ቦቲ ጫማዎች ከቦምቤይ እንዲላኩለት አዘዘ። 15 ሺህ ተጨማሪ ብርድ ልብሶች፣ 15 ሺህ ጥንድ የሱፍ ካልሲዎችም በተጨማሪ እንዲላኩለት ጠይቋል። በዚያም

ላይ ቀለብ አከሷል። መድፉን ይዞ ቴዎድሮስ መቅደላ ለመድረስ እየታገለ መሆኑ እየታወቀ ኔፒር ይህን ሁሉ ጦር፣ እንዲሁም ስንቅ እና ትጥቅ በማደራጀት እቅድ መጠመዱ ትችት አስከትሎበታል። ለምንድነው ፈጠን ብሎ ቅልጥፍ ያለ ሁለገብ ሠራዊቱን ልኮ ጥቃት በማድረስ ካሰበበት መቅደላ ሳይደርስ ከመንገድ ሊያስቀረው ያልቻለው?

ኔፒር ለዚህ ደንታ አልነበረውም። በእሱ ግምት ቴዎድሮስ ሴቫስቶፖልንም ሆነ ሌላውን መሣሪያውን ጥሎ መቅደላ ላይ በቀናት ውስጥ ይደርሳል። ከንፍ ያለው ካልሆነ በቀር ምንም ዓይነት ጦር እዚያ ከመድረስ ሊያግደው አይችልም ሲልም ደምድሟል።



## ምዕራፍ ሰድሳ አራት

ኔፒር ግምት ትክክል አልነበረም። ቴዎድሮስ መሣሪያዎቹን ትቶ መሄድ አይችልም። የዋግሹም ጎበዜ ቃኚ ወታደሮች ለጉዞው የሚያመቸውን መንገድ በገደልና ሸለቆው መካከል ሲያሠራ በቅርብ ርቀት ይከታተሉታል። 30 ሺ ወንዶች ጥቃት ሊያደርሱበት አድብተው ቢጠብቁም ያሉትን መሣሪያዎች በመፍራት ደፍረው ያሰቡትን ማድረግ አልቻሉም። ቴዎድሮስም ቢሆን መሣሪያዎቹን ትቶ ዞር ቢል ዋግሹም ጥቃት እንደሚሰነዝሩበት ያውቃል። ስለዚህ ከሴቫስቶፖል ጋር ተቆራኝቷል።

በጥር ወር ንጉሡ ከፍተኛ ስሜት ላይ ነበር። ከደላንታዎች ጋር ያደረገው ስምምነት ወደ መቅደላ መልዕክተኛ ለመላክ መንገድ ከፍቷል። ከወራት በኋላም ተራራው ላይ ለሚገኙት ወዳጆች እና ለራሳም ደብዳቤ ላከ። ራሳም በቅርቡ ስለቴዎድሮስ የጭካኔ ርምጃዎች በቀር ሌላ ነገር አልሰማም። የብሪታኒያ ከፍተኛ ጦር መምጣቱን መስማቱ በጠላትነት ያስፈርጀኛል ብሎ ሰግቷል። በመጀመሪያ የቃል መልእክት ደረሰው። መልዕክቱን ያመጣውን ሰው ራሳም ሲመለከተው ከድምፁ የእሥረኞቹ ዕጣ ፈንታ ወለል ብሎ ታየው ። ሞት።

«እንደምነህ ወዳጄ እንደምንነህ? እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ቤት ሆር ደርሻለሁ። በቅርቡ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ወዳንተ እየተቃረብኩ ስመጣ አንተን እንደማገኝ በማመን ደስታ እየተሰማኝ ነው። ትልቅ መድፍ መያዜ ነው ጉዞዬን ያዘገየው። መቅደላ ደርሼ ስትመለከተው ግን በእርግጥ ታደንቀዋለህ። እኔም የደረሰብኝን ችግር ሁሉ እረሳለሁ። ወንድሞችህ ደህና መሆናቸውን ጠይቅልኝ»።

ራሳምም በተመሳሳይ ምላሽ ጻፈ። «ግርማዊነትዎ የላኩልኝን መልእክት በአክብሮት ተቀብያለሁ። ቤትሆር በሰላም መድረስዎን በመስማቴም ተደስቻለሁ። የግርማዊነትዎ ጤንነትም በጥሩ ሁኔታ ላይ በመሆኑ ሳልደሰት አልቀረሁም። ፈጣሪ ጤና እና ብልፅግና ይስጥዎት እና የጥረትዎን ብርሃን በቅርቡ ያሳዮን፤ በተጨማሪም መልካም የገና በዓል ይሁንልዎ። ዶ/ር ብላንክ እና ሚስተር ፕሪዶ፣ ሚስተር ካሜሮን እና ወገኖቹ እንዲሁም ሚስተር ሸተርን እና ባልደረቦቹ ለግርማዊነትዎ የአክብሮት ሰላምታቸውን ልከዋል»።

ለብላንክ እና ሸተርን ግን ደብዳቤዎቹ ትርጉም አልባ ነበሩ። ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ዓይነት። በእርግጥም የቴዎድሮስ እና የራሳም ግንኙነት ግራ አጋቢ ነበር። ላለፉት ሦስት ዓመታት የተጫወተው ዲፕሎማሲያዊ አቀራረብ እና የራሱ ባሕርይ በቴዎድሮስ ዘንድ አክብሮት አስገኝቶለታል። ይህም ይመስላል አውሮጳውያን እሥረኞች የከፋ ቅጣት እንዳያጋጥማቸው የረዳው። ሸተርን ግን

ራሳም ከእሱ በፊት ከነበሩት ዲፕሎማቶች በተቃራኒ ቴዎድሮስን በአጉል መልኩ ለመረዳት ሞከሯል ሲል ይተቸዋል።

በተቃራኒው ግን ምናልባት ራሳም ቴዎድሮስን የተሻለ ተረድቶት ይሆናል። ከሌሎቹ አውሮጳውያን በተለየ ቴዎድሮስ በማይደራደርበት ጉዳይ ፉክክር ውስጥ አይገባም፤ ከእሱ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ መጥፎዎቹን ነገሮች እንዳላየ ያልፋቸዋል። ስለዚህ ራሳም እንጂ ቴዎድሮስ አይደለም ሁለት ገፅ ያለው ማለት ነው። በዚያው ወቅት ለዋግሹም ጎበዜ፣ ለንጉሥ ምኒሊክ እና ለኦሮሞዋ ንግሥት መስታወት ቴዎድሮስ ላይ ጥቃት እንዲያደርሱ ደብዳቤ ይልክ ነበር። በዚያን ወቅት ቴዎድሮስም ከእሥረኞች ጥቂቱን ወደ መቅደላ ላከ። ከሁሉም የሚፈራው ዋግሹም ተፈራ ነበር። እሱ አምልጦ ከዋግሹም ጎበዜ ጦር ጋር ከተቀላቀለ በጋራ ሆነው ቴዎድሮስን ለማጥቃት ሊደፋፈሩ ይችላሉ። ቴዎድሮስ፣ ተፈራን በብዙ ወታደር አጅቦ ነው የላከው። መቅደላ ሲደርሱ ጠባቂዎች ለምልከት ተኮሱ። ቴዎድሮስም እየተቃረበ ስለነበረ ተሰምቶታል።

የኢትዮጵያ የገና በዓል ሲቃረብ ቴዎድሮስ ለ«ንግሥቲቱ» ለየተመኙ እሱ የሚወዳቸውን ምግቦች እንድታዘጋጅ መልእክት በቃል ላከ። በዚህ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም አምስት የሚሆኑ ደብዳቤዎችን ለየተመኙ የላከው። ደብዳቤዎቹ ተመዝግበው ባይቀመጡም ስለቴዎድሮስ ግላዊ ሕይወት የሚያንፀባርቁ ናቸው። መቅደላ ላይ ከጥሩነሽ እና ከልጃቸው ጋር በአንድ ቤት ነበር የምትኖረው። ሁሉም ደብዳቤዎች የሥላሴን ስም አስቀድመው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ የሚለው ይከተላል። ከዚያም ሰላምታው።

«እንደምን ሰነበትሽ? እኔ ደህና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን። ለእናትሽ ለወይዘሮ ሠናይት እና ቤተሰቦቿ፤ እንዲሁም ለሁሉም ቤተሰብ እንደምን ናችሁ? በይልኝ» እያንዳንዱ ደብዳቤ ለየተመኙ ተመሳሳይ መልዕክቶችን የያዘ ነው ።

«አትፍሪ። አሁን ወዳንቺ እመጣለሁ ---------- እግዚአብሔር በፈቀደ ቀን እንገናኛለን ------ የምትፈልጊውን ሁሉ እስኪ ንገናኝ ድረስ በእግዚአብሔር ኃይል ለእኔ ንገሪኝ። ---- አትፍሪ። የእኔ እህት፣ የእናቴ ልጅ። ነፍስና ሥጋዬ ካልተለያዩ በቀር በእግዚአብሔር ኃይል ሳላይሽ አልቀርም»።



## ምዕራፍ ሰድሳ አምስት

በ1859 ዓ.ም በሚርዊዘር የተመራው ቡድን የዙላ ባሕረ ሰላጤን ለመጀመሪያ ጊዜ እግሩ ሲረግጥ ያገኘው ከላዩ ደረቅ የሚመስለውን ረግረጋማ የባሕር ዳርቻ ነበር። የባሕር ሰላጤው ወደኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ ሰጥ ያለ ሜዳ ሆኖ ይዘልቃል በዚህ ሥፍራ የባቡር ሃዲድ መዘርጋት ይጠበቅባቸው ነበር። ለዚህ የሚፈልጋል ያሉትንም የቁሳቁስ ዝርዝር እና ሌሎች ነገሮችን ይልኩላቸው ዘንድ በምቤይ ወደሚገኘው ከፍተኛ ኢንጂነር መልእክት ላኩ። በሺዎች የሚቆጠሩ የጉልበት ሠራተኞችንም መልምለው በጀት አወጡ። ሆኖም መጀመሪያ አካባቢ ቀዳቸው አልሠራም። የተለያዩ አምስት ጭነቶችን የያዙ ተሽከርካሪዎችን ወደዙላ ወደብ ተላኩ። አብዛኞቹ ለሃዲዱ የሚሆኑ ዕቃዎች ግን የጎበጡ ወይም የተበላሹ ነበሩ። የአካባቢው ሙቀት ከአምስት እና ስድስት ወራት በላይ የመሥራት አቅምን አይሰጥም። በዚያ ላይ ለሃዲዱ ሥራ የተሰማሩት የዘርፉ ሙያተኞች ሳይሆኑ ወታደሮች ናቸው። ሥራው ለእነሱ እንግዳ ነበር።

ሀገር ውስጥ ያለውን ጨምሮ እያንዳንዱ ተመራማሪ ብሪታኒያዊ የኔፒር ጦር የሚገጥመው ዕጣ ፈንታ የከፋ እንደሚሆን ለማረጋገጥ በዚህ ወቅት ዙላ መገኘት በቂው ነው። እንደ ባቡር የሚያገለግሉት በቅሎዎች ተሸመደመዱ፤ የባቡር ሃዲዱ ተንገራግጮ ቆመ። የባሕሩን ውኃ መጠቀም ያልቻሉት ፋርጎዎች 1,200 ጋሎን( 4,542.494 ሊትር) ውድ የሆነውን ንፁህ ውኃ በየቀኑ ይፈጁት ጀመር። በዚህም ምክንያት ዝግጅቱ ይህ ነው የሚባል መሻሻል አላሳየም። ኔፒር ሲመጣ ደግሞ ጭራሽ ባሰበት። የባቡር ሃዲድ ግንባታ ዕውቀትና ልምድ ባይኖራቸውም ግን ወታደሮቹ በመንፈስ ዕናት ያሳዩት ጥረት በወቅቱ ተመዝግቧል። በዚህ ምክንያትም በ1860 በርካታ ማይል ጥርጊያ መንገድ የበረሃውን ተከል አያቋረጠ ሊዘረጋ ተቻለ። ሐዲስ ወንዝንም የሚያቋርጥ ድልድይ ተሠራ። የመጀመሪያው የባቡር ጣቢያ ተገነባ፤ የባቡሩ ፉርጎዎቹ በብረት መጓጓዣ መንገዳቸው ላይ መሽከርከር ያዙ። በሳምንታት ውስጥም የባቡሩ መንገድ በየቀኑ ለ15 ሰዓታት ይሠራ ጀመር። በጦር ሠፈሩ የሚገኙት 12 ሺህ ሰዎች እና እንስሳት ኑሮ ቴክኖሎጂው ላይ የተመሠረተ ሆነ። የአሜሪካን እንፋሎት ማቀዝቀዣዎች ንፁህ ውኃን፤ በእንፋሎት የሠሩ መርከቦች ደግሞ ምግብ ያቀርቡላቸዋል። ዙላ የሚገኘውን ጦር በሥራ ላይ ከተሠማሪ ኃይል ጋር የሚያገናኘው ቴሌግራፍ ነበር። ቆየት ብሎ ግን ለስልክ መገናኛ የሚሆን መሥመር ለመዘርጋት የሚያስፈልገው የመዳብ ሽቦ ጭምር ከቦምቤይ እና በርሚንግሀም መጣ። መሥመሩ ሲዘረጋም በአንዳንድ አካባቢ በሰልክ እንጨት ላይ በሌላው ስፍራ ደግሞ ከትላልቅ ድንጋይ ጋር እየታሰረ ከፍ ብሎ ተተከለ። መሥመሩ እየረዘመ በሄደ መጠንም ከአካባቢው ነዋሪዎች ምሰሶዎች እየተገዙ ተዘረጋ። ግንኙነቱም ቀናት እና ወራት መውሰዱ ቀረ። ግን ይሄም እንከን አላጣውም። በየጊዜው ይቆራረጥ ጀመር። መጓጓዣዎች ሲተላለፉ፣

ግመሎች ፣ዝሆኖች እንዲሁም የጦር ሰፈሩ ነዋሪዎች፣ ዝንጀሮዎች እና ራሳቸው አቢሲኒያዎች መሥመሩ ላይ ችግር ይፈጥሩ ነበር። መዳቡ ይሰረቃል፣ ሽክማቸው ሲወርድላቸው በቅሎዎች ከመሥመሩ ተሸካሚ ምሰሶ ላይ ይታከካሉ።

እንዲህ ባለ ያልተፈተሸ ሥፍራ የሚደረገው ጉዞ ሳይንሳዊ ምርምርን ይጋብዛል። ከሮያል ጂኦግራፊካል ሶሳይቲ፣ ከሊመንትስ ማርክሃም፣ ከቦምቤይ የእንስሳት ምርምር ተመራማሪዎች፣ ከካልካታ የሥነምርምር ተመራማሪ፣ እንዲሁም ከሕንድ ጦር የአየር ንብረትና ጠባይ ምርምር ባለሙያ በአንድነት ወደዚያ ተልከዋል። ከጥንታዊ ታሪክ ጋር ቁርኝት እንዳላት የሚታወቀው ሀገር ቅርሶች የመኖራቸው ተስፋ የብሪታንያ ቤተመዘክርን በማማለሉ የሥነ ሰብእ ተመራማሪው ሪቻርድ ሆምስን ለመግዛት የሚያስችላቸው ጠቀም ያለ ገንዘብ አስይዞ አሠማርቷል።

ጥር ወር ማለቂያ ገደማ ኔፒር ዙላ ወደብ ሲደርስ ለዘመቻው የሚያስፈልገው ሁሉ ተጠናቆ በማግኘቱ ረክቷል። ጉዞውን ለማድረግ ተዘጋጀ። እሱ በነበረበት ሥፍራ እና አውሮጳውያኑ እሥረኞች በሚገኙበት መቅደላ መካከል 500 ኪሎ ሜትር ርቀት አለ። በመንገዱም የቴዎድሮስ ጠላቶች የነበሩት ራስ ካሣ እንዲሁም ዋግሹም ይዞታዎችን ማለፍ ግድ ነው። እነዚህ እርስ በርስ ደግሞ ጠላት ነበሩ። እነሱን ማሸነፉ በራሱ ቀላል ሥራ አልነበረም።

# ምዕራፍ ስድሳ ስድስት

ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ እየተቃረበ ሲመጣ የእንግሊዝ ጦር እየተዳረሰ መሆኑን በመስማቱ ስሜቱ ተቅበጥብጧል። የኔፒር ጦር በዚያ ፍጥነት መቃረብ በአንድ ጎን ሲያስደምመው በሌላ ወገን የመደፈር መንፈስ ሰቅዞታል። ለማርቲን ፍላድ ግንኙነታቸውን እንኳ ለመጥራት በመጠየፍ፣

ደብዳቤዎቻቸውን ያመጣህልኝ፣ እነዚያ ይመጣሉ ያልካቸው ሰዎች መጡ » አለው። ለእንግድነት የመጡ ይመስልም፣ «ለምን በተሻለ መንገድ አልመጡም? በጨው ሜዳው በኩል ያለው መንገድ ጤናማ አይደለም» ሲልም የሚመጡበት መንገድ አመቺ አለመሆኑን ገለጸለት።

ቃራሽ ቴክኖሎጂዎቻቸውን ለማየት ከፍተኛ ጉጉት አደረበት። አሁንም ለእሱ ሰላም የመፍጠር መንገዱ የተዘጋ አልመሰለውም። «በፍቅር ሊያሸንፉኝ ይችላሉ። ሌላ ሐሳብ ካላቸው ግን ከምንም ሊገቱኝ አይችሉም። ደም በደም አድርጌው እሞታለሁ» አለው ለቫልድማየር።

«የመጡት በእግዚአብሔር ፈቃድ ይመስለኛል» አለው ቴዎድሮስ ለፍላድ። «ከላይ ያለው ካልገደለኝ በቀር ማንም አይገድለኝም። እሱ መሞት አለብህ ካለም ማንም ሊያድነኝ አይችልም » ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እሱ የሚመርጣቸውን ታሪኮች ደጋግሞ ይጠቅሳል። አንዳንዶቹ ድልን ያመለክታሉ። የሕዝቅያስን እና የሰናክሬምን ታሪክ ለፍላድ አስታወሰው። እግዚአብሔር አሶራውያንን አጥፍቶ ሕዝቅያስ እና ኢየሩሳሌምን ጠብቋል። አሁንም ቴዎድሮስን በመርዳት

መሆኑን መልዕክተኞች ነገሩት። የውጪው ጦር መምጣትም ቴዎድሮስ አጥቶት የነበረውን አንድነትና ትብብር ጋበዘ።

ያም ሆኖ ግን ንጉሡ ለውድቀቱ የሚገፋፋው ኃይል መልሶ ተነሣ ይላል ብላንክ። ከደላንታ ሸለቆ ሲታገል ቆይቶ ከገደሉ አፋፍ ሲደርስ የደላንታን አለቆች ዞረባቸው። ተገደሉ። ከቀናት በኋላ ለጥ ካለው የደላንታ መስክ ደረሱ። ቫልድማየር አብሮት መጓዙን ቀጥሏል። «የሚያምር የስንዴ ማሳ ከፊታችን ተንጣሏል። በቆሎውም እንዲሁ። የደረሰውን እሸት ወታደሮቹ ወረዱበት። የተረፉቸውን እሳት ለኮሱት» ።

ያን ቀን ቴዎድሮስ ለየት ባለ ስሜት ውስጥ ነበር። ቫልድማየር ስለአውሮጳ አብያተ ክርስቲያናት እንዲነግረው ጠየቀው። ከአንድ ቤተክርስቲያን ደጅ ቆሞ «በእኛ ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ትልቅ ቦታ ያለው ፤ አስፈላጊ ነገር ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከምንም በላይ ጨለማው ይወደዳል» አለው ሚሲዮናዊው።

ቴዎድሮስ አስተያየት አልሰጠም። ምናልባት ተስማምቶ ይሆናል። ወደ መንደራቸው ሲመለሱ ቫልድማየር ከኔፒር ጋር ሰላም እንዲወርድ ሐሳብ አቀረበ። መነሻ የሆነው ቴዎድሮስ ለጦሩ ያሳየው አድናቆት እና ያደረበት ስሜት እንዲሁም በየጊዜው የነገረውን ትንቢታዊ ታሪኮች በዚያም ላይ እራሱ እንደጻፈው ሕይወቱ አደጋ ላይ መሆኑ ተሰምቶት ነበር።

ቴዎድሮስ ቁጣ በነደደባቸው ዓይኖቹ እየተመለከተ፣ «አህያ! ለማኝ! ሰላይ! ሀገሬን እንድሸጥ ትፈልጋለህ?! እንጀራዬን አልበላህም? ከእኔ ጋር ልትሞት አይገባህም? ሰላም እንድፈጥር ትፈልጋለህ!» ከወገቡ ሽጉጡን መዘዘ። ቫልድማየር እንደተቀመጠ ሽጉጧን ተመለከተ። ዝም አለ። «ከእነዚህ ነጭ አህዮች ጋር የምታረቅ ይመስልሃል? በል እንጂ?» ቴዎድሮስ አልተከሰበትም። ጦሩን አነሣ እና ቫልድማየር ላይ አነጣጠረ። «በአጠገቤ አልፎ መሬቱ ላይ ተሰካ» ይላል ቫልድማየር። ቁጣው ወደ እራሱ ተመለሰ። ቴዎድሮስ እጆቹን በራሱ ሸማ ሲጠቀለል ቫልድማየር በመገረም ተመለከተው። ንጉሡ ልብሱን ቀድዶ መሬት ላይ ተዘረረ።





በሰሜን የሀገሪቱ ክፍል ወጣቱ የትግሬው ገዢ ራስ ካሣ የኔፒር አዋጅ ቅጂ ደረሳቸው። «ለሀገር ገዢዎች፣ ለአለቆች፣ ለሃይማኖት መሪዎች እና ለአቢሲኒያ ሕዝብ፣ የአቢሲኒያ ንጉሥ ቴዎድሮስ እሥረኞችን መያዙን እናንተም ታውቃላችሁ። የእንግሊዝ ጦር በአካባቢያችሁ በሚያልፍበት ጊዜ የአቢሲኒያ ሕዝብ ሆይ፣ የእንግሊዟ ንግሥት በእናንተ ላይም ሆነ በሀገራችሁ ላይ እንዲሁም በነፃነታችሁ ላይ አኩይ ዓላማ እንደሌላቸው እወቁ« ።

ጊዜው ደርሶ የእንግሊዝ ጦር ወደ እሳቸው ግዛት ገባ። ራስ ካሣም ከኔፒር ጋር ለመገናኘት ተስማሙ። ለሁለቱም ሰዎች ግንኙነቱ ወሳኝ ነበር። ለዓመታት ወጥቶ ንጉሠ ነገሥት እንዲሆን መንገዱን ያመቻቻል። ለእንግሊዙ ጀነራል ደግሞ በእንግሊዝና በቴዎድሮስ መካከል የነበረው ግጭት ካሣ ወደ ከፍታው ማዕረግ ጠቃሚታው አጣዳፊ ነበር። ወደ መቅደላ ከሚያደርሰው መንገድ ከአንድ ሦስተኛው የሚበልጠው በካሣ ቁጥጥር ሥር ነው። ኔፒር 850 ወታደሮቹን አስከትሎ ከዚህ ደርሷል። አንድ ሁለት ቀን ጠበቀ። ካሣ ብቅ አላለም። በእስቸጋሪ መንገድ ተጉዞ እዚህ ሲደረሰው ኔፒር ሁለት ቀን መጠበቁ አቅበጠበጠው። አያንዳንዱ ቀን ለቴዎድሮስ እንደ ገፀ በረከት መስሎ ታየቸው። ያም ሆነ ይህ ስድስት ቀናትን ሳይወድ በግድ ራስ ካሣን ጠበቀ። ጥር ወር ማለቂያ ገደማ ራስ ካሣ 4,000 የታጠቀ ጦር አስከትለው ሐውዜን አቅራቢያ ደረሱ። ሁለቱም ወገኖች ከነሠራዊታቸው በአንድ ወንዝ ማዶ ለማዶ ሠፈሩ። ዕለቱ በጠዋቱ ብሩህ እና ሞቃት ነበር። በርካታ በቡድን በቡድን የሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎቹ ከበስተ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ብድግ አሉ። ያማረ ሸማ የለበሱ ትግሬዎች በመሥመር ተሰደሩ። ነጋሪቱ እየተጎሰመ የራስን ማዕረግ የሚያሳዩ ቀይ እና ቢጫ ሰንደቆች እየተውለበለቡ ወደ ወንዙ ቀረቡ። ወንዙ ጋር ሲደርሱም ለሁለት ተከፈሉ፣ ራስ ካሣም በነጭ በቅሎ ላይ ተቀምጠው ብቅ አሉ። ሹሩባ ለሰበሰው ራሳቸው ጃንጥላ ተዘርግቷል። ኔፒር የመጀመሪያው ነው የኢትዮጵያን ወታደሮች ሲመለከት። ለካሣም የአውሮጳን ጦር መመልከት እንግዳ ነው። ኔፒር ራስን በደፋ በድንኳኑ ተቀበለ። ባለጥንድ አፈሙዝ ጠብመንጃዎች፣ መነፅር እና ሌላም ሥጦታ አቀረበ። እንዲያም ሆኖ ዋግሹም ጎበዜን በመወጋቱ እንደማይተባበራቸው አስታወቀ። ካሣ ለሠራዊቱ እህል እንዲያቀርብለት ጠየቀ። እሱም ተገቢውን ከፍያ እንደሚፈጽም አረጋገጠ። ንግሥቲቱም ራስን እንደሚሸልሙ ቃል ገባለት። እንዲያም ሆኖ ስምምነቱ ለሌላ ጊዜ በይደር ተዛወረ። ካሣ በበኩሉ የእንግሊዝን ጦር ቃኘ። አርምስትሮንግ መድፎቹ ቀልቡን ስለሳቡት ረዥም ሰዓት ተመለከታቸው። ትግሬዎቹ ትጥቃቸውን ከመረመሩ በኋላ የብሪታንያ ጦር በሜዳ ውጊያ የሚደፍር እንዳልሆነ እውነት አመኑ። ሆኖም ግን ተራራማ ቦታ ላይ ዕድል እንደማይኖራቸው ገመቱ። አርምስትሮንግ መድፍ ከቴዎድሮስ መድፎች እጅግ ያንሳል።

ከዚያም የኔፒር ቡድን ወንዙን በመሻገር ወደትግሮቹ ጦር ሠፈር ዘለቀ። ወዲያው ስሜቱ ተቀየረ። ሕዝቡ ወደ ብሪታኒያ መኮንኖች ቀረበ። ነጋሪት ይደለቅ ጀመር። በካሣ ድንኳን ውስጥ በሁለቱም ሰዎች ፊት ላይ ብርሃን አርፏል። አስተናጋጅ ልጃገረዶች መሶቦችን፣ እንጀራ እና ወጡን ያቀርቡ ጀመር። ጠጅ ቀጂዎቹም ብዙ ነበሩ። ጭብጨባው አልፊታው ሙዚቃው ደመቀ። አዝማሪም ቅኔ አዘል ግጥሙን አንጎራጎረ። ኔፒር የብር፣ የእጅ አምባርና የወርቅ ጌጥ ተሸለመ። ካሣ የአንበሳ ለምድን በትከሻው አለበሰው። «ታላቅ ጀነራል እና ሰው ነዎት» አለው ካሣ።

በማግሥቱ ካሣ መጥቶ ኔፒርን ሸኘው። በእንግሊዞች ጉዳይ የገባን ከፋኛ እየቀጣ፣ በየሳምንቱ ከ27 ሺህ ኪሎ ግራም በላይ ስንዴ ያቀርብ ነበር። ከዚህም ግማሹ አንጣሎ(ሕንጣሎ) እና ዐዲግራት ወደሚገኙት የብሪታንያ የጦር ሠፈሮች ይላካል። ከእሱ በሚያገኘው የእህል አቅርቦት የተማመነው ኔፒር ወደ ደቡብ ግሥጋሴውን ቀጠለ።



## ምዕራፍ ስድሳ ስምንት

የካቲት ወር ማለቂያ ግድም የቴዎድሮስ እጅብ ከመቅደላ በሥላሴ ገደል በኩል ዘርቀት መታየት ጀመረ። ከደላንታ ሜዳ ላይ ወታደሮች፣ ምርኮኞች፣ ሲቪሉ ሕዝብ እና ኢጅግ የገዘፈ የጦር መሣሪያዎቹ ይታያሉ። በሽሎ ጦንዘ ዳር ሲደርስ ቴዎድሮስ በድጋሚ ወደመቅደላ ደብዳቤ ላከ። መልዕክተኞች መቅደላ ለመድረስ አራት ሰዓት ወስደባቸው። ቴዎድሮስ እና ሲቫስቶፖል ግን ተጨማሪ ሦስት ሰምንት ይፈጅባቸዋል። «ከእናንተ እጅግ ቅርብ ቦታ ነው ያለሁት። እንዴት እንደከረምክ አልጠይቅህም ግን እንደምን ኢደርክ?» የሚል መልእክት ለራሳም ላከ።

መጋቢት ኢጋማሽ ላይ ራሳም ውስጠ ወይራ ምላሹን ለቴዎድሮስ ላከ፤ ቴዎድሮስ እንደገና የወዳጅነት ሰላምታ ለካሜሮን እና ኮከቢ ሳይቀር ላከ። በዚያውም ለራሳም 2,000 የጀርመን የብር ሣንቲሞች፣ አንድ መቶ በጎች እና ሃምሳ ጊደሮች አብሮ ላከለት። «በእግዚአብሔር ኃይል ፈቅዶልኝ በሰላም ከደረስኩ ፊት ለፊት ተገናኝተን እናወጋለን። አታስብ!» እግረ መንገዱንም የራሳም የእሥራት ሰንሰለት እንዲፈታለት አዘዘ። መጋቢት መገባደጃ ላይ ብርቱ ዝናብ እየጣለ (ዶፍ እየወረደ) ቴዎድሮስ መቅደላ ደረሰ። ቀሪው መንገድ እስኪዘጋጅ መድፉን ከሰላምጌ በታች ገደሉ ላይ አስቀመጠ።

ጉዞው አምስት ወራት ተኩል ፈጅቶበታል። የሚብላላው ሐሳቡ፣ እንዲሁም የቆጣው ኃይል በአብዛኛው በድንጋይ ፈለጣው፣ በመንገድ ቅየሳ እና በጦር መሣሪያው ኩብደት ተደነቃቅፏል። የጉዞው ስኬት ደግሞ አሁን አዲስ ጥርጣሬዎች አመጣ። ሊፋለማቸው የሚገቡ አንጃዎች አሉ፣ ተከራካሪዎችና ከዳተኞችን ማጥፋት፣ ሀገር ከጂዎችን የመዳኘት የከዱ ወታደሮችን የመበቀል፤ በዚያም ላይ ታማኝ ወዳጆች፣ ቤተሰቦች እንዲሁም እሥረኞች አሉ።

የመቅደላ አምባ አለቃዎችን ሰብስቦ የእያንዳንዳቸውን የሥራ ክንውን አደመጠ። አምብዛም ለማይቀርቡት ባለቤቱ እቴጌ ጥሩነሽ እና ለአቂባቱ የተመኙ መምጣቱን የሚገልፅ መልእክት ላከ። በጎን ደግሞ ለጥሩነሽ እንዳይመጡ ሌላ መልእክት ላከ።

ለቤተክህነቱ አገልጋዮች በማግሥቱ እንዲሰበሰቡ ትዕዛዝ አስተላለፈ። እጅግ በርካታ መነኮሳት፣ ካህናት እና ደብተሮች፣ ቃጭልና የሚያንፀባርቁ መስቀሎቻቸውን ይዘው ከእሥር ቤቱ ፊት ለፊት ባለው መስክ ላይ ተሰበሰቡ። ሁሉም እጅ ነሱና ንጉሡ እስኪናገር መጠባበቅ ጀመሩ።

ከፊቱ ተደርድረው ሲመለከታቸው የቴዎድሮስ ንዴት ጋለ። የቤተክርስቲያኗ እምቢተኝነት ከአማፅያኑ ባልተናነሰ የቴዎድሮስን አስተዳደር አሽመድምዷል፤ ከሚሲዮናውያኑ አንዱ በ1852፤ «የሀገሪቱን አብዛኛውን መሬት የሚይዘው

መንፈሳዊው ክፍል ሲሆን፣ ንጉሡ ከዚህ ግብርም ሆነ ከወታደሮቹ ሩብ ያህሉን የሚደጉም ገቢ አያገኝም» በማለት ቴዎድሮስ የገጠመውን ሥጋት ጽፏል።

«ራሳቸውን አጬጌ እና አቡን የሚሉት ሕዝቡን እና ሀገሪቱን ጨቁነዋል» አለ ቴዎድሮስ።

የመነኮሳቱ የበላይ፣ አጬጌ ወደፊት ተራመዱ፣ «ጃንሆይ! ምን አልኩ ማንንስ በደልኩ? ከወታደሮችዎም አንዱ ይህን አድርጓል ካለኝ ቅጣቱን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ» አሉ። መነኩሴው ድንጋይ አንስተው በጫንቃቸው ተሸክመው እና ከንጉሡ እግር ሥር ጣሉት። ቴዎድሮስ ቆፍጠን ብሎ ተመለከተው።ሌላኛው የትግራይ ተወላጅ ቄስ አባ ገብረ መስቀል ንጉሡ በእስክንድሪያ ሃይማኖት ፀንቶ እንዲለ በመጠየቅ ሞገቱ።

«ከእስክንድርያ እምነት በቀር የትኛውን ልከተል እችላለሁ?» ጠየቀ።

«የፈረንጆቹን እምነት ተቀብለዋል ይላሉ»።

ከዚያም ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን እምነት ጠብቆ መቆየቱን ለካህናቱ ለማሳመን መታገል ነበረበት። ካህናቱ በበኩላቸው ነገሮች የሚመቻቹ ከሆነ ወደ ሮም ሃይማኖት የሚገቡ ወይም ወደ ሌላው የሚሻገሩ መኖራቸውን ማስረጃ እየጠቃቀሱ ሞገቱ። ቄሶች እና እንደ ንጉሤ ያሉ ከሃዲዎች ሀገሪቱን ለፈረንጅ ለመሸጥ እንደሚያሴሩም ተናገሩ። አሁን ደግሞ በተመሳሳይ ክስ ጣታቸው ወደእሱ እየጠቆመ ነው።

እንዲቀመጡ አዘዙ። ወደ ታዋቂው ዳኛ ወደ አለቃ ገብረ ኢየሱስ ዞረ እና፤ «ለምን ይሆን ሳኦል አቢሜሌክን እና ካህናቱን የገደለው?» ሲል ጠየቃቸው። ምን ሊከተል እንደሚችል ያውቃሉ። አቤሜሌክ ዳዊትን ደብቆ የቤተ መቅደሱን ኅብስት እና የጎልያድን ጦር እንደሰጠው ሳኦል ሲደርስበት «በእኔ ላይ ለምን አደማችሁ?» አላቸው። ከዚያም አቢሜሌክ እንዲገደሉ አዘዘ። ምክንያቱም ዳዊት እንዲያመልጥ ተባብረዋልና። ቴዎድሮስ በድጋሚ ጠየቀ፤ «ይህ የተደረገው በፍርድ ሂደት ነውን? » አለቃ ብልህ ሰው ነበሩ። የሚቀጥለው መዘዝ ታያቸው። «አዎ በፍርድ ሂደት ነው» ቢሉ ቴዎድሮስ ሁሉንም ለመፍጀት መነሻ ሊያገኝ ነው። «አይደለምም» ቢሉም ቴዎድሮስ በእርሱ ላይ የተደረገ ጥቃት አድርጎ ሊወስደው ነው። ስለዚህ አለቃ «ይህ በፍርድ ሂደት ይሁን አይሁን አላውቅም» አሉ፤ ያን ዕለትም ካህናቱ ሁሉ ተረፈ።

ቴዎድሮስ ግን ጉዳዩን አልዘነጋውም። በማግሥቱ ቴዎድሮስ ከአንድ ከፍተኛ ድንጋይ ላይ ወጣ እና ወደ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሄደ። በቁጣ እንደነደደ



የተመለከቱት ሁሉ ገብቷቸዋል። ከቤተክርስቲያኑ ደጃፍ የአንዱን ቄስ ጺም ጨምድዶ «ሃይማኖቱን ሊለውጥ ይፈልጋል አልከኝ?» ሲል አምባረቀባቸው። «ሌላ ሰው ሳያስገድደኝ አንገቴን እቆርጣለሁ»።

ጣሀኑ አስተያየት ንጉሡን አቀዘቀዘው እና ደም ከማፍሰስ አተረፈው። ንጉሡ ጥቂቱን በመርገም ለማስታገሥ ሞከረ። ጦር አንስቶ ምንጣፉን በኃይል ወጋ እና «የሚያዋርዱኝን ፈረንጆች እንዲህ ነው የማደርጋቸው» ሲል አምባረቀ። ከቤተክርስቲያን ወጥቶ ወደ እሥር ቤቱ ተጓዘ። ከሁለት ዓመታት ገደማ በኋላ አውሮጳውያን እሥረኞቹን ሊያይ ነው።

## ምዕራፍ ስድሳ ዘጠኝ

ለወራት ፈረንጆቹ አሥረኞች ቴዎድሮስ መቅደላ አይደርስም የሚል ተስፋ ነበራቸው። በጥር ወር ዶ/ር ብላንክ የቴዎድሮስን ጉዞ እና የብሪታንያን ጦር ግሥጋሤ እያነፃፀረ ጉጉት እና ደስታ በተደባለቀበት ስሜት «ታላቅ የመንፈስ ደስታ» ሲል ጽፎ ነበር፡፤ አሁን ደግሞ ንጉሡ እዚያው ይገኛል እናም ደስታቸው ተኑኗል። የሚሰማቸው ተስፋ መቁረጥ ብቻ ነው። ቴዎድሮስ መቅደላ እንደደረሰ ፈረንጆቹን የሚጠብቁት ወታደሮች ቁጥር እንዲጨምር አዘዘ። ኢብዛኞቹም የውጪ ዜጋ ነበሩ፡፤ አሥረኞቹ ይህን ርምጃ እንደ መጥፎ ምልክት ወሰዱት። የቴዎድሮስም ለራሳም የሚያደርገው ላላ ያለ አያያዝም የመከራቸው መቅለል አመላካች ሊሆን አልቻለም።

ቴዎድሮስ ከዛሬ ነገ መጥቶ ያየናል በሚል በሚጠባበቁበት ወቅትም ብላንክ «ነገ ምን የከፋ ነገር ይዞብን ይመጣ ይሆን በሚል ሥጋት በቂ እንቅልፍ አልተኛንም» በማለት የሚገኙበትን ሁኔታ ጽፏል። በመጋቢት ማለቂያ በአንዱ ዕለት፣ አኩለቀን ካለፈ በኋላ ቴዎድሮስም ወደ እነሱ እየመጣ የመሆኑን ዜና አውሮጳውያኑ አሥረኞቹ ሰሙ። በየጎጇቸው በጥድፊያ ወረቀቶችን ለመደበቅ ተራወጡ። ራሳምም ቢሆን ከቴዎድሮስ ጠላቶች የተላኩለት በርካታ ደብዳቤዎች ነበሩት። ከዋግሹም ጎበዜ፣ ከኢማም አህመድ፣ ከኦሮሞዎች መሪ እንዲሁም ከአንድ ሰዓት በፊት ከእጁ የገባው የንጉሥ ምኒሊክ ደብዳቤዎች በጎጆው ይገኛሉ። በየግድግዳው ቀዳዳዎች እና እንደኮርኒስ ከዘረጋው የሰሌን ንጣፍ ውስጥ ወሸቃቸው። አገልጋዮቹ ግን ራሳቸውን ነቀነቁ።«አይ ይህ ቦታ መጀመሪያ የቴዎድሮስ ወታደሮች ሲመጡ ሊፈትሹት የሚችሉት ሥፍራ ነው» ።ከዚያም ሁሉን ለቃቅሞ እሳት ውስጥ ወረወራቸው።

ቴዎድሮስ ወደ አምባው የሚያደርሰውን የገደል አፋፍ ወጣ። የአሥረኞቹን ጎጆ አልፎ ወደ ቤተ ክርስቲያን አመራ። ለራሳም፣ «የሀገሬን ቤተ ክርስቲያን ልሳለም ሄጃለሁ። አንዳንድ ቂሎች «ፈረንጅ» ይሉኝ ጀምረዋል------ እኔን ለማግኘት ተዘጋጅ» ሲል ላከበት።

የብላንክ አገልጋይ «ንጉሡ የጠጡ ይመስላሉ» ብሎታል። በመጨረሻም ራሳም ብቻ ተጠራ። ከቀትር በኋላ ሰማያዊ የደንብ ልብሱን ለብሶ ሄደ። ከረኸርም ወራት በኋላ መሆኑ ነው እንዲህ ሲለብስ እናም የአሥረኞቹን መንደር አልፎ ወረደ። ቀይ ድንኳን ተተክሏል። ለመጀመሪያ ጊዜ ቴዎድሮስን ሲያገኝ የነበረውን አስታወሰ። በመቶ ስኩዌር ሜትር ግምት ዙሪያው ምንጣፍ ለብሷል። እምስት መቶ የሚሆኑት የቴዎድሮስ ሹማምንት እዚያው ነበሩ። ሁሉም የፈረንጁ ግርማ ሞገስ ያለው አለባበስ ግርታ የፈጠረባቸው ይመስላሉ። ወዳጅ ነው ወይስ



ጠላት? ይህ የፍርድ ችሎት ይሆን ወይስ የወዳጅነት አቀባበል? ራሳም ወደ ድንኳኑ ሲቃረብ ቴዎድሮስ ወጥቶ ወደ እርሱ መጣ። እጁን ጨበጠውና «ዛሬ ሁላችንም እንግሊዛዊ መሆን አለብን» አለው በፈገግታ።

ድንኳኑ ውስጥ ራሳም ከቴዎድሮስ በስተቀኝ ቦታ ተሰጠው። ቫልድማየር እና መንገዱን ሲጠርጉ የነበሩት የእጅ ባለሙያዎች ደግሞ በስተግራ። ቴዎድሮስ የብሪታንያውን መልዕክተኛ እየተመለከተ፣ «እንዴት ነው አቶ ራሳም ሸብተሃል የሚል ነገር ሰምቼ ነበር፣ ሆኖም አንዲት እንኳ የሸበቱች ፀጉር በራስህ ላይ የለም። እኔን ተመልከተኝ ፤ እንዴት እንደሸበትኩ»። እውነት ነው። የቴዎድሮስ አብዛኛው ፀጉሩ ሸብቷል። ከራሳም ጋር ሲተያይም በእሥር ዓመት ያረጀ መስሏል። አሁን የብሪታንያው መልዕክተኛ ወቅታዊ የሆነች መልዕክቱን የሚያስተላልፍበት ጊዜ ደረሰ።

"ይህ ተአምር አይደለም! ግርማዊነትዎ የሸበተው እስደሳች የትዳር ህይወቱን እያጣጣመ ነው፣ እኔ ግን በችግር ተይገፎ ስለ ሚስት አያስብኩ ነው» ።ቴዎድሮስ ከሚስቱ ተነጥሎ በእቁባቶች ተከቧል። ሁሉም ደግሞ መቅደላ ነው የሚገኙት። ነገር ግን ሁለቱ ወንዶች ከዚህ እነጋገር ጀርባ ያለው መልእክት ገብቷቸዋል። «አሁን ከቶኛ አገኘኸኝ ወዳጄ ራሳም!» አለና ንጉሡ በእጁ ፊቱን ሸፈነ።

ጠጅ ጠጡ። ቴዎድሮስ የወትሮውን ፕሮቶኮል ወደጎን ብሎ ራሳም ሌሎች እንደየተቀረዳቸው እንዲቆሙ እንዲያደርግ አዘዘው። የብላንክ እና ፕሪዶ ሰንሰለት እንዲወልቅላቸው አዘዘ --- ትዕዛዙም ወዲያው ተፈጸመ። ሚቺን አቡን፣ ካሜሮን እና እሽተርንን ማንሳት የንጉሡን ቁጣ ቀሰቀሰው። እንደምንም ብሎ ለማረሳሳት ሞከረ። እንዲህ ዘና ብሎ እንኳን የቴዎድሮስ አደገኛ ቁጣ በአስጊ ሁኔታ ላይ ነበር። ድንገት ቁጣ ወይም ፍርሃት እሲያም ፍንዳታ በየደቂቃው ይፈራረቃሉ። እዚያ ተራራ ላይ የሚገኙት ሁሉ እንደሚያደርጉት የእሱም ሐሳብ እየተወገሰ ነው ከሚባለው የብሪታንያ ጦር አልተለየም። መሣሪያቸው እንዴት ያለ ይሆን? ቴዎድሮስ ጠላቶቹ የሚተኩስ በዚያም ላይ የሚወጋ ጠብመንጃ መያዛቸውን ሰምቷል። የእሱ ደግሞ «ውዳቂ» መሆኑን ተረድቷል። ራሱን በሆዱ ያለው ሕፃን ሲት ይሁን ወንድ ከማታውቅ ነፍሰ ጡር ሴት ጋር አመሳሰለ።

«ወንድ ልጅ እንድወልድ ትረዳኛለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አለው ራሳምን። ለ18 ወራት በሰንሰለት መታሰሩን ወደጎን አድርጎም ጎጆው ምንጣፍ እንዳለው ጠየቀው። ራሳም በበኩሉ ሁሉም የተሟላ ነው ሲል መለሰ። «የምኖርባትን ግሩም ጎጆ ቢመለከት ግርማዊነትዎም ይደሰታል»። ቴዎድሮስ ወደ ሰማይ እየተመለከተ፣ «ወዳጄ አመነኝ ልቤ ይወድሀል፤ የምትፈልገውን ሁሉ ጠይቀኝ የራሴን ሥጋም ቢሆን እሰጥሃለሁ» አለው፡፤ ትርጉም አልባው ንግግር ቀጠለ።

ድንገት ቴዎድሮስ ድምፁን ዝቅ አድርጎ «ሰዎችህ ሲመጡ ጥቁር በመሆኔ እንደማይንቁኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አለ። ቀጠለና «አንድ ቀን ሞቼ ብታይ በኀዘን ከአስከሬኔ አጠገብ ትቆማለህ ወይስ በእናንተ ላይ በፈጸምኩት መጥፎ ድርጊት ትረግመኛለህ?» በዚያን ምሽት ወደ ሰላምጌ ሲመለስ ቴዎድሮስ ለመኳንንቶቹ አስደንጋጭ ፊት ነው ያሳያቸው። «ራሳም አሹፎብናል፣ እኔንም አታልሎኛል» ። «የብሪታኒያው ልዑክ ሁልጊዜም ወደጅነትን የሚያበረታታ ቢመስልም በሌላ ወገን የንጉሡን ወታደሮች «እንዲገድሉ» የራሱ መንግሥት የጦር ኃይል እንዲልክ ይወተውታል» ። በማግሥቱ ቴዎድሮስ ለማርቲን ፍላድ «ለራሳም መልካም እንደሆነ እና ከእርሱ ጎን መኖር ቢችል እንደሚመኝ ነገረው» ።



# ምዕራፍ ሰባ

ከጥቂት ቀናት በኋላ የሸማውን ጫፍ በትክሻው ዙርያ ጠመጠመና በጠዋቱ የጦር ሠፈሩን ለቅቆ ወጣ ቴዎድሮስ። ወደ መቅደላ መልዕክተኛውን ልኮ ሜዳውን አቋርጦ ወደ ሰላምጌ ገደል ተጓዘ።

መልዕክተኛው ፈረንጆቹ እሥረኞች ጋር ደርሶ ራሳም፣ ብላንክ እና ፕሪዶ ወደታች ወርደው ንጉሡን እንዲያገኙ ነገራቸው። ምን እንደሚያጋጥማቸው አላወቁም። «ትሕትና የተላበሰ አቀባበል፣ እሥር ወይም የከፋ ነገር» በማለት ብላንክ ጽፎታል። መደበኛ የደንብ ልብሳቸውን ለበሱ። ፈጥነው ወደዚያ ሲጓዙ በአምባው ሙተላለፊያ እና ጠባቂዎች ቤት ደረሱ። ቴዎድሮስን ከሰላምጌ ገደል አፋፍ ላይ ተመለከቱት። በወገቡ ላይ ባለው ቀበቶ ሥር ሁለት ሽጉጦች ተሸጠዋል። በእጁም ሁለት ጦር ያፋጫል። የማለዳዋ ፀሐይ በከፊል ፊቱ ላይ አርፋለች። ለሦስቱም የተረጋጋ ሰላምታ ሰጥቶ ከድንጋዩ ላይ እንዲቀመጡ ጋበዛቸው። እሱ ራሱም ከፊታቸው ተቀመጠ። ከዚህ ሁሉ ወራት በኋላ ብላንክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚጠላውን አሣሪያቸውን በመደናገር ተመለከተ። «ድንገት ብንገፈትረው በገደሉ ይንከባለል ነበር» ተመኘ።

ዝቅ ብሎ ሙቶ ጫማዎች ግድም በገደሉ ሥር የቴዎድሮስ የመጀመሪያዎቹ የጦር መሣሪያዎች ለመጨረሻው ጉዞ ተዘጋጅተው ተቀምጠዋል። ከደብረ ታቦር ተጉዘው ከዚህ ደርሰዋል። ንጉሡ በዝምታ ሰዎቹ እየተጋገዙ ዳገቱን ለመውጣት ሲታትሩ ይመለከታል። በእዚያ በተሰባሰቡበት ሰዎች መካከል ትልቁ አስፈሪ መድፍ ጉብ ብሏል፤ ሴቫስቶፓል።

ቴዎድሮስ ወደራሳም ዞር አለና፤ «ስለእሱ ምን ታስባለህ?»

«የሚያስገርም መሣሪያ ነው» ራሳም አጋነነ። «የብሪታንያ ኃይሎችም እኔ እንዳልኩት እንደሚመለከቱት ተስፋ አደርጋለሁ» ። አስተርጓሚው ዝም አለ። ቴዎድሮስ ምን እንዳለ መስማት እንደሚፈልግ አጥብቆ ጠየቀው። እያፈረ ነገረው። ቴዎድሮስ ሳቀ። «እኔም ተስፋ አደርጋለሁ»።

ከበታቻቸው መድፉን የሚገፋት በረድፉ በረድፉ ተሰልፈው በቆዳ እሥረውና ደግፈው ይታገላሉ። ቴዎድሮስ ተነስቶ ቆመ። አብረውት የነበሩም ተከተሉት። ወደፊት ተራመደ። አቀበቱን በ45 ዲግሪ ገምቶታል ራሳም። አቀበቱን መውጣቱ ቀላል አልነበረም። ተሸካሚና ገፊዎቹ ግን ተስፋ አልቆረጡም። ብዙ ታግለው ጋሪውን ወደላይ አወጡ። መድፉ ወደኋላ ቢንከባለል ምን እንደሚከተል ስለሚያውቁ ባለ በሌለ አቅም ተፍጨረጨሩ። «አይዞን! አይዞን!» ማበረታቻው፣ ትዕዛዙ ከየአቅጣጫው ይኀርኀደኀዳል። ቴዎድሮስ እጁን ሲያነሳ ሁሉም እረጭ

አለ። «ከቴዎድሮስ በቀር ያንን አስቸጋሪ ዘመቻ ሊመራ ማንም አይችልም» ይላል ብላንክ በማስታወሻው።

ሲቫስቶፖል የተደላደለ ቦታ ላይ ሲደርስ ቴዎድሮስ እስረኞቹ እንዲመለከቱት ፈቀደላቸው። «ሦስታችንም ዘልለን ሄድንና በአንድነት ዙሪያውን ተመለከትን። ግርምት ደስታችንንም ጮክ ብለን ገለጽን" ብሏል ብላንክ። ቴዎድሮስ በድጋሚ አብረውት እንዲቀመጡ ጋበዛቸው።« ለረዥም ሰዓት ተቀምጠው በእርጋታ "ወዳጃዊ ወግ አወጉ»። ከቤታቸቸው ጠብመንጃዎችን ወደአምባው የማጋዙ ተግባር ቀጥሏል።ሲቫስቶፖልን ማድነቁ ቀጥሏል። ሲቫስቶፖል አሁን ከተደላደለው የተራራው አናት ላይ ወጥቷል። ቴዎድሮስ ስለጉዞው አጫወታቸው። በመንገድ ላይ ሽፍቶች ሊያደርሱበት የሞከሩትን ጥቃት እሱም የፈጸመውን አጸፋ ተረከላቸው። ፀሐይ እየበረታ ሲሄድ ኮፍያቸውን እንዲያደርጉ ፈቀደላቸው፣ ለራሱ ደግሞ ጃንጥላ እንዲዘረጋለት አዘዘ።

ይሄን ያህል ዘመን ሲዋጋ ከውጭ ኃይሎች ጋር የተጋጠመው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከ20 ዓመታት በፊት ደባርቂ፣ ስናር ላይ ግብፆች ከወታደሮቹ ከፊሉን በጠብመንጃ ገድለውበታል። ከአውሮጳውያን ጋር ጦር ሜዳ ላይ ተጋጥሞ አያውቅም። አሁን ታዲያ ራሳምን ደጋግሞ ይጠይቃል። የሚሰጠው ምን አይነት ትዕዛዝ ነው? ምን ዓይነት መሣሪያ ይይዛሉ? ምን ያህል ወታደሮች ይመጣሉ? ሰላም እንዴት ሊፈጠር ይችላል?

የብሪታንያው ልዑክ በመሰለው ለመመለስ ይሞክራል። ግን ደግሞ እኔ እኮ ወታደራዊ ኤክስፐርት አይደለሁም ይላል።


«አውቃለሁ፣ አንተ የምላስ ሰው ነህ» አለው ቴዎድሮስ እየሳቀ። 5,000 ተዋጊ የብሪታንያ ጦር መምጣቱን ሲሰማ ተቅበጠበጠ። «ልክ እኔ ኃያል እንደነበርኩበት ጊዜ ማለት ነው። ወደ ሰዎቻችሁ ሄጄ ምን ፍለጋ እንደመጡ መጠየቅ ነበረብኝ። ነገር ግን እንዴት እችላለሁ?» ቀና ብሎ ወደ መቅደላ እየተመለከተ፣ « መላ አቢሲኒያን አሁን እጥቻለሁ፣ የቀረኝ ይህ ገደል ብቻ ነው» አለ።

በእንክሮ እየተመለከተ ማንባሩ ፊታ አለ። «እዚሁ እገኛችዋለሁ፣ ራሲንም በፈጣሪዬ ጥበቃ ሥር እጥላለሁ»።

ፀሐዩ ጠንክሯል። ከታች የእሱ ሰዎች ቀሪዎቹን የጦር መሣሪያዎች ወደ አምባው ለማውጣት ይታገላሉ። ራሱን እየነቀነቀ፣ «እኒህን ጎስቋላ ወታደሮቼን በወጉ ከለበሱት ከእናንተ ወታደሮች ፊት እንዴት አቆማቸዋለሁ?» አለ ለራሱ በመሰለ ድምፅ። ድንኳኖች ተተከሉ። በቤተ ክርስቲያን የሁዳዴ ጾም ጸሎት ይደርሳል፤



ጸሎት ሲያበቃ ምግብ ይታደላል። ቴዎድሮስ ተነስቶ ቆመ። ያን ዕለት ከቀትር በኋላ ቴዎድሮስ ለራሳም ይህን መልእክት ላከ። «ትክክለኛው የመድፍ መጠን ምን ያህል ይሆናል?» ሲቫስቶፖል የተሠራ ዕለት እና ዛሬ ቴዎድሮስ የተለየ ስሜት ተሰምቶታል። ራሳም ደግሞ በሌላ መልክ ነው የተረዳው። ምንም እንኳን እንደዛሬው ንጉሡ ተረጋግቶ አይቶት ባያውቅም ታላቅ ኀዘን እንደተሰማው ግን ተረድቷል። ቴዎድሮስ ሥጋት አድሮበታል። ሠራዊቱ መድፉን ሲጎትቱ እንዴት ይመለከት እንደነበረ ራሳም በዚያን ዕለት ማለዳ ሲያስተውለው ነበር። «ሰቀቀን የተላበሰ ገጽታውን በፍፁም አልረሳውም» በማለት ጽፏል።


ምዕራፍ ሰባ አንድ

# ምዕራፍ ሰባ ሁለት

ካፒቴን ቻርለስ ትረስትራም ሰውየር ስፒዲ፣ ዋና አዛዡን ለማየት የጦር ሠፈሩን አቋርጦ ሄደ። ጥቁር ሱሪ እና ሸማ ለብሷል። እንዲያም ሆኖ ከቀዩ ጢሙ እና መነፅሩ በቀር ኢትዮጵያዊ ነው የሚመስለው ከርቀት።

ደማቅ አለባበስ ከሚያዘወትሩት የታኘው ጦር አባላት አንዱ ስፒዲ ነበር። አባልነቱ የመደበኛው ጦር ሳይሆን የስለላው ነው። የተገኘበትን ሀገር ባህል የሚወድ እና ከእጁ በማይለዩት ሳንጃ በግ አርዶ ለማወራረድ ጊዜ የማይፈጅበት ነው። ኔፒር በጦሩ ውስጥ ያከተተው ኢትዮጵያን ያውቃል፤ አማርኛም ይችላል በዚያም ላይ ከቴዎድሮስ ጋር ይተዋወቃል በሚል ነው። ዋና አዛዡ የተሰማውን ስሜቱን ደብቆ «በቅሬታ እና በሥጋት ድምፀት » የምግብ አቅርቦት እያሳሳ መሆኑን ነገረው።

ስፒዲ ሐሳብ እንዳይገባው አሳሰበው። ምክንያቱም የአቢሲኒያ ለም የሚባል ቦታ ነው ያሉት፣ ንጉሡ ምናልባት የደላንታን ተከሎች አውድሞ አልፎ ይሆናል ግን ደግሞ የአጎራባቹን የዳውንትን አካባቢ ኃላፊ ስፒዲ ስለሚያውቀው ጎራ ብሎ እህል እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል። ግን ከሁሉ አስቀድሞ «ትልቁ ዝሆን ሊሰጠኝ ይገባል» ሲል ጠየቀ። የዛሬ ሰባት ዓመት ወጣት ሳለ ከራጎት የሚያደርገው ስፒዲ ከሕንድ ጦር ኃይል ተሰናብቶ በአንድ የጅዳ ቡና ቤት ውስጥ መረር ያለ ሞካ ቡና ይጎነጫል። ቀይ ፀጉሩን እንደ ህንዶች በጨርቅ አስሮ እና የሃይማኖት ተሳላሚዎች የሚጠቀሙበትን ጀለቢያ አድርጎ እንደ ጅማናው አርአያው ሪቻርድ በርተን ወደ ተከለከለችው መካ ከተማ ገባ። አንድ የኔ ቢጤ ወደ ተቀመጠበት ጠረጴዛ አሻግሮ «በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም፤ ምፅዋት ስጠኝ አለው። ስፒዲ በዚህ ስፍራ አንድ ሙስሊም የሥላሴን ስም ጠርቶ መለመኑ አስገረመው። ሆኖም ሰውየው ዙሪያ ገባውን ቃኘ እና «ኢትዮጵያዊ ካህን ነኝ፣ ኢየሩሳሌምን ተሳልሜ መመለሴ ነው። ከሀገር ከመንደሬ ለመድረስ በቂ ገንዘብ የለኝም አባክዎ? ጌታው» አለው።

ሲፒዲ ሰውየውን ወደማረፊያው ወሰደው በነፃነት እንዲያወራው። ታሪኩን በመስማትም የጉዞ አቅጣጫውን ለውጦ ሊከተለው ተመኘ። ኢጋጣሚው የሕይወት መሥመሩን የሚለውጥ ዓይነት ነበር።

«ወደዚህች ሀገር የመሄድ ከፍተኛ ፍላጎት በውስጤ ተነሳሳ» ሲል ጽፏል። መካን የመጎብኘት እቅዱን ሰርዞ አነስተኛ ጀልባ ተከራይቶ ቄሱን እንደ መንገድ መሪው በማድረግ ባሕሩን ተሻግረው በረሃውን አለፉና የደጋውን ጎዳና ተያያዙት።

አድዋ ከተማ መልዕክተኛ ደረሰ። በመቶዎች ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ቴዎድሮስም የእንግሊዛዊውን መምጣት ሰማ። ደብረታቦር መምጣት



ያስፈልጋል። ንጉሡ ሊያገኘው ፈልጓል። ንጉሡ ጋር ለመድረስ የአንድ ወር ጉዞ ያስፈልጋል። ስፒዲ ፈቃደኛ አልነበረም። ወደ አደን ለመሄድ ጓጉቷል። መልዕክተኛው ግን ሥራውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። እናም ስፒዲ የንጉሡን ትዕዛዝ ማክበር እንደሚያስችል አስረግጦ ነገረው። ስፒዲ ለመጀመሪያ ጊዜ ቴዎድሮስን ሲያገኘው በሰማያዊ መከዳ ላይ ዘና እንዳለ ተጋድሞ ነበር። ከበላዩ ያለ ድንኳኑ በነፋስ ይውለበለባል። ስፒዲ የተገናኘበት ሥርዓት ጥብቅ እና ጠንካራ እንደሆነ ገባው፤ የቴዎድሮስአምባት መሥመር ሹሩባ በአናቱ ወርዷል። ከምንም በላይ መርማሪ አስተያየቱ አስገርሞታል። 50 ዓመት ገደማ እንደሚሆነው ተናገረ። ለንጉሡ ከአርባ ዓመት ነበር ከፍ የሚለው። «ሁሉም አውሮጳውያን ደስ ይሉኛል፤ እንግሊዞችን ግን እወዳቸዋለሁ። በነሱም የነበሩኝ ምርጥ ወዳጆች ፕላውደን እና ቤል ናቸው። አንተንም እወድሃለሁ» አለው ቴዎድሮስ።

ስሙን ሲጠይቀው «ስፒድ»የሚለውን አስተካክሎ ለመጥራት አዳገተው። ለመሆኑ ምን ማለት ነው?» ጠየቀ። አስተርጓሚው ለማስረዳት ሲሞክር በሰዓቱ የስፒዲ መጠሪያ ላይ አርፋ አንጠባረቀች --- ከዚያም ቴዎድሮስ «ፈልታ» አለ እና እንዲያውም «ባሻ ፈለቀ ብዬሃለሁ» አለው።

ዝናብ እየመጣ ነበር። ቴዎድሮስ የገናብ ወራት እስኪያልፍ ስፒዲ ጋፋት ከሚሲዮናውያኑ «ልጆቹ» ጋር እንዲቆይ እና አማርኛም እንዲማር ነገረው። ቴዎድሮስ ራሱ ወይጎኛም ከሸፍቶች ጋር ሊዋጋ ተነሳ፤ ሲመለስ ለመነጋገር ቀጠሮ ያዙ። አሁን ስፒዲ ከሀገር መውጣት እንደማይችል ግልጽ ሆነለት።

ከአንድ ወር በኋላ በድጋሚ ሲገናኙ ሁለቱም የሚወዱትን የጦር ጨዋታ ጀመሩ፤ የጦር ስልት። ስፒዲ እግረኛ ጦር በወንዝ ስልጥኖ ከተዘጋጀ፤ ፈረሰኛ ጦርን መከቶ ማሸነፍ ይችላል ባይ ነው። ይህንንም በተግባር ማረጋገጥ እንደሚችል ተናግሮ 100 ወንዶች እንዲሰጡት ጠየቀ።

ከአንድ ወር ዝግጅት በኋላ ሰልጣኞቹን ማጠናቀቁን አስታወቀ። ንጉሡ ፈረሰኛ ጦሩን አሰባሰቦ ፤ ከፍ ካለች መለስተኛ ኮረብታ ላይ ሆኖ ፍልሚያውን መመልከት ጀመረ። ቴዎድሮስ ለፈረሰኞቹ ትዕዛዝ እንደሰጠ የስፒዲ እግረኛ ጦር ወደቦታው ተሰበሰበ። ባሻ ፈለቀ ቀይ መሐረብ ይዞ ከእጠገባቸው ቆመ። ፈረሰኞቹ ረጃጅም ጦር እና ጋሻ ይዘዋል። ግር ብለው ጭቃ ውስጥ ገቡ። ስፒዲ በተራው ለእግረኞቹ ምልክት ሲያሳይ ጥቁር ጭስና ማስገምገም ተሰማ። ፈረሰኞቹ በጭሱ ውስጥ ተበታትነው አንዳንዶቹ ቆሻሻ ውስጥ ገቡ. ንጉሡ የፈረሰኞቻቸውን አንገት የሙቀኝ አሉ።

ስፒዲ እንዲያወርዷቸው አዘዘ። ድጋሚ የተደረገ ነገር ግን አልነበረም፤ የተናገረውን በተግባር አሳየ። ቴዎድሮስ ተቆጣ። ከምንም በላይ በፈረንጅ ስልት መበለጡ ያብሰከሰከው ሳያንስ ይህን ስልት ጠላቶቹ ሲጠቀሙበት የሚከተለውን እስቦ ተብከነከነ፡፡ ቴዎድሮስ አስጠራው እና ስፒዲ መቼ ለመሄድ እንደሚፈልግ ጠየቀው። «ነገ» አለ ስፒዲ ድንገት እንደ ዕድል።

«እሁኑኑ ሂድ ነገ ምናልባት ሰይጣን ሐሳቤን ሊያስቀይረኝ ይችላል» አለው።

ይህ የሆነው የዛሬ ስድስት ዓመት ነበር። በ1854 ዓ.ም ካፒቴን ከሀገር ለመውጣት ሲጓዝ መንገድ ላይ ከዳውንት ገገር ወልደ ጊዮርጊስ ጋር ተገናኘ። ሲጫዋወቱም ስፒዲ ስለ ሕንድ እንግዳ የሆኑ ነገሮችን ለወልደ ጊዮርጊስ ተረከ። ስለቴሌግራም እንዲሁም ሥራ ስለሚሠሩ ዝሆኖች። እንደ ስፒዲ ገለጻ የሕንድ ዝሆኖችን ከአፍሪቃ ዝሆኖች ይልቅ ማሠልጠን ይቻላል። ከሁለት ቀን በኋላ ወልደ ጊዮርጊስ ወደ ቤተከርስቲያን ስፒዲን ወሰደውና ከመቅደሱ ፊት ለፊት ተንበርክኮ ለፈረንጁ ይቅርታ እና ጭንቅላቱን ስለሞሉት እሰፈሪ ምናቦች ፀለየለት። አሁን በ1860 ደግሞ ወልደ ጊዮርጊስ ከኮረብታማው ሥፍራ ሆኖ ወደታች ይመለከታል። ከደላንታ ሰፊ ሸለቆ ስለሚለየው እህሉን ከዘረፉ ማትረፍ ችሏል። አንድ ዝሆን ከወደታች እሱ ወዳለበት አቅጣጫ ሲያቀና ተመለከተ። በዝሆኑ ላይ ደግሞ አንድ ሰው ተቀምጧል። ያ ሰው ማን እንደሆነ ሲመለከት ወልደ ጊዮርጊስ ቁልቁለቱን እየተንደረደረ «ፈለቀ፣ ፈለቀ ባሻ ፈለቀ! ልጄ፣ ልጄ!» እያለ ጮኸ።

ስፒዲ ፈጥኖ ወረደ። አገረ ገዢው እንገቱን አቅፎ ደጋግሞ ሳመው። ከዚያም ስፒዲ እንደምንም አግባብቶት ወልደ ጊዮርጊስ ዝሆኑ ላይ ወጣ። ወደ ብሪታኒያ ጦር ሠፈር ሄዱ። እርግጥ ነው እንግዳ ቀን ሆኖበታል ለወልደ ጊዮርጊስ። በጦር ሠፈሩ ውስጥም ስፒዲ የቴሌግራም መሣሪያውን አሳየው። ቀደም ብሎ በስተሰሜን ራቅ ብላ ወደምትኖረው የወልደ ጊዮርጊስ እህት በቴሌግራም ወደዚህ እንድትመጣ መልእክት አስተላልፎ ነበር። አሁን ደግሞ ራሱ ወልደ ጊዮርጊስ መልዕክቱን እንዲያስተላልፍለት ጋበዘው። «እንደ ሕፃን የትኛዋን ጣቴን እጣ ይሆን?» መልሱ ፈጥኖ መጣ። ወልደ ጊዮርጊስ ማሽኑ ላይ አፈጠጠ።

«ይህን ነገር ተው! የሰይጣን ሥራ ነው» ተቃወመ።

ሆኖም ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ከወደ ዳወንት አንድ ሙቶ በቅሎዎች ብቅ አሉ። 10 ሺህ ፓውንድ ወይም ከ 4536 ኪሎግራም የሚ በልጥ እህል ወደ ብሪታንያ የጦር ሰፈር ገባ። በቀጣይ ቀናትም ከዚህ በሦስት እጥፍ የሚበልጥ ስንዴ፣ ዱቄት እና ገብስ መጣ። አሁን ኔፒር ሠራዊቱን ለቀጣይ 11 ቀናት የሚመግበው በቂ እህል አገኘ።



አሁን ለዘመቻው የመጨረሻ ርምጃ ዝግጁ ነው። ቀሪውን መንገድ ለመጓዝ አስቸጋሪ ገደሎች እና ጠንካራ ወታደራዊ ይዞታዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። ሁኔታው ለሁሉም ወታደራዊ አዛገሮች ግልጽ ነበር። «እንዲህ ያለ ቦታ ካልሆነ ቴዎድሮስ መቅደላን እንዴት ይመርጠዋል? ለመሆኑ ራሱ መቅደላስ እንዴት ያለ ይሆን?» መጋቢት ማለቂያ ላይ አንድ የመኮንኖች ቡድን ወደ ደላንታ ጫፍ ተጉዞ ወደ ደቡብ ቁልቁል ተመለከተ። ቴዎድሮስ ያሠራው መንገድ 1.2 ኪሎ ሜትር ገደማ ወደ በሽሎ ሸለቆ ይወርዳል። በኮረት ተሞልቶ በእቀበቱ ላይ የተሰራው መንገድ ወደ መቅደላ አፋፍ ይዘልቃል። «እንዲህ ያሉ አስገራሚ ኮረብታዎች አይቼ አላውቅም» ሲል ከእነሱ ጋር የተጓዘ አንድ ጋዜጠኛ ጽፏል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኔፒር ወደ ገደሉ ጫፍ እየሄደ በቴሌስኮፕ ዙሪያውን ያጠና ጀመር። በወታደራዊ ዓይኑ ቅኝትም ከጠላቱ አቅራቢያ መሆኑን ተገነዘበ። በመካከላቸው ያለውን ርቀትም መመዘኑን ቀጠለ። «ልናደርሰው ያሰብነውን ጥቃት አስፈሪነት በገለጻ ብቻ ለማሳየት አዳጋች ነው» በማለት ራሱ ኔፒር በማስታወሻው ከትቧል።

# ምዕራፍ ሰባ ሦስት

ቴዎድሮስም እየተመለከተ ነው።

ሰኞነ ሕማማት ነው። የሆሳዕና ዕለት እሑድ በቅሎው ላይ ወጥቶ ወደ ሥላሴ በሚያደርሰው ድንጋያማ መንገድ ጋለበ እና ቴሌስኮፑን ወደ ሰሜን አቅንቶ ተመለከተ። በቀጣይ ባሉት ቀናትም ይህንኑ ደጋገመ።

ለጥቂት ቀናት ምንም ያየው ነገር አልነበረም። ማክሰኞ ዕለት ግን በሚንቀጠቀጠው በደብዛዛው ሰማያዊ አቅርቦ መመልከቻ መነፅሩ ውስጥ ቀይ ነገር ተመለከተ። ወደ በሽሎ ሸለቆ የሚወርደው የመጀመሪያው የብሪታንያ ሠራዊት ነበር። እሱ ራሱ የጠረገውን ጥርጊያ መንገድ ነበር የሚጠቀሙት።

«ኧረ ጉድ! እህዮቹ አኒያው!» ጮኸ። ቫልድማየር አጠገቡ ነበር። ቴዎድሮስ መነፅሩን እያቀበለው ወደ በሽሎ ተመለከተ። « ከእንግሊዝ እኔን ለመግደል የመጡትን ወገኖችህን ተመልከት» ቴዎድሮስ ጥቃት ተሰማው። ቫልድማየር ገጹ ልክ እንደ ምሽት ሲጨልም እና ቁጣው እንደ ሲኦል ሲነድ ተመልክቶ «በፍርሃት ተንቀጠቀጥኩ» አለ።

የብሪታንያ ወታደሮች ወዳለበት በቀረቡ ፣ መጠን የቴዎድሮስ ቁጣም እንዲሁ ይግል ይቀዘቅዝ ገባ። እምቢተኝነት በመግባባት፣ መንፈሳዊነት በስካር፣ ጉራ በተሸናፊነት፣ ጭካኔ በፀፀት፣ በራስ ማዘን ወደቁጣ ሲሸጋገር ደግሞ ወደእንቢተኝነት ሲያቀና ሰነበተ። ሐቁን መጋፈጥ የማይቀር ነበር። ሁሉም ተራራው ላይ ታግቷል። እሥረኞች እና ካህናት፣ ወታደሮች እና ሚኒስትሮች፣ በሙሉ የህልውናቸው ነገር ከጦር ሜዳው ትንቅንቅ ይልቅ በታወከችው የንጉሡ ነፍስ ዕጣ ፋንታ የታሠረች መሆኗን ተረድተዋል።

በተቀደሰው ሳምንት በሰሞነ ሕማማት ረቡዕ ዕለት ቴዎድሮስ ያልተለመደ አለባበስ ለብሶ በማለዳ ተነሳ። ቀይ ጥለት ያለው ሸማውን የሚያዘወትረው ቀለል ያለ አለባበሱ የራሱ ማንነት ስልት እስከመሆን ደርሷል። ያን ቀን የለበሰው ግን ከዚህ ይለያል። በወርቃማ ሀር የተዘመዘመ ቀለል ያለ ልብስ።

ወታደሮቹን ሰብስቦ ስለሚገጥሙት ጦርነት ነገራቸው። በቁጥር ከእነሱ አይበልጡም፣ ሆኖም ዘመናዊ መሣሪያ አላቸው። ወታደሮቹ ተዋግተው በሚማርኳቸው ነጭ ባሪያዎች ንብረት ራሳቸውን ማስታጠቅ እንደሚችሉም ነገራቸው።

ከቴዎድሮስ ነባር ደጋፊዎች አንዱ ፊንጠር ብለው ወደፊት መጡ፣፤ አፈ ንጉሥ ባሕሩ። አፈ ንጉሥ ባሕሩ በራስ አሊ ጊዜም አፈ ንጉሥ ነበሩ። ፕላውደን እና ቤልን ያውቋቸዋል። የወጣቱን የካሣን አነሳስም ጠንቅቀው ያውቃሉ። ከትንሽ



ሸንፊት ወደ አማፂነት ከዚያም ወደታላቅ ቴዎድሮስ ሁለተኛ ያደረገውን ሽግግር በሚገባ ያውቃሉ።

«ግርማዊነትዎ ይጠብቁ፤ እነዚህ እህዮች ብቅ ይበሉ ያኔ እንቆራርጣቸዋለን» በማለት ፎከሩ።

ቴዎድሮስ ወደ እሳቸው እየተመለከተ «ምን አልክ አንተ ሞኝ አዛውንት! ለመሆኑ የእንግሊዝ ወታደር ምን እንደሚመስል አይተህ ታውቃለህ? እንዴት አይነት መሣሪያስ እንዳለው ታውቃለህ? ማንነታቸውን አጣርተህ ከምትህ በፊት ሆድህ በጥይት እንደሚሞላ እርግጠኛ ነኝ» አላቸው።

ያን ቀን ማለዳ ቴዎድሮስ እሥረኞቹን መቅደላ ላይ ሰበሰባቸው። አውሮጳውያኑ እሥረኞች ከአማራው፣ ከትግሬው፣ ከኦሮሞው፣ በአንድ ወቅት የቴዎድሮስ ደጋፊ ከነበሩት፣ ከባለሥልጣናት፣ ከሌቦች፣ በጦር ሜዳ ከተማርኩ ወታደሮች፣ ከድተውት ከጠፉ ቤተሰቦች፣ ከዕድለቢስ እና ከተዘነጉት፣ ከታማሚ እና ከንጹሓን ጋር በአንድ ላይ ተሰበሰቡ። አብዛኞቹ ተባይ በሚፈነጭባቸው እሥር ቤቶች ከርመዋል፤ ከወረርሽኝ በሽታ ከረሃብ እና ከግድያ የተረፉም ናቸው። ምኒሱ በእግር ብረት እንደታሰሩ ይንፏቀቃሉ። ቴዎድሮስ ለደህና ነገር ሰበሰበን የሚል ከመካከላቸው አንድስ እንኳ አልነበረም።

በመጨረሻ ግን ያልተገመተው ሆነ። 75 እስረኞችን ፈታ። ከዚያም አቅርቦ መመልከቻ መነፅሩን አንግቦ ወደ ሥላሴ ገደል አመራ። ምንም ነገር አላየም። በቀጣዩ ቀን ቀሪዎቹ ኢትዮጵውያንእሥረኞች እንዲፈቱ አዘዘ። ቀጠለና መነፅሩን አነጣጠረ፤ ወደ በሽሎ ሸለቆ። እሁንየሆነ ጓዝ ወደ ወንዙ ሲወርድ አየ። በዚያም ላይ አራት ዝሆኖች እና ባለጥቁር ራስ ነጫጭ ፍጥረታትንም ተመለከተ። ራሳም የበርበራ በጎች ሳይሆኑ አይቀሩም ይላል። ለማንኛውም ቴዎድሮስ፤ «እሻግሮ መመልከቱ ደከመኝ፤ እስኪ ትንሽ ልረፍ፤ ለመሆኑ ሰዎቻችሁ የዘገዩት ለምንድነው?» ሲል ራሳምን ጠየቀው። ንጉሡ ለዕረፍት ወደድንኳኑ ሄደ። ከቀትር በኋላም አረቄ ጠጣ። በዙሪያው ያሉት ቀኑን ለሁለት እየከፈሉ ማሰብ ተለማምደዋል። ሰላማዊ ጠዋት ፤ ሥጋት የሞላበት ከቀትር በኋላ። የዚያች ቀን ከቀትር በኋላም ከወትሮው የተለየች አልነበረችም።

ቴዎድሮስ ጠዋት እሥረኞች በመፍታት ጀመረ። የእግራቸውን ሠንሰለት ማላቀቁ ቀላል ሥራ አልነበረም፤ እናም ከሰዓት በኋላ በአሥር ሰዓት ላይ ነጻ የሆኑት 95ቱ ብቻ ነበሩ። ቀሪዎቹ ደግሞ ትዕግስት አጡ፤ ምግብ እና ውኃ እንዲሰጣቸው መጮህ ጀመሩ። ቴዎድሮስ ከሞቀው ድንኳን ልክ እንደ ተቆጣ አንበሳ ዘሎ ተነሣ ። ሰይፉን መዘዘ። ከድንኳኑ ወጥቶ እሥረኞቹን ወደእሱ ጠራ። ሁለቱን ራሱ ገደላቸው። ቀሪዎቹ ተራ በተራ ወደ ፊቱ እየቀረቡ ስማቸውን እና ከየት እንደመጡ

በመግለጽ የተከለከሉትን ተናገሩ። ቴዎድሮስ እየያዙ ወደ ሰላምጌ ገደል እንዲጨምሯቸው አዘዘ።

ራሳም ቴዎድሮስ ይህን ርምጃ የወሰደው በበቀል ስሜት በመገፋት ብቻ አይደለም ባይ ነው። ዕብደትም ተቀላቅሎበታል ሲል ማሳያ ያለውን እንዲህ ይተርካል። «ከእሥረኞቹ አንዱ የቴዎድሮስን ዕቁባት ሊዳራ ሞክሯል በሚል የተያዘ መሆኑን ሰማ። የዚህ ሰው ሁለት ልጆች የ12 እና የ15 ዓመት የሚሆኑ አብረው በዚሁ መዝገብ ታሥረዋል። ልጆቹ በገደሉ ተጣሉ። አባትየውን ግን በነጻ አሰናበተው።

በዚያን ዕለት ከቀትር በኋላ ብቻ ከ300 የሚበልጡ ተገደሉ። ከዚያም ቴዎድሮስ ለጥቂት ሰዓታት ተኛ፤ ዳግም ሥጋት እና ጥፋት ወዳላበት ዓለም እስኪነቃ። አልባሹ ወልደ ጋብር የግድያ ትዕዛዙን ሲያስተላልፍ ከቀልቡ እንዳልነበር ይልቁንም በስካር መንፈስ እንዳደረገው በመናዘዝ ሌሊቱን ሁሉ በሰቀቀን የፈጣሪውን ምሕረት ሲለምን ማደሩን መስማታቸውን ተናግረዋል። ዕለተ ስቅለት ነበር።

«ፈላጭ ቆራጩ እና ከፉው መሪ በፈጣሪው ላይም የሚሳለቀው፤ ደግሞ የታደለው፤ ከሁሉ ቀድሞ በማለዳ ቤተ ክርስቲያን ነበር» በማለት ሽተርን ጽፏል።

ቴዎድሮስ የብሪታንያ ወታደሮች ያን ዕለት ከተራራው ሥር እንደሚደርሱ ያውቅ ነበር። ለመጨረሻ ጊዜ ትልቅ መድፉ እንዲንቀሳቀስ አዘዘ። አብዛኞቹ በፈላ በኩል፤ ጥሚሱ ወደ መቅደላ በሚወስደው ዳገት ዙሪያ መሸጉ ከእነሱ መካከል ሴቫስቶፖል አለ።



## ምዕራፍ ሰባ አራት

የሥቅለት ዕለት ዓርብ በበሽሎ ሸለቆ አቋርጦ የንጋሪት ድምፅ ከብሪታንያ የጦር ሠፈር ድረስ ተሰማ። ተዋጊው ጦር በደላንታ ሳሪማ ሜዳ ላይ ተሰበሰበ። ወደ ታች ሜዳ ተንቀሳቀሱ እና መውረድ ጀመሩ። በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በሰልፍ የተሰለፈው ሠራዊት ኮረብታውን እየወረደ ወንዙን በሚያሻግረው ብቸኛ ጎዳና ላይ ፈሰሰ።

ኔፒር ወታደራዊ ቅኝትና ሥምሪቱን ሲያጠና እና ሲወያይ ነው የሰነበተው። ለአዛዦቹም ሁኔታውን አብራርቷል። አጠቃላይ የጥቃት ዝርዝሩን አውጥቷል። «እያንዳንዱን መኮንን ከ1 ኪሎ ጥቂት የሚያንስ ብስኩት እና ተመሳሳይ መጠን ያለው የበሰለ ሥጋ እንዲይዝ፤ እያንዳንዱ ወታደር በሽሎን በባዶ እግሩ እንዲሻገር እና ኮዳውን ውኃ እንዲሞላ፤ የቢሮ ሠራተኛ የሆኑ መኮንንኖች ደግሞ በቂ ወረቀት እና እርሳስ እንዲይዙ፤ ከአጥቂው ጦር ውስጥ ማንም ቢሆን የተጎዳ ለመርዳት እንዳይቆም፤ የሞተ ሰው በቃሬዛ የሚያነሱት ከበሮ መቺዎች እና የፑንጃብ በቅሎ ጋላቢዎች እንዲሆኑ ------»

ወደ መቅደላ የሚወስደው መንገድ የወርቅ ውኃ ሸለቆን የሚያቋርጠው ደረቅ የውኃ መውረጃ ነበር። በዚህ ነበር ቴዎድሮስ ከነመድፉ የተጓዘው። ይህ መንገድ ለኔፒር ክፍት አልነበረም። ወርቅ ውኃ ከሁሉም አቅጣጫ ቁልቁል ለጥቃት የተጋለጠ ነው። ኔፒር አሮጊ ኮረብታ ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ ከፍታ ቦታ ያስፈልገዋል። ከበሽሎ ራቅ ብሎ ጉምባጂ ላይ ሠፈረ። ወደላይ የመውጣቱ ሂደት በጣም ፈታኝ ነበር። ወታደሮቹ አዳጋች በነበረው የተፈጥሮ መንገድ መጓዝ ምን ያህል ያሠቃይ እንደነበር መዝግበውታል። ከባድ ሙቀት እና የውኃ ጥም ከጠናባቸው መካከል አብዛኞቹ በድካም ዝለው ጉዞውን መቀጠል አልቻሉም ነበር።

መንገዱ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን መሣሪያ ለተጫኑት ለእንስሳቱም አዳጋች ነበር። በብዙ ድካም ከላይ የደረሱት ትንፋሻቸውን ውጠው ጥቂት በመጓዝ ይገፋሉ። ኔፒርም ቢሆን በተመሳሳይ መንገድ ተጉዞ አሮጊ ኮረብታ ላይ ሲደርስ ከማዶ የፈላ እና ሥላሴን ግዙፍ ተራራዎች በቅርብ ርቀት መመልከት ቻለ። ጥቂር ዳመና አንዣብቦባቸዋል። ሰዓቱ ገና 10 ሰዓት አልሆነም። እዚያ እንደወጣ ወዲያው ችግር መኖሩን ኔፒር ተረዳ። ወደ ወርቅ ውኃ ሲመለከት እዚያ የደረሰ ምንም ኃይል አልነበረም። በዚያ ቅፅበትም የመጀመሪያዎቹ በቅሎዎች እንጉታቸውን እንደደፉ ከሸለቆው ወደ ላይ ሲወጡ ተመለከተ። ምንም ከለላ አልተደረገላቸውም። ወዲያው ኔፒር ፑንጃቦቹ ፈጥነው ወደፊት እንዲገሥግሱ ትዕዛዝ አስተላለፈ።

ከወርቅ ውኃ ከመጡት መካከል ሄንሪ ሞርተን ስታንሊ ይገኝ ነበር። በኮረብታዎቹ ላይ ስለነበረው ጥርጣሬ የተሞላበት ፀጥታ ተናግሯል። ሰላም አልሰጣቸውም።

ከአሮጌ ኮረብታ ላይ ከወጡ በኋላ ቁልቁል አሻግረው ወደ ፊላ ሲመለከቱ አቧራማ ደመና አዩ። የሚንቀሳቀስ ነገር መኖሩንም አስተዋሉ። በሰከንዶች ውስጥ በተራራው ላይ የነበረው ሁሉ አቅጣጫውን ለወጠ።

በዚያው ቅፅበት ከፊላ የተራራ ጫፍ ከላይ ነጭ የለበሰ ቡድን ብቅ አለ። በመኮንኖቹ እና በኔፒር አናት ላይ ጥይት እየጮኸ አልፎ ከኋላቸው መሬት ላይ ወደቀ።

ተኩሱ ምልክት ይመስል በየአቀበቱ መተላለፊያ እና ከፊላ በኩል ካሉ ተራራዎች እጅግ ብዙ ተዋጊዎች አካባቢውን ሞሉት። በሺዎች የሚቆጠሩ በርካታ ወንዶች ገሚሱ በፈረስ ገሚሱ ጠብ መንጃቸውን ይዘው ወደ እንግሊዝ ጦር ቁልቁል ግር ብለው ወረዱ።



# ምዕራፍ ሰባ አምስት

በዚያን ቀን ማለዳ ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ሁለት መልዕክተኞች ወደ ቫልድማየር ድንኳን መጡ። ቴዎድሮስ ጋር እንዲቀርብ ነበር የተላኩት። በዚያን ወቅት አሥረኞች እየተጨ ፈጨ ፉ እንደ ነበር ሁሉም ያውቃሉ። እናም ቫልድማየር መልዕክተኞቹን ትክ ብሎ ተመለከታቸው። ለምን እንደተጠራ የሚያውቁ መስሎት በጣም ደነገጠ።

ቫልድማየር ወደ ቴዎድሮስ ሲቀርብ ንጉሡ በተዘባረቀ ስሜት ውስጥ ሆኖ ወደ መሬት አቀርቅሯል። ለምን እንዳስጠራው የዘነጋ ሁሉ ይመስላል። ቫልድማየር አዚያው ቆሞ የዕለቱን የመጀመሪያ ውሳኔዎች በእማኝነት ተመለከተ። የመጀመሪያው የቴዎድሮስ ትዕዛዝ ራሳምና ሌሎች አውሮጳውያን እሥረኞች መቅደላ ወደሚገኘው እሥር ቤታቸው እንዲመለሱ የሚል ነው። ቫልድማየር «ይህ ውሳኔ እጅግ አስጊ ነበር። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተባብረው የአውሮጳውያኑን ፍጻሜ አስከፊ ያደርጉታል ብዬ አሰብኩ»" ብሏል።

በተቃራኒው ሽተርን ተደስቷል። ከንጉሣዊው መኖሪያ አካባቢ ተለይቶ ለጥቂት ሰዓታትም ቢሆን ሞትና ደም ከከበበው ሥፍራ ዘወር ብሎ የአፎይታ ትንፋሽ መተንፈስ መቻላቸው አስደስቶታል። ከአካባቢው ተነስተው ወደ አምባው ከመውጣታቸው አስቀድሞ ግን ራሳም በድጋሚ ቴዎድሮስ ለኔፒር ደብዳቤ እንዲጽፍ ተማፀነው። ቴዎድሮስ ግን «ደግሞ ሴት ለላከው በፍፁም እንዲህ ያለ ነገር አላደርግም» አለ።

አውሮጳውያኑ መንቀሳቀስ ሲጀምሩ በድጋሚ ራሳም ከናፒየር ለቴዎድሮስ የተላከ መልእክት መኖሩ ተነገረው። ቴዎድሮስ ግን መልዕክተኛም ሆነ መልእክት ለመቀበል አሻፈረኝ አለ። እንደውም ራሳም ከብሪታኒያ ኃይሎች ጋር ግንኙነት ማድረጉን እንዲያቆም አስጠነቀቀው። «ያንተን ደብዳቤ የሚያመላልሱ መልዕክተኞች ደም ባንተ ላይ ነው። ተጠንቀቅ!»

አውሮጳውያኑ ከአካባቢው እንደሄዱ ቴዎድሮስ የጦር ዕቅዱን መንደፍ ቀጠለ። መድፉ ወደፋላ እንዲወሰድ አዘዘ። የጦር መሣሪያዎቹን በመሥራት የተባበረው ቫልድማየር አሁን ደግሞ በጦርነቱ ላይ አጠቃቀማቸውን እንዲያሳይ ተመደበ።

«ቤተሰብህን ተሰናበት። ምክንያቱም ዛሬ ከንጉሥ ጋር የክብር ሞት ልትሞት ትችላለህ» አለው ቴዎድሮስ።

ቫልድማየር በኀዘን የከበደ ልቡን ተሸክሞ ወደ ድንኳኑ ሄደ። ውድ ባለቤቱ ሱዛንን እና ትንሽ ልጁን ሮዛን ተሰናበተ። ሮዛ ከጥቂት ዓመታት በፊት በደስታ የአንበሳውን ግልገል ሃጎስን ስትጋልብ ነበር። ሁለቱንም አቅፍ አድርጎ ሳመ እና ቴዎድሮስን

ተከትሎ ወደ ሰላምጌ ተጓዘ። ባዶ እግሩን በኮረኮንቹ መንገድ ሲሄድ እንባው ጉንጩን እየሰነጠቀ ወረደ። «ከመቅደላ ወደ ፈላ የሚወስደው መንገድ እጅግም ረዥም አልነበረም። ነገር ግን በቪያ ደሎሮዛ ላይ የተደረገው የዕለተ ስቅለት ጉዞ ማለት ነበር» በማለት የተሰማውን በወቅቱ ጽፎታል።

ቴዎድሮስ ፈላ ላይ ሆኖ የመድፍ ተኩሱን መምራት ነው ያሰበው። እጅግ ታማኝ ጀነራሉን አስጠራው። ይህ ታማኝ ጓዱ እንደሱ «የቋራ ሰው» ነው። ፊታውራሪ ገብርዬ። ወልደ ጋብር እንደሚለው 30 ዓመታትን የዘለቀ ወዳጁ ነው። ቴዎድሮስ ገብርዬን የእግረኛውን ጦር እንዲመራ ሾመው።

እኩለ ቀን ገደማ ደመና ተራራውን ሲከብ ቴዎድሮስ የጦር ፈረሱ ላይ ወጣ እና ለሠራዊቱ ንግግር አደረገ። አሁን የማወላወል ስሜት የለም። ጠላት ከበታቻቸው በቅርብ ርቀት ይገኛል። ቴዎድሮስ ወጣትነቱን እንፀው ያደመቁትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች አሰበ።

«ልጆቼ እነዚህን የእንግሊዝ ወታደሮች አትፍሯቸው፤ ምክንያቱም እነሱ ከዳዊት ጋር እንደተፋለሙት ፍልጤማውያን ማለት ናቸው። ሆኖም ግን አስታውሱ እነሱን ዳዊት ድል አድጓቸዋል፤ እናም እኔም በእግዚአብሔር ኃይል አሸንፋቸዋለሁ»። ፈረሱ በሠልፉ መካከል ወደፊት እና ወደኋላ ተቅበጠበጠ።

«እኔ የዳዊት እና የሰሎሞን ልጅ አይደለሁምን? እግዚአብሔርስ የኢትዮጵያ ንጉሥ አድርጎ አልቀባኝምን? ለፈሪዎች የእሳት ዓምድ የሆንኩ የጥንቱ የጦር ሜዳ ጀግና አይደለሁምን?»

ቴዎድሮስ የብሉይ ኪዳን ጦረኞችን ታሪክ በማውሳት ብቻ አላበቃም። የካህኑን ቦታም ያዘ። «አባታችን አቡነ ሰላማ ቢሞቱም፤ በእግዚአብሔር ስም፣ በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ከአውሮጳውያን ጋር ከሚካሄደው ውጊያ የሚያፈግፍግ ወታደርን ሁሉ አወግዛለሁ!»

ከበታች የመጀመሪያዎቹ ግመሎች ወርቅ ውኃ ላይ ብቅ አሉ። በአሮጌ ኮረብታ በኩልም የእንግሊዝ ወታደሮች እንሰው ይታያሉ። "ተመልከቷቸው እነዚህን ባሪያዎች! ሴቶች ናቸው! ተመልከቱ ልብሶች ሃብትና ደመወዝ ይዘውላችሁ መጥተዋል! ውረዱና ራሳችሁን አስተናግዱ!"

በእንስሳት ጭምር ተጭኖ የመጣው ጓዝ በእርግጥም ሠራዊቱን ለድል የሚያጓጓ ነበር። የሠራዊቱ የደስታ ሁካታ ተሰማ። የአዛገሮቻቸውን ድምፅም ዋጠው።



ይገነት ቴዎድሮስ አቅማማ። ባልደረባውን ቫልድማየርን ጠየቀው። ምናልባት ለውጊያው ፈጥነው ይሆናል። ከአፍኞ ኮረብታ በኩል ተጨማሪ ጦር ተመለከተ። ስልታቸውን ለማወቅ ጥቂት መቆየት ይኖርበታል።

ሠራዊቱ እንዲመለስ ተጣራ ---- ግን ዘግይቷል። ሠራዊቱ ተንቀሳቅሷል፤ አዛገሮቻቸው እንኳ ሊያስቆሟቸው አልቻሉም።

«በሉ እኔ በመድፍ ሽፋን እሰጣለሁ»።

ቫልድማየር የመድፎቹን የመወንጨፍ ርቀት እንዲለካ ቴዎድሮስ ጠየቀው። የመጀመሪያ ተኩስ ከኮረብታው በላይ ነነ።

# ምዕራፍ ሰባ ስድስት

ቴዎድሮስ ተሳስቷል። እሱ ባሠራው መንገድ ላይ ከወርቅ ውኃ እና ከአሮጊ ኮረብታ በኩል የሚመጡት በቅሎዎች ዕቃ ብቻ የጫኑ አልነበሩም። ይልቁንም የባሕር ኃይል ብርጌዱን የሮኬት ቀለህ እና የኮለኔል ፔንን መድፎች የተሸከሙ ነበሩ።

የተጫኑት እንስሳት አስቀድመው ብቅ ሲሉ፣ ግልብጥ ብሎ ከመጣው የቴዎድሮስ ሠራዊት ራሳቸውን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው አልተዘጋጁም ነበር። ተዋጊ ጦር አልተከተላቸውም። ወዲያው ግን 4,000 የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን ቁልቁል ኾ እያሉ ሲመጡባቸው ራሳቸውን ለማዳን መሣሪያቸውን ለተኩስ ለማዘጋጀት ተጣደፉ። የሮኬቱንም ቀለህ እያስተካከሉ መተኮስ ጀመሩ። የኢትዮጵያውያኑ እንቅስቃሴ ሰከን አለ።

የቴዎድሮስ ሠራዊት እዚያ ቀድሞ ከደረሰው የብሪታንያ ጦር ይበልጣል። 3,000 የሚሆነው የታጠቀ ነው፣ ያው ግን ያለው አሮጌ ጠብመንጃ ነው። ለሁለት ተከፈለ። የብሪታንያ ጦር ገሚሱ ሮኬቱን ሲይዝ ገሚሱ ቀለሃውን ባሩድ እያጎረሰ ለመተኮስ ተጣደፈ። ሰማዩ በጥቁር ዳመና ተሸፈነ። መብረቅ እያንባረቀ በተራራው ላይ አስተጋባ። ከአራት ሜትር ከፍታ ገደማ የንጉሡ መድፍ አሳቱን እያስፈነጠረ ከኮረብታው እናት ላይ ይወረውረው ጀመር።

ቴዎድሮስ ይህን ለማየት ለወራትና ዓመታት ጠብቋል። አሁን ያለው ኃይል ከዚህ በፊት ከነበረው የቀነሰ ነው። በጠላት ተከቧል። እንዲያም ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ የጦር መሣሪያዎቹን ጦር ሜዳ ላይ አውሏል። በዚያም ላይ የመቅደላ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የአንድ ሺህ ጦር ግምት ነው።

እናም የሠራዊቱን ድንገተኛ ግሥጋሤ እና የብሪታኒያ ጦር ፈጥኖ ለመቧደን መንቀሳቀሱን አይቷል። የእሱ የጦር መኮንኖች በተጌጠ አለባበስ ሲታዩ የብሪታንያ ደግሞ ለውጊያ መዘጋጀታቸውን በካኪያቸው ያመለክታሉ። ከጥቂት የሮኬት ተኩስ በኋላ የእሱ ሰዎች ዳግም ተሰባሰቡ። እንደውም ጠላትን በቀለበት ውስጥ ሲያስገቡ ተመለከተ። ከበስተኋላም ዘጉባቸው። እንግሊዞች ተከበቡ።

ከፊላ በኩል የደስታ ጩኸት ተስተጋባ፣ ወዲያው መልካም ዜና የያዘ መልዕክተኛ ወደመቅደላ ሮጠ። ቫልድማየር መጀመሪያ አካባቢ መድፎቹን በማስተኮስ ረድቷል። ሆኖም ግን ከቴዎድሮስ ወገን አንድ ኮፐት(ቅብጥ) በእርሱ ቦታ ሆኖ ትዕዛዝ ይሰጥ ጀመር። ውጤታማ ግን አልነበረም። የሚተኩሰው አንድም ከብሪታንያ ጦር አልፎ አንድም ወደ መሬቱ የሚቀረቀር ሆነ። ፈላ ላይ ከተጠመዱት መድፎች አንዱ «ቴዎድሮስ» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ቫልድማየር ብዙም ሳይርቅ ቆሟል። ድንገት መድፉ ፈነዳ። ያለ እቅሙ እጥፍ



እንዲተኩስ ተደርጎ ነበር። ንጉሡ ይህን በቁጣ እና እልህ ነበር የተመለከተው። በእልህ ተንቀጠቀጠ።

ከጦር ሜዳው አዲስ ድምፅ ተሰማ። 446 የሚሆኑ የኢትዮጵያ ተዋጊዎች ወደ ኮረብታው ደረሱ። የመጀመሪያዎቹ ተኩሶች አስቆሟቸው። ግን ደግሞ ጥቂት ቆይተው ወደፊት ገፉ። ለተኩሱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ። የመጀመሪያው ተኩስ ከተረፍክ ሁለተኛው ቀለህ ሳይሞላ ወደ ጠላት ፈጥኖ መድረስ ያስፈልጋል። ሠላሳ ሰከንድ በመካከል ክፍተት አለ። ፖርቱጋሎች የመጀመሪያውን የጦር መሣሪያ ካመጡ አንስቶ ያለው የጦር ሜዳ ውሎ ይህ ነው። ከዚያ ወዲህም ቢሆን ያን ያህል የተለወጠ ነገር የለም።

ለእንግሊዞቹ ግን እንዲህ አልነበረም። ፋታ ሳይሰጥ ጥይት የሚያዘንበውን መሣሪያ በጦር ሜዳ ላይ ሲጠቀሙ የመጀመሪያቸው ነው። የተኩስ እሩምታው ያለማቋረጥ ቀጠለ። ያለምንም ፋታ ሠላሳ ወይም አርባ ጊዜ። መሣሪያ ደግነው ከፊት የነበሩት የኢትዮጵያ ተዋጊዎች ወደቁ። ቀሪዎቹም አፈገፈጉ፣ እናም ዳግም ወደፊት ገሠገሡ ። ተኩሱ ፋታ አይሰጥም። በመጨረሻ ኢትዮጵያውያኑ ወደኋላ ወደቁ። ገሚሱ ከፊላ ኮረብታ በታች ወዳለው የሙስሊሞች የመቃብር ሥፍራ፣ ቀሪዎቹ ከቋጥኝ በታች ወረዱ። እዚያም ሆነው ግን መተኮስ ቀጠሉ።

ከከፍታው ሥፍራ ቴዎድሮስ አሻግሮ ውጊያውን ይመለከታል። ሠራዊቱ ወደፊት ሲገፋ እና ጥንካሬው ሲፍረከረክ፣ በርካቶችም እየተመቱ ሲወድቁ አየ። ዳግም ተሰባስበው ሲዋጉም ተመለከተ። በዚህ ሁሉ መካከል የእንግሊዝ ጦር ሳይነካ ተሰልፏል። ቴዎድሮስ ይህን ሁሉ ቢያይም ምንም ማድረግ ግን አልቻለም። ሽንፈት ተሰማው። የባሕር ኃይል ብርጌዱ አሁን የሮኬቱን አፈሙዝ ወደፊላ አዞረ። ከቴዎድሮስ ብዙም ሳይርቅ አንዱ ወደቀ፣ «ራሴን መትቶኝ ነበር!» አለ።

ድንግዝግዝ አለ። በውጊያው ወቅት ከባድ ዝናብ ዘንቧል። አሁን እየቀነሰ ሄደ እና አባራ። በተሰባበረው ደመና መካከል ፀሐይ ወጣች። ጨለማውን ተገን አድርገው ቤተሰቦቻቸው የጠፉባቸው በዝናብ ወደጨቀየው አካባቢ ወደ እርጊ ወረዱ። ለሰዓታት የእነሱ ጩኸት ከቆሰሉት ጣር ጋር ተዳምሮ አካባቢውን አወከው። የተረፉት ወደፊላ ኮረብታ ወጡ። በጨለማው መካከል ቴዎድሮስ ጠራቸው። «ፊታውራሪ ገብርዬስ?» ጀነራሉ ሞቷል። ቴዎድሮስ ተራ በተራ የጦር አዛዦቹን ስም ይጠራ ጀመር። ሁሉም ሞተዋል። ከፈረሶቻቸው ላይ ሆነው ሲዋጉበት በነበረው የጦር ሜዳ ላይ አልፈዋል። እዚያው ቀርተዋል። ከእንግሊዝ ጦር ወገን 20 ዎቹ ቆስለዋል። ከመካከላቸው የሁለቱ ጉዳት የከፋ ነው። ከኢትዮጵያ ወገን 700 ሲሞቱ 1,500 ቆሰሉ።

ቴዎድሮስ ወደ ድንኳኑ ተመለሰ። ቀላል ዝናብ ሲወርድ ይሰማል። ንጉት ዋጠው። መተኛት አልቻለም። ለወትሮው የጦር ዕቅድ ያወጣ፣ በጦር ኃይሉ ውስጥ ያለውንም ሁኔታ በፍጥነት ለመፍታት ይሞክር ነበር። አሁን ግን የጦር መሣሪያዎቹ የተከሩለት ነገር የለም። ጦሩ ተሸንፏል። አማራጮቹም ተዘግተዋል። በውጊያው መግፋት ወይም ሽንፈቱን መቀበል ብቻ ከፊቱ ተጋርጧል። እሥረኞቹን መግደል ወይም አሳልፎ መስጠት ይችላል። የቀረው ቢኖር እሥረኞቹ፣ ጥቂት ደጋፊዎቹ እና ተራራው ብቻ ነው። «እግዚአብሔር የፈለገውን ያድርግ! ሂዱ ተኙ!» አላቸው።

ጀርመናውያኑ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ተቀስቅሰው ወደን ጉሡ ዘንድ ተጠሩ። በዚያ ፀጥ ባለ ሌሊት የሥቃይ ድምፅ ከየአቅጣጫው ይሰማል።

«ይህን ሰቀቀን ትሰማላችሁ?» አላቸው ቴዎድሮስ። «ጓደኛውን ወይም ወንድሙን ያላጣ ወታደር የለም። እጠቃላይ ጦር ቢመጣ ምን ይፈጠር ነበር? ምን ማድረግ አለብኝ? አማክሩኝ» አላቸው።

«ግርማዊነትዎ ሰላም ይበጃል!» አለ ቫልድማየር በተማፅኖ። ፍላድም ይህኑ ደገመ። ቴዎድሮስ ሐሳብ ውስጥ ገባ። «እሺ» ከማለቱ በፊት ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ። «መልካም!» ከዚያም ፍላድ ወደ መቅደላ ሄደ ፕሪዶን ሊያመጣ። ወደ ብሪታንያ የጦር ሠፈር አብሯቸው እንዲሄድ የተመኙን ልጅ ያገባውን ደጃዝማች ዓለሜን ቴዎድሮስ ነገረው። ወገግ ሲል ፍላድ፣ ፕሪዶና ዓለሜ ጉዟቸውን ጀመሩ። ቴዎድሮስ ቀለል ያለ ልብስ ለበሰ፣ አቅርቦ የሚያሳይ መነፅሩን ወደ ሥላሴ ኮረብታ አነጣጠረ።



ቀደም ባለው ቀን ገስግሶ በሸሎ ሸለቆ የወረደው የብሪታንያ ጦር ወንዙን ተሻግሮ፣ የጉምባጅን አቀበት ወጥቶ፣ የአፍቅን ኮረብታ ተሻግሮ ድንገት እንደመብረቅ የቴዎድሮስን ጦር ማሸነፍ ችሏል። አሁን መሬት ላይ ወርደው ተኙ። ሌሊቱን ሁለተኛው ብርጌድ መጥቶ ተቀላቀለ። ከብርጌዱ ጋር የአርምስትሮንግ መድፎችን የጫኑ ዝሆኖች አብረው መጡ።

ማለዳ በወፍ ጫጫታ ሲነቁ ፀሐያማ ዕለት ነበር። ጥቂት ሰው ተጎድቶባቸው ለቀጣዩ ትናንት ድል ስለቀናቸው እርስ በእርሳቸው እንኳን ደስ አለን ተባብለው ጠግያ ከካፒቴን ስዊይ ጋር ተንቀሣቀሡ። በአካባቢው የነበረው ግን የሚያስፈራ ነበር። ቁስለኞች በጭቃማው ሜዳ ላይ ወዳድቀዋል። ጅቦቹ አብዛኞቹን ዘነጣጥለዋቸዋል። ገሚሶቹ በሥቃይ ያቃስታሉ። እንግሊዞቹ እነዚህን ለማከም ወደ ጦር ሠፈራቸው ወሰዱ። ወዲያው ከወደላይ ተኩስ ተሰማ። የሁሉም ዓይን አሻቅቦ አፈጠጠ። ከፊላ አቀበት በኩል ጥቂት ወንዶች ነጭ ሰንደቅ እያውለበለቡ መጡ። ከመካከላቸው የብሪታንያ ወታደራዊ የደንብ ልብስ የለበሰ ሰውም አለ። ቡድኑ እየቀረበ መጣ። ወደጠባቂዎቹ ሲጠጉ፣ ዋርድያዎቹ በደስታ እየጮኹ ሰላምታ ሲሰጡ ተሰማ። ሌፍተናንት ፕሪዶ ፣ ማርቲን ፍላድ እና ደጃዝማች ዓለሜ፣ የቴዎድሮስን የቃል መልእክት ይዘው ከናፒየር ፊት ቆሙ። ናፒየርም በተራው የቃል መልሱን ሰጠ።

«ግርማዊነትዎ እንደ ጀግና ተዋግተዋል፣ በላቀው የብሪታንያ ጦርም ተበልጠዋል። ከእንግዲህ ደም እንዳይፈስ ፈቃዴ ነው። ይህ የሚሆነው ግን ግርማዊነትዎ ለንግሥቷ በማደር በቁጥጥርዎ ሥር የሚገኙትን አውሮጳውያን በጥሩ ሁኔታ ወደ ብሪታንያ የጦር ሠፈር አሳልፈው ከሰጡ ነው። ለእርስዎም ሆነ ለግርማዊነትዎ የቤተሰብ አባላት ሁሉ አክብሮት የታከለበት አያያዝ እንደሚደረግ ዋስትና? እሰጣለሁ»።

ኔፒር ቃላቱን በጥንቃቄ ነው የመረጠው። በቴዎድሮስ ላይ ጠንካራ ድል ተቀዳጅቷል፣ የጦር መሣሪያ የበላይነቱንም አረጋግጧል። እነዚህ እንግዲህ ተራ ጨዋታዎች ናቸው። ለዓለሜ በዝሆኖች ላይ ተጭነው የመጡትን መድፎች አሳዩት። እንዲያም ሆኖ ኔፒር ገና እሥረኞቹን በእጁ አላስገባም። የትኛውም ዓይነት ዘመናዊ መሣሪያም የእነሱን መለቀቅ እስተማማኝ ሊያደርግለት አይችልም። መልዕክተኞቹ ከብሪታንያ የጦር ሰፈር ሲመለሱ ቴዎድሮስ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ ፀሐፊው አሊቃ እንግዳን በቃሉ ያጽፋል። የኔፒር ደብዳቤ እንዲነበብለት አቋረጠ። ፍላድ እና ቫልድማየር በየተራ እንዲተረጉሙለት አደረገ። የኔፒር «የክብር አያያዝ» እንድምታ ትኩረቱን ሳበው። «የአክብሮት የሚሉት

እንደ እሥረኛ ማለት ነው ወይስ ከአማፅያኑ ሀገሬ ተላቃ እንድታገግም ይረዳኛል ማለት ነው?»

ቴዎድሮስ በመጠኑ የብሪታንያን ወዳጅነት አገኛለሁ የሚል ተስፋ ያለው መሰለ። ሆኖም ግን እጅግ ጥቂት እንደቀረው ዳግም ተረዳ። ለቤተሰብዎ «የእከብሮት እያያዝ» እናደርጋለን የሚለውን ማባበያም አላመነውም። «እንደ ራሴ ፀጉር የበረከቱ ልጆች እና ሚስቶች ስላሉኝ ይህን ሁሉ ቤተሰቤን ለመንከባከብ ቢያስብ ለእንግሊዝ ከፍተኛ ወጪ ይሆንባቸዋል»። እንግዳን ጠርቶ ማጻፉን ቀጠለ። በእዚህ የቅዳሜ ስሑር ዕለት ስለቴዎድሮስ ሁሉንም ፉከራውን፣ ሥላቁን፣ ድፍረት እና ታዋቂነቱን፣ ጉራውን፣ ታማኝነቱን እና ሐቀኝነቱን፣ በሙሉ የሚገልጽ ነበር የተጻፈው። በጥቅሉ በመጨረሻ ሰዓት የሚነገር ኑዛዜ ይመስላል።

«በስመ አብ ወወልድ ወ መንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ! በአንድነት እና ሦስትነት፣ በክርስቶስ የሚያምነው ካሣ!

የሀገሬ ሕዝብ በእግዚአብሔር ኃይል መጥቼልህ ነበር! ፍርድህን እንዴት ታደርገው ይሆን? ክርስቲያኖችን ሁሉ አጥፍቼ ወደ ኢአማንያን ምድር ያመጣኋችሁ መስሎ ተሰማኝ። ባል የሌላቸው ኮረዶች አሉ፣ ልጆች የሌላቸው ጎ ማግለዎች፣ እንዲሁም ልጆቻቸውን ያጡ አሮጊቶች አሉ። እንዲህ ያሉ የእነ ርዳታ የሚፈልጉ በርካቶች በከተማዬ ይገኛሉ። የኢአማንያን ምድር እንደመሆን እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ላይ ለግሏቸው፣ ግብር አስገቡ ባልኳቸው ጊዜ የሀገሬ ሕዝብ ከእኔ ጋር ተጣሉ። በሥርዓት የምትመሩት እናንተ ግን ይኸው ወረራችሁኝ። የሚወዱኝ እና ይከተሉኝ የነበሩት ጥይት የማይፈሩት ሰዎቼ ጥለውኝ ሸሹ። እናንተ ጥቃት በሰነዘራችሁባቸው ጊዜ ከእነሱ ጋር አልነበርኩም። በቂ ያልሆነ የጦር መሣሪያ ይዤ አሊቃ ነኝ ብዬ ሳስብ የእኔ ነገር አበቃ። የሀገሬ ሰዎች አሥር ምክንያት ሊሰጡኝ ይችላሉ፣ የፍራንክን ሃይማኖት ተቀብለክ፣ እንዲሁም ሙስሊም ሆንክ ሊሉኝ ይችላሉ። በእነሱ ላይ መጥፎ አድርጌ ከሆነ እግዚአብሔር ይፍረድላቸው! እርሱ እንደፈቀደውም ይሁን! እግዚአብሔር ሁሉን እንድገዛ እንደፈቀደልኝ አስቤ ነበር! እግዚአብሔር ይህን ከእኔ ከወሰደ መሞት አለብኝ! ይህ ነበር ሐሳቤ። ከተወለድኩ ጀምሮ የትኛውም ወንድ እጄን ይዞ አያውቅም። ሰዎቼ ሲሸሹ መልሼ እነሱን የማሳመን ልማድ ነበረኝ። ጨለማው አገደኝ። ትናንት የተደሰታችሁ እናንተን እግዚአብሔር በእኔ እንዳደረገው አያድርግባችሁ። የሀገሬ የኢትዮጵያ ጠላቶችን ብቻ ሳይሆን ወደ ኢየሩሳሌምም ዘምቼ ቱርኮችንም አባርራለሁ ብዬ ነበር። ሌሎች ወንዶችን ይዞ የነበረ ወንድ በተራው በሌሎች መያዝ የለበትም።»

## ምዕራፍ ሰባ ዘጠኝ

ቴዎድሮስ የሚያጽፈውን ደብዳቤ ፈጸመ። ከኔፒር ደብዳቤ ጋር አድርጎ ወደ ብሪታንያ የጦር ሠፈር ላከው። ድንገት መረጋጋት ታየበት። በዙሪቻው የነበሩትን እንዲሄዱ አዘዛቸው። በአገዛዝ ዘመኑ ወሳኝ ጉዳይ ሲገጥመው እንደሚያደርገው ሁሉ ብቻውን ተረጋግቶ ድንጋይ ላይ ቁጭ አለ። ታላቁ የበሽሎ ሸለቆ ከበታቹ ተዘርግቷል። ድንገት ተነስቶ ውኃ ጠጣ እና ዳግም መጸለይ ጀመረ። ሦስት ጊዜ ሠገደ። ከዚያም ከወገቡ የተሻጠውን ባለሁለት አፈሙዝ ሽጉጥ መዘዘ፣ አፉ ውስጥ ከተተ እና ቃታውን ሳበ።

ወታደሮቹ የሚያደርገውን ሲመለከቱ ወደ እርሱ ሮጡ። ለሁለተኛ ጊዜ ቃታውን ሲስብ ከንዱን ያዙት። አሁን ተተኮሰ። ጥይቱ ጆሮ ግንዱን ገነጠለው። ሁሉም ወዲያው መሬት ላይ ወደቁ። ቴዎድሮስ ዘለግ ላለ ጊዜ ተወራጨ። ሆኖም ወዲያው እንቅስቃሴው ቀነሰ። ሽማውን ወደ አፍንጫ ሳበ እና ፀጥ ብሎ ተንጋለለ።

የቴዎድሮስ ራስ የማጥፋት ሙከራ በዙሪያው ለነበሩት ዘግይቶ ግልጽ የሆነ ነገር ነበር። ካጠገቡ እነሱን ማሰናበቱ፣ ለኔፒር የጻፈው ደብዳቤ፣ አሮጌ ላይ የገጠመው ሽንፈት፣ በታላቅነት ሲመራ የነበረ ኃያልነት እጅ ላለመስጠት የሚኖረው እምቢተኝነት፣ ሁሉ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ሊያደርግ የሚፈልገውን የሚያመላክቱ ናቸው።

ከአምስት ዓመታት በፊት ሔንሪ ዱፍተን በመጨረሻ አዕምሮውን ያቃጥላል የሚል ግምት ሰንዝሮ ነበር። ነገር ግን ከዚያ አምልጧል። ተነስቶ ነበር ነገር ግን ራሱን ጣለ። አሁንም ግን እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ዓላማ እንዳለው ያምን ነበር። ባለፉት ሁለት ወራት በዚህ በትንሣኤ በዓል ሊገጥመው የሚችለው ዕጣ የሚታይ ነበር። የጾሙ ን ወራት መድፎቹን በዚያ ባልተመቻቸ ጎዳና ሲያጓጉዝ ነው የሰነበተው። የሥቅለት ዕለት ከሰዓት አሮጌ ላይ የተካሄደው ውጊያ ሠራዊቱን እና የተሰፋውን ዓለም አወደመበት። ሆኖም ግን ዛሬ እንሠራራ። ዳግም ወሳኝ ሆነ። እንደ ድሮው የቅርቡ ያልሆነችውን ንግሥት ጥሩነሽን አስጠራት እና ሁለቱ ለብቻቸው ለጥቂት ሰዓታት አብረው ቆዩ። ይህ እንግዲህ ከረዥም ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው።

የመጨረሻ የሚሆነውን ቃሉን ሲያጽፍ የሆነ ነገር እየሆነ ነበር። ከጦሩ የተረፈው ሠራዊት ዳግም በዙሪያው ተሰባሰበ። ከአንድ ቀን በፊት ያጋጠመው ሽንፈት ቁጭት ረገብ አለ። ለመዋጋት የነበረው ፍላጎት ተከታዮቹ ላይ ይታያል። «እንግሊዞች ሙተኛት ይወዳሉ፣ ሌሊት ልናጠቃቸው ይገባል» ሲባባሉ ይሰማሉ። ቴዎድሮስ አማካሪዎቹን ሰብስቦ ምክር ጠየቀ። ራስ እንግዳ፣ ደጃዝማች ዑብይ፣ ደጃዝማች ወርቄ፣ እንግዳወርቅ እና ሌሎችም አሉ። ቫልድማየር ተደብቆ ውይይታቸውን ቢያዳምጥም፣ ባላደረኩት ኖሮ በሚል ተቆጨ።

«ለዚህ ጦርነት ምክንያት የሆኑትን እነዚህን አውሮጳውያን አሁኑኑ መፍጀት ነው» አለ አንዱ። ሌላኛው ደግሞ «እንጨት ቤት ውስጥ አስገብተን በእሳት እናቃጥላቸው» ሲል ሐሳብ አቀረበ። «እጅ እና እግራቸውን እንቁረጠው እና እንግሊዞች መጥተው ይውሰዷቸው »አለ ሌላው።

ከሰዓት በኋላ ቫልድማየርን እና ሌሎቹን የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች አስጠራቸው እና ቴዎድሮስ በዝምታ ተመለከታቸው። ለቫልድማየር የመጨረሻዋ ሰዓት የመጣች መሰለው። አውሮጳውያኑን የመበቀሉ ስሜት በተራራው ላይ ገዘፎ ይታይ ነበር። በቀደመው ቀን ያጋጠመው ሽንፈት ያስከተለው የሥቃይ ስሜት ታጋቾቹን ጭራሽ በረዶ ውስጥ ከተታቸው።

«እናንተን እና አውሮጳውያኑን በሙሉ እንድገድላችሁ ሁሉም መከረውኛል፤ አንዱ ብቻ ነው የተሟገተላችሁ። ነገር ግን እናንተ ምንም ስላላደረጋችሁኝ አልገድላችሁም»።

በተቃራኒው ቴዎድሮስ የታሠሩት የውጭ ዜጎች በሙሉ እንዲለቀቁ አዘዘ። የምስራቹንም ለራሳም እና ለሌሎቹ እንዲያበሥሩ ሁለቱን የጦር መኮንኖቹን ወደ መቅደላ ላካቸው። ውሳኔውን ማንም አላመነም። መልዕክተኞቹ እሱ ጋር ሲደርሱ ራሳም ቅሬታቸውን ከፊታቸው ላይ ተገነዘበ። ከተመለከታቸው ኢትዮጵያውያንም « ንጉሡ በመንገድ ላይ እንዲገደሉ» እንደፈረደባቸው ተረዳ።

በፍርሃት እና ጥርጥር ውስጥ እንዳሉ ለረዥም ጊዜያት በሞት ጥላ ሥር የከረሙት ወንዶች፣ ሴቶች፣ ሕፃናት እና አገልጋዮቻቸው መቅደላን ለቀው ጉዞ ጀመሩ። ወደ ረባዳው መሬት ወደ ሰላምጌ ወረዱ። እየመሸ ነበር። ደመናው ከበላያቸው እንግዒል። የራስ ቅል የመሰለው የመቅደላ ተራራ ከበስተኋላቸው ጨለመ።

አንድ ሰው ወደ እነሱ ሲመጣ ተመለከተ። ትንፋሹ እየተቆራረጠ የንጉሡን መልእክት አደረሰ። «ከመሄዱ በፊት ራሳም ቴዎድሮስን ማየት ይፈልግ እንደሆነ ሊያየው ይችላል። ጽዱ ሜማ እና የዲፕሎማቲክ የደንብ ልብሱን እንደለበሰ ራሳም ከሚ ጓዘው ቡድን ተለየ። ተስፋ ያለው ነገር መስሎ አልታየውም። የዛሬ ሁለት ዓመት ከዘጌ ሊወጡ ሲሉ የገጠማቸው እያንዳንዱ አስደንጋጭ ሁኔታ እንደገና ታወሰው።



## ምዕራፍ ሰማንያ

ራሳም ብቻውን ወደ ቴዎድሮስ ሄደ። በሥላሴ ገደል ላይ በድንጋዮች መካከል ብቻውን ቆሞ አገኘው። አብረውት ወደ ሃያ የሚገመቱ ጠብመንጃ የያዙ ወታደሮች እና የዕደ ጥበባት ባለሙያዎቹ፣ ቫልደማየር እና ፍላድ እንዲሁም ሌሎች አሉ። አቅፎ ሰላም አለው። በገደል አሻግሮ የምትጠልቀውን ጀንበር ተመለከተ። "አሁኑኑ መሄድ ትፈልጋለህ? ወይስ ሌሊቱን አብረኸኝ መሆን ትሻለህ?" አለው።

"ግርማዊነትዎን የሚያስደስተውን ማንኛውም ቢሆን አደርጋለሁ።" መለሰ ራሳም። በምላሹ ቴዎድሮስ እፎይታ ያገኘ መሰለ። " መልካም፣ እንግዲያው አሁኑኑ ብትሄዱ ይሻላል።" ራሳምን ሊለቀው ወሰነ። ስንብታቸው እውነተኛ ኀዘን አጠላበት።

«ከመሄድህ በፊት ጥቂት እንነጋገር» እንዲቀመጥ አመለከተው።

«እንደምታውቀው ሚስተር ራሳም አንተ እና እኔ ሁልጊዜም ግንኙነታችን መልካም ነበር። ያንተን ልብ እግዚአብሔር ይወቀው፣ በእኔ በኩል ግን ላንተ አክብሮቴ እውነተኛ ነበር። እርግጥ ነው መጥፎ ጠባይ አሳይቼህ ነበር፣ ያ የሆነው ግን በመጥፎ ሰዎች ምክንያት ነው»።

ቴዎድርስ የሌለውን ዓይነት አቅም ያለው ሰው አድርጎ ራሳምን እንደሚመለከተው ቫልድማየር አስተውሏል። አሁንም ከኔፒር ጋር ሰላም እንዲፈጥርለት ተስፋ አድርጎበታል።

«አንተ ወዳጅነትህን ካቋረጥከ ራሴን ልገድል ወይም ልመነኩስ እንደምችል አስተውል። አሁን ደህና ሁን። እየመሸ ነው። ነገ ከቻልክ መጥተህ ልታየኝ ሞክር» አለው። እሞክራለሁ አለ ራሳም። ቴዎድሮስ የድሮ ወዳጁን እየተመለከተ፣ «ነገ ዳግም ትመጣለህ?» ጠየቀው።

«ሁሉም የጦር አዛዡ በሚለው የሚወሰን ይሆናል»። ሁለቱም ተነሱ። ተጨባበጡ። የቴዎድሮስ ዓይኖች እንባ አቀረሩ። «በል ፍጠን እየመሸ ነው፣ በደህና ግባ»።

ራሳም ትቶት ሄደ። ወደኋላ ዞሮ ሲመለከት ቴዎድሮስ ጠብመንጃ ይዞ ከኋላው ድንጋይ ላይ ቆሟል። ቀጥል ------ ሲል አመለከተው።

ራሳም እግሮቹን እንሥቶ በወጉ መራመድ አቃተው። የቴዎድሮስን ስሜት የተቀላቀለበት ስንብት ሊጋራ አልቻለም። በዚህ ሰዓት የሚሰማው ፍርሃት ብቻ ነው፤ ሲለቀቁ ሌሊት ባልደረቦቹም ይገደላሉ የሚል ፍርሃት መንቀሳቀስ እንዳገደው ዓይነት ስሜት ነው ያደረበት።

ሌሎቹ በሌላ መሥመር ነው የሄዱት። ቴዎድሮስ በምንም መልኩ ሽተርን እንዳያየው በሚል ምክር ተሰጥቷቸዋል። መንገዱ ጠባብ መውረጃ ነው። ከበላያቸው ኢትዮጵያውያን ተሰብስበው መሄጃቸውን ይመለከታሉ። ብላንክ ሁሉን ቀድሞ ከፊት ገሥግሧል።

በአንድ አሳሳች መንገድ እንደዞረ ራሱን ከቴዎድሮስ በቅርብ ርቀት ላይ አገኘው። ንጉሡ ጭንቅላቱን አዙሯል፤ ሆኖም ብላንክ በሆነ የፍርሃት ስሜት ውስጥ እንዳለ መመልከት ችሏል። ጠብመንጃ ያነገቡ 20 የሚሆኑት ሰዎቹም በአቅራቢያው አሉ።

አንድ ዘጋቢ እንዳረጋገጠው ቴዎድሮስ ራሳምን ካሰናበተው በኋላ ጠብመንጃ እንስቶ በቁጣ ከሌሎች ባለመሣሪያዎች ጋር በመሆን አውሮጳውያኑን ከነተከታዮቻቸው በመንገድ ሲያገኛቸው ወስኖ ነበር። ዶክተሩን ሲመለከት ግን መሣሪያውን ጣል አደረገ። «ዝቅ ባለ ድምፅ እንዴት እንደሆንን ከጠየቀኝ በኋላ ደህና ሁን አለኝ» በማለት ብላንክ ጽፏል።

ሽተርንም እንደሚለው ቴዎድሮስ አይቶት ነበር። ልክ እንደ ብላንክ ሰላምታ ሰጥቶት ደህና ሁን ብሎታል። «እጅግ ጣፋጭ የሆነች አማርኛ በጆሮዬ ስትገባ ልዩ ስሜት የፈጠረችብኝ ሰላምታ» ብሏታል።

ጥቂት ተጉዘው ከራሳም ጋር ተገናኙ። አብረው ወረዱ። የብሪታንያን የጦር ሠፈር ኬላ እንዳለፉ መሸ። ራሳም በቀጥታ ወደ ኔፒር ድንኳን ሄደ። ቀጠለና ከብላንክ እና ፕሪዶ ጋር በመሆን ወደ ሜ ርዌዘር አመራ።

ራሳም ከኤደን ከመጣ ሦስት ዓመት አልፎታል፣ እዚያ ሆኖ በሜርዌዘር ሥር ነበር። እንደሜርዌዘር ይህ ዘመቻ እንዲሳካ ሳይታክት የለፋ የለም። ከምፅዋ ገንዘብ በመላክ እና ታማኝ ደብዳቤ አመላላሽ በማፈላለግ ሕይወታቸውን ያሰነበተውም እሱ ነው። ከለንደን የሚመጡ ጋዜጦችን እየቆረጠ መረጃዎችንም ሲያሾልክላቸው ከርሟል። ለራሳም የቲማቲም ዘር የላከለትም ራሱ ነው።

ሜርዌዘር በሰላምታ ተቀበላቸው። ምንም እንኳን ኔፒር ጓዝ እንዳይበዛ ጥብቅ መመሪያ ቢያስተላልፍም ለዚህ ወቅት የሚሆኑ ነገሮችን አካቶ ይዟል። ከድንኳኑ ጥግ ስድስት ጠርሙስ ሻምፓኝ አመጣ።



# ምዕራፍ ሰማንያ አንድ

በቀጣዩ ቀን የትንሣኤ በዓል ነበር። ቴዎድሮስ ወደ እንግሊዞች የጦር ሰፈር የሚላክ ደብዳቤ አጻፈ። «ሰይጣን በራሴ ሽጉጥ የመግደል ሐሳብ አሳደረብኝ» በማለት ከአንድ ቀን በፊት ለላከለት የጥላቻ ደብዳቤ ኔፒርን ይቅርታ ጠየቀው። አሁን ሰላም ማውረድ ይቻላል ብሎ አምኗል። ሁለቱ ወገኖች በጦርነት ሊደረግ የሚችለውን አድርገዋል፤ ቴዎድሮስም ያገቷቸውን ለቅቋል፤ ዛሬ ደግሞ ቀሪዎቹን አውሮጳውያን የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን እና ቤተሰቦቻቸውን ይለቅቃቸው ይሆናል።

«የትንሣኤ በዓል እንደመሆኑ ጊደር እንድልክልዎት ይፍቀዱልኝ» ሲልም አከለ። ከዚያም አንድ ሺህ ከብቶች እና አምስት መቶ በጎችን ከደብዳቤው ጋር ወደ ኔፒር ላከ። የላከውን በአቅርቦ መመልከቻ መነፅር ቁልቁል ተመለከተ። ከብቶቹ ከእንግሊዞቹ የጦር ሰፈር ሲደርሱ ያለመቀበል እምቢታ ነገር ታየ። ቴዎድሮስ ግራ ገባው። ሆኖም ወደ ተራራው የቃል መልእክት መጣ፤ «ሊቀበሉ ይችላሉ» የሚል። አሁን መደራደር ሲኖር ይችላል በሚልም የመጨረሻ ያለውን ርምጃ ወሰደ። እዚያ ለቆዩት አውሮጳውያን አሁን ነፃ ናችሁ መሄድ ትችላላችሁ የሚል መልእክትም ላከ።

ቫልድማየር ሊሰናበተው መጣ። ከአንድ ቀን በፊት ከራሳም ጋር እንደነበረው ቴዎድሮስ ስሜቱ ተረበሸ፤ እንባ በዓይኖቹ ሞላ። መልካሙ የንግሥናው ዘመን እና የግል ባሕሪው ከቫልድማየር ጋር በነበረው ግንኙነት ውስጥ ተጋምዷል። ዝምተኛውን ጀርመናዊ ሁልጊዜም ይወደው ነበር። ሚኒስትሩ የነበረው የጆን ቤልን ልጅ ሱዛን ቤልን እንዲያገባ የገፋፋው ራሱ ቴዎድሮስ ነው። ያ አሥር ዓመት ሆኖታል። ከዚያን ጊዜ እንስቶ እስኪታሠር ድረስ ቫልድማየር የንጉሡን ፍላጎቶች ለማሟላት ታዛዥ ሆኖ ቆይቷል።

ከሚሲዮን ኮሌጅ እንደተመረቀ «እምነት» ወደ ኢትዮጵያ ጠራው። እምነት ወደፊት እየነዳችው ነው። የሠራውን ሁሉ አምኖበት ነው ያደረገው። የጦር መሣሪያ የሚመረትበትን ሲገነባ፤ ጠብመንጃ ለመሥራት ሲታትር ሁሉንም አምኖበት ነው። ከብዙ ሂደት በኋላ በቴዎድሮስም እምነት ነበረው። አሁን ደግሞ ለዓመታት በጥርጣሬ ውስጥ ኖሯል።

አሁን ቴዎድሮስ ከፊቱ ቆሟል። «ደህና ሁን ውድ ወዳጄ ፤ ልክ ጆን ቤልን እንደወደድኩት ወድጄህ ነበር» ተጨባበጡ። ቫልድማየር ድንገት በሆነው የመለቀቅ ነገር እንደደነዘዘ ነው። «ነጻነት እና ሰላም ከሰው ልብ የመረዳት አቅም በላይ ናቸው» አለ። «እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ ------ እኛም እንደዚያ ነበርን ---------»

አውሮጳውያኑ ሁሉ ሄዱ። ዘውድ ተቀዳጅቶ ከነገሠ ወዲህ ጆን ቤል ከራስ አሊ ጎራ ወደ እሱ ከመጣ ጀምሮ ቴዎድሮስ ከሕዝቡ ጋር ብቻውን ሆኖ አያውቅም። ቁልቁለቱን ለመውረድ ሲታገሉ ተመለከታቸው። ታማ የነበረችው ፓውሊን ፍላድን በቃሬዛ ተሸክመው ሚሲዮናውያኑ፣ ቤተሰቦቻቸው እና አገልጋዮቻቸው ባጠቃላይ ከሁለት መቶ የሚበልጡ ሰዎች፣ ከሦስት መቶ እንስሶቻቸው ጋር በተራራው ወገብ እየተግተለተሉ ወረዱ። ከእነርሱ ጋር መንቀሳቀስ የሚችለው ጓዝ ሁሉ አብሮ ሄደ። ድንኳኑ፣ ጋሪው፣ የእነርሱም ሆነ ከእንድ ቀን በፊት የተለቀቁት ወገኖቻቸው መጠቀሚያ የነበረው ሁሉ ተከትሎ ተጓዘ።

ቴዎድሮስ ወደ ወገኖቹ ዞረና፣ «እርግጥ አሁን ሰላም ነው፣ ኃይሌን ሁሉ ወሰዱት። በእርግጥ አሁን ሰላም ነው» አላቸው። ነገር ግን ሰላም አልነበረም። የትንሣኤ ዕለት አመሻሹ ላይ ፀሐይ ስትጠልቅ ከብሪታንያ የጦር ሰፈር መልእክት መጣ። የሁዳዴ ጾም ፍቺን ለማክበሪያ እንዲሆነው ለኔፒር የላከው የከብቶች ስጦታ ተቀባይ አጣ። ቴዎድሮስ ተታለለ። ስጦታውን እንደተቀበለ ተደርጎ የነበረው ቀሪዎቹን ታጋቾች ለማስለቀቅ ነበር። የቅርብ አገልጋዩ ወልደ ገብርኤል ከንፈሩን ክሶ እንዲህ ሲል ሰማው፣ «እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን ሁሉ ካገኙ በኋላ እኔን መግደል ይፈልጋሉ»።

ሐሳቡ ወደ ትውልድ ቦታው ቋራ ተመለሰ። ሊያመልጥ ይችላል። የጦር መኮንኖቹ ቀሪዎቹን ወታደሮች እንዲሰበስቡ አዘዘ። ሌሊቱን አካባቢውን ለቀው ጨጨሆንተሻግረው ጣና ሐይቅ ለመድረስ። ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ፈጥነው ይጓዛሉ። በዚያ አካባቢ ሊነካቸው የሚችል የለም። ነገር ግን ከተከታዮቹ መካከል ቤተሰቡን ጥሎ ለመሄድ የሚደፍር አልነበረም። ቴዎድሮስን ተከትሎ ወደ ቋራ የሚሄድ እንደማይኖር ግልጽ ሆነ።

ወደ መቅደላ ራሱ ወጥቶ አብረውት እንዲሄዱ ጠየቃቸው። እነሱ ግን ከብሪታንያ ጋር ሰላም ማውረድ እና እጅ መስጠት ይሻላል አሉት። «ፈሪዎች!» አላቸው። እነሱ በተራቸው እሥረኞቹን በመልቀቁ ወቀሱት። ገድለናቸው የመጣው ቢመጣ ይሻል ነበርም አሉት።

"እኛ እስከሞት ድረስ የግርማዊነትዎ ልጆች ነን። ሆኖም ግን እኛ የምንሰጥዎትን ምክር ተቀብለው ከፈረንጆቹ ጋር ለመግባባት ሞክሩ»። ቴዎድሮስ ወደ ጨለማው ሄደ። ከአምባው መውጫ ደጃፍ ከገደሉ ላይም ብቻውን ተቀመጠ።



## ምዕራፍ ሰማንያ ሁለት

በጥቂት ኪሳራ ኔፒር የቴዎድሮስን ኃይል ሰባብሮ የታጋቾቹን መለቀቅ አረጋግጧል። አሁን ወደ ባሕር ወደቡ ባስቸኳይ የሚመለስበት በቂ ምክንያቶች አሉት። የአቅርቦት መሥመሩ ለጥቃት የተጋለጠ ነው። በዚያም ላይ ከወዲሁ በተለያዩ ቦታዎች ጥቃት ገጥሞታል። ወንዞቹ እየጨመሩ ነው። ከጦር ሠፈሩ በላይ ያንዣበበው የሥላሴ ገደል ቴዎድሮስ የተፈጥሮ ምሽጎችን የመምረጥ ጥበቡ ማስታወሻ ነው። ሕንድ ለሚገኘው የብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጻፈው መልእክት «የተራራማው አካባቢ ስልታዊ አዳጋችነት ከገመትነው በላይ ከፍ ያለ ነው» በማለት ገልጾታል።

ባለፉት ቀናትም ቢሆን የኔፒር ተዋጊ ኃይል የሥነ ምግባር ለውጥ ማሳየት ጀምሯል። በጣም ደክሟቸዋል። ንፁሃን አውሮጳውያንን ቂምሰቅል ከሚያሳያቸው ያልሠለጠነ ኃይል መዳፍ ውስጥ ለማውጣት በነጻ አውጭነት መንፈስ ለሳምንታት ተራራ ሸንተረሩን በስሜት ተጉዘዋል። ባለፉት ሳምንታት ደግሞ በጭቃ ላይ አደገኛ ጠላታቸውን ተጋፍጠው በዘመናዊ መሣሪያቸው አሰላለፉን አመናመኑ። የእንግሊዝ እና እንዲያም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑ ተመልሰው ተገዳደሯቸው። የእንግሊዝ እና ሕንድ ወታደሮች በጀግንነታቸው ተደነቁ፣ ግን ደግሞ የሞቱት ሰዎች ብዛት ፍርሃት ለቀቀባቸው።

ከዚያ በኋላ ምስኪን ታጋቾች ራሳቸው ወደ እነሱ መጡ። ወታደሮች እና የባሕር ኃይል አባላቱ የጠበቁት እጥንታቸው የገጠጠ፣ ለመራመድ የሚውተረተሩ እና አይጦች በሚተራመሱበት እሥር ቤት ሁኔታ የቀወሱ እሥረኞችን ማዳን ነበር። ነገር ግን ከነቤተሰባቸው በደስታ የሚያውካኩ ሰዎች ወደጦር ሠፈሩ ገቡ። እንድ መቶ ሰማንያ ሰባት አገልጋዮች አብረዋቸው አሉ። ከእነሱ መካከል ሦስት እጅ ሴቶች መሆናቸውንም ወታደሮቹ ተመለከቱ። ይህ ስብስብ የጥቢቃውን ኪላ ሲያልፍ የወታደሮቹ ፊንጠዝያ ቀነሰ። ብሪታንያውያን አልነበሩም። ሁለት የአየርላንድ ዜጎች እና ካሜሮን፣ የተቀሩት ግን ጀርመናውያን ናቸው። ለመሆኑ አሣሪዎቻቸውንም ሆነ መሪዎቻቸውን ለምን አሳደዱ?

እንዲያም ሆኖ ኔፒር ለመመለስም ሆነ ለመሄድ አልፈለገም። ከትግራዩ ራስ ካሣ እና ከዋግሹም ጎበዜ ጋር ግንባር በመፍጠር ያቃታቸውን የቴዎድሮስን መንግሥት የመጣል ተግባር ማከናወን እንዳለበት ተረድቷል። ይህን ካላደረገ ኔፒር እና ሰዎቹ ከዚህ የሚወጡበትን መንገድ ለማግኘት መታገል ይኖርባቸዋል።

## ምዕራፍ ሰማንያ ሦስት

ያን ምሽት መቅደላ እና ሥላሴ ላይ የቀሩት ኢትዮጵያውያን ካሉበት ከፍታ ሆነው ወደታች ተመለከቱ። በጨለማው ውስጥ ከጠላት መንደር የሚንቀለቀለውን የእሳት ብርሃን ማየት ይችላሉ። በአንድ ወገን የብሪታንያ ጦር በቀረው ደግሞ አርሞው ልክ እንደ ጅብ ተራራው እስኪናድ ይጠባበቃል። በኩል ጨረቃዋ እንግዳ በሆነ ቀይ ቀለበት ተከባ ከፍ ብላ በኮረብታው ላይ ታየች። በሌሊት የቴዎድሮስ ሰዎች ያንን እንደ መጥፎ መልእክት ወሰዱት። ወደየጎጇቸው የገቡት ይህ ትዕይንት በፈጠረባቸው መጥፎ ስሜት በቀጣዩ ቀን ሊመጣ የሚችለውን አስከፊ ነገር በማሰብ ነው።

ቴዎድሮስ ራሱም ቢሆን ፍፁም እንቅልፍ በዓይኑ አልዞረም። በሰላምጌ እና በሥላሴ መካከል ብቻውን የቀረውን የድንጋይ ክምር እየረገጠ ተንጎራደደ። የጠላቶቹን እሳትም ተመለከተ። ቀረው ሰማይ በከዋክብት ተውቦ እሱ ሲገዛው በነበረው ምድር ላይ በቤጌምድር እና ሰሜን፣ በትግራይ እና ላስታ እንዲሁም ከዚያም አልፎ ወደ አውሮጳ፣ እንግሊዝ፣ ሕንድ እና ኢየሩሳሌም ባለው ግንብ ላይ ተንጣሏል። በአምስት አሥርት ዓመታት ውስጥ ቴዎድሮስ ባሕር አይቶ የእቶማ አያውቅም። ከዓመታት በፊት ስለውጪው ዓለም እንቅስቃሴ ሲሰማ የወደፊቱ ዕጣ ፈንታ ከዚያኛው ዓለም ጋር የተቆራኘ፣ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ከክርስቲያን አውሮጳ እና ከእሷ ከተገናኘው ኃይል ጋር እንደሚሆን ገብቶታል። ነገር ግን በልቡ ጦረኛ እንጂ የሀገር መሪ አልነበረም፣ ፕላውደን ትብብር ለመፍጠር ሲጋብዘው ሊያዳክመኝ ይችል ይሆናል ያለውን ሁሉ ለመስጠት ዝግጁ አልነበረም።

እሱ ለረዥሮም ጊዜያት ሲናፍቀው የነበረውን ነገር ሌሎች ሰዎች ሲያመጡለት ስድብ፣ ማዋረድ፣ እና ቅሌት ነው የተረፈው። እናም በድንገት በበቀል፣ በምቀኝነት፣ በጭፍን ጭካኔ በመያዙ እምነው ይከተሉት የነበሩትን ሳይቀር ለከፋ ችግር እና ውድቀት ዳርጓል።

በመጨረሻም እንቅልፉ መጣ። ከመቅደላ የታችኛው መውረጃ ላይ ጋደም ሲል ሽማ በሁለት ጦሮች ከበላዩ ተጋረደለት። ለጥቂት ሰዓታት ተኛ። ማለዳ ተነስቶ በቆቂት በር መውጫ ብቅ አለ። በአካባቢው ባለው እነስተኛ ሥፍራ ተሻገረ። በጠባቂዎቹ ጎጆ አካባቢ ጭስ አለ። ወደ ጠባቧ አምባ ወጣ። ባዶዎቹ የእሥረኞቹ ጎጆዎች በነበሩበት አካባቢ እሳት ከበው የተቀመጡት ጠባቂዎቹ በዝምታ ይመለከቱታል። በሚያውቁት ጠንከር ያለ ድምፀት፣ «እኔን የምትወዱ ተዋጊዎች፣ ተሰብሰቡ፣ ከመሣሪያችሁ በቀር ሁሉንም ትታችሁ ተከተሉኝ። ሌላ መኖሪያ የሚያስፈልገን ጊዜ መጥቷል» አላቸው።

ከአራት የጦር መኮንኖች ጋር በመሆን 2000 የሚሆኑትን አስከትሎ አምባውን፣ እሥር ቤቱን እና የመድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን አልፈው ቢቃፉር በር በኩል



አድርገው ወጡ። እጅግ ጠባብ በሆነው እና በእግር ብቻ መራመድ በሚያስችለው ገደል አፋፍ በኩል አለፉ። ብዙም ሳይሄዱ አብዛኞቹ «ወታደሮች»ማመንታት ጀመሩ። መሪያቸው ሳይሆን እነሱ ነበሩ በታውን ላለመልቀቅ የፈለጉት፤ «መቅደላ ላይ ብንሞት ይሻላል» አሉት።

ቴዎድሮስ ጥቂት አሰላሰለ። ከቅርብ ርቀት በቴዎድሮስ ላይ ጥላቻ ያደረባቸው አሮሞዎች ጨዉ ኸት ይሰማቸዋል። ኔፒር በበኩሉ ቴዎድሮስን ይዞ ለሚያስረክበው 10,000 የጀርመን የብር ገንዘብ አሰጣለሁ ብሏል።

«እሺ፣ መልካም ነው!» አለና ወደኋላቸው ተመለሱ። ቴዎድሮስ አምባውን አልፎ ወደ ሰላምጌ ተመለሰ። በአነስተኛ ቡድን እየተመሳጠሩ አንዳንዶች ንጉሣቸውን እየከዱ አመለጡ። ከጥቂት ታማኝ የጦር መኮንኖቹ እና አዛገሮቹ ጋር ቀረ።

ከእነሱ ጋር በመሆን መድፎቹን ከሰላምጌ ወደ መቅደላ መዳረሻ ወሰደ። አምባውን ለመከላከል አቅዷል። እሱ ይህን ሲያደርግ ወታደሮቹ እሱን እያለፉ ወደ ሥላሴ አቅጣጫ ወረዱ እንግሊዞችን ለመጠበቅ።

ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት። ቴዎድሮስ ቀና ብሎ ሰማዩን ሲመለከት ዐሐይ በጥቁር ቀለበት ተከባ ተመለከተ። እኩለ ቀን አካባቢ ሥላሴ ላይ ከእሱ ሰዎች መካከል መጀመሪያ የተንቀሳቀሰውን የእንግሊዝ ፈረሰኛ ጦር ተመለከተ። የጠላትን ፈረሰኛ ወታደሮች መመልከቱ የውጊያ መንፈሱን ቀሰቀሰው። የጦር ፈረሱን ሐመርን አስመጣ፤ «ገዛሆን ጠብመንጃ» የሚለውን ከዓመታት በፊት የፕላውደን ረዳት ሲቸር ባርኒ የሰጠውን ነፍጡን አነገበ። ኮርቻው ላይ ወጣ እና ለጥ ባለው ደንጋያማ ኮረብታ ሽምጥ መጋለብ ጀመረ። በወርቀዘቦ የተጠለፈ ከንብንቡን እንደለበሰ በፈረሱ ላይ ወደፊት እና ወደኋላ እየጋለበ፣ መሣሪያውን እየተኮሰ የቀድሞ የጦርነት ኃይሉን፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ድሎች ተረከ። አንድ ሰው እንኳ በየትኛውም ጦርነት እንዳላሸነፈው አወሳ።

ከፊት ከገሥገሡት የብሪታንያ ወታደሮች ጋር ባሻ ፈለቀ ማለትም ካፒቴን ስፒዲ ነበር። አልበገር ካለው መሪያቸው ጀርባ የቀሩት የቴዎድሮስ ሰዎች መሣሪያውን ማንቀሳቀስ ጀመሩ። ትተዋቸው የመጡት የጦር መሣሪያዎች አሁን በብሪታንያውያኑ እጅ ገቡ እና ወደ እነሱ አነጣጠሩ። በዘመናዊ አነጣጣሪ መሣሪያቸውም ተኩስ ከፈቱባቸው። የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ተመትቶ ሲወድቅ ተረዎቹ መሣሪያዎቹን እየጣሉ ወደ መቅደላ አቀበት አፈገፈጉ። ቴዎድሮስ አብሯቸው ሄደ። ወደ አምባው እናት የሚያስገቡ ሁለት መንገዶች አሉ። በመካከላቸው አነስተኛ የድንጋይ ካብ አለ። በግንብ እና በእሾህ አጥር ተያይዟል። ቴዎድሮስ እና ሰዎቹ ከመጀመሪያው መግቢያ ጀርባ ተሸሸጉ። በቴዎድሮስ እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ እንግዳ መሪነት ጠፍጣፋ ድንጋዮችን ሰብስበው መግቢያውን ዘጉት።

እንደ ሰውዬው(መይሳው) ታላቅ የሥነ ቴክኒክ ፊቅር፣ ጉንተና ጀምር ቢሆን ኖሮ፣ ኢትዮጵያ፣ ማን ያውቃል፧ በአሁኑ ዘመን ሰውንወደ ማርስ ለመላክ ከሚዘጋጁት መንግሥታት ተራ መመደብ በቻለች ነበር፤

«መጫሚያ አልባው ንጉሥ»፣ ስለ አንቶልና አልባው ንጉሠ ነገሥት ከበድ ባለ እንግሊዘኛ የቀረበውን የታሪክ መጽሐፍ፣ ውብና ጥሩፍነት ባለው ቋንቋ ወደ አማርኛ የመለሰ ከሞላ ጎደል የተሟላ የትርጉም ሥራ ውጤት ነው። የ 19ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓውያን«አገር አሳሾች»፣ ሚሲዮናውያን፣ ዲፕሎማቶችና የጦር ጠበብት፣ የራሳቸው የረዥም ጊዜ ሥልጣኔ እምነትና ባህል ያላቸውን አገሮችሕዝብ፣ «ኋላ-ቀርነ» እያሉ በሌላ በኩል የእነዚህን አገሮች የዳበረ ሥልጣኔ መገለጫ የሆኑ የከበሩ ቅርሳቅርሶችን እየዘረፉና እያጋዙ ታላላቅ አብያተ መዘክሮቻቸውን የሞሉበት ምሥጢር ምን ይባላል?

ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃ፣ ወደ ጥንታዊ ክብሯና ዝናዋ እንድትመለስ መጣር ብዙ ተጋዳሮቶች እንደነበረበት፣ ባዕዳን ታሪካዊጠላቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ከልጆቿም ጥቂቶች የራስን ጥቅምና ዝና በማስቀደም በየጊዜው ለጉዳት እንደዳረጓት መጫሚያ አልባውንጉሥ ከተሰኘው መጽሐፍ እንገነዘባለን።

በኢትዮጵያ ባህልና እምነት ጠንከርና ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ባላት የቀድሞ ባልደረባዬ ጋዜጠኛ ሸዋዬ ለገሠ ተተርጉሞ የቀረበው ይህመጽሐፍ፣ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ስለ አፄ ቴዎድሮስ ባሕርይና ዓላማ ተጨማሪ ግንዛቤከማስጨበጥም ሌላ ስለ ቴክኒዮሎጂ እድግ ተፈላጊነት፣ አገር ወዳድነትና ጀግንነት፣ በአጠቃላይ የጎደለ በጎ ነገርን ስለመሙላትአስፈላጊነት ጠቃሚ ምልከታን ያጎያል።

ተክሌ የኋላ

የዚህን መጽሐፍ የእንግሊዘኛ ህትመት ከአነበብኩ ዓመታት አልፈዋል። የጋዜጠኛ ሸዋዬ ለገሠን የአማርኛ ህትመት በአነበብኩ ግዜሌላ መጽሀፍ የማነብ መስሎኝ ለማመን ምንም አልቀረኝም ነበር። ምክንያቱም ደግሞ : ወ/ሮ ሸዋዬ መጽሀፉን በእቻ ትርጉምእሳምራ ከመተርጎሟ ባሻገር : ያሉትን ምዕራፎች ሁሉ አዲስ የአጻጻፍ ስልት በመጠቀም ኢትዮጵያዊ ለዛና ይዘት እንዲኖራቸውተግታ በማድረጓ ነው። የእኛን ኢትዮጵያውያንን ነገር የአነጋገር ዘዬና የቋንቋ ጥራት በመጠበቅ ለዛ ባለው አገላለጽ፣ የንባብ ፍሰቱንናየታሪክ ጭብጡ ሳይዛነፍ ግሩም በሆነ ብእር በአዲስ መልክ ከሽና ለንባብ አቅርባዋለች። ይህ የታላቁ ንጉሠ ነገሥት የአፄ ቴዎድሮስመልካም አርአያነት ባለፉት 45 ዓመታት በእኔ ትውልድ ዝንድ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አዲሱ ትውልድ የሚያከብረውናየሚወደውን መሪ ሳያገኝ ቀርቷል። አሁን ግን ወ/ሮ ሸዋዬ ይህን ታላቅ ሥራ በመሥራቷ : የእኛን ትውልድ ተከተ ለአሁኑ ኢትዮጵያዊወጣት ትውልድ እውነተኛ የታሪኩ መኩሪያ፣ ባለቤትና ዋና መመኪያ እንዲሆነው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች። ወንድሞቻችንናልጆቻችን ይህን የተቀደሰ አርአያ ይከተላሉ ብዬ እምናለሁ። ለዚህም ከ105 ሚሊዮን 85 እጅ (%) የሚወክል በኢትዮጵያ እድሜውከ25 ዓመት በታች የሆነው ትውልድ የዚህን አገር ወዳድ ጀግና መሪ ራዕይ ተከትሎ የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውና ጠባቂ እንዲሆንእየተማጸንኩ፣ ወ/ሮ ሸዋዬ ላበረከተችልን ለዚህ ታላቅ ምሁራዊ ተግባርና ታሪካዊ የስነ ጽሁፍ ትሩፋት ያለኝን አድናቆት ለመግለጽእወዳለሁ።

**ልዑል ዶ/ር አስፋወሰን አሥራተ : ካሣ የውርስ ኢትዮጵያ ማህበር የቦርድ ሊቀመንበር**

ዋጋ 100 ብር

€ 20 $ 20

ከሥላሴ አቅጣጫ የብሪታንያ ተኳሾች ሁለቱን መግቢያዎች በጥይት ይደበድቡ ጀመር። ቀዳሚው ጦር ወደ አቀበቱ በመገሥገሥ ወደ መጀመሪያው መግቢያ ተጠጋ። ከቀትር በኋላ አሥር ሰዓት ሆኗል። በአምባው አናት ላይ ተሰብስበ የነበረው ደመና በመብረቅ ይታረስ ገባ።

የመቅደላን ቁልቁለት ለመርገጥ የብሪታንያ ጦር ቀዳሚ ነበር። ከውጭኛው ግንብ ቢደርሱም መጠበቅ ነበረባቸው። የተወሰነ ባሩድ እና ዛቢያ እዚያው አሉ። (የሆነ ሰው እዚያው ትቶት ሄዷል።)

ከግንቡ በሌላ ወገን በፍርሃት የተሸበቡት ከሞት የተረፉት የቴዎድሮስ ሰዎች ይገኛሉ። አንድ ወይም ሁለት ወታደሮች ቢኖሩ ነው እንጂ ቀሪዎቹ በአብዛኛው ሚኒስትሮች እና ከፍተኛ የጦር አዛገሮች ነበሩ። ራስ እንግዳ፣ የቴዎድሮስን የጦር መሣሪያዎች ይመራ የነበረው የአባ ሚርዛ ልጅ እንግዳ ወርቅ፣ እንደ ቴዎድሮስ ከቋራ የሆኑት ራስ ብሩክ፣ አዛውንቱ ደጃዝማች ዐብይ፣ አጋፋሪ መሸሻ፣ የንጉሡ አንጋች አማኒ፣ እንዲሁም የቀድሞው አንጋች የአሁኑ የንጉሡ አልባሽ ወልደ ገብርኤል ሁሉ እዚያው ናቸው። የከባድ መሣሪያው ተኩስ ሲጀመር በድጋሚ ሁሉም አስተማማኝ ወደሆነው ወደ ውስጠኛው የአምባው ወገን ሸሹ። ደርዘን የሚሆኑት ደግሞ ከቴዎድሮስ ጋር ቀሩ።

እሱ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ነበር። አቅርቦ ማሳያ መነፅሩን ወደ ዓይኑ አስጠጋ። ከሥላሴ አቅጣጫ ተኩሱን ይመለከት ነበር። አንድ የመድፍ አረር በአቅራቢያው አርፎ ሁለት ላሞችን ሲገድል ድንጋጤ ታየበት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ እንግዳ እና ወንድማቸው አሁንም ከቴዎድሮስ ጋር ናቸው። ራስ ለቴዎድሮስ እጅግ ታማኝ ነበሩ። ራሳም እንደውም «ከታማኝነታቸው የተነሳ መርዝም ቢሆን ስለእሱ ሲሉ ሊውጡ ይችላሉ» ሲል ገልጿቸዋል።

ወደላይ እንዳፈገፈጉ በ12 እና 14 ዓመት መካከል የሚገኙ ልጆቻቸው መቅደላን ለቀው እንዲሄዱ አደረጉ። አሁን በሥላሴ አቀበት ላይ የሚገኙት ልጆቻቸው የሚወርደውን የመድፍ እሩምታ ከታች ሆነው በእንባ ይመለከታሉ። ተኩሳቸውን እንዲያቆሙ ም የብሪታንያ ወታደሮችን በጠጅ ለመደለል እየሞከሩ ነው። ግን አልተሳካም። በመግቢያዎቹ መካከል የወደቀው የመድፍ አረር አባታቸውን እና የአባታቸውን ወንድም ገደለ። አማኒ እና ሌላ ሰውም ተገደሉ። ተኩሱ ሲበረታ ቴዎድሮስ የወደቁት እስከሬኖች ወደ መግቢያው ታዛ እንዲዛወሩ አዘዘ።

ብሪታንያውያኑ መግቢያውን ፈንቅለው ለ መግባት እየታገሉ ነው። በመጨረሻም ተሳካላቸው እና ከፈቱት። ያንን ቢያልፉም የተከመሩትን ጠፍጣፋ ድንጋዮች ማንሳቱ ጊዜ ወሰደባቸው። በዚያ መካከልም ብዙዎቹ በተኩስ ቆሰሉ። ወልደ ገብርኤል የቴዎድሮስን መሣሪያ ጥይት አጉርሶ ሰጠው። የብሪታንውያኑ ሌላ ቡድን በታች በኩል ተከልሎ ወደ ተራራው ላይ ወጣ። እንደ ገባም ተኩስ ከፈተ።



ከተረፉት ጥቂት ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ ወደቁ፣ ቆሰሉ ወይም ሞቱ። ቀሪዎቹ -- አምስት የሚሆኑት በድንጋይ ደረጃዎቹ ጡ ብ ጡ ብ ብለው እየተፋጠኑ ወደ ውስጠኛው በር ገቡ። ቴዎድሮስ ራሱ ወደኋላ ተራመደ። ወደ ውስጥ እንደገባም ለቀሪዎቹ፣ «አምልጡ! ካለባችሁ ኃላፊነት ነጻ ለቅቄያችኋለሁ። እኔ መቼም ቢሆን በጠላት እጅ አልወድቅም» በማለት ጮኾ ትዕዛዝ አስተላለፈ።

ከወገቡ ላይ ሽጉጡን መዘዘና አፉ ውስጥ አስገብቶ ቃታውን ሳበ። በዚህ ጊዜ ግን ተተኮሰ። የመጀመሪያው የብሪታንያ ወታደር መቅደላ አምባ ላይ ብቅ ሲል፣ ቴዎድሮስ መሬት ላይ ወደቀ።

###ተፈጸመ###